# የቅንጅት

# ለአንድነትና ለዲሞክራሲ

# የምርጫ ማኒፌስቶ

1997 ዓ. ም.

አዲስ አበባ







1. መግቢያ....................3
1.1 ራዕይ....................4
1.2 ተልዕኮ....................4
1.3 ቅንጅት የሚመራባቸው ቁልፍ እሴቶችና መርሆዎች....................5
2. ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ውድቀቶች....................18
2.3 ኢንቨስትሜንት....................20
2.3.1 የግል ኢንቨስትሜንት....................20
2.3.2 የመንግሥት ኢንቨስትሜንት....................21
2.4 ሚዛኑ የተዛባ የወጪና ገቢ ንግድ....................22
2.5 ጤናማ ያልሆነ የፋይናንስ ኤኮኖሚ....................25
2.5.1 የመንግሥት ፋይናንስ....................27
2.6 ያልተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ....................29
2.7 ዕድገቱ የተገታ የግብርና ዘርፍ....................31
2.8 ከኋላ ቀርነት ያልተላቀቀ የኢንዱስትሪ ዘርፍ....................37
2.9 የአካባቢ መጐዳት....................42
2.10 ሥራ አጥነት....................44
2.11 የድህነት መባባስ....................45
2.12 ትኩረት የተነፈገው አነስተኛ ዕደ ጥበብ....................50
2.13 ዘላቂ ለውጥ የማይታይበት ማህበራዊ አገልግሎት....................51
2.13.1 ትምህርት....................51
2.13.2 ጤና....................59
2.13.3 የተዳከመ መሠረተ ልማት....................62
2.14 የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር እጦት....................66
2.14.1 ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም አለመኖር....................69
2.14.2 ተቋማዊ ሙስና....................70
2.14.3 የአሠራር ነፃነት የሌለው ሲቪል ሠርቪስ....................77
2.14.4 አስከፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣና የእርስ በርስ ግጭቶች..79
2.15 የሀገር ሉዓላዊነት መደፈር....................82
3.ቅንጅት ትኩረት የሚሠጥባቸው ጉዳዮች 90
3.1 ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ ማድረግ....................88
3.2 የኢኮኖሚ ተሃድሶ ማድረግ....................93
3.2.1 የገጠር ልማት....................93
3.2.2 የከተማ ልማት....................98

3.2.3 የኢንዱስትሪ ልማት ....104
3.3 ልማትን የሚያፋጥን አገልግሎት ማስፋፋት ....110
3.4 ማህበራዊ ፍትህን የሚያረጋግጥ ልማት ....114
3.4.1 ትምህርት ....114
3.4.2 በመከላከል ላይ የተመሠረተ የጤና ልማት ....119
3.4.3 ለወጣቱ ችግሮች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ....121
3.4.4 ተጨባጭ ጥረት ለሴቶች እኩልነት ....123
3.4.5 የሠራተኞችን የሥራ ሞራል የሚያነሣሣ ጥረት ማድረግ ....125
3.5 ለተረሱት ወገኖችና አካባቢዎች ትኩረት የሚሠጥ መሠረተ ልማት ....126
3.6 የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓትን ማሻሻል ....127
3.7 ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ትኩረት የሚሠጥ የውጭ ፖሊሲ ....127
3.8 የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተቋሞችን መመሥረት ....129
4. ማጠቃለያ ....132
4.1 የማኒፌስቶው አፈፃፀም ....132
4.2 ሀገራዊ ጥሪ ....133





# 1. መግቢያ

በ1997 ዓ. ም. ግንቦት ወር ላይ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ምርጫ ነጻ፣ ትክክለኛና ፍትሃዊ እንዲሆን ቅንጅት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ነው። የዘንድሮው ምርጫ ከዚህ በፊት ከተፈፀሙት ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች በቂ ትምህርት የተቀሠመበትና ስህተቶች የማይደገሙበት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሆን እንፈልጋለን። በአሁኑ ምርጫ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚያስችል መሠረት ካልተጣለ የሀገሪቱ ችግሮች የሚወሣሰቡበትና አስከፊ ውጤት የሚያስከትሉበት ሁኔታ ይከሠታል። እንዲህ ዓይነቱ ውጤት ደግሞ የማይፈለግ ብቻ ሣይሆን ለማንም የማይጠቅም ነው።

የአሁኑ ምርጫ ሕዝብ ራሱ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ መሆኑን በተግባር የሚያረጋግጥበት፣ በፖለቲካ ሥልጣን የሚወዳደሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ የሚያገኙበት፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የምርጫ መርሆዎች ሥራ ላይ የሚውሉበት እንዲሆን ከፍተኛ ፍላጐትና ትግል የማካሄድ ቁርጠኝነት አለ። ይኸንን ምርጫ እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የራሱን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ባህሪይ ለመሸፈንና በሕዝብ ድጋፍ የቆመ መስሎ ለመታየት እንዲገለገልበት መፍቀድ ትልቅ ስህተት ነው። ገዥው ፓርቲ ወደ ሥልጣን መንበር የተንጠላጠለው በሕዝብ ፈቃድ ሣይሆን በጠመንጃ ኃይልና በአፈና እንደመሆኑ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ለሆነ ምርጫ እምነትና ከበሬታ እንደሌለው ይታወቃል። ይሁን እንጂ ሕዝቡና የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች ከዚህ በኋላ ይህ ሁኔታ እንዲቀጥል መፍቀድ አይገባቸውም። ሀገሪቱ የምትገኝበት እውነታም ይኸንን ለመሸከም የሚችል አይደለም።

በመሆኑም ቅንጅት በዚህ ዓመት የሚደረገው ምርጫ ነፃ፣ ትክክለኛና ፍትሃዊ እንዲሆን በቅድሚያ መሟላት የሚገባቸውን የሕግ፣ የአደረጃጀትና የአሠራር አማራጮች አዘጋጅቶ አቅርቧል። በሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል ነጻ፣ ገለልተኛና ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ተቋም የለም። ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ነጻ የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖር በሚያስችል መንገድ የተዘጋጀ የሕግ ሥርዓት የለም። እነዚህ መሠረታዊ ጉድለቶች እንዲሟሉ ለማድረግ የምርጫ ቦርዱ፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካሉና የምርጫ ሕጉ የሚስተካከሉበትን አማራጭ አዘጋጅተን ለሚመለከተው ሁሉ አቅርበናል። እስካሁን ተጨባጭ መልስ ባይገኝም መፍትሄ እንዲፈለግ የጀመርነውን ትግልና ግፊት ሣናቋርጥ በምርጫው ለመወዳደር የሚያስችለንን ሁለገብ

ዝግጅት ቀጥለናል፡፡ በምርጫ ውስጥ ገብተን ለመወዳደር የሚያስችለንን አቋምና ፕሮግራም ለመራጩ ሕዝብ በማስረዳት እምነቱንና ውክልናውን እንዲሠጠን በማሠብ ይኸንን የምርጫ መወዳደሪያ ማኒፌስቶ አዘጋጅተናል፡፡

ማኒፌስቶው የቅንጅትን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ መርሆዎችና አሠራሮች፣ አባል ድርጅቶች (መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድኅን፣ ኢዴሊ እና ቀስተ ደመና) አስካሁን ያደረጓቸውን ትግሎችና ልዩ የሚያደርጓቸውን ባህሪያት በአጭሩ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት በማያበቁ መሠረታዊ ችግሮች የታጠረ መሆኑን ለማመላከት የሚረዱና የዚህን አገዛዝ ገመናዎች የሚያጋልጡ ዋና ዋና ሃሣቦች በማኒፌስቶው ውስጥ ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም ቅንጅት በመራጩ ሕዝብ ፈቃድ የመንግሥት ሥልጣን ውክልና ቢያገኝ ቅድሚያ የሚሠጣቸው አበይት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በዚህ የምርጫ ማኒፌስቶ ውስጥ ቀርበዋል፡፡

ቅንጅት በነፃ ምርጫ፣ በሕዝብ ፈቃድና ሠላማዊ በሆነ መንገድ የመንግሥት ሥልጣን የሚያዝበትና የሚለቀቅበት አዲስ ምዕራፍ በኢትዮጵያ እንዲጀመር ትግል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ አሁንም ሆነ ወደፊት ይኸንኑ ትግል ይገፋበታል፡፡ በመሆኑም መራጩ ሕዝብ የቅንጅቱ ተጨባጭ ጥረትና በዚህ የምርጫ ማኒፌስቶ የቀረቡትን ሀገራዊ አጀንዳዎች መዝኖ ቅንጅትን በመደገፍ ድምፁንና ውክልናውን እንዲሠጥ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

## 1.1 ራዕይ

የዜጎች ሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ሙሉ በሙሉ የተከበሩባት ኢትዮጵያን፣ ለሕዝቡ ፍላጐት መሟላት በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሚሠራ አመራር፣ በሁሉም ደረጃ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት የሚሠራ መልካም አስተዳደር፣ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነት ያለውና ራሱን ከኋላ ቀርነትና ድህነት ለማውጣት አብሮ የሚሠራ ሕዝብ ማየት ነው፡፡

## 1.2 ተልዕኮ

በኢትዮጵያ ፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት ማረጋገጥ፣ ዜጐች ለሀገራቸው ፍቅር እንዲኖራቸው፣ የዜግነት ክብርና ኩራትም እንዲሰማቸው አስፈላጊ በሆነ ጊዜና ደረጃ ዜጐችን ለመደገፍ የሚያስችል የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት ማቅረብ፣ የዜጐች ዲሞክራሲያዊና ሠብዓዊ መብቶች በህግ እንዲከበሩና ተፈጻሚም እንዲሆኑ በጽናት መቆም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና





ግለሠቦች ነፃ፣ ትክክለኛና ግልጽ በሆነ መንገድ የሚወዳደሩበት ብቁ የምርጫ ሥርዓት ለመመስረት መታገል፣ ሀቀኛ ብቃትና ተጠያቂነት ባለው አመራር፣ አማካይነት ታታሪና የፈጠራ ችሎታ ያለው ሕብረተሰብ መመሥረት ነው፡፡

በትምህርት አማካኝነት የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ ግንዛቤ ለማሣደግና ዜጐች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ በንቃት እንዲሣተፉ፣ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውንም እንዲወጡ ጥረት ማድረግ፣ የእያንዳንዱን ግለሠብ ዜጋ ችሎታ ሙሉ በሙሉ በማሣደግ በአካባቢ፣ በሀገርና በዓለም ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ያለውን ምኞት ማሣካት፣ በውስጥና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ያላቸውን ሠብዓዊና ቁሣዊ አቅም በሀገራቸው ኢንቬስት እንዲያደርጉና ለሕዝቡ ቁሣዊና መንፈሣዊ ሕይወት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ መፍጠር፣ በሀገራችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ ስለሀገራቸው የሚያሠሙት ድምጽ እንዲደመጥ የሚረዳ የስምምነት ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲኖር መታገል ነው፡፡

ለብሔራዊ አንድነት፣ ሠላም፣ መረጋጋትና ዘላቂ ልማት የሚመች ጤናማ ሁኔታ በኢትዮጵያ እንዲኖር ብሔራዊ እርቅ መፍጠር፣ ዓለምን ለመረዳትም ሆነ የዓለም ሕብረተሰብ በአግባቡ እንዲረዳው የማድረግ ችሎታ ያለው፣ በነፃነት የሚያስብና ራሱን የሚገልጽ ሕብረተሰብ መመስረት፣ የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በራሱና በወረሰው መልካም ነገር የኩራት መንፈስ እንዲያዳብር ጥረት ማድረግ፣ በሕይወቱ ውስጥ ጥሩ ተስፋ እንዲኖረውና ለከፍተኛ ግብ እንዲሠራ ማደፋፈር ነው፡፡

## 1.3 ቅንጅት የሚመራባቸው ቁልፍ እሴቶችና መርሆዎች

❖ **የግለሰብ ነፃነት**

ቅንጅት የማንኛውም የኢትዮጵያዊ ግለሰብ የዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ሙሉ በሙሉ የሚከበርበት ሕብረ-ብሔራዊ ሕብረተሰብ እንዲያብብ ይታገላል፡፡ እጅግ ውድ የሆነው የሰው ልጅ እሴት ነፃነት እንደመሆኑ በሁሉም መስክ የግለሰብ ነጻነት ቀዳሚ ስፍራ ይይዛል፡፡

❖ **የቡድን መብቶች**

ምንም እንኳን የአንድ ማህበረሰብ የመጨረሻ ግብ የእያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል ግለሰብ ነፃነትና መብቶች ሳይጓደሉ እንዲከበሩ ማድረግ ቢሆንም የተወሰኑ የማህበረሰቡ አባላት በጋራ የሚፈልጓቸውና እንዲከበሩላቸው የሚጠይቋቸው መብቶች እንዳሏቸው ግልፅ ነው፡፡ እነዚህ

የአንድ ማህበረሰብ የተወሰኑ ክፍሎች የጋራ መብቶች የግለሰብን ነፃነት በማይሸረሽርና አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ መከበር እንደሚገባቸው ቅንጅት ያምናል፡፡

ከዚህ አንፃር አገራችን የብዙ ብሔር-ብሔረሰቦች ሀገር እንደመሆኗ መጠን እነዚህ የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ኢትዮጵያዊ እንደመሆናቸው አንድ የሚያደርጋቸው በርካታ መሠረታዊ ቁምነገሮች የመኖራቸውን ያህል የራሳችን የሚሉት ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ስነ-ልቦና ልማዳዊ ሥርዓትና ሌሎች መሰል እሴቶችና መለያዎች አሏቸው፡፡ ስለዚህም ቅንጅት በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔርና ብሔረሰቦች

- በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋቸውን የማሳደግ፣
- ባህላቸውን የማስተዋወቅና የማዳበር፣
- ራሳቸውን የማስተዳደርና አካባቢያቸውን የማልማት፣
- እምነታቸውን፣ ባህላዊና ልማዳዊ ሥርዓቶቻቸውን ያለተፅእኖ ተግባራዊ የማድረግ መብቶች አሏቸው ብሎ ያምናል፡፡ ለዚህም በፅናት ይቆማል፡፡
- ከዚህ ባሻገር ቅንጅት፡-
- የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የሙያ ማህበራትንና የመሳሰሉትን የቡድንና የጋራ መብቶችን ያከብራል፡፡

## ❖ ኃላፊነት

ቅንጅት መብትን የመጠቀም ጉዳይ ሲታሰብ ታማኝ፣ ሀቀኛና ሰብዓዊ ከመሆን ኃላፊነት ጋር የግድ መተሣሰር አለበት ብሎ ያምናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ኃላፊነቶች፡-

- ግለሰቦች እርስ በርሳቸው ባላቸውና ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት፣
- ባህላዊም ሆኑ ዘመናዊ ሲቪክ ማህበራት እርስ በራሣቸውና ከሕብረተሰቡ ጋር ባላቸው ግንኙነት፣
- መንግሥት ራሱ ከሚያስተዳድረው ሕዝብና በሌሎች መንግሥታት ስር ከሚገኝ ሕዝብ ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡






## ❖ ግልጽነት

ቅንጅት በሁሉም ተግባሮቹ የግልጽነት መርህን ይከተላል፡፡ ማንኛውም ሰው ሕይወቱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ የሚነካን እቅድና አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ሂደት የማወቅ መብት አለው ብሎ ያምናል፡፡

## ❖ ተጠያቂነት

ቅንጅት ማንኛውም ግለሠብ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ ምንም ይሁን ምን ራሱ ለሚወስነውና ለሚፈጽመው ጉዳይ ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል፡፡

## ❖ ምላሽ ሠጪነት /Responsiveness/

ቅንጅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ተገቢና ወቅቱን የጠበቀ መልስ የመስጠት መርህ ይከተላል፣ ግለሰቦች፣ ሲቪል ማህበራትና መንግሥት በኃላፊነታቸው መጠን ለግለሰብና ለሕብረተሰብ ፍላጎቶች መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል፡፡

## ❖ አንድነት በልዩነት

ቅንጅት በተለያየ ቋንቋ፣ ባህልና ኃይማኖት ያሸበረቀና ጥብቅ በሆነ አንድነት እንዲቆም በሚያስችል ዓላማ ላይ የተሣሰረ ሕብረተሰብ ለመገንባት በቁርጠኝነት ይሠራል፡፡ የቅንጅቱ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት በግለቦችና ማኅበረሰቦች መካከል ላለው ልዩነት ዋጋና ግምት የሚሠጥ እንደመሆኑ ልዩነት ያሉት ኅብረ ብሔር ኅብረተሠብን ይቀበላል፡፡ ይህም ማለት የአንዱ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነትና ልማድ በሌላው ላይ ተፅእኖ አያደርግም ማለት ነው፡፡ ባህላዊ መሪዎች በዴሞክራሲ መርህ ተገቢ ቦታ ይኖራቸዋል፡፡ ኃይማኖትና የአምልኮ ነጻነት መሠረታዊ መብት እንደመሆናቸው አንድም ኃይማኖት አይገለልም ወይም አድሎ አይፈፀምበትም፡፡

## ❖ ሀቀኛነት (ትክክለኛነት)

ቅንጅት ሁሉም ሰዎች እኩል የተፈጠሩ ናቸው፣ እኩል ደረጃና ክብር አላቸው፣ አቅማቸውን ለማሣደግ እኩል ዕድል አላቸው፡፡ በመሆኑም መንግሥት ሁሉም ሰው እኩል ዕድል እንዲያገኝና መድሎም እንዳይኖር በማድረግ ሀቀኝነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት ብሎ ያምናል፡፡

### ❖ ዲሞክራሲ

ቅንጅት ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ የራሱን ሕይወት በሚነካ ውሣኔ ላይ ሃሣብ የመስጠት መብት ሊኖረው ይገባል ለሚለው መሠረታዊ መርህ ይቆማል፡፡ ይህ መብት፡-

- መንግሥትን በመምረጥ እኩል ተሣትፎ ማድረግን፣
- በሥራ ቦታ ውሣኔ በሚሠጥበት ጊዜ ትርጉም ያለው ድምጽ ማሰማትን፣
- ሕይወትን የሚነካና በአካባቢ፣ በክልልና በብሔራዊ ደረጃ በሚሠራ ዕቅድ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ውስጥ መሣተፍን ይጨምራል፡፡

### ❖ አሳታፊነትና (Participatory) አሰባሳቢነት (Inclusive)

በፖለቲካ፣ በኢክኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በዲሞክራሲና በሰብአዊ ግንባታዎች ሕዝቡ ገለልተኛና ተመልካች ሣይሆን በባለቤትነት መንፈስ እንዲንቀሳቀስ፣ ቀጥተኛ ተሳታፊና ዋነኛ ኃይል እንዲሆን መደረግ አለበት ብሎ ቅንጅት ያምናል፡፡

### ❖ የጋራ ጥቅም

ቅንጅት ሕልውናችን፣ እድገታችንና የወደፊቱ ደህንነታችን ለጋራ ጥቅም በአንድነት በምናከናውነው ተግባር ይወሰናል ብሎ ያምናል፡፡

### ❖ ሠላማዊ ትግል

ቅንጅት ምንም ያህል መስዋዕትነት ቢያስከትል ለሠላማዊ ትግል ይሠለፋል፡፡ በአግባቡ የተያዘና የሚመራ ሠላማዊ የሕዝብ ትግል እንደ እኛ በብዙ አስጨናቂ ሁኔታ የተከበበን ሕብረተሰብ ወደተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግር ተዓምር ይፈጥራል ብሎ ያምናል፡፡

### ❖ ተቆርቋሪነት (Compassion)

ቅንጅት የአካል ጉዳት የደረሠባቸውንና ተጠቃሚ ያልሆኑ ወገኖችን ጥቅም ለመጠበቅና ለመደገፍ ቁርጠኝነት አለው፡፡ የቅንጅቱ ባህል ሁልጊዜም ጥበቃና ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች መድረስ፣ መንከባከብ፣ መከላከልና መደገፍ ነው፡፡







### ❖ አርዓያነት ያለው ስብዕና

ምንም እንኳ ግለሰቦች እንደ ዜጋና የፓርቲ አባል የራሣቸውን የኑሮ ዘይቤ ለመከተል ተፈጥሯዊ መብት ቢኖራቸውም ቅንጅት መልካም ባህርይ፣ አርዓያነት ያለው ስብዕናና የኑሮ ዘይቤ የጤናማ ሕብረተሰብ መሠረት ይሆናሉ ብሎ ያምናል፡፡ መገለጫቸውም ሀቀኝነትና ጠንካራ የሞራል መርህ፣ መቻቻል፣ ፅንፈኛ አለመሆን፣ አስተዋይነት፣ ታታሪነትና ታጋሽነት፣ ንጽህናና አርዓያነት ያለው ስብዕና ናቸው ብሎ ቅንጅት ያምናል፡፡

### ❖ እኩልነት

ቅንጅት ሁሉም ሰዎች በተፈጥሯቸው እኩል በመሆናቸው ኢትዮጵያዊያን በዘር፣ በቀለም፣ በትምህርት፣ በሀብት፣ በፆታ፣ በኃይማኖት፣ በአመለካከት ወዘተ... ላይ የተመሠረተ አድሎ ሊደረግባቸው አይገባም ብሎ ያምናል፡፡

### ❖ የሕግ የበላይነት

ቅንጅት በመንግሥት ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ ባለሥልጣኖችና ተራ ዜጎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ መንግሥትን ጨምሮ ማንኛውም ተቋም፣ ኅብረተሰብና ግለሰብ ለሕግ የበላይነት መገዛት አለበት ብሎ ያምናል፡፡

እነዚህ እሴቶች በዋነኛነት የቅንጅት መሠረታዊ መርህ ከሆነው የግለሰብ ነፃነትን ከሚያከብር አስተሣሠብ የሚመነጩ ይሁኑ እንጅ ከሶሻል ዴሞክራሲና ከስምምነት (ከኮንሰንሰስ) ዴሞክራሲ አመለካከቶች መካከል ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችንም ያካተቱ ናቸው፡፡ ሊበራሊዝም ሲባል የግለሰብ ነጻነት፣ በውድድር ላይ የተመሠረተ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ፣ የሰከነ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ መኖር አለበት በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ የንድፈ ሃሣብና የተግባር መርህ ነው፡፡ ይኸንን መርህ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሥራ ላይ ለማዋል በሚታሰብበት ጊዜ በቅድሚያ የሀገሪቱን እውነታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ቅንጅት የሚከተለው የግለሰብ ነፃነትን የሚያከብር አስተሣሠብ ኢትዮጵያ አሁን ከምትገኝበት ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን ከሶሻል ዴሞክራሲና ከስምምነት (ከኮንሰንሰስ) ዴሞክራሲ ጠቃሚ እሴቶችን መውሠድና ፈጠራ በተሞላበት ዘዴ ማዳበርን ይጠይቃል፡፡

በእኛ ሀገር ሁኔታ ነፃ የገበያ ሥርዓት በመከተል ብቻ የማይሸፈኑ

ብዙ ክፍተቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እንደ እኛ ሀገር ባለ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገሮች ይቅርና የበለፀገ ካፒታሊዝም ሥርዓት የገነቡትም ቢሆኑ በነጻ ገበያ የማይሸፈኑ ክፍተቶችን ለመሙላት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ እኛም ከዚህ አጠቃላይ ልምድና ግንዛቤ ውጭ ልንሆን አንችልም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ዜጎች እኩል ዕድል የሚያገኙበት ሁኔታ ስላልነበር ተመሣሣይ መነሻ ያላቸውና አንድ ዓይነት የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አይደሉም፡፡ በትምህርት፣ በሃብት፣ በኑሮ ሁኔታና በመሳሰሉት ያሏቸው ልዩነቶች ቀላል አይደሉም፡፡ የሀገሪቱ ልዩ ልዩ ክልሎች ተመሳሳይ የሆነ የልማት መነሻ የሌላቸው እንደመሆናቸው የሚገኙበት ደረጃም የተለያየ ነው፡፡ በትምህርት፣ በጤና፣ በመገናኛና በመሳሰሉት የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችም ሆነ በሌሎች ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅሞች የሚገኙበት ደረጃ አንድ አይደለም፡፡ በድኃውና በሃብታሙ፣ በገጠርና በከተማ፣ በመሀልና በጠረፍ አካባቢ ወዘተ… ሠፊ ልዩነቶች አሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ልዩነቶች ለማጥበብ የሚያስችሉ ጥረቶች ያስፈልጋሉ፡፡ በተለያየ ምክንያት የተረሱትንና እኩል ዕድል የማግኘት መብት የተነፈጋቸውን የሚደግፍ የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካል ጉዳተኞችን፣ በጤና ችግርም ይሁን በአደጋና ወይንም በዕድሜ ምክንያት ከሥራ የሚገለሉትን አቅመ ደካሞችንና ደጋፊ የሌላቸውን ወገኖች መንከባከብ የሚያስችል ፖሊሲ መኖር አለበት፡፡

እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚቻለው ታክስና ቀረጥ የመክፈል አቅም ካላቸው ዜጎች የሚሠበሠበውን ገንዘብ መልሶ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ይኸንኑ ዓላማ ለመደገፍ የሚያግዝ የማህበራዊ ደህንነት ፈንድ መመደብና ሌሎች ተገቢ አማራጮችን ሁሉ መጠቀምም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መንገድ ማህበራዊ ፍትህ እንዲረጋገጥ ማድረግ ከሶሻል ዲሞክራሲ ጠቃሚ እሴቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች፣ እምነቶችና አመለካከቶች ትስስር ፈጥረው አንድ ላይ የሚኖሩባት ሀገር ነች፡፡ ይህ ትስስር በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም፣ በመተማመንና በፍቅር የሚገለጽ ግንኙነት እንዲጠናከርና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ዘላቂ አንድነት እንዲፈጠር የሚያስችል ሥርዓት የግድ መኖር አለበት፡፡ አንዱ ሌላውን የሚያጠቃበት፣ ያንዱ ድምጽ በሌላው የሚታፈንበት፣ አንዱ በሌላው ላይ ፍላጐቱን የሚጭንበት ሁኔታ…ወዘተ መፍትሄ እስካልተፈለገለት ድረስ ጤናማ፣ ትስስርና አንድነት መመስረት አይቻልም፡፡ በተለያየ ምክንያት የሚፈጠሩ ልዩነቶችን ለማጥበብ የሚረዳው ትክክለኛ መንገድ ደግሞ በመከባበር፣ በመደማመጥና በመቻቻል አንድ ዓይነት







መግባባት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ከግለሠቦች ጀምሮ በማህበረሰቦችና በሀገር ደረጃ የሚከሰቱ ልዩነቶችን እያጠበቡና እየተቻቻሉ አብሮ ለመኖር በቅድሚያ መስጠትና መቀበልን መልመድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ መግባባት በኢትዮጵያ እንዲፈጠር ማድረግ ከስምምነት (ከኮንሰንሰስ) ዴሞክራሲ ጠቃሚ እሴቶች መካከል ዋነኛው ነው፡፡

በቅንጅት እምነት በኢትዮጵያ ውሰጥ መሠረተ ሠፊ ዲሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሠላምና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ ከሶሻል ዲሞክራሲና ከስምምነት (ከኮንሰንሰስ) ዴሞክራሲ ጠቃሚ እሴቶችን መውሰድና ከራሱ መሠረታዊ እሴቶች ጋር አዋህዶ ስራ ላይ ማዋል የሚችል የግለሰብ ነፃነትን የሚያከብር ዲሞክራሲያዊ መርህ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የቅንጅቱን ራዕይ ተልዕኮና ዓላማ የሚገዙ ቁልፍ እሴቶችና መሠረታዊ እምነቶች እነዚህ ከላይ የተገለፁት ናቸው፡፡

የመናገርና የመደራጀት መብት፣ የሥልጣን ክፍፍልና ሥልጣንን ወደ ሕዝቡ የክልል የራስ በራስ አስተዳደር ማውረድ፣ የሕግ የበላይነት፣ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት መዘርጋት፣ የግል ሃብት ባለቤትነትና የኢኮኖሚ ነፃነት፣ የሚሉትም ቅንጅት የሚመራባቸው ቁልፍ እሴቶችና እምነቶች ናቸው፡፡

በቅንጅት እምነት የፖለቲካ መረጋጋት ሊረጋገጥ የሚችለው እነዚህ የሊበራሊዝም እሴቶች ሲከበሩ፣ በሲቪል ማህበረሠቡና በዴሞክራሲያዊ መንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በእነዚህ መርሆዎች ላይ ሲመሠረት ብቻ ነው፡፡ በቅንጅት እምነት የሊበራል የገበያ ኢኮኖሚ መርሆዎችን ከኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ በማራመድ ጠንካራ የካፒታል ክምችትና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ እነዚህን እሴቶችና መርሆዎች በመጠበቅ በራሣችን ልዩ ሁኔታ ላይ ተመስርተን ሥራ ላይ በማዋል ሀገራችን አሁን ለተጋፈጠቻቸው ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ይቻላል ብሎ ቅንጅት ያምናል፡፡

## *1.4 ቅንጅትና አባል ድርጅቶች ያደረጓቸው ትግሎች*

ቅንጅት በትግል ልምዳቸውና በመንቀሳቀሻ ክልላቸው የተለያዩ፤ ነገር ግን የዓላማ አንድነት ያላቸው አራት ፓርቲዎች በቅንጅት የፈጠሩት የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም የፓርቲው ትግል በሚታሰብበት ጊዜ ሁኔታውን ከዚህ የፓርቲው ልዩ ባህሪይ ጋር በማገናዘብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ቅንጅት የጀመረውን ትግል ከግቡ ለማድረስ የመረጠው ስልት ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ነው፡፡ ይኽንን ሠላማዊ የትግል ስልት መከተል ያስፈለገው የጠመንጃ ትግል ከሚጠይቀው መስዋዕትነትና ዋጋ በቀለለ መንገድ ውጤት ያስገኛል ከሚል ስሌት አይደለም፡፡ የጠመንጃ ትግል መስዋዕትነት እንደሚጠይቅ ሁሉ ሠላማዊ ትግልም የሚጠይቀው ዋጋ አለ፡፡ የሠላማዊ ትግል ስልት ተመራጭ የሚሆነው አነስተኛ መስዋዕትነትና ዝቅተኛ ዋጋ ስለሚያስከፍል ሣይሆን ይልቁንም ከጠመንጃ ትግል ጋር ሲወዳደር የላቀ ውጤት ስላለው ነው፡፡ የጠመንጃ ትግል አንዱን ኃይለኛ በሌላ ኃይለኛ የመተካት አዙሪት ውስጥ ከማስገባት አልፎ የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ዕድል አይሠጥም፡፡ ሠላማዊ ትግል ደግሞ ኃይልን በኃይል ከመተካት ይልቅ በሃሣቦች ዙሪያ በሚደረግ ክርክርና ፍጭት የሰውን ዕምነት የሚገዛው ሃሣብ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ በማድረግ የሕዝቡን ሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

የቅንጅት ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ሀቀኛ ዴሞክራሲና አስተማማኝ ሠላም በማስፈን የዘላቂ ልማትና ብልፅግና ባለቤት የሆነ ሠላማዊ ኅብረተሰብ መፍጠር ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ መሣካት ደግሞ ትክክለኛው አማራጭ ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ማድረግ ነው፡፡ ሠላማዊ የትግል ስልት ተመራጭ የሚሆነው የሰው ልጅ የማይቀር ግዴታ ከሆነው ሞት የማዳን ምትሃታዊ ኃይል ስላለው አይደለም፡፡ ይልቁንም ሠላምን አስተማማኝ በሆነ መንገድ የማምጣት ዓላማ ለያዘ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የሰውን እምነትና ልቦና የሚገዛ ትክክለኛ ሃሣብ ከማራመድ የበለጠ ነገር ስለሌለና የሰውን ልጅ መግደል ተገቢ ስልት ባለመሆኑ ነው፡፡

በጠመንጃ ኃይል የተገኘ ሥልጣን ሕጋዊነት የሌለው ሲሆን በሰላማዊ ትግል የሚገኝ ሥልጣን ግን በሕዝብ ፈቃድና ነፃ ውሣኔ የሚገኝ በመሆኑ ሕጋዊነቱና ተቀባይነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ በትጥቅ ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም ተሠላፊዎች መሪዎች ሣይሆኑ የትግሉ ተከታዮችና







ደጋፊዎች ናቸው፡፡ በሠላማዊ ትግሉ ደግሞ በፍልሚያው ወረዳ ቀድመው የሚገኙት መሪዎቹ እንጅ የትግሉ ተከታዮችና ደጋፊዎች አይደሉም፡፡ የተከታዩችና ደጋፊዎች ድርሻ የመሪዎቹን አርዓያነት እየተከተሉ የማያቋርጥ ድጋፍ መስጠትና ትግሉን ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

ቅንጅት በዚህ መሠረታዊ አስተሣሠብ እየተመራ የወያኔ/ኢሕአዴግ የጭቆና አገዛዝ እንዲያበቃና በምትኩ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲመሠረት ከፍተኛ ትግል እያደረገ ነው፡፡ የቅንጅቱ አባል የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝቡን አደራጅተው ለለውጥ እንዲንቀሣቀስ በሚያስችል ሠላማዊ ትግል ውስጥ ገብተው መስዋዕትነት እየከፈሉ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውሰጥ የሠፈነው ፍትህ አልባ ሥርዓት በሕዝቡና በሀገሪቱ ላይ ያደረሠው ጥፋት በጥልቀት እንዲታወቅ ሠፊ ትግል አካሂደዋል፡፡ በሕዝቡ ውስጥ የትግል ተነሳሽነትና ፍላጐት እንዲጐለብት፣ የመንፈስ መነቃቃትና ዝግጁነት እንዲፈጠር ጥረት አድርገዋል፡፡

ለትግሉ አስፈላጊ የሆነውን የመንፈስ ዝግጁነት ከመፍጠር ጐን ለጐን ሕዝቡ የተደራጀ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲችል አቅጣጫ የማመላከት፣ የማስተባበርና የማቀናጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ የአገዛዙን ገመናዎች የሚያጋልጡ፣ ዜጐች ለነፃነታቸውና መብታቸው መከበር ማድረግ የሚገባቸውን ትግል የሚያሣዩ በርካታ የውይይት መድረኮች በሀገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት ተዘጋጅተዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያየ መልክና ይዘት የተቀነባበሩና በፍትህ አልባነት ላይ የሚያነጣጥሩ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡

የተገኙትን አጋጣሚዎች ሁሉ በመጠቀም ከወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ መሪዎች ጋር የመድረክ ላይ ክርክሮች ተደርገዋል፡፡ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሕዝቡን ግንዛቤ የሚያዳብሩ ሕዝባዊ ስብሠባዎች በአዳራሾችና በአደባባዮች ተካሂደዋል፡፡ የሕዝቡን ብሶትና ቅሬታ በአደባባይ ለመግለጽ የሚያስችሉ የተቃውሞ ስብሠባዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህ ረገድ እንደምሣሌ የሚጠቀሱት በአዲስ አበባ፣ በአምቦ፣ በናዝሬት፣ በሐረር፣ በጅማ፣ በአዋሣ፣ በባህር ዳር፣ በደብረ-ማርቆስ፣ በጐንደር፣ በደሴ፣ በመቀሌ፣ በደብረ ብርሃንና በሌሎችም የወረዳ ማዕከላትና የገጠር ቀበሌዎች የተዘጋጁት መድረኮች ናቸው፡፡

ሕዝቡ የትግሉን ባህርይና አቅጣጫ በየጊዜው እንዲገመግምና የራሱን ተሣትፎ እንዲያጠናክር የሚያግዙ በራሪ ጽሑፎች፣ ፖስተሮች፣ ጋዜጦችና

መጽሔቶች እየተዘጋጁ ተሠራጭተዋል፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጁ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተደርገዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ጥረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሣይሆን በውጭው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያን በሚገኙበት አካባቢ ሁሉ ተካሂደዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመመስረት ትግል በዋነኛነት የራሣችን ብሔራዊ ጉዳይ ቢሆንም የዴሞክራሲ መጥፋት፣ የሠብዓዊ መብት መጣስና የሠላም መናጋት የሚያስከትለው መዘዝ ለሌሎችም መትረፉ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ለዴሞክራሲ ሥርዓት የምናካሂደው ትግል ለኢትዮጵያ በጐ አመለካከት ባላቸው የውጭ ወዳጆችና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ሊታወቅና ሊደገፍ ይገባዋል፡፡ ይህንን እምነት በመከተል ስለሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሠብ የማሣወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ጥረት አዲስ አበባ በሚገኙ የውጭ ሀገር ኤምባሲዎች ብቻ የተወሠነ ሣይሆን የተለያዩ ሀገራት መሪዎችና ባለሥልጣኖች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የሠብዓዊ መብት ተንከባካቢ ተቋሞች ተወካዮች ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ቁጥር የተደረጉ ውይይቶችን ይጨምራል፡፡ በመላው ዓለም በሚደረግ ዝውውር ከተለያዩ ሀገራት ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ዓለም አቀፍ ተቋሞች ኃላፊዎች ጋር ግንኙነቶች በመፍጠር የተደረጉ ጥረቶች በርካታ ናቸው፡፡

የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ቅሬታዎች እንዲገነዘብና ድጋፉንም እንዲሠጥ ከተደረጉት ከፍተኛ ጥረቶች መካከል የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት ተከትሎ በአልጀርስ የተደረሠውን ስምምነት በመቃወምና የድንበር ኮሚሽኑ ይኸንን ስምምነት መሠረት አድርጐ ብይን ከመስጠት እንዲቆጠብ በመጠየቅ ከሕዝብ የተሠበሠበው ፔቲሽንና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቀረበው አቤቱታ በምሣሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ አቤቱታ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከመቅረቡ በፊት የሀገሪቱ ፓርላማ እንዳያፀድቀው ሕዝቡ በአደባባይ ተቃውሞውን ከማሰማቱም በላይ በፓርላማው ስብሠባ ላይም በጽሑፍ የተዘጋጀ የተቃውሞ አቤቱታ አቅርቦ ምላሽ ሣይሠጠው ቀርቷል፡፡

እነዚህ ትግሎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሲደረጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሣየው ተሣትፎና ያደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነው፡፡ በሕዝቡና በቅንጅቱ አባል ድርጅቶች የታየው መደጋገፍ በአገዛዙ ላይ ያሣደረው ተፅእኖም ከባድ ነው፡፡ አገዛዙ በውስጥ ችግሮች እንዲወጠርና እርስ በርሱ እየተጠላለፈ እንዲዳከም ያደረገው ይኸው የተቀናጀ የሕዝቡ ግፊት ነው፡፡ የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች






ሠላማዊ ትግል ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ እያገኘ መምጣቱ ለገዥው ፓርቲ ሠላም እንዳልፈጠረለት የታወቀ ነው፡፡ የቅንጅቱ ሃሣቦች በሕዝብ እየተወደዱና ተቀባይነታቸው በፍጥነት እየጨመረ መምጣቱን ለመቀበል ትዕግሥት ያጣው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ቅንጅቱንና አባል ፓርቲዎችን ለማዳከም የተቀነባበረ አፈናና ግፍ ፈጽሟል፡፡ የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች መሪዎች፣ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው በጥይት ተደብድበው ሞትና የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፤ በተለያዩ ወህኒ ቤቶች ታስረው ተሠቃይተዋል፡፡ በመላ ሀገሪቱ ከተማና ገጠር የሚገኙ የፓርቲዎች አባላት በመንግሥት ታጣቂዎችና በካድሬዎች የሚፈፀምባቸው የሠብዓዊ መብት ረገጣ ቃላት ሊገልፀው ከሚችለው በላይ ነው፡፡ በመንግሥት መገናኛ ብዙሃንና በገዥው ፓርቲ ልሣኖች በተከታታይ የሚነዛው አሉቧልታና የስም ማጥፋት ዘመቻም ከፍተኛ ነው፡፡

ሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት መቃወም ብቻ የሚፈለገውን ለውጥ እንደማያስገኝ በመገንዘብ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሠላምና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ ገንቢ አማራጮችን አጥንቶ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከአምስት አመታት በፊት ተካሄዶ በነበረው ሀገራዊ ምርጫ ተወዳድሮ የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት በተዘጋጁ መድረኮችና በተካሄዱ ክርክሮች ላይ ገንቢ አማራጮችን በማቅረብ ከፍተኛ ትግል በመደረጉ የመራጩን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ቢቻልም በገዥው ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኙት የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፣ የመከላከያ ሠራዊት፣ የፖሊስና ደህንነት ተቋሞችና ቢሮክራሲው ተቀናጅተው በፈፀሙት ሕገ ወጥ ተግባር የሕዝቡን ድምፅ ነጥቀዋቸዋል፡፡

## *1.5 የቅንጅት ልዩ ባህርያት*

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ቅንጅትን ልዩ የሚያደርጉ ዋና ዋና ነጥቦች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

1.5.1 ኢትዮጵያ የተለያየ ባህል፣ የተለያየ ኃይማኖትና የተለያየ ፖለቲካዊ እምነት ወዘተ ያለው ሕብረተሰብ የሚኖርባት ሀገር እንደመሆኗ ልዩነቶችን ለማቻቻልና ለማጥበብ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ለመፍጠርና የጋራ ልማትና ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ የሚያስችለው አሠራር ለኮንሰንሰስ (ለስምምነት) ዴሞክራሲ እሴቶች ዋጋ የሚሠጥ የሊበራል ዴሞክራሲ መሆኑን የሚያምን ሕብረ-ብሔር የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡

1.5.2 በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ እንደመጥፎ ገጽታ የሚታዩ የእርስ በርስ ግጭቶች፣ ደም ያፋሰሱ ጦርነቶችና እልቂቶች በተለያዩ ምክኒያቶች ተከስተዋል። በሀገራችን የሚመሠረተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማይናወጥ ጠንካራ መሠረት ላይ መቆም ካለበት የእስካሁኑ የጥላቻ፣ የበቀልና ያለመተማመን ምዕራፍ ተዘግቶ ለተከታታይ ትውልድ የሚዘልቅ አዲስ ምዕራፍ መከፈት ይኖርበታል። በመሆኑም እያንዳንዳችን ከራሣችን፣ ሕዝብ ከሕዝብ፣ መንግሥት ከሕዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር ለመግባባት የሚችሉበት ብሔራዊ ዕርቀ ሠላም ከሁሉ በፊት መቅደም አለበት ብሎ ቅንጅት ያምናል።

1.5.3 ቅንጅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የተለያየ ልምድ፣ አሠራርና ዝንባሌ ያላቸውን አራት ሕብረ-ብሔር ፓርቲዎች በማስተሳሰር ልዩነቶችን በውይይት፣ በድርድርና በመቻቻል ማስወገድ እንደሚቻል በተጨባጭ ያረጋገጠ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

1.5.4 ቅንጅት ከታችኛው የፓርቲው መዋቅር ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራር ድረስ ሠፊ የወጣቶችና በተነጻጻሪነት የተሻለ የሴቶች ተሣትፎ እንዲኖር በማድረግ እያደገ በሚሄድ ጠንካራ የወጣት ኃይልና የሕብረተሰቡን ልዩ ልዩ ፍላጐቶች ለመወከል በሚያስችል ልዩ ቅንብር የተገነባ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

1.5.5 ግልፅ ሆነው በተቀመጡ መመዘኛዎች ላይ ተመስርቶ የሚቋቋም የፌደራል ሥርዓት፣ ባለሁለት ምክር ቤት ፓርላሜንተሪ የመንግሥት ቅርጽና ሕገ-መንግሥቱን የመተርጐም ኃላፊነት ያለው ሕገ-መንግሥታዊ ምክር ቤት መቋቋም እንዳለበት አቋም የያዘ ሕብረ-ብሔር የፖለቲካ ድርጅት ነው።

1.5.6 የኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ በታሪክ፣ በሕግና በዲፕሎማሲ ትግል የማስከበር ዓላማውን በፕሮግራሙ ውስጥ በግልጽ ማስቀመጡም ቅንጅትን ልዩ ያደርገዋል።

1.5.7 ቅንጅት በኢትዮጵያ የግል ሃብትና ንብረት ባለቤትነት መብት ሁነኛ ዋስትና እንዳለው የሚረጋገጠውና ራሳቸውንና ሀገሪቱን ለመጥቀም ፍላጐት ያላቸው የግል ባለሃብቶች በሙሉ ልብ ወደልማት እንዲገቡ





ቀዳሚ መተማመኛ መፍጠር የሚቻለው ድንጋጌዎችን በመጻፍ ብቻ ሣይሆን የሚጨበጥ ተግባር በመፈፀም ነው ብሎ ያምናል። ከዚህም በመነሣት በደርግ መንግሥትና በወያኔ/ኢሕአዴግ ያለ አግባብ የተወሠዱ የግለሠብ፣ የማሕበራትና የመንግሥት ንብረቶች ለሕጋዊ ባለቤቶቹ እንዲመለሱ በፕሮግራሙ ውስጥ በግልፅ ያስቀመጠ ሕብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅት ሲሆን ይህ አቋሙ ዝርፊያና ውንብድና መሸለም አይገባውም ከሚለው እምነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ይህ አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረትን የመመለሱ ተግባር አፈፃጸም በዜጐች ላይ መፈናቀል፣ የዋጋ ውጣ ውረድና መመሰቃቀል እንዳያስከትል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የመፍትሄ አማራጮችን ከመፈለግ ባሻገር ሕዝብን ባሳተፈ፣ ተቀባይነት ባለው ስልትና የሕግ ሥርዓት ይመራ ዘንድ ቅንጅቱ ተገቢ ጥናትና ጥንቃቄ ያደርጋል።

# 2. ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ውድቀቶች

ባለፉት 14 ዓመታት ነፃ በሆነ ምርጫ የሕዝቡን ፈቃድና ውክልና ሣያገኝ በጠመንጃ ኃይል ኢትዮጵያን ሲገዛ የቆየው መንግሥት የሀገሪቱን መሠረታዊ ጥቅሞች የሚጐዱ በርካታ ጥፋቶችን ፈጽሟል። እነዚህ ጥፋቶች ኢትዮጵያን ለከፍተኛ ውድቀት የጋበዙ ብቻ ሣይሆኑ በወደፊቱ ሕልውናዋም ላይ ፈታኝ አደጋዎችን ከመደቀን አልፈው እጅግ የተወሣሠቡና በቀላሉ መፍትሔ የማይገኝላቸው ናቸው። ይህ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ችግሮችን እንዲባባሱና ስር እንዲሠዱ ከማድረጉም በላይ በርካታ አዳዲስ ችግሮችንም ፈጥሯል። ለሀገሪቱና ለሕዝቡ መሠረታዊ ጥቅሞች ደንታ ቢስ ሆኖ ከመቆየቱም በላይ አደገኛ ፖሊሲዎችን እንዲቀይር ከሕዝብ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብለትም ፈቃደኛ ሣይሆን ቀርቷል። ይህ መንግሥት የሀገሪቱን ችግሮች የመፍታት ፍላጐትና ዝግጁነት ቢኖረው ኖሮ ያለፉት 14 ዓመታት አጭር ጊዜያት አልነበሩም።

የኢትዮጵያ ችግር በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ እየተከማቸ የመጣና ስር የሠደደ ከመሆኑም በላይ በዓይነትና በመጠን እየጨመረ እንጂ እየቀነሠ አልሄደም። አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ "ገጠርን ማዕከል ያደረገ ግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂ" ሲሆን ተግባራዊ መሆን የጀመረው ከ10 ዓመታት በፊት ነበር። ይሁን እንጂ በስትራቴጂው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ማለትም በ1987/88 እና በ1988/89 ለእርሻ የሚመች የአየር ፀባይ በማጋጠሙና ተጨማሪ መሬት ሊታረስ በመቻሉ መጠነኛ የምርት መጨመር ከመታየቱ በስተቀር የሀገራችንን ኤኮኖሚያዊ ችግር የሚያቃልል ዘላቂ መፍትሔ ባለማምጣቱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በተከሠተ ድርቅ ከፍተኛ ረሃብ ተፈጠረ።

እስካሁን ድረስ ዝናብ ሲኖር ምርት እየጨመረ፣ ዝናብ ሲጠፋ ደግሞ ምርት እየቀነሰ ኤኮኖሚው የዝናብ ጥገኛ እንደሆነ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ዋነኛ ችግር የዝናብ ጥገኛ በሆነ ባህላዊ ግብርና ላይ የተመሠረተ መሆኑና መዋቅራዊ ሽግግር አለማድረጉ ነው። የአገዛዙ ብልሹ ፖሊሲ ውጤቶች በተለያየ መንገድ የሚገለፁ፣ አይነታቸውና መጠናቸው የበዛ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።







## 2.1 የአገልግሎት ዘርፍ አለመስፋፋት

የኢትዮጵያ አገልግሎት ዘርፍ በዋናነት በማከፋፈልና ሌሎች አገልግሎቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ያለው ድርሻ 41% ገደማ ነው። ባለፉት 12 ዓመታት ከአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ የማከፋፈያ አገልግሎት ንዑስ ዘርፍ (ይህ ንዑስ ዘርፍ ንግድና ሆቴልን፣ ምግብ ቤትን፣ ትራንስፖርትና መገናኛን ያካትታል) ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ በአማካይ 14% ገደማ ነው። ይህ ደግሞ በደርግ መንግሥት ለ17 ዓመታት ከነበረው አማካይ ድርሻ ጋር ተመሣሣይ ነው። ሌሎች አገልግሎቶች የሚባሉት የባንክን፣ የመድህንን፣ መስተዳድርን፣ ትምህርትን፣ ጤናን፣ መከላከያንና የመሣሠሉትን የሚያካትት ሲሆን ባለፉት 12 ዓመታት ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ያለው ድርሻ 27% ገደማ ነበር። በደርግ መንግሥት ጊዜ በአማካይ ከተመዘገበው 17% ድርሻ የበለጠ መሆኑን ቢያሳይም ዕድገቱ ዘላቂና ትርጉም ያለው እንዲሆን የመከላከያና የመስተዳደር ድርሻ እየቀነሠ መምጣት አለበት። የመስተዳድርና የመከላከያ ድርሻ በደርግ ጊዜ በአማካይ ከነበረው 7% ባለፉት 13 ዓመታት በአማካይ ወደ 12% አድጓል። በአንጻሩ ባንክና ኢንሹራንስ በተመሣሣይ ጊዜ ያሣዩት ዕድገት 2% ብቻ በመሆኑና ከዚህ በባሠ ደግሞ ትምህርት ያደገው በ0.3% ብቻ በመሆኑ ሀገሪቱ እጅግ አስፈላጊ በሆኑት የአገልግሎት ንዑስ ዘርፎች ያስመዘገበችው ዕድገት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

## *2.2 ዘላቂ ዕድገት የማይታይበት ቁጠባና ካፒታል ምሥረታ*

የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ዋነኛ ገጽታ ዝቅተኛ የቁጠባ ደረጃ ያለው መሆኑ ነው። ለዚህ ሁኔታ መከሠት ትልቁ ምክንያት የዜጐች የነፍስ ወከፍ ገቢ አነስተኛነት ነው። ባለፉት 13 ዓመታት ደግሞ የነፍስ ወከፍ ገቢ ይባሱኑ እያሽቆለቀለና የዜጐች የመቆጠብ አቅም እየወረደ በመምጣቱ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃም በሚያሣዝን ሁኔታ ወድቋል። በ1960ዎቹ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ የነበረው ድርሻ 14.2% ሲሆን በ1970ዎቹ ወደ 9.7% ወርዷል። በ1980ዎቹ ደግሞ ወደ 7.5% ዝቅ ሲል፣ ባለፉት 13 ዓመታት ግን የባሠውኑ በመቀነስ ወደ 4% ደርሷል።

ከ1980/85 ጀምሮ የአሁኑ መንግሥት የፋይናንስ ማረጋጊያ እርምጃዎችን ለመውሠድ ቢሞክርም የሀገር ውስጥ ቁጠባ ደረጃ ማሽቆልቆልን ሊገታው አልቻለም። በተሃድሶው ጊዜ ውስጥ የተመዘገበው የሀገር ውስጥ

ቁጠባ ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው አማካይ ድርሻ መጠን ከዚያ በፊት በነበሩት 30 ዓመታት ከታየው ያነሠ ነው፡፡ እንደውም በአንዳንድ ዓመታት ወደ ዜሮ የተጠጋበትና ከዜሮ በታች የወረደበትም ጊዜ አለ፡፡ ለምሣሌ፣ በ1991/92 0.9% እና በ1994/95 ደግሞ ከዜሮ በታች -2.1% የተመዘገበባቸው ዓመታት ናቸው፡፡

በካፒታል ምስረታ ረገድ ከ1984/85 ጀምሮ ከዚያ በፊት ከነበሩት 30 ዓመታት የተሻለ ዕድገት ቢያሣይም ዕድገቱ የተገኘበት ምንጭ ግን ጤነኛ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የካፒታል ምስረታ መሻሻል ያሳየው የሀገር ውስጥ ቁጠባ በቀነሰበት ጊዜ በመሆኑ የዕድገቱ መነሻ የውጭ ብድርና ዕርዳታ እንጅ ሀገሪቱ ቆጥባ ባገኘችው በራሷ ሃብትና ጥሪት ላይ ባለመመስረቱ ነው፡፡ በጠንካራ የሀገር ውስጥ ቁጠባ የማይተማመን የካፒታል ምስረታ ደግሞ ኤኮኖሚው የሚያስፈልገውን የኢንቨስትሜንት ገንዘብ ለማግኘት የውጭ ብድርና ዕርዳታን መጠበቅ ስለሚያስከትል ለከፋ ጥገኝነት ያጋልጣል፡፡ ለምሣሌ በ1994/95 ከተመዘገበው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ካፒታል ምስረታ 110% ያህሉ የመነጨው ከውጭ ብድርና ዕርዳታ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የወጪና ገቢ ንግድ ሚዛን መዛባት እንዲቀጥል የሚያደርግ፣ የሀገሪቱን የውጭ ዕዳ ክምችት የሚያባብስና የሀገር ውስጥ ሃብትን ጥቅም ላይ የማዋል አቅምን የሚያዳክም በመሆኑ ከፍተኛ የሪሶርስ ክፍተት (Resource gap) ይፈጥራል፡፡ በ1994/95 ሀገሪቱ ያለባት የውጭ ዕዳ መጠን ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ ወደ 107% ገደማ የነበረ ሲሆን ይህ አሀዝ በኢትዮጵያ ዝቅተኛ የካፒታል ምስረታ በታየበት 1983/84 ዓ.ም. ተመዝግቦ ከነበረው የ20% እና 30% የውጭ ዕዳ ድርሻ መጠን በ5 እና 4 እጅ የበለጠ ነው፡፡

## 2.3 ኢንቨስትመንት

### 2.3.1 የግል ኢንቨስትመንት

በሀገሪቱ ያለው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ካፒታል ጥንቅር ሲታይ የኢትዮጵያዊያን ባለሃብቶች ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ከ1984/85 ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ከጠቅላላው የኢንቨስትመንት ካፒታል ውስጥ ያላቸው ድርሻ 65% ገደማ ሲሆን ከጠቅላላው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውስጥ ደግሞ ድርሻቸው 95% አካባቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የግል ኢንቨስትሜንት ዘላቂ ዕድገት በማሣየት ፋንታ የማሽቆልቆል አዝማሚያ ይታይበታል፡፡ በተለይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ





ካገኙ በኋላ ወደ ስራ የሚገቡት ቁጥር በየጊዜው እየቀነሠ ነው፡፡ የግል ባለሃብቶች በራሣቸው ካፒታልም ይሁን ከባንክ ተበድረው የሚያኙትን ገንዘብ ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ ባንክ በማስቀመጥ ከሚገኝ ወለድ የመጠቀም ፍላጐት በማሣየታቸው ለልማት መዋል የሚገባው ገንዘብ በባንክ እንዳይከማችና ብድር ወስዶ ለማልማት የሚያደፋፍር ሁኔታ እንዲኖር መንግሥት ከ1993/94 ጀምሮ ከባንክ ቁጠባ የሚገኘውን የወለድ ምጣኔ ከ6% ወደ 3%፤ ተበዳሪዎች የሚከፍሉትን የወለድ ምጣኔ ደግሞ ከ10.5% ወደ 7.5% ዝቅ እንዲል አድርጐታል፡፡ ይኸንኑ ተከትሎ በሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የቀረቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ቁጥርና ካፒታል ከበፊተኞቹ ዓመታት ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ዕድገት ቢያሳይም በአንድ በኩል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ቁጥር ሲያድግ የካፒታላቸው መጠን የሚያንስበት ሁኔታ መኖሩና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሠዱ በኋላ ወደ ስራ የሚገቡት ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑ አሁንም ያልተፈታ ችግር ነው፡፡

የውጭ ኢንቨስትሜንት ተሣትፎ ከሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ጋር ሲነፃፀር በፕሮጀክቶች ቁጥርም ሆነ በካፒታል መጠን ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ከዓመት ወደ ዓመት መቀነስ ይታይበታል፡፡ የኢንቨስትሜንት ሕጉ በተደጋጋሚ ጊዜ ቢሻሻልም ሀገራችን የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሣብ ያሣየችው ውጤት በማንኛውም መመዘኛ ዝቅተኛ ነው፡፡ ከሠሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች ከ1983-1986 ከጠቅላላው ቋሚ ኢንቨስትሜንት ውስጥ 3.71% ብቻ የነበረውን ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትሜንት ድርሻ ከ1987-1990 ባሉት ዓመታት ወደ 10% አሣድገውታል፡፡ በኢትዮጵያ ግን በ1992/93 እና በ1993/94 ከነበረው ጠቅላላ ቋሚ ኢንቨስትሜንት ውስጥ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትሜንት ድርሻ 0.9% ብቻ ነበር፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትንና ካፒታልን መሣብ ካልተቻለ ኤክስፖርትን ለማስፋፋት፣ ለቴክኒዎሎጂ ሽግግር፣ ከሀገር በቀል ተቋሞች ጋር ትስስር ለመፍጠርና የሥራ ዕድል ለመክፈት አይቻልም፡፡ ወደ ልማት ከተሸጋገሩት መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ሲሆኑ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ድርሻ ግን አነስተኛ ነው፡፡ ለኢንቨስትመንት ዕድገት አዝጋሚነትና ዘላቂነት ማጣት ዋነኛው ችግር ባለሃብቶችን የሚስብ ፖሊሲና ምቹ ሁኔታ አለመኖሩ ነው፡፡

### 2.3.2 የመንግሥት ኢንቨስትመንት

የመንግሥት ኢንቨስትመንት በፕሮጀክት ቁጥርም ሆነ በካፒታል መጠን ዕድገት አይታይበትም፡፡ በ1993/94 ዓ.ም የመንግሥት ኢንቨስትመንት

ካፒታል ከ108 ሚሊዮን ብር ወደ 1.6 ቢሊዮን ብር ቢያድግም ይህ መጠን በ1990/91 ከነበረው ጋር ሲነጻጸር በ72% ያነሠ ነው። በአጠቃላይ በሀገራችን ያለው የኢንቨስትሜንት እንቅስቃሴ በፍጥነትና በዘላቂነት የሚያድግ ሣይሆን አዝጋሚ ነው። ከዚህም በላይ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካገኙት ፕሮጀክቶች መካከል ወደ ስራ የሚገቡት አማካይ ቁጥር አነስተኛ ነው። ከ1984/85-1993/94 ባሉት 10 ዓመታት ውስጥ ለጠቅላላው የኢንቨስትሜንት ፈቃድ ካገኙት ፕሮጀክቶች መካከል ወደ ልማት የተሸጋገሩት በአማካይ 29% ብቻ ናቸው።

## 2.4 ሚዛኑ የተዛባ የወጪና ገቢ ንግድ

የካፒታል ዕቃዎችና ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ ከሚገኝባቸው ምንጮች መካከል የኤክስፖርት ገቢ አንደኛውና ዋነኛው ነው። በኤክስፖርት ገቢ መቀነስ የሚከሰት የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ዕጥረት ለምርት አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎች ከውጭ ለማስገባት የሚያስችል የኢምፖርት ፋይናንስ አቅም እንዳይኖር ያደርጋል። ከውጭ ማስገባት ለሚገባን ነገር መግዣ የሚሆን በቂ የኤክስፖርት ገቢ ሲጠፋ እጅግ መሠረታዊ ዕቃዎችን ለመግዛት ከውጭ ለመበደር ስለምንገደድ የዕዳ ጫና ይበዛል። በዚህ ላይ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትሜንትን ለመሣብ አለመቻሉ ሲታከልበት የካፒታልና ሌላም አስፈላጊ ዕቃዎችን ከውጭ ለመግዛት ያለንን አቅም ውስን ያደርገዋል።

የሀገራችን ኤክስፖርት ገቢ አንድ ችግር ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት በተወሠኑ የኤክስፖርት ምርቶች ላይ የተመሠረተ መሆኑና በተለይም ለውስጥና ለውጭ ተፅእኖዎች ተጋላጭ በሆነው ቡና ላይ ጥገኛ መሆኑ ነው። ከቡና ውጭ ያሉት የኤክስፖርት ምርቶች የተወሰነ የአቅርቦት መሻሻል ቢያሳዩም በዓይነትም ሆነ በመጠን እጅግ አነስተኛ በመሆናቸው የሀገሪቱን የኤክስፖርት አቅም በሚፈለገው ደረጃ ላይ አላደረሱትም። ዋነኛው የኤክስፖርት ገቢ ምንጭ የሆነው ቡና ደግሞ በዓለም ገበያ ያለው ዋጋ ከዓመት ዓመት እየወደቀ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ኤክስፖርት ከባድ ችግር ገጥሞታል። በ1993/94 ብቻ በቡና ኤክስፖርት የታየው ውድቀት 8.3% ነበር። ከ1962/63 ጀምሮ እስከ 1989/90 ድረስ የሀገሪቱ ኤክስፖርት በዋናነት የቡና ጥገኛ ነበር። በ1989/90 ከጠቅላላው የሀገሪቱ ኤክስፖርት መጠን የቡና ድርሻ 69.8% የነበረ ሲሆን በ1993/94 ወደ 36.1 ቀንሷል። ይህ ሁኔታ የተፈጠረው ቡናን የሚተኩ ሌሎች የኤክስፖርት ምርቶች በዓይነትና በመጠን ከፍተኛ ዕድገት በማሣየታቸው ሣይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዋጋ







በመውደቁ ምክንያት ነው። የዓለም ገበያ ውጣ ውረዱን ለማካካስ ጥራትንና አቅርቦትን ለመጨመርና ለኦርጋኒክ ቡና ምርት ጠንካራ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ፖሊሲና አሠራር አለመኖሩ ደግሞ ሌላው ችግር ነው።

የሀገራችን የኤክስፖርት ችግር በዋነኛነት በአንድ ዓይነት ምርት ላይ ጥገኛ መሆኑ ብቻ ሣይሆን የኤክስፖርት ምርት የምናቀርብባቸው ሀገሮችም ውስን መሆናቸው ጭምር ነው። የምርትና የገበያ ዳይቨርሲፊኬሽን ችግር ያለበት የኢትዮጵያ ኤክስፖርት ጠቅላላ እንቅስቃሴ ደካማ ነው። ከአውሮፓ ጀርመንና ኢጣሊያ፣ ከኤዥያ ጃፓንና ሣውዲ አረቢያ፣ ከአፍሪካ ደግሞ ጂቡቲ የሀገራችን ኤክስፖርት ገበያዎች ሲሆኑ የዚህ ዓይነቱ የንግድ አጋሮች ውስንነት ኤኮኖሚያችን ላልተጠበቁ አደጋዎች ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል። በመሆኑም ባለፉት 40 ዓመታት የኤክስፖርት ገቢያችን ከውጭ ለምናስገባው ዕቃና አገልግሎት የሚያስፈልገንን ወጪ ለመሸፈን ያለው አቅም ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቷል። የኢምፖርት ወጪን በመሸፈን ረገድ የሀገራችን ኤክስፖርት ገቢ አቅም በተከታታይ እየተዳከመ በመምጣቱ የሚሸፍነው የኢምፖርት ወጪ መጠን በአማካይ ከ20-30% ብቻ ነው።

ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሬ በአብዛኛው የምታገኘው ከብድርና ዕርዳታ እንጅ ራሷ ከምታፈራው የኤክስፖርት ገቢ አይደለም። የውጭ ምንዛሬ ዋነኛ ምንጭ የሆነው የቡና ኤክስፖርት በየጊዜው በዓለም ገበያ ለሚከሠቱ የዋጋ ውጣ ውረድ ችግሮች ስለሚጋለጥ አስተማማኝ ሊሆን አልቻለም። የሌጦ ዋጋ ለውጣ ውረድ ችግሮች ስለሚጋለጥ አስተማማኝ ሊሆን አልቻለም። የሌጦ ኤክስፖርትም እየቀነሠ ነው። አግዋ (AGOA) በሚባል ፕሮግራም አሜሪካ ከቀረጥና ኮታ ነፃ በሆነ መንገድ ዕቃዎችን ወደ ሀገሯ እንዲያስገቡ ለተወሠኑ ሀገሮች በመፍቀዷ አንዳንዶቹ ከፍተኛ ጥቅም ሲያገኙ ኢትዮጵያ ግን አጋጣሚውን በሚገባ ልትጠቀምበት አልቻለችም። በአሁኑ ጊዜ አበባን ወደ ውጭ በመላክ ውጤታማ መሆን ይቻላል በሚል መንግሥት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ፍላጎት እንዳለው እየገለፀ ነው። የአበባ ገበያ ከምርት ሂደቱ ጀምሮ በፓኬጂንግ፣ በትራንስፖርትና በግብይት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ የአበባ ገበያ በጥራትና በብዛት ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ ውጤታማ ለመሆን ጊዜ መጠየቁ አይቀርም። ኤክስፖርትን ለመደገፍ ያስችላል በሚል የተቋቋመው የኤክስፖርት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ የታሠበውን ዓላማ ሊያሣካ ቀርቶ የራሱንም ሕልውና ለማቆየት ተስኖት በመንገዳገድ ላይ ነው። በአጠቃላይ በኤክስፖርት ዘርፍ ያለው ችግር ከዓለም ገበያ ውጣ ውረድ ጋር የተያያዘ ብቻ ሣይሆን ይኸንን ለመቋቋም የሚያግዝ ተገቢ ፖሊሲ አለመኖሩም ጭምር ነው። ለኦርጋኒክ ቡና ጠንካራ ድጋፍ

መስጠት የሚያስችል፣ የኤክስፖርት አቅርቦትን መጠንና ጥራት የሚያሣድግ፣ የባለሃብቶችን ተሣትፎ የሚያደፋፍር ፖሊሲና አሠራር ባለመኖሩ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ የኤክስፖርት ምርት በማምረትና ለገበያ በማቅረብ የተሠማሩትን ክፍሎች የሚያበረታታ የመረጃ፣ የሥልጠና፣ የብድርና የሕግ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ እስከሌለ ድረስ ችግሩ መቀጠሉ አይቀርም፡፡

የኢትዮጵያ ገቢ ንግድም (ኢምፖርት) የራሱ ችግሮች ያሉት ነው፡፡ ቀደም ሲል ከነበሩት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በ1993/94 የ11.7% ዕድገት የታየ ሲሆን ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት የኢምፖርት ድርሻ በ1992/93 ከነበረበት 24% በ1994/95 ወደ 28% ደርሷል፡፡ ይህ ዕድገት በውጭ ብድርና ዕርዳታ ላይ የተመሠረተ እንጂ በሀገሪቱ የኤክስፖርት ገቢ መጨመር የተገኘ ባለመሆኑ ጤናማ አይደለም፡፡ ከዚህ ሌላ በቅርብ ዓመታት የኢምፖርት ንግድ ጥንቅሩ ከካፒታል ዕቃዎች ይልቅ ወደ ፍጆታ ዕቃ እያዘነበለ ነው፡፡ ከ1991/92 ጀምሮ የፍጆታ ዕቃዎችን ከውጭ የማስገባት ሂደት እየጨመረ ነው፡፡ የዋጋ ቁጥጥር መላላቱንና የድርቁን መክፋት ተከትሎ እንደ ቴሌቭዥን ሴት፣ መኪናና የምግብ እህል የመሣሠሉት የፍጆታ ዕቃዎችና ምርቶች ከውጭ በግዥ ወደ ሀገራችን እየገቡ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በ1993/94 1.3 ቢሊዮን ብር የሚገመት እህል ከውጭ በግዥ ያስገባች ሲሆን ይኽ አሀዝ በ1992/93 ሀገሪቱ ከውጭ በግዥ ካስገባችው በ104.6% የበለጠ ነበር፡፡

በአጠቃላይ በገቢ ንግድ አልፎ አልፎ የሚታዩ መሻሻሎች ቢኖሩም የውጭ ብድር፣ እርዳታና እዳ ቅነሣ የሚፈጥሯቸው እንጂ ከኤክስፖርት አቅም ዕድገት ጋር በቀጥታ የተያያዙ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ የውጭ ንግድ ሚዛን ጉድለት አለብን፡፡ ከ1990/91 ጀምሮ እየጨመረ የመጣው የንግድ ሚዛን ጉድለት ይበልጥ ተባብሷል፡፡ በደርግ ጊዜ ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ 6% የነበረው የንግድ ሚዛን በአሁኑ ጊዜ ወደ 25% አሻቅቧል፡፡ በቅርቡ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ወደ ሀገር ውስጥ የሚሸጋገረው ገንዘብ መጠን ጥቂት መሻሻል ከማሣየቱ ጐን የንግድ ሚዛን ጉድለት እየተባባሠ ነው፡፡ ለረጅም ዓመታት ከታየው የንግድ ሚዛን ጉድለት ጐን በ1993/94 አጠቃላይ የንግድ ሚዛን መሻሻል ቢያሣይም ለንግድ ሚዛን መሻሻል 85% አስተዋፅዖ ያደረገው ከድህነት ቅነሣ ጋር በተያያዘ የተገኘው የውጭ ብድር፣ ዕርዳታ፣ የዕዳ ክፍያ ጊዜ መራዘምና የዕዳ ስረዛ ድጋፍ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ብሔራዊ ባንክ ያለው መጠባበቂያ በ1994/95 በ3226.3 ሚሊዮን ብር የጨመረው ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ስለዚህ የሀገራችን የገቢና ወጪ ንግድ ሚዛንም ሆነ የመጠባበቂያ አቅም ከውጭ






ብድርና ዕርዳታ ጥገኛነት የሚላቀቁበትና ከሀገሪቱ ኤክስፖርት ገቢ ዕድገት ጋር የሚተሣሰሩበት ፖሊሲ ማውጣት እስካልተቻለ ችግሩ መባባሱ የማይቀር ነው፡፡

## 2.5 ጤናማ ያልሆነ የፋይናንስ ኤኮኖሚ

የፋይናንሱ ክፍለ ኤኮኖሚ የገንዘብ አቅርቦትን፣ መጠንን፣ ጥራትንና የባንክ ሥርዓት አወቃቀርን የሚመለከት ሲሆን በኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ውስጥ የገንዘብ አጠቃቀም የሚገኝበት ደረጃ ዝቅተኛ ነው፡፡ በገንዘብ አቅርቦትና ለልውውጥ በሚቀርበው ዕቃና አገልግሎት መካከል ያለው የዝውውር ፍጥነት ከ1985 ጀምሮ መጠነኛ ውጣ ውረድ የሚታይበት ነው፡፡ ከ1991/92 ወዲህ ይፋዊ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት 2.1% ሲያድግ፣ የገንዘብ አቅርቦት ደግሞ ከ12% በላይ አድጓል፡፡ በውጤቱም ከ1990/91 በኋላ ከገንዘብ የሚገኘው ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ ከ1990 ጀምሮ በወለድ ምጣኔ ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ተደርጓል፡፡

መንግሥት ከብድርና ተቀማጭ ወለድ ምጣኔ ጋር በተያያዘ አብዛኞዎቹን የቁጥጥር ሁኔታዎች ሲያነሣ በ1994 የቁጠባና የማስቀመጫ ጊዜ ዝቅተኛ ወለል ክለሳ በማካሄድ ከ6% ወደ 3% ዝቅ አድርጐታል፡፡ በዚህም የተነሣ በ1992/93 6.3% የነበረው አማካይ የተቀማጭ ምጣኔ በ1993/94 ወደ 3.5% ወርዷል፡፡ አማካይ የብድር ወለድ ምጣኔም ከ12.75% ወደ 10.25% ቀንሷል፡፡ እነዚህ ለውጦች ቢኖሩም እስካሁን ድረስ ባንኮች የብድሩን ፍሰት የሚወስኑት ተበዳሪዎች በሚያቀርቡት የብድር ዋስትና (መያዣ) ጥራት ላይ ተመስርተው እንጂ ብድሩ የሚያስገኘውን ዋጋ ወይንም ትርፍ እያሠሉ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠራር በ1990/91 እና በ1993/94 መካከል ባሉት ጊዜያት በተለያዩ ባንኮች ውስጥ የሚታየው የብድር ምጣኔ ልዩነት በጣም አነስተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በቅርብ ዓመታት ውስጥ መንግሥት ያለበትን የበጀት ጉድለት ለማሟላት የሚያስችል ከፍተኛ ብድር ማግኘት በመፈለጉ አብዛኛውን የሀገር ውስጥ ብድር እየወሠደ ነው፡፡ በ1993/94 ከነበረው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ብድር መንግሥት የወሰደው መጠን 58% ነው፡፡ መንግሥታዊ ያልሆነው የሀገር ውስጥ ብድር መጠን ግን ከ1990/91 ጀምሮ በአማካይ በየዓመቱ በ2.2% እየቀነሰ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከባንክ ብድር ጋር የተያያዙ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ይታያሉ፡፡ እነዚህም የመጀመሪያው ችግር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሠጠው ብድር ውስጥ ከ30% በላይ፤ የልማት ባንክ ከሠጠው

ብድር ውስጥ ደግሞ ከ50% በላይ የሚሆነው የማይመለስ ገንዘብ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው የመንግሥት ባንኮች የትኛው ዓይነት ብድር ጤነኛ እንደሆነና እንዳልሆነ ለመለየት ባለመቻላቸው ለተበዳሪዎች መዋል የሚገባውና ካለአገልግሎት የተቀመጠ 17 ቢሊዮን ብር ገደማ ነው። ከዚህ ውስጥ 98% የሚሆነው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚገኘው ነው። ለባለሃብት የሚሠጠው ብድር መጠን ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ በአማካይ ወደ 19% ቢያድግም ከ1987/88 -1992/93 ያለአገልግሎት በባንክ የተቀመጠ ትርፍ ገንዘብ 46.7% ነበር።

በኢትዮጵያ የኢንቨስትሜንት እንቅስቃሴ እጅግ ደካማ ነው። በዚያው መጠን የቁጠባ አቅማችንም አነስተኛ ነው። በኢንቨስትሜንት ለመሠማራት የሚፈልጉ በርካታ ሰዎች ብድር ለማግኘት ባለመቻላቸው እንዲህ ዓይነት መሠረታዊ ችግር ባለበት ሀገር ውስጥ የግል ባለሃብቶች ለልማት የሚያውሉት ብድር እንዲያገኙ የሚያስችልና የቆጠብነውን ገንዘብ ደግሞ በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ፖሊሲ አለመኖሩ ችግሩን አባብሶታል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በነጻነት እንዲሠራ የሚያስችለው ኦቶኖሚ (ሥልጣን) ስለሌለው የፋይናንሱን ክፍለ ኤኮኖሚ የሚያጠናክር እርምጃ መውሠድ አይችልም። ባንኩ አሁን ሥራ ላይ ያዋለው ፖሊሲ የአንድን ቢዝነስ ወይም የኢንቨስትሜንት ፕሮጀክት አዋጭነት አጥንቶ ብድር ለመስጠት የሚያስችል ሣይሆን በዋስትና የሚያዝ ሃብትና ንብረት መኖሩን እያረጋገጠ ነው። ይህ አሠራር ደግሞ በአንድ በኩል ውጤታማ ፕሮጀክት ኖሯቸው የተሣካ ቢዝነስ መስራት የሚችሉትን እስረኛ ያደረገ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ባንኩ ዋስትና ማቅረብ በመቻላቸው ብቻ ብድር ወስደው ውጤታማ መሆን ያልቻሉትን ተበዳሪዎች ንብረት ሸጦ ገንዘቡን ተመላሽ ለማድረግ ስለተሣነው የሀገር ሃብት እየባከነ ነው።

በፋይናንሱ ኤኮኖሚ ያለው ሌላ ችግር ለግሉ ዘርፍ የሚሠጠው ብድር ትኩረት የአጭር ጊዜ ንግድ እንቅስቃሴ በሚያደርጉት በተለይም ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዙ ሥራዎች ላይ ብቻ ያረፈ መሆኑ ነው። የረጅም ጊዜ ብድር ለሚፈልጉ የግል ባለሃብቶች ማበደር የሚያስችል ተስማሚ ፖሊሲ ጨርሶ የለም። በፋይናንሱ ዘርፍ ለሚታየው ችግር እንደምክንያት ከሚቀርቡት ጉዳዮች መካከል ከብድር ገበያ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ዕጥረት፣ ስለቢዝነስ የወደፊት ትርፋማነት የተዛባ ግንዛቤ መኖር፣ በአበዳሪውና በተበዳሪው መካከል መተማመን መጥፋት፣ ብድርን የመመለስ ባህል አለመዳበርና የመሣሠሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ይሁን እንጂ መሠረታዊው ችግር የፋይናንስ ዘርፉ ተቋማዊ ድክመት፣ ከሁኔታዎች ጋር ሊጣጣም





የማይችል ግትር የአሠራር ሥርዓትና ለዘርፉ እድገት የሚበጅ ሁነኛ ፖሊሲ አለመኖር ነው። በዚህም ምክንያት መንግሥት የሚፈልጋቸውን እየመረጠ ከፍተኛ ብድር ሲሠጥ ለማይፈልጋቸው ደግሞ ይከለክላል። በዚህ ዓይነቱ የብድር ራሽን (ክፍፍል) አሠራር በአንድ በኩል ትርፋማ ያልሆኑና ስትራቴጅያዊ የኤኮኖሚ ጥቅም የሌላቸው ተበዳሪዎች የማይገባቸውን መጠን ይወስዳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ለሀገሪቱ ኤኮኖሚ ትልቅ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ተበዳሪዎች የሚፈልጉትን ብድር አጥተው ባሉበት ሁኔታ ካለአንዳች ጥቅም ባንክ ውስጥ በርካታ ገንዘብ ታስሮ ተቀምጧል።

## 2.5.1 የመንግሥት ፋይናንስ

ይህ ዘርፍ የመንግሥትን ገቢና ወጭ መጠንና አደረጃጀት፣ የታክስ አወቃቀሩንና የመንግሥት ወጪ ጥንቅርን፣ የበጀት ሁኔታንና የገቢ ወይም የበጀት ጉድለት የሚሟላበትን ሥርዓት የሚያጠቃልል ነው። ከ1984/85-1990/91 በነበሩት የበጀት ዓመታት አጠቃላይ የመንግሥት ገቢ ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ የነበረው ድርሻ ከ18.5% እስከ 23% ድረስ የነበረ ሲሆን በ1992/93 እና በ1993/94 ፈጣን ዕድገት አሣይቷል። የመንግሥት ገቢ ዕርዳታን ጨምሮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሠው በ1993/94 በጀት ዓመት ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ ወደ 24.8% በማደጉ ነው። በ1994/95 ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት የነበረው ድርሻ 28.9% ደርሷል።

ከታክስ የሚገኘው ገቢ በ1993/94 ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ ያለው ድርሻ 15.3% ነበር። ይኸ ደግሞ ከ1983/84-1993/94 በነበሩት 10 ዓመታት ውስጥ ከታየው አማካይ ድርሻ በ12% የበለጠ ነው። የገቢ ታክስና የንግድ ትርፍ ታክስ አሠባሠብ በ1993/94 ከፍተኛ ዕድገት ያሣየው የፌደራሉ ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በወሠደው የማሻሻያ እርምጃ ነው። ይሁን እንጂ የታክስ አሠባሰብ ሥርዓቱ ፍትሃዊነት የጐደለውና ከአድሎ ያልፀዳ ነው። የታክስ መሠረቱን በሚያሠፋ ጥናትና አቅምን ባገናዘበ አሠራር ላይ የተመሠረተ ሣይሆን ከዘፈቀደ አወሣሰን ያልተላቀቀና ሕግ አክባሪዎችን የሚቀጣ ነው። የግል ባለሃብቶችን የሚያሸማቅቅ፣ ሠርቶ የመኖር ነጻነትንና ሃብት የማፍራት መብትን ከመጻረር ባሻገር እንቨስትሜንት እንዳይስፋፋ ያደረገ ነው። ወደ ግል ንብረትነት ከተዛወሩት የመንግሥት ድርጅቶች ሺያጭ የተገኘውን ገቢ ሣይጨምር ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የተገኘው ገቢ መጠን ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ 24% ድርሻ ነበረው።

የቅርብ ጊዜ የበጀት አፈጻጸም ሁኔታዎች የሚያሣዩት አዝማሚያ የመንግሥት ወጪ ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ በ1992/93 ከነበረው የ29.1% ድርሻ በ1994/95 በጀት ዓመት ወደ 32.3% ማደጉን ነው፡፡ ከኤርትራ ጋር የነበረው ጦርነት ካበቃ በኋላ በመንግሥት ወጪ ጥንቅርና ባህርይ ላይ ለውጥ ተፈጥሯል፡፡ መደበኛ በጀት በ1991/92 ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ የ26% ድርሻ የነበረው ሲሆን በ1993/94 ወደ 20.4% ቀንሷል፡፡ ይህ ቁጥር በጦርነቱ ወቅት ከነበረው የመደበኛ በጀት ወጪ መጠን ያነሰ ቢሆንም በአለፉት 10 ዓመታት ከነበረው አማካይ ወጪ ግን የበለጠ ነው፡፡ በተነጻጻሪ ሁኔታ የካፒታል በጀት ወጪ በ1984/85 በጀት ዓመት ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርት ውስጥ የነበረው የ6.7% ድርሻ በ1993/94 ወደ 12% አድጓል፡፡ የመደበኛ በጀት ድልድል ጠቅላላ አገልግሎትን፣ የኢኮኖሚ አገልግሎትን፣ ማህበራዊ አገልግሎትን፣ ወለድን፣ የውጭ ድጋፍንና ሌሎችን የሚያካትት ነው፡፡ ከመደበኛ በጀት ወጪ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ጠቅላላ አገልግሎት (መከላከያ፣ ፀጥታና ደህንነት) ሲሆን ከዚህም ወጪ በተለይ ለመከላከያ የተመደበው ከፍተኛ ነው፡፡ በ1994/95 ለጠቅላላ አገልግሎት ተመድቦ ከነበረው 38% ወጪ ውስጥ 50% የሚሆነው የመከላከያ ድርሻ ነው፡፡ ይኸም ማለት ለመከላከያ የተመደበው በጀት 19% ነበር ማለት ነው፡፡

ሌላው የመደበኛ በጀት ባለድርሻ የኤኮኖሚ አገልግሎት ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ በ1994/95 ተመድቦ የነበረው በጀት 10.8% ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለግብርናና ተፈጥሮ ሃብት 5.9%፣ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ደግሞ 1.1% ነው፡፡ አንደኛው የመደበኛ በጀት ባለድርሻ ማህበራዊ አገልግሎት ሲሆን በ1994/95 ለዘርፉ ተመድቦ የነበረው 25.9% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ለትምህርት 18.5%፣ ለጤና 4.3% ተመድቧል፡፡ ከዚህ የበጀት ድልድል ማየት እንደሚቻለው የኢኮኖሚ አገልግሎት ድርሻ ለጠቅላላ አገልግሎት ከተመደበው 1/3ኛ የሚያንስ ሲሆን ማህበራዊ አገልግሎት ከተመደበው ደግሞ ከግማሽ በታች መሆኑን ነው፡፡ ከኤርትራ ጋር የነበረው ጦርነት እንደቆመ የመከላከያ ወጪ እየቀነሠ ቢመጣም አሁንም ለትምህርትና ለጤና ከሚመደበው የበለጠ ድርሻ እየወሠደ ነው፡፡

የካፒታል በጀት ድልድል ደግሞ በዋነኛነት ኤኮኖሚ ልማትና ማህበራዊ ልማትን የሚያካትት ሲሆን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ለኢኮኖሚ ልማት የሚመደበው ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከ1989/ 90 ጀምሮ እስከ 1994/95 ያለው የካፒታል በጀት ድልድል ሲታይ የኤኮኖሚ ልማት ዘርፍ ድርሻ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ባለፉት 7 እና 8 ዓመታት ውስጥ ለዘርፉ ከተመደበው ካፒታል በጀት ከፍተኛ የነበረው በ1992/93 በጀት ዓመት






የተመደበው 63.2% ሲሆን በ1993/94 እና በ1994/95 የተመደበው በጀት ግን ከበፊቶቹ ዓመታት ያነሠ ነው፡፡ በኤኮኖሚ ልማት ዘርፍ ውስጥ የሚገኘው የግብርናና የተፈጥሮ ሃብት ንዑስ ዘርፍም የካፒታል በጀት ድርሻው ከ1989/90 እስከ 1994/95 በተከታታይ እየቀነሠ መጥቷል፡፡ ለምሣሌ በ1989/90 20% የነበረው በ1994/95 ወደ 13% ወርዷል፡፡ በአንጻሩ በኤኮኖሚ ልማት ዘርፍ ስር ያለው ሌላው ንዑስ ዘርፍ (የትራንስፖርትና ኮንስትራክሽን) በካፒታል በጀት ድልድል መጠነኛ መሻሻል ታይቶበታል፡፡ በዚህም ንዑስ ዘርፍ የሚታየው ዕድገት በየዓመቱ ከፍና ዝቅ ስለሚል አስተማማኝነትና ዘላቂነት አይታይበትም፡፡

ሌላው የካፒታል በጀት ባለድርሻ የማህበራዊ ልማት ዘርፍ ነው፡፡ የዚህ ዘርፍ ድርሻ አንዴ ሲጨምር ሌላ ጊዜ ሲቀንስ ዘላቂ መሻሻል ማሣየት አልቻለም፡፡ በ1989/90 24% የነበረው የዘርፉ ድርሻ በ1994/95 ወደ 23% ዝቅ ብሏል፡፡ በዚሁ ልማት ዘርፍ ስር ያለው የትምህርት ንዑስ ዘርፍ የካፒታል በጀት ድልድል መውጣትና መውረድ የሚታይበት ነው፡፡ በ1989/90 10% ድርሻ ነበረው፡፡ በ1993/94 ደግሞ ወደ 8.8% ወረደ፡፡ በ1994/95 የነበረው ድርሻ 13.6% ነበር፡፡ በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ስር የሚገኘው የጤና ንዑስ ዘርፍም ተመሣሣይ ችግር አለበት፡፡ ይኸኛው ንዑስ ዘርፍ በ1989/90 የነበረው የካፒታል በጀት ድርሻ 6.5% የነበረ ሲሆን በ1994/95 ደግሞ ወደ 5% ዝቅ ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ለልማት የሚመደበው በጀት ስርጭት ፍትሃዊነቱና ዘላቂነቱ አስተማማኝነት የለውም፡፡

የመንግሥት ፋይናንስ ወጪ በከፍተኛ ፍጥነት ከገቢው እየበለጠ የመጣ በመሆኑ የበጀት ጉድለቱን እያሠፋው ነው፡፡ በዚህም መሠረት በ1992/93 ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት 10.3% የነበረው የበጀት ጉድለት መጠን በ1993/94 ወደ 14% አድጓል፡፡ በአንጻሩ መንግሥት በ1991/92 ከሀገር ውስጥ ባንክ ወደ 5.5 ቢሊዮን ብር በብድር ወስዶ የነበረ ቢሆንም በ1993/94 ግን ያለበትን የበጀት ጉድለት ከውጭ በሚገኝ ብድር የመሸፈን ዕድል በማግኘቱ ከሀገር ውስጥ ባንክ ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ የተበደረው 723 ሚሊዮን ብር ብቻ ነው፡፡ መንግሥት ከሀገር ውስጥ ባንክ የሚወስደው ብድር ማነስ የበጀት ጉድለቱን እየቀነሠ መምጣት የሚያሣይ ሣይሆን በውጭ ብድር ለመሸፈን መቻሉንና ይኸም የሀገሪቱን ዕዳ ጫና የሚያበዛው መሆኑን ነው፡፡

## 2.6 ያልተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ

ከ1990/91 እስከ 1994/95 ባሉት 5 እና 6 ዓመታት የነበረውን ሁኔታ ብቻ እንኳ ብናይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታ በተፈጥሮ ችሮታ ላይ የተንጠለጠለ መሆኑን እንገነዘባለን። የዋጋ መውጣትና መውረድም የተፈጥሮ ጥገኛ ከሆነው የሀገሪቱ ግብርና ዘርፍ እንቅስቃሴ ጋር በጥብቅ የተሣሰረ ነው። መልካም የአየር ፀባይ ሲያጋጥምና የግብርና ምርት ሲጨምር ዋጋ ይወርዳል። ድርቅ በመጣና ጦርነት በተከሠተ ቁጥር የግብርና ምርት ሲቀንስ ዋጋ ወደ ላይ ይወጣል። በ1992/93 ጥሩ የአየር ሁኔታ በመኖሩ በሀገሪቱ የተሻለ የግብርና ምርት ተገኝቶ ስለነበር የዋጋ መውረድ ተከሠተ። በ1994/95 ደግሞ ከፍተኛ ድርቅ በማጋጠሙ የግብርና ምርት በከፍተኛ ደረጃ ሲቀንስ የዋጋ ንረት ተፈጠረ። በ1992/93 ያገጠመውን የግብርና ምርት መጨመር ተከትሎ የዋጋ ንረት መጠን ከዜሮ በታች -5.2% ሲወርድ የ1994/95 ድርቅ እንደተከሠተ ወደ 15% አደገ። በ1992/93 ድርቅ የምግብ እህል ዋጋ በ19.4% ወድቆ ነበር። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ የዋጋን ሁኔታ በዋናነት የሚወስነው ሠፊ የገንዘብ አቅርቦት መኖር አለመኖር ሣይሆን የግብርናው እንቅስቃሴ መዳከምና መጠናከር ነው። የዋጋ ንረት ከዜሮ በታች በወረደበትና የግብርና ምርት ባደገበት የገንዘብ አቅርቦት በ10.5% አድጐ የነበረ ሲሆን የግብርናው ምርት በድርቅ በወደቀበትና የዋጋ ንረት ወደ 15% ባደገበት 1994/95 ጊዜም የገንዘብ አቅርቦት ዕድገት ተመሣሣይ ነበር።

በግብርና ምርትና በዋጋ መካከል ያለውን ትስስር መነሻ በማድረግ ሦስት ገጽታዎችን መገንዘብ ይቻላል። እነዚህም አንደኛ የግብርና የምርት ዕጥረት ሲያጋጥም ከሚከሠተው የዋጋ ንረት የበለጠ የግብርና ምርት ሲትረፈረፍ ከፍተኛ የዋጋ ውድቀት ይታያል። ሁለተኛ ከእርሻ ምርት መጨመር ጋር ተያይዞ የምግብ ዋጋ ስለሚቀንስ ገበሬው በዋጋ ተጠቃሚ አይሆንም። ሦስተኛ የገንዘብ ተቋማት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ፖሊሲ ስለሌላቸው በዚህ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ዝቅተኛ ነው።

በአጠቃላይ የሀገሪቱ ኤኮኖሚ ባህርይ ሲታይ የኢኮኖሚው ዕድገት ከሕዝብ ዕድገት ወደ ኋላ የቀረ ነው። በፍጥነት የሚጨምረውን የሕዝብ ዕድገት ተከትሎ ባለፉት አምስት ዓመታት ትክክለኛው ብሔራዊ ገቢ በሁለት ዕጥፍ ቀንሷል። በገጠርም ሆነ በከተማ የዜጐች የነፍስ ወከፍ ገቢ እየቀነሠ መጥቷል። የዋጋን መውጣትና መውረድ ሁኔታ የሚያረጋጋ ፖሊሲ በሌለበት ሁኔታ ዋጋ ከግብርና ምርት ማደግና መቀነስ ጋር ተያይዞ ይዋዥቃል። የኤኮኖሚው እንቅስቃሴ ለውጭና ለውስጥ ክስተቶች ከመጋለጥ አደጋ ማምለጥ አልቻለም። የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ለዓለም ገበያ በደንብ የተከፈተ





ባይሆንም በዓለም ገበያ የተከሠተው የቡና ዋጋ መውደቅ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ከመገደብ አልፎ ጠቅላላ ኤኮኖሚውን ደካማ አድርጐታል።

ከ40 ዓመታት በላይ የሀገሪቱ ኤክስፖርት በዓይነት፣ በመጠንና በሚሸጥበት ክልል ውስንነት እንደታሠረ በመሆኑ ሁልጊዜም ለውጫዊ ክስተቶች በቀላሉ ይጋለጣል። በኤኮኖሚው መዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግና ድህነትን ለመቀነስ የተደረገው የፖሊሲ ማሻሻያ ከ12 ዓመታት ሙከራ በኋላ ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም። የግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ከተጀመረ 12 ዓመታት ቢያልፉም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም ሆነ በምግብ ራስን ለመቻል የተደረገው ሙከራ አልተሣካም። በ1994/95 ዓ.ም. 14 ሚሊዮን ሕዝብ በድርቅ ተጐድቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ200 ሺህ ሕዝብ በላይ ሞቷል። በድርቁ መመላለስና በኤኮኖሚው እንቅስቃሴ ድክመት የደረሰው አስከፊ ርሃብ ፖሊሲው ከዚህ ዓይነቱ አደጋ የመከላከል ብቃት እንደሌለው አሣይቷል።

ጥሩ ምርት ሲኖር እንኳ ከመዋቅሩ ገታራነትና ከገበያ ችግር የተነሣ ገበሬውም ሆነ በአጠቃላይ ኤኮኖሚው ተጠቃሚ ሊሆኑ አልቻሉም። የተመረተውን ምርት መጠቀም የሚችል የሀገር ውስጥ ፍላጐት በሌለበትና የውጭ ገበያ ዕድልን መጠቀም በማይቻልበት ሁኔታ የሀገሪቱ ግብርና ምርት ዕድገት ዘላቂ ሊሆን አይችልም። እነዚህን አጠቃላይ ግንዛቤዎች በመውሠድ የተጣጣመ የከተማና የገጠር ልማት ስትራቴጅ ካልተቀየሠና የእያንዳንዱ ክፍለ ኤኮኖሚ ዕድገት ትርጉም ባለው ሁኔታ ከሌላው ጋር መደጋገፍ ወይንም መተሣሠር ካልቻለ ገጠርን ብቻ ማዕከል ያደረገው የግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ውጤት እንደማይኖረው በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

## *2.7 ዕድገቱ የተገታ የግብርና ዘርፍ*

የሀገራችን ግብርና ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ 85% የሚሆነው የሠው ኃይል የተሰማራበት የሥራ መስክ፣ ከጠቅላላው የሀገሪቱ ምርት ውስጥ ወደ 50% የሚጠጋ ድርሻ ያለውና ከሀገሪቱ ኤክስፖርት ምርት ከ85% በላይ የሚሆነውን የሚያበረክት ነው። የግብርና ምርት ሲያድግ የሀገሪቱ ጠቅላላ ምርትና የኤክስፖርት መጠን ያድጋል። ሲቀንስ ደግሞ አብሮ ይቀንሣል። ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ የዝናብ ጥገኛና ኋላ ቀር በሆነ የአመራረት ዘይቤ ስለሚመራ፤ ፈጣን በሆነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት የገበሬው የነፍስ ወከፍ ይዞታ ከግማሽ ሄክታር እያነሰ ስለመጣ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሀገሪቱ

የእርሻ መሬት ጉዳት ስለደረሠበት ምርታማነቱ እየቀነሰ የመጣ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። በመሆኑም የዚህ ዓይነት መዋቅራዊ ችግር ያለበት የኢትዮጵያ ግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚያሸጋግር መሪ ሚና ሊጫወት ቀርቶ በዘርፉ የተሠማሩትንም ገበሬዎች የምግብ ፍጆታ መሸፈን አልቻለም። እስከ 1995 በነበሩት 5 ዓመታት ግብርናው ያሣየው ዕድገት በአማካይ -1.5% ነው። በ1992/93 11.5% ቢያድግም በ1993/94 ያሣየው ዕድገት -3.1%. እንዲሁም በ1994/95 —12.12% በመሆኑ የ3ቱ አመታት እድገት ከ0 በታች -1.3% ነበር። በዚህ ዓመት በታየው ጥሩ ዝናብ ተመዘገበ የሚባለው የግብርና ዕድገት ከነበረበት ዜሮ የዕድገት ደረጃ ማገገሙን እንጂ በዘርፉ የታየ ዘላቂ እድገት ስለማያመለክት ዝናብ ከጠፋ ተመልሶ የሚወርድ ነው።

ላለፉት 42 ዓመታት የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ወደ ዜሮ የተጠጋ ነው። ይኸም ማለት የአሁኑ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከ40 ዓመታት በፊት ከነበረው አልተሻሻለም ማለት ነው። ባለፉት 13 ዓመታት በየዓመቱ የተመዘገበው የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት በአማካይ ወደ 1.6% የሚጠጋ ሲሆን በደርግ መንግሥት 17 ዓመታት ቆይታ ከተመዘገበው በ1% ያነሰ ነው። በእርሻው ዘርፍ ብቻ ባለፉት 13 ዓመታት የተመዘገበውን የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ከተመለከትን ደግሞ በንጉሡ ጊዜ ከነበረው በ31% ያነሰ ሲሆን በደርግ ጊዜ ከነበረው ደግሞ በ15% ያነሰ ነው። የመሬት ምርታማነት እየቀነሰ በመምጣቱ ባለፉት 40 ዓመታት ከግብርና ዘርፍ ውጭ ያለው የነፍስ ወከፍ ገቢ በ0.8% ዕድገት ሲያሣይ የግብርናው ዘርፍ የነፍስ ወከፍ ገቢ ግን በ1.2% ቀንሷል። ከ40 ዓመታት በፊት በ1 ሄክታር በአማካይ 11 ኩንታል ማምረት ይቻል የነበረ ሲሆን፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያውም የምርት ማሣደጊያ ግብዓቶች በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ ውለዋል በሚባልበት ጊዜ በ1 ሄክታር ማምረት የተቻለው አማካይ ምርት ከ10 ኩንታል አይበልጥም። እያንዳንዱ ገበሬ በነፍስ ወከፍ የሚያመርተው ምርት ከ20 ዓመታት በፊት በዓመት በአማካይ 170 ኪሎ ግራም የነበረ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ከ97 ኪሎ ግራም አይበልጥም። የግብርናው ዘርፍ ዓመታዊ ዕድገት የአለፉት 13 ዓመታት በአማካይ 1.7% ሲሆን በደርግ የሥልጣን ዓመታት ከተመዘገበው 0.6% አማካይ ዕድገት የሚለየው በ1% ብቻ ነው። በወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ዘመን አልፎ አልፎ የግብርናው ዘርፍ ለሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት የሚያበረክተው ድርሻ ከ50% ሲወርድ የነበረው የሌሎች ሴክተሮች ድርሻ ስላደገ ሳይሆን ግብርናው የዝናብ ጥገኛ በመሆኑና በድርቅ በመጐዳቱ ነው።

ባለፉት 30 ዓመታት በሀገሪቱ ውስጥ በቋሚነት ለከብት ግጦሽና







እርባታ ይውል የነበረው 46 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከ20 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በታች ወርዷል። የግጦሽ መሬት መቀነስ፣ የእንስሳት ሕክምና አለመጠናከርና በተከታታይ የሚከሠት ድርቅ የሀገሪቱን የእንስሳት ቁጥር ቀንሶታል። ከ10 ዓመት በፊት የነበረው 30 ሚሊዮን አካባቢ የእንስሳት ቁጥር በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። ይኸንኑ ተከትሎ የወተት፣ የሥጋና የቆዳ ምርት መጠን እየቀነሠ ነው። በዚህም የተነሣ ላለፉት 15 እና 20 ዓመታት በእርዳታ ብቻ የሚኖሩ ሠዎች ቁጥር እየጨመረ ነው። ለምሣሌ በ1984 ዓ.ም ለረሃብ የተጋለጠው ሕዝብ ቁጥር 6.2 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በ1994/95 ደግሞ ከ14 ሚሊዮን በላይ ነበር። መልካም የአየር ፀባይ በታየበት በአሁኑ ዓመት እንኳ እርዳታ የሚፈልገው ሕዝብ ቁጥር 7 ሚሊዮን ገደማ ነው።

ባለፉት 14 ዓመታት የታየው የመሬት ምርታማነትና የነፍስ ወከፍ ገቢ መቀነስም ሆነ የእርዳታ ፈላጊው ቁጥር እየጨመረ መሄድ የሚጠቁመው የመንግሥት ፖሊሲ ውጤታማ አለመሆኑን ነው። የፖሊሲው ትኩረት ለክፍለ ኤኮኖሚው ሽግግር የሚረዳ መፍትሔ በማምጣት ፋንታ የችግሩ ምልክቶች በሆኑ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው። ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት የሚሠጥ ፖሊሲ እየተከተልን ነው በሚባልበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ውድቀት መታየቱ የመንግሥት ፖሊሲ የተሣሣተ መሆኑን ያሣያል። ፖሊሲው የኢንዱስትሪ ምርት ገበያ እንዲያገኝ የገበሬውን ገቢ ማሣደግ፣ ለልማት የሚውል የሀገር ውስጥ ቁጠባ ማፍራት፣ ከፍተኛ የካፒታል ኢንቨስትሜንት ሣያስፈልግ በግብርና ምርት የሚገኝ ኢንቨስትመንት ማሣደግ፣ በድህነት ውስጥ የሚገኘውን አብዛኛውን ሕዝብ በምግብ እህል ራሱን ማስቻል፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት የሚሉ ዓላማዎች ቢኖሩትም ከ10 ዓመታት በላይ በተጨባጭ ተግባር ተሞክሮ በቲዎሪም በተግባርም ውድቅ ሆኗል።

ባለፉት 14 ዓመታት የግብርና ግብዓት በተለይም የማዳበሪያ አቅርቦትና ፍጆታ መጠን ዕድገት ቢያሣይም የመሬቱን ምርታማነትና የገበሬውን ገቢ በማሣደግ ረገድ ለውጥ አላመጣም። በ1983 ወደ ሀገር ውስጥ ይገባ ከነበረው ማዳበሪያ መጠን በአሁኑ ጊዜ የሚገባው ከ200% በላይ ጨምሯል። ፍጆታውም በ1982 ዓ.ም. በሄክታር 34 ኪሎ ግራም የነበረው አሁን በሄክታር 46 ኪ.ግ. ሆኗል። ነገር ግን ገበሬዎች አንድ ዓይነት ምርት ላይ እንዲያተኩሩ፣ የመሬት ንጥረ ነገር እንዲሟጠጥና ምርታማነት እንዲቀንስ፣ የተሻሻለ ዘር የመጠቀም ፍላጐትም እንዲቀዘቅዝ አስተዋፆ አድርጓል። ከሀገሪቱ የተለያየ ሥነ-ምህዳርና የአፈር ፀባይ ጋር ያለው ተስማሚነት እየተጠና ጥቅም ላይ አለመዋሉም ያስከተለው ችግር ቀላል

አይደለም፡፡ በዚያው ልክ የማዳበሪያ ዋጋ በየዓመቱ 8.5% ገደማ ስለሚጨምር የገበሬውን የመግዛት አቅም መፈታተኑ አልቀረም፡፡

የምርጥ ዘር በማቅረብ ረገድ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ማባዣ ድርጅት እየተንቀሣቀሰ ቢሆንም የማሠራጨት ችግር አለበት፡፡ የችግሩ መንስኤዎች፤ የዋጋው መናር፣ የገበሬዎች ፍላጐት መቀነስ፣ የተሻሻለ ምርትን የማስተዋወቅ ድክመትና በኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ በገበያ ኤጀንሲዎች፣ በገበሬዎችና በምርጥ ዘር ማባዣ ድርጅት መካከል ያለው ቅንጅት መላላት፣ የዘሩ ጥራት ጉድለት ናቸው፡፡

የእርሻ ምርት ግብይት ሥርዓት ሌላው የዘርፉ ትልቅ ችግር ነው፡፡ ገበሬዎች ጥሩ ምርት ሲያገኙ ከፍጆታ የሚተርፈውን በመጋዘን የማቆየት ልምድና አቅም ስለሌላቸው፣ የመንግሥት ግብር እንዲሁም የማዳበሪያ ብድር ክፍያ ለገበሬዎች ግብይት ተስማሚ ባልሆነ ወቅት መሆኑና በመሣሠሉት ችግሮች የተነሣ አብዛኛውን ምርት በመኸር ጊዜ ገበያ አውጥተው ለነጋዴና ለከተማው እህል ፈላጊ በርካሽ ዋጋ ይሸጡታል፡፡ በዚህ ጊዜ አቅርቦቱ ይበዛና የእህል ዋጋ ይወድቃል፡፡ ለምሣሌ በ1986 ምርት ዘመን የእርሻ ምርት ዋጋ በ25% ቀንሶ ነበር፡፡ በግብይቱ ሂደት የሚታዩት መሠረታዊ ችግሮች የትራንስፖርት መረብ ብቃት አለመኖር፣ የገበያ መረጃ ሥርዓት አለመዘርጋት፣ የገበሬው የመደራደር አቅም ማነስና ዝቅተኛ አግሮ ኢንዱስትሪ ደረጃ መኖር ናቸው፡፡

ሌላው ችግር የኢትዮጵያ ማዳበሪያ ገበያ በተመረጡ አቅራቢ ድርጅቶች ተሣትፎ ብቻ የተገደበ መሆኑና የማዳበሪያ አስመጭዎች 100% ዋስትና እንዲያስይዙ በሚያስገድድ የባንክ ብድር ሕግ የታሠረ መሆኑ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ማዳበሪያ የሚያስመጡትና የእርሻ ግብዓት የሚያቀርቡት አምባሰልና ወንዶ የሚባሉት የገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ሲሆኑ የግል ዘርፉ በዚህ መስክ ምንም ዓይነት ተሣትፎ የለውም፡፡ ፌርቲላይዝንና የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ በተለያየ ተፅእኖ ከገበያው እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ የገዥው ፓርቲ ንግድ ድርጅቶች ሞኖፖሊ ተፈጥሯል፡፡

ገበሬዎች ለማዳበሪያ መግዣ የሚሆን ብድር የሚያገኙት የክልል መንግሥታት ከበጀታቸው ለመንግሥት ባንክ የተወሠነ ማስያዣ በዋስትና መልክ እያቀረቡ ብድር ከወሠዱ በኋላ መልሰው ለገበሬዎች ከሚያበድሩት ገንዘብ ነው፡፡ ማዳበሪያውን የሚያከፋፍሉት ደግሞ የወረዳ ግብርና ቢሮዎችና አምራቾች ናቸው፡፡ ገዥው ፓርቲ ማዳበሪያ አስመጪና አከፋፋይ፣ ብድር







ሠጪና ዕዳ ሠብሣቢ የሆነበት የተጠላለፈ አሠራር የግብርናውን ግብይት ከሚያውኩት ችግሮች መካከል ዋነኛው ነው፡፡ በዚህ ላይ የማዳበሪያ ዋጋ ከእህል ዋጋ በበለጠ ፍጥነት ስለሚያድግ ችግሩን አባብሶታል፡፡ ለምሣሌ ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1992 በነበሩት 5 ዓመታት ውስጥ የእህል ዋጋ በ14.6% ዕድገት ሲያሣይ፣ ዳፕ የሚባለው ማዳበሪያ ዋጋ ደግሞ ከእጥፍ በላይ በሆነ መጠን ማለትም በ37.5% አድጐ ነበር፡፡ ሁሉም የትራንስፖርትና መገናኛ ዋጋ በ61.1% ወደላይ ወጥቶ ነበር፡፡ ይኸ የሚያሣየው የንግድ ልውውጥ ምጣኔው ለግብርና ምርት ዋጋ አጋዥ አለመሆኑን ነው፡፡ ምን አልባት የእህል ዋጋ መውደቅ ከእርሻ ዘርፍ ውጭ ለሚኖረው ሕዝብ ኑሮ መርከስ አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችላል ይባል ይሆናል፡፡ እውነቱ ግን ይህ አይደለም፡፡ በአሁኑ የሀገሪቱ ሁኔታ ግብርና በጠቅላላው ኤኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደመሆኑ በዘርፉ የሚደርስ ማንኛውም ዓይነት ጉዳት በአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያስከትለው ተፅእኖ ከፍተኛ ነው፡፡

የሀገራችን ገበሬዎች ለግብርና ብድር በአጠቃላይና ለረጅም ጊዜ ብድር ደግሞ በተለይ ዝቅተኛ ፍላጐት ያሣያሉ፡፡ ምክንያቱም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ምርት ሥርዓት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ የእርሻ ምርት ዋጋ ዝቅተኛ በመሆኑና አስቀድሞም ለመገመት ስለሚያስቸግር፣ ከመሬት ዋስትናና ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ባለባቸው ስጋት፣ የእርሻ ግብዓት ገዝቶ ለመጠቀም የሚያስችል አቅም ማጣት፣ የልምድ መጥፋትና የመሳሰሉት ችግሮች ስላሉባቸው ነው፡፡ የማዳበሪያ ብድር ግን በተለየ መንገድ የሚታይ ነው፡፡ በአንድ በኩል መንግሥት የሠብል ምርትን ለመጨመር ማዳበሪያን እንደ ስትራቴጅያዊ ግብዓት ስለሚቆጥረው የሚያደርገው ሠፊ ግፊት በመኖሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ገበሬዎች ራሣቸው በተከታታይ ጊዜ አንድ ዓይነት ሠብል በማምረት እየቀነሠ የመጣውን የመሬት ምርታማነት ለማሻሻል ሲሉ ማዳበሪያን የመጠቀም ፍላጐት ስላላቸው ለዚህ ግብዓት መግዣ ብድር ቢያገኙ አይጠሉም፡፡

ነገር ግን የማዳበሪያ ብድር ገበያ የገበሬዎችን ፍላጐትና የብድሩን ቀጣይነት የሚፈታተኑ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ በ1980ዎቹ የተደረጉ የፖሊሲ ማሻሻያዎች የፋይናንስ ፍሰቱን (በዋናነት የብድር ፋይናንስን) አቅጣጫ ከመንግሥት ወደ ግል ሴክተር እንዲዞር መጠነኛ መሻሻል ቢያስገኙም የእርሻውን ኤኮኖሚ ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትሜንት የሚመችና ማራኪ ማድረግ አልቻሉም፡፡ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ የግብርናው ዘርፍ ብድር ድርሻ ከጠቅላላው ብድር ድልድል ውስጥ ከ19% በልጦ አያውቅም፡፡ ከዚህ ውስጥ አብዛኛው (ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል) የግብርና ብድር ለአጭር ጊዜ ሥራ

የሚያገለግል በመሆኑ ለዘርፉ መዋቅራዊ ሽግግር ያለው አስተዋፅዖ ትንሽ ነው። ግብርና ለሀገሪቱ ኤኮኖሚ ዕድገት ከሚጫወተው ሚና አንጻር የሚያገኘው ብድር መጠን እጅግ ዝቅተኛ ነው። እዚህ ላይ በጥንቃቄ መረዳት የሚያስፈልገው ለዘርፉ ኢንቨስትሜንት ዝቅተኛ መሆን የግብርናው ዘርፍ ብድር ድርሻ ማነስ አስተዋፅዖ አድርጓል ሲባል ኢንዱስትሪና ሌሎች ዘርፎች ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው ማለት አለመሆኑን ነው። የእነዚህም ዘርፎች ብድር ድርሻ እንደግብርናው ዝቅተኛ በመሆኑ የግብርናን ኢንቨስትሜንት በመሻማት ዋነኛ እንቅፋት ተደርገው ሊታዩ አይችሉም።

የግብርና ዘርፍ ኢንቨስተሮችንና ገበሬዎችን የመሣብ አቅሙ ዝቅተኛ ለሆነበት ሁኔታ ከሚቀርቡት ምክንያቶች መካከል፤ የመሬት ባለቤትነት ዋስትና አስተማማኝነት የሌለው መሆኑና መንግሥት በሚያራምደው የተሣሣተ የመሬት ፖሊሲ ምክንያት የመሬት ይዞታ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ መምጣቱ ዋነኞቹ ናቸው። ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ባለበት የሀገሪቱ ገጠር የኢንቨስትሜንት አለመኖር የአካባቢና የመሬት መጐዳት እንዲባባስ እያደረገ ነው። በኢትዮጵያ ኢንቨስትሜንት ባለሥልጣን የ1994 ዓ.ም. መረጃ መሠረት በእርሻው መስክ ኢንቨስት ለማድረግ ፈቃድ የወሠዱ ብዙ ቢሆኑም ሥራ የጀመሩት ወይም ባቀረቡት ፕሮጀክት የቀጠሉት ቁጥር በጣም ትንሽ ነው። በግብርናውም ሆነ ከግብርና ውጭ የኢንቨስትሜንት ፈቃድ ከተሠጣቸው ፕሮጀክቶች መካከል 52% የሚሆኑት ባቀረቡት የፕሮጀክት ፕላን መሠረት መሥራት አልቻሉም። ወይም ፕሮጀክታቸውን በጠቅላላው እርግፍ አድርገው ትተውታል። እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ በኢትዮጵያ ኢንቨስትሜንት ባለሥልጣን ተቀባይነት ካገኙት ፕሮጀክቶች መካከል የግብርናው ዘርፍ ድርሻ 11.3% ብቻ የነበረ ሲሆን ከጠቅላላው የኢንቨስትሜንት ካፒታል መጠን የግብርናው ዘርፍ ድርሻ 6.7% ብቻ ነው።

ለግብርናው ኢንቨስትሜንት ማነስ ከሚጠቀሱት ሌሎች ምክንያቶች መካከል በገጠር ያለው ዝቅተኛ የመሠረተ ልማት ሁኔታና ደካማ ገበያ፣ የመሬት ዋስትና አስተማማኝ አለመሆንና መሬት ለማግኘት አለመቻሉ፣ መሬትና የእርሻ ማሽነሪዎች (መገልገያዎች) ለብደር ዋስትና አለመያዛቸው፣ በቂ የቅድመ ብድር ማበረታቻዎችና የመቋቋሚያ ጊዜ አለመስጠቱ፣ የመሬትና የካፒታል አስተዳደር ብቃት ማነስ፣ የተንዛዛ ቢሮክራሲ መኖርና የተረጋጋ ዘላቂ ሠላም መጥፋት ይገኙባቸዋል። የኢንቨስትሜንት ሕጉን ለማሻሻል ሙከራዎች ከመደረጋቸውም በላይ ተበዳሪዎች የሚከፍሉትን ወለድ መጠን በመቀነስ ኢንቨስተሮችን ለማደፋፈር የተወሠዱት እርምጃዎች በአበባ ምርት መጠነኛ ለውጥ ቢያመጡም አጠቃላይ ሁኔታው አልተቀየረም። አሁንም በገጠር የረጅም ጊዜ ኢንቨስትሜንት እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን በአንጻሩ በባንክ







ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጠ በርካታ ገንዘብ መኖሩ የሚያመለክተው በኢትዮጵያ የኢንቨስትሜንት ፍላጐት መቀነሱን ነው። ስለዚህ መሠረታዊው ችግር የመንግሥት ፖሊሲ ትክክል ካለመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው።

በአጠቃላይ ኢህአዴግ ገጠርን ማዕከል ያደረገ ግብርና ልማት መር ፖሊሲ እያራመድኩ ነው በሚልበት ጊዜ ከተፈጥሮ ሁኔታ መስተካከል ጋር ተያይዞና በባህላዊ ዘዴ የሚታረሠው መሬት መጠን ሲጨምር አልፎ አልፎ ከሚታየው መጠነኛ የምርት መሻሻል በስተቀር የግብርናው ዘርፍ እየተሟሟተ እንጅ እየተሻሻለ አልመጣም። ለዚህም ጠቋሚ የሆኑት የመሬት ምርታማነት አለመጨመር፣ የገበሬው የነፍስ ወከፍ ገቢ እየቀነሰ መምጣትና የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ናቸው። የማዳበሪያ ግዥና ፍጆታ በየጊዜው ቢጨምርም የመሬትን ለምነት በማሻሻል ያስገኘው ውጤት ደካማ ነው።

በጠቅላላ ምርት ዕድገት በሚመዘገብበት ጊዜ ሣይቀር በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መጨመር የተነሣ በእያንዳንዱ ቤተሰብ የእርሻ ገቢ ዕድገት የሚገኝበት ዕድል የመነመነ ነው። በአሁኑ ጊዜ የተጀመረው ኩሬ ማዘጋጀትና የውኃ ማቋት ሥራ መጥፎ ባይሆንም በጥናት ላይ አለመመስረቱ፣ ከባለሙያዎች ጋር በቂ ምክክር ሣይደረግ መጀመሩ፣ አንዳንዴ የሞያተኞችን ምክር በጥሬው ወስዶ ሥራ ላይ ለማዋል መሞከሩ፣ በዘመቻና በኮታ አሠራር የሚካሄድ መሆኑ፣ ከፍተኛ ጉልበት፣ ገንዘብና ጊዜ ከባከነ በኋላ ውጤታማነቱንና ዘላቂነቱን አደጋ ላይ ጥሎታል። በደርግ ጊዜ ተጀምረው የነበሩት እንደ አልዌሮ፣ ጣና በለስና ዋቢ ሸበሌ የመሣሠሉት ትላልቅና ተስፋ የተጣለባቸው የመስኖ ፕሮጀክቶች በሚሊዩን የሚቆጠር ዶላር ከፈሠሠባቸው በኋላ በፖለቲከኞች የተሣሣተ ውሣኔ መቆማቸው የግብርናው ዘርፍ ችግሮች እንዲቀጥሉ አስተዋፅዖ አላቸው። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የዘርፉን ዕድገት አዝጋሚነትና መዋቅራዊ ችግር ብቻ ሣይሆን ችግሩን ከመሠረቱ መቀየር የሚያስችል ፖሊሲ አለመኖሩን የሚያሣዩ ናቸው። በዚህ አይነት የተሳሳተ ፖሊሲ የሀገሪቱን ግብርና የገደለው ወያኔ/ኢሕአዴግ በመንግሥት ሥልጣን ላይ እንዲቆይ ሊፈቀድለት አይገባም።

## *2.8 ከኋላ ቀርነት ያልተላቀቀ የኢንዱስትሪ ዘርፍ*

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ለጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የሚያበረክተው ድርሻ ባለፉት 40 ዓመታት ትርጉም ያለው መሻሻል ማድረግ ባለመቻሉ ባለበት እየረገጠ ነው። ላለፉት 10 ዓመታት ኢንዱስትሪው ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 10% ገደማ ሲሆን በደርግ ጊዜ

ከነበረው የ11.4% ድርሻ ያነሠ ነው። የሀገራችን ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አሁን ያለው ድርሻ ከሠሀራ በታች ካሉ ሀገሮች ጋር ሲነጻፀር ከግማሽ በታች ያንሣል። በወያኔ/ኢሕአዴግ የመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታት በመንግሥት ይዞታ ስር የነበሩ ድርጅቶች ብቃት በመጠኑም በመጨመሩና አቅምን የመጠቀም መሻሻል በመታየቱ ለ6 ዓመታት ያህል በኢንዱስትሪው ዘርፍ በአማካይ 7.4% ዕድገት ተመዝግቦ ነበር። ነገር ግን ከዚያ በኋላ የዘርፉ ዕድገት እየቀነሰ መጥቷል። በደርግ ጊዜ የሀገሪቱ ጠቅላላ ምርት እንዲያድግ ዘርፉ ያደረገው አስተዋፅኦ 20.8% የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ መንግሥት ጊዜ ግን ወደ 13.5% ወርዷል። ትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ለጠቅላላው ኢንዱስትሪ ምርት ያላቸው አስተዋፅዖ 39% ሲሆን ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ ደግሞ 4.2% ነው። ትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በደርግ ጊዜ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የነበራቸው ድርሻ 4.4% ስለነበረ በአሁኑ ጊዜ ካላቸው ድርሻ በ0.2% የተሻለ ነበር ማለት ነው። በኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ንዑስ ዘርፎችም ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ ኮንስትራክሽን 2.6%፣ ጥቃቅን ኢንዱስትሪና ዕደ ጥበባት 1.9%፣ መብራትና ውኃ 1.6%፣ ማዕድንና ቁፋሮ 0.5% ነው።

የኢትዮጵያ የፋብሪካ ኢንዱስትሪ በ1993 የወጣ የዓለም ባንክ መረጃ እንደሚያሣየው በጠቅላላው የሀገር ውሰጥ ምርት የነበረው ድርሻ 7% ሲሆን ከሠሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ቢነጻጸር ከግማሽ በታች ያነሠ ነው። ዓመታዊ ዕድገቱ ደግሞ ከ1988-1994 በዓመት በአማካይ 1.8% ነበር። በተለይ በ1993/94 ከዜሮ በታች -8% ወርዶ ነበር። በዚህም የተነሣ የሀገሪቱ ፋብሪካ የነፍስ ወከፍ ምርት በዓመት ከ5 ዶላር ያነሠ ነው። የመዋቅር ማስተካከያ እርምጃ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተደረጉትን የታሪፍ ቅነሣ ለውጦች ተከትሎ ሕገወጥ ገበያ በመስፋፋቱ፣ የፋብሪካዎች ተወዳዳሪነት አቅም ዝቅተኛ በመሆኑና በመሣሠሉት ምክንያቶች የተወሠኑት ፋብሪካዎች ተዘግተው ነበር። በዚሁ ጊዜ የሠራተኛ ቁጥር ሲቀንስ በ1994 ብቻ ነው መጨመር ያሣየው። ፋብሪካው መሠረታዊ የማምረቻ ዕቃዎችን ከውጭ በማስገባት የውጭ ጥገኛ ብቻ ሣይሆን የግብርና ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀምም የግብርና ጥገኛ ነው። የፋብሪካው ዘርፍ መዋቅራዊ ችግሮች ያሉበትና ከሌሎች የሀገር ውሰጥ የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ጠንካራ ትስስር ያልፈጠረ ነው። ይኸንን የትስስር ድክመት ለመረዳት የሚከተሉትን ማነጻጸሪያዎች ማየት ይበቃል።

❖ የኢትዮጵያ ፋብሪካ ከሚፈልገው ጠቅላላ የምርት ግብዓት ውስጥ 34.3%







የሚገኘው ከግብርና ነው።

❖ የኢትዮጵያ ፋብሪካ ከሚፈልገው ጠቅላላ የምርት ግብዓት ውስጥ 1.3% የሚሆነውን ከማዕድን ያገኛል።
❖ የኢትዮጵያ ፋብሪካ ከሚፈልገው ጠቅላላ የምርት ግብዓት ውስጥ 19.1% የሚሆነውን ከፋብሪካ ያገኛል።
❖ የኢትዮጵያ ፋብሪካ ከሚፈልገው ጠቅላላ የምርት ግብዓት ውስጥ 45.2% የሚሆነውን ከውጭ በግዥ ያገኛል።
❖ የኢትዮጵያ ግብርና ከሚፈልገው ጠቅላላ የምርት ግብዓት ውስጥ 1.3% የሚሆነውን ከፋብሪካ ያገኛል።
❖ በአንጻሩ ግብርና ከውጪ በግዥ የሚያገኘው ግብዓት በጠቅላላ ከሚያስፈልገው ውስጥ 98.7% ነው።
❖ የኢትዮጵያ ግብርና ወደ ውጪ የሚልከው ደግሞ 79.7% ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ፋብሪካ ወደ ውጪ የሚልከው 20.3% ነው።

ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው የሀገራችን ፋብሪካ ከሀገር ውስጥ ኤኮኖሚ ሴክተሮች ጋር ካለው ትስስር (55%) በማይተናነስ ደረጃ ከውጭ ኤኮኖሚ ጋር ከፍተኛ ትስስር ያለው መሆኑን ነው። ፕሮሠስድ ከሆነው ግብዓት ውስጥ ከሀገር ውስጥ የሚያገኘው $^{1}/_{3}$ኛውን ብቻ ሲሆን $^{2}/_{3}$ኛውን ደግሞ ከውጭ ነው። እስካሁን ያየነው ፋብሪካው ከሌሎች የኢኮኖሚ ሴክተሮች በሚያገኘው ግብዓት የተፈጠረውን ትስስር (Back ward Linkage) ሲሆን፣ ቀጥሎ ደግሞ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚያቀርበው ምርት የተፈጠረውን ትስስር (Forward Linkage) እንመለከታለን።

❖ ከፋብሪካው ጠቅላላ ምርት ውስጥ ወደ እርሻ የሚሄደው 0.5% ምርት ነው።
❖ ከፋብሪካው ጠቅላላ ምርት ውስጥ ወደ ፋብሪካ የሚሄደው 50.8% ምርት ነው።
❖ ከፋብሪካው ጠቅላላ ምርት ውስጥ ወደ ውጪ የሚሄደው 48.7% ምርት ነው። በአንጻሩ ከግብርናው ጠቅላላ ምርት ወስጥ ፋብሪካ የሚሄደው 32.4% ምርት ነው።

ከዚህ የምንረዳው የኢትዮጵያ ፋብሪካ የሀገሪቱ ግብርና ከዘርፉ የሚፈልገውን ምርት የማያመርት መሆኑንና ከእርሻው ክፍለ ኤኮኖሚ የሚወስደው ግብዓትም ዝቅተኛ መሆኑን ነው። በዚህም የተነሣ የፋብሪካው ዘርፍ ከሌሎች ክፍለ ኤኮኖሚዎች ጋር ደካማ ትስስር ያለውና የውጭ ጥገኛ ነው። የፋብሪካው ምርት አወቃቀር እንደዚሁ ከፍተኛ ችግር አለበት። ከሀገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ውስጥ 20% የሚሸፍነውና የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከሚያፈራው የቋሚ ካፒታል ጥሪት ውስጥ 15% የሚያበረክተው

ስኳርና ስኳር ነክ ንዑስ ዘርፍ ነው፡፡ ከጠቅላላው የፋብሪካ ኢንዱስትሪ የሰው ኃይል ውስጥ ከ27% የሚበልጠውን የያዘው ሥራ ፈጣሪ ንዑስ ዘርፍ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ነው፡፡ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው ዘርፍ 14% የቋሚ ካፒታል ጥሪት ያፈራል፡፡ ቢራ ፋብሪካ ደግሞ 10% የቋሚ ካፒታል ጥሪት ለኢንዱስትሪው ያበረክታል፡፡ በጠቅላላ የፋብሪካው ዘርፍ ለኢንዱስትሪው 53% ተጨማሪ እሴት ያስገኛል፡፡ ከኢንዱስትሪው የሠው ኃይል ውስጥ የ44% ድርሻ ሲኖረው ለዚሁ ክፍለ ኤኮኖሚ 48.5% የቋሚ ካፒታል ጥሪት ያፈራል፡፡

የፋብሪካው ዘርፎች ከሚያመርቱት ምርት አንጻር ያላቸው ጥንቅር ሲገመገም፡-

ሀ. የፍጆታ ዕቃ የሚያመርቱት ከፍተኛ የሰው ኃይል፣ ተጨማሪ ዕሴትና የቋሚ ካፒታል ጥሪት ያስገኛሉ፡፡

ለ. የሚሸጥ ዕቃ የሚያመርቱት መካከለኛ የሰው ኃይል፣ ተጨማሪ እሴትና የቋሚ ካፒታል ጥሪት ያፈራሉ፡፡

ሐ. የካፒታል ዕቃ የሚያመርቱት ዝቅተኛ የሰው ኃይል፣ ተጨማሪ እሴትና የቋሚ ካፒታል ጥሪት ያፈራሉ፡፡ የሀገሪቱ ፋብሪካዎች ጥንቅር ሲታይ ከፍተኛ ብቃት፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት እንዲኖር የሚያግዝ አይደለም፡፡ ከዚህ የምርት ጥንቅር መገንዘብ የሚቻለው፣ የፋብሪካው ዕድገት የውጭውንና የሀገር ውስጡን ውድድር ለመቋቋም በሚያስችለው ብቃት ላይ አለመሆኑን ነው፡፡

ሁሉም የኢንዱስትሪ ዘርፎች በቋሚነት ዕድገት ማስመዝገብ ያልቻሉ ሲሆን በተለይም የፋብሪካው ዘርፍ ዕድገት ምጣኔ በጣም አዝጋሚ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የፋብሪካው ዘርፍ የውጭ ጥገኛና በውጫዊ ሁኔታዎች ለሚከሠቱ አደጋዎች የተጋለጠ ነው፡፡ ስለሆነም መሪ ቴክኒዎሎጂ የሚጠቀሙ ማለትም እንደኬሚካልና ብረታ ብረት የመሣሠሉት የኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ባለመስፋፋታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ነጻ፣ ውስጣዊ ጥንካሬና ትስስር ያለው ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት መፍጠር አልተቻለም፡፡

በመንግሥት ይዞታ ስር ያሉት አብዛኞቹ ፋብሪካዎች በተፈጥሮ ሃብት ላይ የተመሠረቱና (አግሮ ኢንዱስትሪዎች) ቀላል ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የኤሌክትሮኒክስ፣ የኬሚካልና የማሽን ኢንዱስትሪ፣ የብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ፣ የትራንስፖርት መሣሪያዎች፣ የመለኪያ ዕቃዎችና







የመሣሰሉትን ስትራቴጅያዊ ኢንዱስትሪዎች በማስፋፋት ረገድ ኢትዮጵያ ያለችበት ደረጃ ሲገመገም እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ከኬንያ በግማሽ የምታንስ ሲሆን የግብፅን 1/3ኛ (ሲሶ) የሚያክል አቅም አልገነባችም፡፡ ይህ መዋቅራዊ ችግር ደግሞ የተፋጠነ የኢንዱስትሪ ልማት እንዲኖር የሚያግዝ ፖሊሲና የኢኮኖሚ አመራር ባለመኖሩ የመጣ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩት መንግሥታት ፖሊሲዎች ለዚህ ከፍተኛ ጉዳይ ትኩረት የሚሰጡ እንዳልነበሩ ሁሉ የአሁኑ መንግሥት ፖሊሲም ይኸንኑ ሚዛናዊ ያልሆነ አወቃቀርና ጥገኝነት በባሠ ሁኔታ እንዲቀጥል የሚያደርግ እንጅ የቀድሞውን ስህተት የሚያርም አይደለም፡፡

የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ፍላጐት ለማሟላት የሚጫወቱትን ሚና ለማጠናከር በተፈጥሮ ሃብት ላይ የተመሠረቱ አግሮ ኢንዱስትሪዎችን የቴክኒዎሎጂ ደረጃ ማሻሻል ጠቃሚ ቢሆንም እነዚህን ዘርፎች ቁልፍ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ስትራቴጅ ማዕከል አድርጐ መውሠድና የኢንቨስትሜንት ቅድሚያ እንዲያገኙ ማድረግ የእስካሁኑን መዋቅራዊ መዛባት ይበልጥ ያባብሰዋል፡፡ በረጅም ጊዜ ሂደትም በቴክኒዎሎጅ የተራመደ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመፍጠር አያስችልም፡፡ አሁን ያለው ፖሊሲ ቴክኖዎሎጅያዊ መሪነት ያላቸውን፣ ለኢኮኖሚው አዳዲስና ፈጣን የሆነ ተነጻጻሪ ጥቅም ማመንጨት የሚችሉትን ስትራቴጂያዊ ኢንዱስትሪዎች ሙሉ በሙሉ የረሣ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ የሀገሪቱ ኤኮኖሚ ውስጣዊ መመጋገብ አይታይበትም፡፡ የኢትዮጵያ ፋብሪካዎች ባላቸው አነስተኛ የማምረት አቅምና በሚታይባቸው የምርት ጥራት ጉድለት የተነሣ የእርስ በርስ ትስስራቸው ደካማ ነው፡፡ የሀገሪቱ ፋብሪካዎች የካፒታል ዕቃዎችን ብቻ ሣይሆን የፍጆታ ዕቃም ጭምር ከውጭ የሚያስገቡ በመሆናቸው ለዓለም አቀፍ ቀጥተኛ ተፅእኖ የተጋለጡና የውጭ ጥገኛ ናቸው፡፡ መለዋወጫ፣ ቅባት፣ ነዳጅና የመሣሰሉት በርካታ ዕቃዎች ከውጭ ይገባሉ፡፡ ፋብሪካዎች ለእንቅስቃሴያቸው የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት በማግኘት በከፍተኛ ደረጃ ኢምፖርት ቢያደርጉም በዚያው መጠን ለሌላው ዓለም የሚያገለግል ምርትና ግብዓት ለውጭ ገበያ አይሸጡም፡፡ ከኤክስፖርታቸው ሦስት እጥፍ የሚበልጥ ኢምፖርት ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም በሀገራችን የፋብሪካ ኤክስፖርት ገና ጨቅላ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኤኮኖሚ ኤክስፖርት መጠን ውስጥ የፋብሪካው ድርሻ 10% ብቻ ነው፡፡ በ1993/94 የፋብሪካው ኤክስፖርት ግኝት 20% እና 15% የደርሰው የቡና ዋጋ በመውረዱና ከቡና ይገኝ የነበረው ኤክስፖርት ግኝት በመቀነሱ ሲሆን የፋብሪካው ኤክስፖርት ግኝት

የሚሸፍነው የኢምፖርት መጠን ከ40% በታች ነበር። ይህ የሚያሣየው በኤክስፖርትና በኢምፖርት መካከል ሠፊ ክፍተት መኖሩን ነው። የዘርፉ የኤክስፖርት አቅም አለማደጉ ደግሞ ሀገሪቱ ላለባት የውጭ ምንዛሬ ዕጥረትና ከፍተኛ የብድር ጫና የራሱን ሚና ይጫወታል።

በሀገራችን የፋብሪካው ዘርፍ ኤክስፖርት ዳይቨርስፊኬሽን የጐደለው ከመሆኑ በተጨማሪ ሙሉ በሙሉ ምርቱን ኤክስፖርት የሚያደርግ መሆኑ ደግሞ ሌላው ችግር ነው። ከፋብሪካዎች መካከል ኤክስፖርት በማድረግ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የቆዳው ዘርፍ ቢሆንም ሁሉንም ምቹ አጋጣሚዎች ለመጠቀምና በሙሉ አቅሙ ለመስራት አልቻለም። ሌዘር ፕሮሰስ የማድረግ አቅሙ አሁንም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው። እስካሁን ተነጻጻሪ ጥቅም ማግኘት የቻለው በሌላ ሣይሆን ተፈጥሯዊ መሠረት ያለው አግሮ ኢንዱስትሪ በመሆኑ ምክንያት አስተማማኝና በዝቅተኛ ዋጋ የሚቀርብ ጥሬ ዕቃ ስለሚያገኝ እንዲሁም አንፃራዊ በሆነ መልኩ ርካሽ ጉልበት ስለሚጠቀም ነው። ይኸንን ዕድል ተጠቅሞ ቴክኖሎጂያዊ አቅሙን አላሣደገም። ሌሎቹ ደግሞ እንደ ጨርቃ ጨርቅ፣ ስኳርና ቅመማ ቅመም የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የቆዳውን ዘርፍ ያህል እንኳ ተነፃፃሪ ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ አልቻሉም። የተሽከርካሪ አካል የሚያመርቱ በጣት የሚቆጠሩ ፋብሪካዎች በአነስተኛ መጠንና ተከታታይነት በሌለው ሁኔታ ኤክስፖርት ከሚያደርጉ በስተቀር ኤክስፖርት እንዲያመርቱ ሆነው የተቃኙ የካፒታል ዕቃ ማምረቻ ፋብሪካዎች በሀገሪቱ የሉም ማለት ይቀላል።

የፋብሪካው ዘርፍ ኤክስፖርት መጠን ዝቅተኛ መሆን የዘርፉን ኋላ ቀርነት ብቻ ሣይሆን በመንግሥት በኩል የፖሊሲ ትኩረት አለመኖሩንም ያመለክታል። እስካሁን ድረስ የመንግሥት ሥልጣን የያዙት የኢትዮጵያ ገዥዎች ኤክስፖርት ላይ ተጣብቀው የኖሩት በሌላ ሳይሆን የተሣሣተ የኤኮኖሚ ፖሊሲ በመከተላቸው ነው።

## *2.9 የአካባቢ መጐዳት*

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሠተውን ረሃብ ከሚያባብሱት ሁኔታዎች መካከል የአካባቢ መጐዳት አንዱና ዋነኛው ነው። ተገቢ ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም የአፈርና ውኃ ሃብታችንን እያባከነ ነው። ከማገዶና ከኮንስትራክሽን ፍላጐት ማደግ ጋር ተያይዞ ደን እየተመነጠረ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ከባድ የአካባቢ ጉዳት አስከትለዋል። የኢትዮጵያ ግብርና እንቅስቃሴ የተፈጥሮ ጥገኛ እንደመሆኑ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጥያቄ ከዘላቂ





የአፈርና ውኃ ጥበቃ እንዲሁም ከመሬት ለምነት ጋር የተያያዘ ነው። በ1980ዎቹ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሣዩት ሀገሪቱ ወደፊት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ልማት ለማምጣት ያላት ዕድል በመሬት መጐዳት ትልቅ አደጋ ላይ መውደቁን ያሣያሉ። እየቀጠለ ያለውን የመሬትና አካባቢ ጉዳት ችግር ለማስቀረት በሚገባ የተቀናጀና በግልጽነትና በትኩረት የሚሠራ ተቋማዊ እንቅስቃሴ የለም።

የመሬት ፖሊሲው ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ጤናማ እንቅስቃሴ እንዳይኖር በማድረጉ የገጠር ሕዝብ ቁጥር ከሚገባው በላይ እየጨመረ ነው። ለኢትዮጵያ ግብርና አለመሻሻል የመሬት ሃብት በኤኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለውን ሚና የተገነዘበ የመሬት ይዞታ ፖሊሲ አለመኖር አንደኛው ምክንያት ነው። መንግሥት የሰው ኃይል አቅምን በመገንባትና በአነስተኛ ይዞታ ላይ የተመሠረተውን የገጠር ጉልበት አሟጦ በመጠቀም ውጤት ይመጣል በሚል እምነት ላይ በመመስረት በኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካይነት ለገበሬዎች ሰፊ ድጋፍ ሲሠጥ ቆይቷል። ይሁን እንጅ የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ የሀገሪቱን የምግብ ዋስትናና የግብርና ልማት ሊያረጋግጡ አልቻሉም። ፖሊሲው በአጠቃላይ ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርጉ መዋቅራዊ ችግሮች ያሉበት ሲሆን ከእነዚህም መካከል እየጨመረ የሚሄድ የሕዝብ ብዛት፣ አስከፊ የመሬት መጐዳት፣ ያልዳበረ የገበያ ሥርዓት፣ ደካማ መሠረተ ልማት፣ ከእርሻ ውጭ ያሉት ዘርፎች የሚለሙበት አቅጣጫ አለመተለምና የመሣሠሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በዚህም ምክንያት በገጠርና በከተማ የተስፋፋው ድህነት የሕዝቡን የመግዛት አቅም እንዲወድቅ ስላደረገው በሀገሪቱ የግብርና ልማት ሊረጋገጥ አልቻለም።

በገጠር የሚታየው የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የኑሮ አማራጭ መጥበብ ግብርናውን አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ጥለውታል። አሁን 70 ሚሊዮን የደረሠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በ2022 ወደ 138 ሚሊዮን እንደሚደርስ ስለሚገመት በመጪዎቹ አስርተ ዓመታት ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ 76% የሚሆነው በገጠር መኖሩን ይቀጥላል። በኢኮኖሚው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግ ባለው ክብደትና የገጠሩን ትርፍ ጉልበት የሚቀበል አማራጭ በማይታይበት ሁኔታ ላይ የግብርናን ምርታማነት እንዳያድግ አስሮ የሚይዝ ከፍተኛ የመሬትና የተፈጥሮ ሃብት ጉዳት ተባብሶ ቀጥሏል።

የገጠሩ ሕዝብ ቁጥር መጨመር የመሬት ይዞታውን መጠንና ጥራትም ስለሚቀንሠው በግብርና ምርታማነት ላይ ያለው ተፅእና እጅግ ከፍተኛ ነው። የአካባቢን መጐዳት ተከትሎ በመባባስ ላይ ያለውን ድህነት

በመቀነስ በመንግሥት በኩል ተቀየሱ የሚባሉት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት፣ የድርቅ ተጠቂ አካባቢዎችን ኢኮኖሚ ሁኔታ ለማጠናከር ሚዛናዊ የዕርዳታ ስርጭት፣ የታቀደ ልማት የማረጋገጥ ስልትና የሠፈራ ፕሮግራም ድርቅን ለመከላከል ውጤታማ ዘዴ ሆነው አልተገኙም። ከደርግ ጊዜ ጀምሮ የሚሠራበት አስቸኳይ የምግብ ዋስትና መጠባበቂያ፣ የአሁኑ መንግሥት የቀየሠው የምግብ ዋስትና ስትራቴጅ፣ ከእርዳታ ሠጪዎች ጋር የፈጠረውና የ15 ሚሊዮን ሕዝብ የምግብ ዋስትና ከ3 እስከ አምስት ዓመታት ያሻሽላል የሚለው የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አዲስ እቅድ ውጤታማ አልሆኑም።

በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ እየተባባሠ ለመጣው የአካባቢ መጐዳት፣ በገጠርና በግብርና ልማት ረገድ ለሚታየው ውድቀትና ገበሬው ለተዘፈቀበት ድህነት ዋነኛው ምክንያት ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የልማት ሃሣብ ቴክኒዎሎጅና የተግባር መመሪያ የሚመነጨውና የሚሠራጨው የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው ገበሬ ተሣትፎና እውቀት ውጪ በሆነ መንገድ መሆኑ ነው። ፖሊሲና ዕቅድ አውጭዎች፣ የልማት አስተባባሪዎችና ባለሥልጣኖች የመሠላቸውን ሕግና መመሪያ አውጥተው በገበሬው ላይ ከመጫን በስተቀር በፖሊሲ ቀረጻና ትግበራ የሚጠቅም ሃሣብ ከታች ወደ ላይ የሚመጣበትን መንገድ ተከትለው አያውቁም። የኢትዮጵያ ገበሬ ከላይ ወደ ታች የሚወርድ ትዕዛዝ እንዲፈጽም ከሚገደድ በስተቀር በራሱ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለው ፖሊሲ በሚዘጋጅበት ጊዜ ሃሣቡን እንዲሠጥና ተሣትፎ እንዲያደርግ ዕድል አግኝቶ አያውቁም።

## *2.10 ሥራ አጥነት*

ኢንቨስትሜንትን የሚያደፋፍርና አዳዲስ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል የልማት ፖሊሲ ባለመኖሩ የሥራ አጥነት ችግር እየተባባሰ ነው። የሀገሪቱ ትምህርት ሥርዓት ከጠቅላላው የልማት ፍላጐት ጋር የተጣጣመ የሠለጠነ የሠው ኃይል ለማፍራት በሚያስችል ዓላማ ላይ ባለመመስረቱ ከትምህርት ቤት የሚወጡ አብዛኞቹ ወጣቶች ሥራ ፈተው የቤተሰብና የሀገር ሸክም ከመሆን ሌላ የተሻለ ዕድል የላቸውም። በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድገውን የሕዝብ ብዛት ለመቆጣጠር፣ የአካባቢ ጉዳትን ለመከላከልና የመሬትን ምርታማነት ለማሣደግ የሚያስችል ተስማሚ ስትራቴጂ ስለሌለ በግብርና ከተሠማራው የሠው ኃይል መካከል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ሥራ አጥ ሆኗል። የገበሬው የይዞታ መጠን በየጊዜው እያነሠ፣ የመሬት ለምነትም እየተሟጠጠ በመሄዱና የሀገሪቱ ግብርናም የዝናብ ጥገኛ በመሆኑ አብዛኛው ገበሬ ሙሉ ኃይሉን ተጠቅሞ ከማምረት ይልቅ ጉልበቱ በከንቱ እየባከነ ነው።







በተለይም የመሬት ፖሊሲው የባለቤትነት መብትን በመከልከሉ ከግብርና ሥራ የሚተርፈው ጉልበት ወደሌላ መስክ እንዳይንቀሣቀስ አስሮ በማስቀመጥ በገጠር ከፍተኛ መጠን ያለው ሥራ ፈት እየተፈጠረ ነው።

ከትምህርት ቤት እየወጡ ሥራ ለሚፈልጉ ዜጐች አዳዲስ የሥራ ዕድል ሊፈጠር ቀርቶ የመንግሥት ድርጅቶችን ወደ ግል ማዛወርና የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በሚል ሰበብ ስራ የነበራቸውም በርካታ ዜጐች በየጊዜው ከመደበኛ ሥራቸው እየተባረሩ ወደ ሥራ አጡ ጐራ እየተቀላቀሉ ነው። በ1994 የወጣ መረጃ እንደሚያሣየው ዕድሜያቸው ለሥራ ከደረሱ 44.7 ሚሊዮን ዜጐች መካከል 32.4 ሚሊዮን የሚሆኑት ሥራ አጥ ናቸው ። ይኸም ማለት ለሥራ ከደረሱ ዜጐች ውስጥ 72% ሥራ የላቸውም ማለት ነው። በከተሞች ብቻ ያለው የሥራ አጥ መጠን ሲታይ ከጠቅላላው የከተማ ነዋሪ መካከል ከ30-40% የሚሆነው ሕዝብ ሥራ የለውም።

## *2.11 የድህነት መባባስ*

ሀገሪቱ የምትገኝበትን ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታና አስከፊ ድህነት ለማየት እንዲቻል የታወቁ የዕድገት መለኪያዎችን በመጠቀምና ከተመረጡ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች ጋር ኢትዮጵያን በማነፃፀር ነገሩን ግልፅ ማድረግ ይገባል። ለምሳሌ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአጠቃላዩ ብሔራዊ ምርት የሚያገኘው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ድርሻ 100 ዶላር ነው። በዚሁ ወቅት የአፍሪካ አማካይ የነፍስ ወከፍ ድርሻ 800 ዶላር ነው። በተናጠል የተወሰኑ ሀገሮችን ብንመለከት ደግሞ ኬንያ 360 ዶላር፣ ሱዳን 330 ዶላርና ግብፅ ደግሞ 1390 ዶላር ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ አላቸው። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ100 ኢትዮጵያዊያን መካከል ወደ 50 ገደማ የሚጠጉት ከድህነት ወለል በታች ናቸው።

የምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ ኤሽያን ብንመለከት ከ40 ዓመታት በፊት 35% የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ነው በፍጹም ድህነት ደረጃ ላይ የነበረው። ይሁን እንጂ በ20 ዓመት ውስጥ ይኸንን ቁጥር ወደ 10% ዝቅ ለማድረግ ችለዋል። በእኛ ሀገር ግን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ መሄድ አልቻለም። እነሱ ባደጉበት ፍጥነት በየዓመቱ ዕድገት ማስመዝገብ ብንችል እንኳ የሀገራችንን ፍጹም ድሃዎች ቁጥር የተጠቀሱት ሀገሮች ከ40 ዓመት በፊት ወደነበሩበት 35% ደረጃ ዝቅ ለማድረግ በቀላሉ ወደ 40 ዓመት ገደማ ይወስድብናል።

ከዚህ ባነሰ ጊዜ በፍጹም ድህነት ውስጥ የገቡትን ዜጎች ደረጃ ለማሻሻል ከተፈለገ ቢያንስ ለ20 ተከታታይ ዓመታት በእያንዳንዱ ዓመት 8% የኢኮኖሚ ዕድገትና በየዓመቱ ለ1 ሚሊዮን ገደማ ዜጎች የስራ ዕድል የሚያስገኝ የልማት እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሀገራችን ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ከ15% ትንሽ ከፍ ያለ ሕዝብ በከተማ የሚኖር ሲሆን ከሠሀራ በታች ባሉ ሌሎች ሀገሮች ግን 34% ይደርሳል፡፡ ድህነት በሀገሪቱ ገጠርና ከተማ በጠቅላላው የተስፋፋ ሲሆን በገጠር ያለው ሁኔታ ደግሞ ከከተማው የባሰ ነው፡፡ ለዚህ ዋና ዋና ከሚባሉት ምክንያቶች መካከል የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲው ለገበሬውና ለመሬቱ ምርታማነት መጨመር የማያግዝ መሆን፤ በቂ የእርሻ መሬት አለመኖር፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውሃና፣ የመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፣ ተደጋጋሚ ድርቅ ወዘተ… ይገኙበታል፡፡ የዛሬ 5 ዓመት ገደማ በተደረገ ጥናት በሀገር ደረጃ ከጠቅላላው ፍጆታ ውስጥ 60% የሚሆነው ለምግብ ፍጆታ የሚውል ሲሆን በገጠር ደግሞ ለምግብ ፍጆታ የሚውለው መጠን ከ60% የበለጠ ነው፡፡ በዓለም የጤና ድርጅት የሚታመንበት የካሎሪ መጠን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው በቀን 2200 ካሎሪ ሲሆን በእኛ ሀገር አንድ ሰው በቀን የሚያገኘው መጠን ከ954 ካሎሪ አይበልጥም፡፡ በዚሁ ጥናት መሠረት ከሁለት ሦስተኛው የሚበልጡት ሕፃናት እድገታቸው የቀጨጨ ነው፡፡ በወንድና በሴት መካከል ከፍተኛ ልዩነት በሌለው ሁኔታ ከገጠሩ ሕዝብ መካከል ከአንድ አራተኛ የሚበልጡት በምግብ እጥረት መጐዳት የደረሰባቸው ናቸው፡፡ ይኸ ቁጥር በ1994/95 ውስጥ በጣም ጨምሯል፡፡

አንድ ዓመት ያልሞላባቸው ሕፃናትና ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሞት በ1990 ዓ.ም. በተደረገ ጥናት ከአንድ ሺህ ልጆች ውስጥ 173 እና 107 ነበር፡፡ በሌሎች ከሠሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ይኸ ቁጥር እንደቅደም ተከተላቸው 151 እና 92 ብቻ ነው፡፡ በሌላ መረጃ ደግሞ ከሚወለዱት ሕፃናት መካከል ከ10% በላይ የሚሆኑት አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ ከ8% በላይ የሚሆኑት ደግሞ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ ይኸ ቁጥር ከሠሀራ በታች ካሉ ሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው፡፡ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ የሀገራችን ሕፃናት የምግብ እጥረት መጠን 48% ሲሆን ይህ ከሠሀራ በታች ባሉ ሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡

በተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ አመልካቾች የሀገራችንን ሁኔታ ከሌሎች






ሀገሮች ጋር ለማነጻፀር ቢያስፈልግ በ1989 በተገኘ መረጃ ኢትዮጵያ በየአንድ ሺህ ሰው 3 ሰዎች ብቻ ስልክ፣ 6 ሰዎች ብቻ ቴሌቪዥን፣ 196 ሰዎች ብቻ ሬዲዮ፣ ወደ ዜሮ መጠን የሚጠጋ የሰዎች ቁጥር ሞባይል ነበራቸው፡፡ ይህ እንደ ቅደም ተከተሉ በኬንያ ሲታይ 9፣ 22፣ 104 እና 1 ነው፡፡ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል በሱዳን ያለው ሁኔታ ሲታይ 3፣ 173፣ 271 እና 0 ነው፡፡ በዚሁ ቅደም ተከተል መሠረት በግብፅ ያለው ሁኔታ ደግሞ 9፣ 183፣ 160 እና 3 ነው፡፡ በቅላላው በአፍሪካ ያለው ሁኔታ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ሲታይ በአማካይ 18፣ 59፣ 214 እና 14 ነው፡፡ በዚሁ ዓመት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ከመሃይምነት በተላቀቁ ሰዎች ቁጥር፣ በልጆች የርሃብ ጉዳት፣ በመጠለያ ችግር፣ በንጽህና አገልግሎት አለመኖርና በመሳሰሉት የኑሮ ሁኔታ አመልካቾች ከሠሀራ በታች ከሚገኙ ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

በሰብዓዊ ልማት መመዘኛዎች ማለትም በምርታማነት፣ በእኩል ተጠቃሚነት፣ በዘላቂ የልማት እድገት፣ በፖሊሲ አወጣጥና አወሳሰን ረገድ ባለ ተሳትፎና በመሳሰሉት የኢትዮጵያ ዕድገት 25% አካባቢ ነው፡፡ ይህ ነጥብ ከዓለም አማካይ ነጥብ አንድ ሦስተኛ ብቻ ሲሆን ከታዳጊ ሀገሮች አማካይ ነጥብ ደግሞ ከግማሽ ያነሰ ነው፡፡ በጣም ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች ካገኙት አማካይ ነጥብ በሦስት አራተኛ ዝቅ ያለ ነው፡፡ በሰብዓዊ ልማት ረገድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ስለኢትዮጵያ የሚያወጣቸው መረጃዎች በየጊዜው ወደታች የማሽቆልቆል ካልሆነ በስተቀር የነበረውን ሁኔታ እንኳ ይዞ ለመቆየት እንዳልተቻለ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በ1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በሰብዓዊ ልማት ረገድ የነበረችበት ደረጃ 138ኛ ነበር፡፡ ባለፉት 2 ዓመታት ደግሞ ከ175 ሀገሮች መካከል 169ኛና 170ኛ ነበረች፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች በቅርብ ጊዜ ይሻሻሉ ይሆናል ብሎ ተስፋ ለማድረግ እንዳይቻል ከአጠቃላይ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሩ በባሰ ፍጥነት የሕዝብ ብዛት እየጨመረ 70 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ይህ ቁጥር ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ውስጥ ከናይጀሪያ ቀጥላ በ2ኛ ደረጃ ከዓለም ደግሞ በዘጠነኛ ደረጃ እንድትቀመጥ አድርጓታል፡፡ በሕዝቧ ብዛት መጨመር የተነሳ በአንድ ስኰየር ኪሎ ሜትር የሚኖረው ሰው ቁጥር ከ63 በላይ ነው፡፡ ከሠሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ግን 27 ሰው በ1 ስኰየር ኪሎ ሜትር ውስጥ ይኖራል፡፡ የሕዝቡ አሰፋፈር ደግሞ ቆላማው የሀገሪቱ ክፍል አነስተኛ ሕዝብ በተበታተነ ሁኔታ የሰፈረበት ሲሆን በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ

በተጠጋጋ ሁኔታ በደጋማው (ከሀገሪቱ ቆዳ ስፋት ከ40% ያነሠ ነው) የሀገሪቱ ክፍል የሰፈረ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በአሁኑ ጊዜ ወደ 3% ገደማ ዓመታዊ ዕድገት የሚታይበት ነው፡፡ በ1965 ዓ.ም. 38 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን በ1997 ደግሞ 70 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ አሁን በየዓመቱ በሚታየው 3% ጭማሪ የሚቀጥል ከሆነ በየ23 ዓመቱ በእጥፍ ስለሚጨምር በ2020ዓ.ም. ወደ 138 ሚሊዮን ይደርሳል፡፡ የኢትዮጵያ ሴቶች በአማካይ እስከ 6 ልጆች እንደሚወልዱ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ ወደ ግማሽ የሚጠጋው እድሜው ከ16 ዓመት በታች ነው፡፡ እድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑት ቁጥር ከ5% አይበልጥም፡፡ እ.ኤ.አ ከ1990-98 ባሉት ዓመታት ከ15-49 ዓመት እድሜ ካላቸው ያገቡ ሴቶች መካከል የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙት በአማካይ 4% ብቻ የሚሆኑት ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃዎች የሚያሳዩት ቢኖር ከፍተኛ የወሊድ ሁኔታ መኖሩንና ዝቅተኛ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መኖሩን ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ ቢስፋፋ ውልደትን ስለሚቀንስ የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን ፍጥነት ለመቀነስና ሁኔታውን ለመቀልበስ ይቻላል ብሎ ተስፋ ለማሳደር እድል ይገኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁኔታው ይኸንን አያሳይም፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የቀረቡት ማሳያዎች ሀገሪቱ የምትገኝበትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ድቀት ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተባባሰውን ድህነት ስፋትና ጥልቀት ለመረዳት መጠነኛ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው፡፡ የችግሩ ዓይነትና መጠን ከዚህም የከፋ መሆኑን ለመረዳት ደግሞ በምንኖርበት አካባቢና የስራ ቦታ በየዕለቱ የምናያቸውን በልመና የተሰማሩ ዜጎች፣ በረንዳ ላይ የወደቁትንና በየስርቻው ካላአንዳች ምግብና መጠለያ ራቁታቸውን የሚውሉትንና የሚያድሩትን ወገኖች በዓይነ ሕሊናችን ማሰብ በቂ ነው፡፡ ሀገሪቱ የምትገኝበት ድህነት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚገለጽና በቁጥር እየተሰላ ሊቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ በተወሰኑ የኢኮኖሚና የኑሮ ሁኔታ ማሳያዎች ከሚገለፀውና በቁጥር ከሚቀርበው በላይ የሚዘገንን ድህነት በሀገሪቱ ውስጥ ተንሰራፍቷል፡፡

ድህነት ላይ ላዩን ሲያዩት የገንዘብ እጦት ብቻ ይመስላል እንጂ ክብርን የሚያዋርድና ብዙ ጠንቆችን አስከትሎ የሚመጣ ክስተት ነው፡፡ ያልተመጣጠነ ምግብ፣ ያልተሟላ ጤንነት፣ የትምህርት እድል ማጣት፣ በማይረባ ቤት ውስጥ መኖር፣ ስራ ማጣት፣ በማይጠቅም ስራ መሰማራት፣ ፍትህ ማጣት፣ የሕግና የፖለቲካ መብትን መነፈግ፣ ወዘተ… እነዚህ ሁሉ







የድህነት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ድህነት በሌላ ሁኔታም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን ሕይወት በራሱ ለመቆጣጠርና የወደፊት እድሉንም ለመወሰን ካልቻለ፣ ሰብዓዊ ክብሩን ለማስጠበቅ አቅም ካጣ፣ እያደር በሚያከሳ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ከተዋጠና በነገው ተስፋ እምነት አጥቶ ሁሉ አይጥምሽ ለመሆን ከተገደደ እነዚህ ሁሉ የድህነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ የተለያየ ዓይነት ችግር የሚያጠቃው እነዚያ ድህነት አስሮ ተብትቦ የያዛቸውን ወገኖች ነው፡፡ ለምሳሌ በስራ ማጣት የተነሳ የገቢ ማነስ፣ ረሃብ፣ ጤና ማጣት፣ የመጠለያ ችግር፣ ልብስ ማጣትና የሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎቶች መጥፋት በአንድ ላይ ተከታትለው ይከሰታሉ፡፡ የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ አካላዊ ጥንካሬን የሚጎዳና የአእምሮን መዳበር የሚገድብ ነው፡፡ የጤና ጉድለት ደግሞ የአካል ጉድለትን በማስከተል ብቻ ሳይወሰን የኋላ ኋላ አኗኗርን ማቃናት እስከሚሳን ድረስ ከባድ ጉዳት የሚያስከትል ነው፡፡ የቤተሰብ የስራ ሁኔታና የኑሮ ደረጃ በልጆች አስተዳደግ፣ ትምህርት፣ ጤንነትና የወደፊት አኗኗር ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡ የእናትና የልጅ በምግብ መጎዳት ለመጪው ሕይወት መጥፎነት እንደ መጀመሪያ ምልክት ማረጋገጫ የሚታይ ነው፡፡ የተቸገሩ ወላጆች የልጆቻቸውን ጤንነት አሟልተውና በትምህርት አንፀው ለማሣደግ ያዳግታቸዋል፡፡ ራሣቸው ያልተማሩ ከሆኑ ደግሞ ልጆቻቸውን በትምህርት እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ ይቸገራሉ፡፡ ወላጆቻቸውን በትምህርት እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ለማወቅ ይቸገራሉ፡፡

በአጠቃላይ አነጋገር ድህነት ብዙ መልኮችና ባህርያት ያሉት ውስብስብ ጉዳይ ነው፡፡ በሀገራችን የተንሰራፋው ድህነት እንዲህ በቀላሉ መፍትሔ ይገኝለታል የሚባል አይደለም፡፡ በተለይ ደግሞ የዴሞክራሲ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር በሌለበት ሁኔታ ከድህነት መውጣት የሚቻል ጉዳይ አይደለም፡፡ የሀገራችን ድህነት ስር የሰደደውና ከዚህ አስከፊ ደረጃ ላይ የደረሰው ሀገሪቱ ድህነትን ለማስወገድ የሚረዳ፣ ተከታታይ ዕድገትንና ዘላቂ ልማትን ለማስገኘት የሚችል የተፈጥሮ ሃብት ስለሌላት አይደለም፡፡ ለልማት ሊሰለፍ የሚችል የሰው ጉልበት ስለቸገራትም አይደለም፡፡ ችግሯን የሚገነዘብላትና ድጋፍ ሊያደርግላት የሚችል አጋርና ተባባሪ ስላጣችም አይደለም፡፡ በእርግጥ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂና የካፒታል ችግር ያለባት ሀገር መሆኗ ባይካድም እንዲህ ዓይነት ችግር ያለበት ሀገር ድሃ እንደሆነ ይቀራል ማለት አይደለም፡፡ በተፈጥሮ ሃብት፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በቴክኒዎሎጂና በካፒታል ችግር ከኢትዮጵያ በከፋ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ብዙ ሀገሮች ከድህነት ሰልፍ ወጥተው ዘላቂ በሆነ የዕድገትና የልማት መስመር ውስጥ መግባት ችለዋል፡፡ የእኛ ሀገር ችግር በአብዛኛውና ከምንም

በላይ ከዴሞክራሲ ሥርዓትና ከመልካም አስተዳደር መጥፋት ጋር የተያያዘ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ ከድህነት የሚጠቀም አገዛዝ በመተከሉ ድህነትን በማስወገድ ፋንታ እንዲጐለብትና ስር እንዲሠድ አድርጐታል። የአገዛዝ ሥርዓቶች ሁሉ አንድ የጋራ ባህሪይ አላቸው። ይኸውም ሀገርና ሕዝብ ሲለማ ጥቅማችን ይጓደላል ብለው ይሠጋሉ። ድህነት ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ለአገዛዝ ይመቻል ብለው ያስባሉ። በዚህ እምነታቸው በመመራት ድህነትን ያባብሱታል እንጂ አያስወግዱትም። ሕዝቡ ዳቦ ጠግቦ ካደረ ለሥልጣናችን ስጋት ይሆናል ብለው ስለሚያስቡ በድሃ ሕዝብ ጀርባ እንደታዘሉ ለመኖር የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ድህነት ከጠፋ በብድርና በእርዳታ ስም ከየማዕዘኑ የሚቃርሙት ገንዘብ ምንጩ እየመነመነ ስለሚሄድ በድሃ ሕዝብ መሃል የገነቡት የድሎትና የምቾት ደሴት አደጋ ላይ ይወድቃል ብለው ይጨነቃሉ። ከዚህ ሁሉ ጣጣ ሀገርና ሕዝብ ይበልጥ እየደኸዩ የእነሱ ሥልጣን ይበልጥ እየተደላደለና ምቾታቸው እየጨመረ እንዲሄድ ይፈልጋሉ። ማንም በግልፅ እንደሚያውቀው የበለጸጉ ሀገሮችን ከሚመሩ ፕሬዝዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትሮች የበለጠ በትላልቅ ባንኮች ውስጥ ተቀማጭ ወርቅና ዶላር ያላቸው እጅግ ድኃ ሀገሮችን የሚገዙ ፕሬዝዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም። አገዛዝ በሥልጣን መንበሩ ላይ እስከተቀመጠ ድረስ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከድህነት ይወጣሉ ብሎ ማሰብ በሕልም ቅቤ እንደመብላት የሚቆጠር ነው።

## *2.12 ትኩረት የተነፈገው አነስተኛ ዕደ ጥበብ*

ከጠቅላላው ኢንዱስትሪ 76 በመቶ የሚሆኑት የጎጆ (የእደ-ጥበብ) ኢንዱስትሪዎች ናቸው። የግብርናው ዘርፍ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች የሚካሄድ እንደሆነው ሁሉ የኢንዱስትሪውም ዘርፍ በብዛት የሚካሄደው እንዲሁ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው የጎጆና የእደ ጥበብ ተቋማት ባለንብረቶች ነው።

የእደጥበብ ስራ በሀገሪቱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የጥራት ደረጃ የሚከናወንና በቂ ገበያም የሌለው በመሆኑ እድገት አላሳየም። እነዚህ በአነስተኛ የሰው ጉልበትና ወጪ የሚሰሩ የእደ ጥበብ ስራዎች በዘርፉ ለተሰማሩት ዜጎች የኑሮ መሰረት ከመሆናቸው ባሻገር ለኢንዱሰትሪ መስፋፋትም ድጋፍ በሚሰጡ በት መንገድ ሲጠናከሩ ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኙ ይችላሉ። አናፂነት፣ ግንበኝነት፣ ብረት ስራ፣ የቆዳ ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የስፌት ስራ፣ የሽመና ስራ፣ የእንጨት ስራ ወዘተ. በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጁ፣ እንዲስፋፉና ገበያም እንዲያገኙ ቢደረግ አሁን ከያዙት





የሰው ኃይል በተጨማሪ የስራ እድል ሊያስገኙ ይችላሉ። የውጭ ምንዛሬን ለመቆጠብ፣ ለኢንዱስትሪ ግንባታ መነሻ የሚሆን የቴክኒክ ልምድና የስራ ዲስፕሊን ይፈጥራሉ። የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማሟላት ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋሉ። በእነዚህ መስኮች የቴክኒክ ልምድ ያገኙ ሰዎች ወደሌሎች ኢንዱስትሪዎች ተዛውሮ ለመስራት እንዲችሉ የመሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። ነገር ግን ለዚህ ዘርፍ የሚገባው ትኩረት ስላልተሰጠ እስካሁን ድረስ አጥጋቢ ውጤት አልተገኘም።

## *2.13 ዘላቂ ለውጥ የማይታይበት ማህበራዊ አገልግሎት*

### 2.13.1 ትምህርት

አሁን በስራ ላይ ያለው የሀገሪቱ ትምህርት ዓላማ በነጻነት ለማሰብ፣ ለመስራትና ለመኖር ሁለንተናዊ ብቃት ያለው ዜጋና ግልጽ ሕብረተሰብ መፍጠር ሣይሆን በሁሉም መስክ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የሚባለውን የገዥው ፓርቲ ርዕዮተዓለም ልዕልና ማረጋገጥ ነው። ይኸንን ግልጽ ለማድረግ ገዥው ፓርቲ "በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ፣ መሠረታዊ ጥያቄዎች" በሚል ርዕስ ነሐሴ 1992 ዓ.ም. ባሣተመው ፅሁፍ ከገጽ 91-117 ከሰፈረው ውስጥ የሚከተለው ይገኝበታል።

> *"አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሣሠብ ልዕልናን ማረጋገጥ ማለት አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል በተናጠል ብቻውን ሆኖ፣ ስለአንድ ጥያቄ ሲያስብ በውስጡ ያለው መሠረታዊ እምነት አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስለሆነ ዞሮ ዞሮ ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አቋም ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር ማለት ነው። አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሣሠብ ወደ ሁሉም አቅጣጫ ሠርጾ በመግባቱ የተነሣ ሰው በየግሉ ሲያስብ ከሱ ውጭ ሊያስብ የማይችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ ማለት ነው። …አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሣሠብ ልዕልናን ለመፍጠር የዜጐችን አስተሣሠብ በመቅረጽ ላይ ጠንካራ ሚናን የሚጫወቱ መዋቅሮች መኖር አለባቸው። … አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የአስተሣሠብ ልዕልናን በማረጋገጥ ላይ ትምህርት ቤቶች ወሣኝ ሚና መጫወት አለባቸው። … ይህ ደግሞ በቋሚ አካዳሚያዊ ትምህርት ብቻ ሣይሆን በሚሰጥ የሲቪክስ፣ የሕገ-መንግሥት ወዘተ ትምህርት በዕለታዊ የትምህርት ቤቶች አሠራር ወዘተ የሚገለጽ ነው።"* ይላል።

ይህ አመለካከት በአንድ በኩል እያንዳንዱ ሠው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውጭ እንዳያስብ፣ በዚህ ርዕዮተዓለም የተሸበበና የአስተሣሠብ

ነጻነት የሌለው እንዲሆን መታሠቡን የሚያረጋግጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ቤቶችና የመምህራን ቋሚ ተግባር “አብዩታዊ ዴሞክራሲ” የሚባለውን የገዥውን ፓርቲ ርዕዩተ ዓለም ልዕልና ማረጋገጥ ብቻ መሆኑን ያመለክታል። ባለፈው ዓመት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ መባረራቸውን በተመለከተ ሲያስረዱ የችግሩ መንስኤ በትምህርት ተቋሞች ውስጥ የኢህአዴግ የፖለቲካ መዋቅር አለመጠናከሩ ነው ማለታቸውም ይኸንኑ እውነታ ያረጋግጣል። በአጭሩ የሀገሪቱ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ ዜጎችን በአንድ ፓርቲ ርዕዮተዓለም እየጠመቁ (indoctrination) ማውጣት ነው።

አሁን በስራ ላይ ያለው የትምህርት ፖሊሲ እንደሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ሁሉ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ርዕዮተ ዓለማዊ እምነት መገለጫ ነው። የትምህርት ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የሲቪክ ማህበራትና በአጠቃላይ የሕዝቡ ተሣትፎ ሳይኖር የተዘጋጀና በግድ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ነው። ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል የነበሩትን የፍትሃዊነትና የጥራት ችግሮች በሁሉም ደረጃዎች ለማስወገድ በሚያስችል ጥልቅ ጥናት፣ በቂ ምክክርና ዝግጅት ላይ የተመሠረተ አይደለም።

የገዥው ፓርቲ የትምህርት አወቃቀር 8+2+2 ሲሆን ይህ አወቃቀር በየእርከኑ መሠጠት የሚገባው ትምህርት ከተማሪዎቹ የአዕምሮና የአካል ዕድገት ጋር የተመጣጠነ፣ ደረጃውና ተከታታይነቱ የተጠበቀ ትምህርት እንዲሆን ዕድል አይሠጥም። በተለይም 12 ዓመታት የሚወስደውን ትምህርት በ10 ዓመታት መጨረስ ይቻላል በሚል የተሣሣተ ግንዛቤ 10ኛ ክፍል የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ መሆኑ ለሀገራችን ትምህርት ትልቅ ውድቀት አስከትሏል። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ከትምህርት ሥርዓቱ የሚገለሉት ልጆች ዕድሜያቸው ከ14 እና ከ15 የማይበልጡ፣ ለሥራ ያልደረሱና ትምህርት ቤት መዋል የሚገባቸው ናቸው። ፈተናውን ያለፉት የሚገቡበት የመሰናዶ ፕሮግራም ደግሞ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ይሁን የኮሌጅ ተለይቶ የማይታወቅ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ነው እንዳይባል ከ2ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና በኋላ የሚሠጥ ነው። የኮሌጅ እንዳይባል የሚሠጠው ትምህርት አደረጃጀት ይዘትና አቀራረብ ሲታይ በማንኛውም መለኪያ ለኮሌጅ ደረጃ የሚመጥን አይደለም። የ10ኛ ክፍል ፈተና ወድቀው ወደሞያና ቴክኒክ ለገቡ ተማሪዎች የሚሠጠው ትምህርት ደረጃም በተመሣሣይ ሁኔታ የኮሌጅ ይሁን የ2ኛ ደረጃ ለመለየት የሚያስቸግር ነው። በ12+2 እና 12+ 3 መርሃ ግብር በኮሌጆች ይሠጥ የነበረው የዲፕሎማ ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ







የተሠረዘ ሲሆን በዩኒቨርስቲ ለ4 ዓመታት ይሠጥ የነበረው የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በ3 ዓመት እንዲጠናቀቅ የሚያደርግ መዋቅር ስራ ላይ ውሏል። ይህ የትምህርት መዋቅር የትምህርቱን ጥራትና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ዋጋ ቢስ የሚያደርግ ነው።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ከሆኑ ዜጐች መካከል ማንበብና መጻፍ የማይችሉት ከ70% በላይ ናቸው። ይህ አሀዝ በንጉሡ ጊዜ 93% የነበረ ሲሆን በደርግ ጊዜ በተካሄደው ሠፊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ወደ 37% ወርዶ ነበር። በአሁኑ መንግሥት የመሠረተ ትምህርት ብዙም ትኩረት ስላልተሠጠው ማይምነት እንደገና በሀገሪቱ ተስፋፍቷል። ከሀገራችን ሴቶች መካከል በአሁኑ ጊዜ ማንበብና መጻፍ የማይችሉት 68% ሲሆኑ ከወንዶች መካከል ደግሞ 32% ናቸው። በኢትዮጵያ ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ሕጻናት መካከል በአንደኛ ደረጃ 40% ገደማ ገና የመማር ዕድል አላገኙም።

በአሁኑ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መማር ከሚገባቸው ዜጐች መካከል ዕድሉን ያገኙት 12% ገደማ ናቸው። ይህ አጠቃላይ ምዝገባን የሚያመለክት ሲሆን በትክክል ትምህርቱን የሚከታተሉት መጠን ግን ከ8% አይበልጥም። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት አሁንም እንደሰፋ ነው። የሴቶች ተሳትፎ ከ9-10 ባለው ደረጃ 36%፣ በቴክኒክና ሞያ ማሠልጠኛ 47% በመዘጋጃ 28% ነው። በከተማ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጠቅላላ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ 36% ሲሆን በገጠር ደግሞ 29% ገደማ ነው።

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ልምድ ከግማሽ ምዕተ ዓመት ያልራቀ ነው። እስካሁን ድረስ ዕድሜያቸው ለከፍተኛ ትምህርት ከደረሱት መካከል የመማር ዕድል ያላገኙት ዜጐች ከ99% በላይ ናቸው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ስርጭት ከአዲስ አበባ ሌላ በጥቂት የክፍለ ሀገር ከተሞች አካባቢ ብቻ የተወሰነና የመቀበል አቅማቸውም እጅግ አነስተኛ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሚካሄዱ የማስፋፋት ሥራዎች የሚደገፉ ቢሆኑም የነበረውን የሥርጭት መዛባት የሚያስወግዱ ባለመሆናቸው ችግሩ እንደቀጠለ ነው። አንድም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያልተከፈተባቸው አካባቢዎች እያሉ በነበራቸው ላይ ተጨማሪ ተቋሞችን መክፈት ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም።

የትምህርት አመራር ባጠቃላይ በፖለቲካ ተፅእኖ ሥር መውደቁና የትምህርት ጉዳይ ከባለሙያዎች እጅ እየወጣ በካድሬዎች አመራር ሥር

እንዲወድቅ በመደረጉ የተረጋጋ የመማር ማስተማር ስራ የለም። በዚህም የተነሣ ከብቃት ይልቅ በፖለቲካዊ ታማኝነት የሚመደቡና በአመለካከታቸው የተነሣ ከሥራቸው የሚባረሩ መኖራቸው የታወቀ ነው። በርካታ መምህራን በሚደርስባቸው ፖለቲካዊ ጫና ሣይወዱ በግድ ስራቸውን እየለቀቁ ነው።

የመምህራንና የሠራተኛ ምልመላና ቅጥር፣ ሥልጠና፣ ዕድገትና ዝውውር ወዘተ... የሚመራበት ወጥ ሥርዓት ባለመኖሩ ፖለቲካዊ መመዘኛ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል።

የገዥው ፓርቲ ፖሊሲ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ከላይ እስከ ታች ጥብቅ በሆነ ማዕከላዊነትና የመንግሥት ጣልቃ ገብነት እንዲመራ የሚያደርግ ሲሆን የራሱን የፖለቲካ ካድሬዎችና ደጋፊዎች አመራር ላይ እየሾመ በማስቀመጥ፣ ፖሊሲውን የማይከተሉ ናቸው ብሎ ያሰባቸውን መምህራንና ሠራተኞች በፈለገው ጊዜ ከሥራ በማሰናበት ተፅእኖ ያደርግባቸዋል።

በትምህርቱ ሥራ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት መምህራን በሞያቸው ነፃ ማህበር እንዳያቋቁሙና ለትምህርቱ ጥራት ተገቢ ሚና እንዳይጫወቱ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ጫና ስለሚደርስባቸው ለሀገራችን ማበርከት የሚገባቸውን የሞያና የዜግነት አስተዋፅኦ በሚገባ ሊያበረክቱ አልቻሉም። በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤቶች ነፃ የአካዳሚክ ስፍራዎችና የትውልድ አስተሳሰብ የሚቀረፅባቸው ተቋሞች መሆናቸው ቀርቶ ገዥው ፓርቲ የራሱን ካድሬዎች የሚመለምልባቸውና ዓላማውን የሚያስፈጽምባቸው ቦታዎች ሆነዋል።

የሀገሪቱ የትምህርት ምዘና ፖሊሲ ከክልል ክልል የተለያየ ቢሆንም የተቀራረበ አሠራር እንዲኖር የሚያስችልና በጥናት ላይ የተመሠረተ አነስተኛ መመዘኛ (minimum standard) ባለመኖሩ የተዘበራረቀ ነው። በዚህም ምክንያት ባንድ ክልል ውስጥ የተወሠነ ክፍል ደረጃ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በተለያየ ምክንያት ወደ ሌላ ክልል ተዛውረው ትምህርታቸውን ለመከታተል ይቸገራሉ። ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ዓይነት ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር የሚያደርግ ነው።

የሀገሪቱ የትምህርት ምዘና ፖሊሲ የተዘበራረቀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ደግሞ ከሁሉም የባሰ ነው። ከ8ኛ ክፍል ጀምሮ በሁሉም ደረጃዎች የሚወድቁ ተማሪዎች ደግመው ለመማር ወይም ውጤታቸውን ለማሻሻል እድል የላቸውም። በአሁኑ ጊዜ 8ኛ ክፍል ላይ የወደቁ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚመለሱበት ዕድል ከነአካቴው





ከመዘጋቱም በላይ የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የሚሠጠው 10ኛ ክፍል ላይ በመሆኑ የ15 እና 16 ዓመት ወጣቶች በለጋ ዕድሜያቸው ከትምህርት ተለይተው የቤተሠብና የሀገር ሸክም ለመሆን ተገደዋል። በቀድሞ ሥርዓተ ትምህርት 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁና በአሁኑ ሥርዓተ ትምህርት ከ1996 ዓ.ም. በፊት የ10ኛ ክፍል ፈተና ወስደው ፕሪፓራቶሪ ያልገቡ ተማሪዎች በግላቸው ለመፈተንና ውጤታቸውን አሻሽለው ከፍተኛ ትምህርት እንዳይገቡ ተከልክለዋል። በመካከለኛ ሞያ ማሠልጠኛ ገብተው የሚማሩ ተማሪዎች ከ10+1 ወደ ተከታዩቹ ደረጃዎች ለመሸጋገር 75% አማካይ ውጤት እንደሚጠበቅባቸው መጀመሪያ የወጣ መመሪያ ቢኖርም በኋላ ግን 75% ካገኙት መካከል 10%ቱ ብቻ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ገብተው እንዲማሩ በመደረጉ አብዛኛዎቹ በትምህርት የመግፋት ምኞታቸው ተገድቧል። ከብቃት ምዘናና ደረጃ አወሣሠን፣ ከሥልጠና ዓይነት መረጣና ከሥልጠና ጊዜ ጋር በተያያዘ የሚወጡ መመሪያዎች ተለዋዋጭ መሆናቸው የግል ኮሌጆች ተረጋግተው እንዳይሠሩና ከደንበኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትም ጤናማ እንዳይሆን ችግር ፈጥረውባቸዋል። በመዘጋጃ ትምህርት ከተማሪዎቹ አቅም፣ ፍላጐትና ከሀገሪቱ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ በጥራት የሚሠጥ አለመሆኑ አንዱ ችግር ነው። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ከፕሪፓራቶሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቡ ወጣቶች ለከፍተኛ ትምህርት የሚያበቃ ብቁ ዝግጅት እንደሌላቸው የሚያሳይ ውጤት መታየቱ ነው። የገዥው ፓርቲ ፖሊሲ በየትኛውም ደረጃ ፈተና የወደቁ ተማሪዎች እንደገና ለመማርና ውጤታቸውን ለማሻሻል ያላቸውን ሰብዓዊ መብት የሚገድብ ነው።

በሁሉም ደረጃዎች በተገቢው ሁኔታ የሠለጠኑ በቂ መምህራን አለመኖራቸው፣ የፈረቃ ትምህርት፣ አሃዳዊ የትምህርት አሠጣጥ ዘዴ፣ የትምህርት ግብዓቶች ዕጥረትና የጥራት ችግር፣ የመምህራን የደረጃ ዕድገትና የዕርከን ጭማሪ መከልከል፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ችግር፣ የቋንቋ አጠቃቀምን በሚመለከት የጠራና የተቀናጀ አሠራር መጥፋት፣ የመሣሠሉት የትምህርትን ጥራት ችግር አባብሰውታል።

የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ከጀመሩት መካከል 22% የሚሆኑት 3ኛ ክፍልን ሣያጠናቅቁ ያቋርጣሉ። በከተሞች አካባቢ ባለው የመማሪያ ክፍል ጥበት የሚወድቁ ተማሪዎች ደግመው ለመማር ስለማይችሉ የሚያቋርጡት ተማሪዎች ብዛት ከዚህም በላይ ነው። አሁን ያለው የተማሪዎችና መምህራን ጥምርታ በአማካኝ 1 መምህር ለ60 ተማሪ እንዲሁም የተማሪና የክፍል ጥምርታ በአማካኝ አንድ ለ70 ገደማ መሆኑ ደግሞ ጥራት ያለው ትምህርት

ለመስጠት አላስቻለም፡፡ እንዲያውም 120 ተማሪዎች በ1 ክፍል ውስጥ የሚማሩበት ሁኔታ አለ፡፡

በ2ኛ ደረጃ ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል ለደረጃው የሚመጥን ተገቢ ሥልጠና ያላቸው 36% ብቻ ናቸው፡፡ በተለይም በቴክኒክና ሞያ መስክ መምህራን ቅዳሜና እሁድ እየሠለጠኑ ከሠኞ-አርብ ተማሪዎችን ያስተምራሉ፡፡ በዚሁ ደረጃ የመማሪያ ክፍልና ተማሪ ጥምርታ በአማካይ 1 ክፍል ለ80 ተማሪዎች ገደማ ሲሆን የመምህራን ተማሪ ጥምርታ ደግሞ በአማካይ 1 መምህር ለ70 ተማሪዎች ነው፡፡ የመማሪያ መጻህፍት ጥራት የጐደላቸው ብቻ ሣይሆኑ በይዘታቸው ከተማሪዎቹ ደረጃ ጋር የማይጣጣሙና በመጠናቸውም በመደበኛው የትምህርት ጊዜ ሊሸፈኑ የማይችሉ ናቸው፡፡ አንዳንዴ ድግግሞሽ የሚበዛባቸውና ትክክለኛ ያልሆነ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ ሥርጭቱም 1 መጽሐፍ ለ5 ተማሪ ገደማ ነው፡፡ በዚህ ዓመት የተጀመረው የፕላዝማ ትምህርት በበቂ ጥናትና ዝግጅት ላይ ባለመመስረቱ በተለይም የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በሚወሰዱ ተማሪዎች ላይ አሉታዊ ውጤት እንደሚያስከትል ከፍተኛ ስጋት ተፈጥሯል፡፡ ከቋንቋና ከፍጥነት ጋር የተያያዙት ችግሮች እንዳሉ ሆነው የሥርጭቱ ጊዜም ተማሪዎቹ ለፈተና ከሚቀመጡበት ወቅት ጋር የተጣጣመ አይደለም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚማሩ ተማሪዎች በቂ ዕውቀት የሚጨብጡበት ዕድል ባለ መኖሩ የትምህርቱ ጥራት ከምንጊዜም በበለጠ ወድቋል፡፡

ለትምህርት ጥራት ማጣት አንድ ሌላ ተጨባጭ ማስረጃ የሚሆነው ለ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከሚቀመጡት መካከል የሚወድቁት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡ ለምሣሌ በ1996 በብዙዎቹ ትምህርት ቤቶች ለ10ኛ ክፍል ፈተና ከተቀመጡት መካከል ከግማሽ በላይ የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ወደ ፕሪፓራቶሪ መግባት ያልቻሉትና ወደ ሙያ ትምህርት የተመደቡትም ከፍተኛ ችግር አጋጥሟቸዋል፡፡ መጀመሪያውኑ የሠለጠኑ መምህራን፣ የማስተማሪያ ማኑዋሎች፣ የሞያ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች በሥርዓት ሣይዘጋጁ በዘመቻ መልክ ወደ ተግባር መገባቱ ያስከተለው ጉዳት ቀላል አይደለም፡፡ ተማሪዎቹ ባላቸው ችሎታና ዝንባሌ ካለመመደባቸውም ሌላ ትምህርቱን ለመከታተል በማይችሉበት ቦታ በመደልደላቸው ብዙዎቹ ለማቋረጥ ተገደዋል፡፡ እንደምንም ተቸግረው የተማሩት ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቁ በግላቸው ለመሥራትም ሆነ በሌሎች ተቋሞች ተወዳድሮ ለመቀጠር የሚያስችል ምቹ ፖሊሲና የኤንቬስትሜንት እንቅስቃሴ በሌለበት ሁኔታ ሥራ ፈተው ከመቀመጥ በስተቀር ሌላ ዕድል አላገኙም፡፡ የቴክኒክና ሞያ ሥልጠናን በሚመለከት







ትልቁ ችግር መንግሥት ራሱ ከዚህ በፊት ስለሞያ ትምህርት በሀገራችን ከነበረው የተዛባ ባህላዊ ግንዛቤ አሁንም ያልተላቀቀ መሆኑ ነው፡፡ ወደ ቴክኒክና ሞያ ሥልጠና የሚመደቡት ተማሪዎች የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማለፍ ያልቻሉት ብቻ እንዲሆኑ መደረጉ ለመስኩ የተሠጠውን ዝቅተኛ ግምት የሚያሣይ ነው፡፡

ባለፈው መንግሥት የቴክኒክ ሞያና የቀለም ትምህርት በ2ኛ ደረጃ እየተዳበሉ የሚሠጡበትና እንደሞዴል በሚታዩ ጥቂት ትምህርት ቤቶች ብቻ የተወሠኑበት ሁኔታ ነበር፡፡ በአሁኑ ሥርዓተ ትምህርት ደግሞ የቴክኒክ ሞያና የቀለም ትምህርት ተለያይተው እንዲሠጡ ቢደረግም ወደ ቴክኒክና ሞያ የሚገቡት የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ማለፍ ያልቻሉት በመሆናቸው የትምህርቱ ተገቢነት ጥያቄ ውስጥ የወደቀና ተማሪዎቹ በቴክኒክ ሞያ ሠልጥነው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ያላቸውን ዕድል ዝግ በማድረጉ የራሱ ችግር የአለበት ነው፡፡

ከዚህ የከፋው ችግር ደግሞ በአንድ ክልል ውስጥ ተመሣሣይ ፋሲሊቲና ደረጃ ባላቸው ትምህርት ቤት ውስጥ የመዘጋጃ ትምህርት ከተማሩ በኂላ የሚሠጠውን የመግቢያ ፈተና ወስደው የማለፊያ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች በዘርና በትውልድ እየተመዘኑ ወደ ከፍተኛ ትምህርት እንዳይገቡ የሚከለከሉበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡

አሁን በሀገሪቱ ባሉት ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠው ትምህርት ጥራት ከምንጊዜውም በላይ እየወረደ ነው፡፡ ለዚህ ችግር መነሻ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ተገቢ ያልሆነ የመምህራን አያያዝ፣ ከአቅም በላይ የሆነ የተማሪዎች ቅበላ፣ ቁጥርን ለማሟላት ሲባል ተገቢ ያልሆነ መመዘኛን መጠቀም፣ የትምህርት ተቋሞቹ ፋሲሊቲ አለመሟላትና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚሠጠው ትምህርት ጥራት የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል አለመሆኑ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዩኒቨርስቲዎቻችን ሠፊ የምርምር ስራ የማይካሄድባቸው መሆናቸውና ጥቂት ምርምሮች ካሉም በሕዝቡ መሠረታዊ ችግሮች ላይ አለማተኮራቸው አንዱ ችግር ነው፡፡

በአሁኑ ሥርዓተ ትምህርት ከተከሠቱት ችግሮች መካከል በሙያ ማሠልጠኛ የሚመደቡና የ10ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አልፈው ወደ ፕሪፓራቶሪ የሚገቡ ተማሪዎች በየወሩ ለትምህርት እንዲከፍሉ መገደዳቸው አንደኛው ነው፡፡ ከፍተኛ በሆነ የኑሮ ችግር ውስጥ የሚገኙ ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት ክፍያ በየወሩ መሸፈን እያቃታቸው ተቸግረዋል፡፡

ሌላው ችግር የሴቶችንና የአካል ጉዳተኞችን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሣትፎ ለማሳደግ ድጋፍ የሚሠጥበት ፕሮግራም ጠንካራ ክትትል ስለማይደረግበት ውጤታማ ሊሆን አለመቻሉ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የስኮላርሽፕ እድል ለማግኘት የገዥው ፓርቲ አባል መሆን እንደቅድመ ሁኔታ የሚታይበት አሰራር ሰፍኗል። የአጭርና የረጅም ጊዜ የውጭ ሥልጠና የሚያገኙ ሰዎች መመዘኛ አካዳሚያዊ ብቃት መሆኑ እየቀረ በፖለቲካ ወገንተኝነት እየተተካ ነው። ከአንዳንድ የውጭ ዩኒቨርስቲዎች ጋር መንግሥት በፈጠረው የተልዕኮ ትምህርት ግንኙነት ዋነኞቹ ተጠቃሚዎች የገዥው ፓርቲ ግንባር ቀደም ካድሬዎችና አባላት ናቸው። የ2ኛ ደረጃ ትምህርት እንኳ በወጉ ያላጠናቀቁ ካድሬዎች የማስትሬት ፕሮግራም እየተከታተሉ ማስረጃ እንዲያገኙ በማድረግ ትላልቅ ሹመት እንደሚሰጣቸው የሚታወቅ ነው። በሀገር ስም በሚገኝ የስኮላርሽፕ እርዳታና ብድር የአንድን ፓርቲ ካድሬዎች ብቸኛ ተጠቃሚ ማድረግ ፍትሃዊነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን የለየለት ወንጀል ነው።

ሌላኛው ችግር የትምህርት ፋይናንስ ዝቅተኛ መሆን ነው። ከመንግሥት መደበኛና የልማት (ካፒታል) በጀት ውስጥ ለትምህርት የሚመደበው ድርሻ ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ተከታታይ ዕድገት የማይታይበት ነው። ከሀገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ውስጥ የትምህርት ድርሻ ከ4% ያነሰ ነው። ሀገራችን ለትምህርት ከምታውለው ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ወደ 50% የሚሆነው ከውጭ በሚገኝ ብድርና ዕርዳታ ላይ የተንጠለጠለ መሆኑም ሌላው ችግር ነው።

ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት የትምህርት ፋይናንስን ሁኔታ ለማየት የሚከተሉትን ማነፃጸሪያዎች መመልከት ይበቃል። በ1965/66 ከመንግሥት በጀት ውስጥ የትምህርት ዘርፍ ድርሻ 17% ነበር። በ1979 ደግሞ 10.8% የነበረ ሲሆን ከ1989/90 እስከ 1994/95 ባሉት ዓመታት ከካፒታል በጀት የትምህርት ድርሻ ዝቅተኛው 8.8% ሆኖ ከፍተኛው 13.6% ነው። በተጠቀሱት ዓመታት ከመደበኛ በጀት የነበረው ድርሻ ዝቅተኛው 9.5% ሲሆን ከፍተኛው 18.5% ነው።

በሀገራችን የሚታየው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ወደፊት ለዜጐች ትምህርትን ለማድረስ ፈታኝ መሆኑ የማይቀር ነው። የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ 3% ገደማ በመሆኑ ለ1ኛ ደረጃ ትምህርት የሚደርሱ ሕጻናት ቁጥር በ2008 ዓ.ም. አሁን ባለበት ወደ 50% ይጨምራል። በዚህ ሁኔታ በ2008 ለሁሉም





ዜጐች የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ለማዳረስ የታሠበው የምዕተ ዓመቱ የልማት ዓላማ ይሣካል ብሎ ማሠብ አስቸጋሪ ነው።

## 2.13.2 ጤና

በሀገራችን የጤና ይዞታ እጅግ ደካማ ነው። ኢትዮጵያ በሽታ የተንሰራፋባት አገር ናት። የበርካታ ሕፃናት መሞትና ሰዎች በሕይወት የሚቆዩበት የዕድሜ መጠን ማነስ አገራዊ የጤና ይዞታ ዝቅተኛነትን ያመለክታሉ። የሕክምና መስጫ ተቋማትና የሕክምና አገልግሎት የሚገኙት እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው። ሕዝቡም ስለ ጤና እንክብካቤና ጥንቃቄ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው።

በኢትዮጵያ ካሉት የጤና ችግሮች ከ80% በላይ ለመከላከል የሚቻሉ ተላላፊ በሽታዎችና ከአመጋገብ ጉድለት ጋር የተያያዙ በሽታዎች ናቸው። የሕዝቡ ኢኮኖሚያዊ አቅም ዝቅተኛነት፣ ንጽሕና የሌላቸው አካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ የጤና አገልግሎት ሽፋን ዝቅተኛነት እና የሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች አለመሟላት የአገራችንን የጤና ገጽታ የሞት ጥላ ያንዣበበት አድርጎታል። የኢትዮጵያ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋን በ1994 ዓ.ም. 61% ብቻ ነበር።

በበሽታ ከሚሞቱ ሰዎች መካከል ሦስት አራተኛ የሚሆኑት ከ10 በሽታዎች በአንዱ ወይም በጥምር በመያዝ ነው። እነዚህም፤ 17 በመቶዎቹ በወሊድ ምክኒያት የሚሞቱ እናቶች፣ 14 በመቶዎቹ በሳምባና በመተንፈሻ አካላት መመረዝ፣ 14 በመቶዎቹ በወባ በሽታ፣ 8 በመቶዎቹ በተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚሞቱ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሚሆናቸው ሕፃናት፣ 8 በመቶቹ በተቅማጥ በሽታ፣ 7 በመቶዎቹ በኤድስ፣ እንዲሁም 5 በመቶዎቹ በሳምባ ነቀርሳ እንደሆነ ይገመታል። በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በገዳይነቱ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው ኤች አይ ቪ ኤድስ ነው። ይህ ችግር ከማንኛውም በሽታ የበለጠ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ እንደ አንድ ትልቅ ብሔራዊ አደጋ ተደርጐ የሚታይ ነው። በኤች አይ ቪ ኤድስ የሚደርሠው ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግር ሀገሪቷ ካሉባት ችግሮች ሁሉ የከፋው ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ችግር ከተጠቁት የአፍሪካ ሀገሮች በ3ኛ ደረጃ ላይ ስትሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐች ይሞታሉ። ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ከ10% በላይ ከቫይረሱ ጋር ይኖራል። ከኤች አይቪ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ያለው ትልቅ የጤና ችግር በወባ የሚመጣ ነው። በአሁኑ ጊዜ በየዓመቱ ከ20,000 በላይ ሕዝብ ተጠቂ ነው።

በአገራችን ውስጥ ያለው የጤና ችግር በከፊል ከሥርዓተ ምግብ (ኒውትሪሽን) ይዞታ ዝቅተኝነት ጋር የተያያዘ ነው። ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ በዓለም ካሉ ከፍተኛ የአመጋገብ ጉድለት ከሚታይባቸው አገሮች አንዷ ናት። የንጥረ ምግብ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቷል። ከአምስት ዓመት በታች እድሜ ካላቸው ሕፃናት መካከል ግማሾቹ የተመጣጠነ ምግብ አያገኙም። ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ሕፃናት ደግሞ እድገታቸው ስንኩል ነው። አሥር በመቶ ሚሆኑት ደግሞ የከሱና የቀጨጩ ናቸው። በተመጣጠነ ምግብ እጥረትና በሌሎች የጤና ችግሮች የተጐዱ ሕፃናት በአካል አቅመ ደካማና ምርታማነታቸውም ዝቅተኛ ነው። ይህ ችግር በአእምሮ ፈዛዛና ዝቅተኛ የማሰብ ችሎታ ያለቸው በማድረግ ለእድሜ ልክ ችግርም ይዳርጋቸዋል።

እስከአሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በሀገራችን ውስጥ ዋነኛው የጤና አገልግሎት ሰጪ አካል መንግሥት ነው። ይሁን እንጂ በጤናው ዘርፍ በቂ በጀት ባለመመደቡ የጤና አገልግሎት ተሽመድምዷል። የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ብዛት፣ መልክዓ ምድራዊ ሥርጭትና የሚሰጡት አገልግሎት ስብጥር ብቃት የለውም። በዘርፉ የተሠማሩት ባለሙያዎች ቁጥራቸው ጥቂት ናቸው። በኢትዮጵያ ያለው የጤና አገልግሎት ስብጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ከግማሽ ያነሱትን ብቻ ነው ሊያገለግል የሚችለው። የጤና ማዕከሎችና የጤና ጣቢያዎች ቁጥር አንድ ላይ ሆኖ ከሕዝብ ብዛት ጋር ያለው ጥምረት፣ አንድ የጤና አገልግሎት ድርጅት ለ22 ሺህ ሕዝብ ገደማ ነው።

በሕፃናትና የእናቶች ሞት፣ በተላላፊ በሽታዎችና በምግብ እጥረት አማካይነት በሕይወት የመኖር እድሜና በመሰሰሉት ተቀባይነት ባገኙ የጤና መለኪያዎች መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ከሚገኙት አገሮች መካከል ትመደባለች። በ1992 ዓ.ም. የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካና የእስያ አገሮችን ሁኔታዎች በንጽጽር ማየት በጤናው ዘርፍ በምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል።

በጤና አገልግሎት በኩል ያለውን ሁኔታ ብንመለከት፣ በአገራችን አንድ ሐኪም ለ35 ሺህ ሰዎች እንዲሁም አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ4140 ሰዎች ይደርሳል። የሐኪሞች ስርጭት ሲታይ ከጠቅላላው የሐኪሞች ቁጥር ከ50 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ተመድበው የሚሰሩት በአዲስ አበባ ከተማ ነው። በአንፃሩ ግን በኬኒያ አንድ ሐኪም ለ27 ሺህ ሰዎች እንዲሁም አንድ





የሆስፒታል አልጋ ለ602 ሰዎች ይደርሳል። በሱዳን ደግሞ አንድ ሐኪም ለ9548 ሰዎችና አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ919 ሰዎች ይደርሳል። በግብጽ አንድ ሐኪም ለ1573 ሰዎች አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ476 ሰዎች ይደርሳል።

የንፁሕ ውኃ አቅርቦትን ብንመለከት፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 22 ከመቶው ብቻ ንፁህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 77 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 13 በመቶው ብቻ ነው። በአንፃሩ ደግሞ ከኬንያ ሕዝብ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው ሕዝብ 40 ከመቶው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 89 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 25 በመቶው ነው። በሱዳን ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ 67 ከመቶው ንፁሕ ውሃ ሲያገኝ ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 97 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 91 በመቶው ነው። ከጠቅላላው የአፍሪካ ሕዝብ 56 በመቶው ንፁሕ ውሃ ሲያገኝ ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 86 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 43 በመቶው ነው። በኢትዮጵያ ከጠቅላላው ሕዝብ ከ76% በላይ ለውኃ ወለድ በሽታዎች የተጋለጠ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የመፀዳጃ አገልግሎትን ብንመለከት ከኢትዮጵያ ሕዝብ 15 ከመቶው ብቻ የመፀዳጃ አገልግሎት ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 58 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 6 በመቶው ብቻ ነው። በአንፃሩ ደግሞ ከኬንያ ሕዝብ የመፀዳጃ አገልግሎት ያለው ሕዝብ 86 ከመቶው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማ ሕዝብ 96 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 81 በመቶው ነው። በሱዳን ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ 62 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 87 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 48 በመቶው ነው። እንዲሁም በግብፅ ከጠቅላላው ሕዝብ 94 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 98 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 91 በመቶው ነው። ከጠቅላላው የአፍሪካ ሕዝብ 60 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 85 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 45 በመቶው ነው።

በአሁኑ ጊዜ ከ5 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ሕጻናት ሞት በኢትዮጵያ ከ1000 ሕፃናት መካከል 187 ሲሆን ከሠሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች 114 ነው። በወሊድ ዕድሜ የሚገኙ የእናቶች ሞት በኢትዮጵያ ከ1 መቶ ሺ መካከል 871 ነው። በአገራችን ከሚወለዱት ሕፃናት ውስጥ 11 ከመቶዎቹ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ። በአንፃሩ የሕፃናት ሞት በኬኒያ 7 ከመቶ፣ በሱዳን 7 ከመቶና፣ በግብፅ 5 ከመቶ ነው። ከዛሬ 35

ዓመታት በፊት የሕፃናት ሞት በሲንጋፖር 6 በመቶ፣ በሆንግ ሆንግ 3 በመቶ፣ በኮሪያ 6 በመቶ፣ በፊሊፒንስ 7 በመቶ፣ በማሌዥያ 6 በመቶ፣ በታይላንድ 9 በመቶና በኢንዶኔዢያ 13 በመቶ ነበር።

በኢትዮጵያ የአንድ ሰው አማካይ እድሜም 43 ዓመት ብቻ ሲሆን በኬንያ 51 ዓመት፣ በሱዳን 55 ዓመት፣ በግብፅ 67 ዓመት ሲሆን፣ የአፍሪካ አማካይ ደግሞ 54 ዓመት ነው። በሀገራችን ለጤና የሚመደበው በጀት እጅግ አነስተኛ ሲሆን ከጠቅላላው ብሔራዊ ገቢ የ1.5% ድርሻ ብቻ ነው ያለው።

## 2.13.3 የተዳከመ መሠረተ ልማት

መሠረተ ልማት የመጓጓዥና የምርትን ዋጋ ይወስናል። በአንድ ተቋም ብቃትና ተወዳዳሪነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አለው። በኢትዮጵያ እንደ መንገድ፣ የመብራት ኃይል፣ ውኃና መገናኛ የመሣሰሉት መሠረተ ልማቶች አላደጉም። በክልሎች መካከል ያለው ስርጭትም ፍትሃዊ አይደለም። የአገልግሎት አቅርቦት ዕጥረትና በተከታታይ የመቋረጥ ችግርም አለበት። የመሠረተ ልማት ብቃት ማነስ የማጓጓዥ ዋጋ ከፍ እንዲል ከማድረጉ በተጨማሪ፣ አዳዲስ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡም እንቅፋት ፈጥሯል።

- **ትራንስፖርት**

በኢትዮጵያ የትራንስፖርት አገልግሎት ሁኔታ ደካማ ነው። የባቡር ትራንስፖርት በተለይ እጅግ ኋላቀር ነው። ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲወዳደር የኢትዮጵያ የመንገድ ዝርጋታ ዝቅተኛ ነው። በ1992 የወጣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ እንደሚያሣየው በሀገር ደረጃ የኢትዮጵያ መንገዶች መረብ ትስስር ከ15% አይበልጥም። አብዛኛው የሀገሪቱ ገጠር መንገድ አልተዘረጋለትም። ያሉትም መንገዶች የጥገና አገልግሎቱ በኋላቀር ቴክኒዎሎጂ ላይ በመመስረቱና የፋይናንስ አቅም ችግር በመኖሩ በጥሩ ሁኔታ ላይ አይደሉም። ይኸ ችግር በወደብ የተከማቸም ይሁን በሀገር ውስጥ ከቦታ ቦታ የሚንቀሣቀስ ዕቃ በፍጥነት እንዳይጓጓዝ ተፅእኖ አሣድሯል። የዕቃ ዝውውር መዘግየት ደግሞ የመጓጓዣ ዋጋን አንሮታል። ርካሽ ጥሬ ዕቃዎች ወደ ሚገኙበት ቦታ ለመድረስና ምርትን ወደ ገበያ ለማቅረብ እንዳይቻል እንቅፋት ሆኗል።

ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ጋር ብቁ የአየር ግንኙነት በመፍጠር ዝና ያተረፈ የአየር መስመር ቢኖራትም በሀገር ውስጥ የሚሠጠው አገልግሎት ውስን ነው። ከየብስ ትራንስፖርት ጋር ሲነጻጸር ዘርፉ የሚሠጠው






አገልግሎት ውስን ነው።

የመኪና ኪራይ አገልግሎት በሚገባ ካለመስፋፋቱም በላይ ከዋና ዋና ከተሞች ርቀው የሚገኙ ተቋሞች ተጨማሪ ዋጋ እንዲያወጡ ተገደዋል። የጋራጆችና የተሽከርካሪ ቴክኒሽያኖች ብዛትና ጥራት ዝቅተኛ መሆን የትራንስፖርት ዘርፉ ሌላው ችግር ነው።

- **ኢነርጂ**

ኢነርጂ ለኅብረተሰቡ ሕልውናና ለኢኮኖሚ ልማት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ በጥቅም ላይ የዋሉና ያልዋሉ፣ መኖራቸው የተረጋገጠላቸውና ፍንጭ የታየባቸው ታዳሽና አላቂ የኢነርጂ ሃብት አለኝታዎች አሏት። የሰውና የእንስሳት ጉልበት ሳይታከል 94 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ የኢነርጂ ፍላጎት የሚሟላው ከባህላዊ የኢነርጂ ምንጮች ማለትም ከእንጨት፣ ከእንስሳት ፍግና ኩበት፣ ከእርሻ ቃርሚያና ከመሳሰሉት ሲሆን ቀሪው 6 በመቶ ደግሞ ከዘመናዊ የኢነርጂ ምንጮች ማለትም ከነዳጅ ዘይት፣ ጋዝና ኤሌክትሪክ ኃይል የሚሟላ ነው። በአገሪቱ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ የቤተሰብ አገልግሎት ዘርፍ ነው። ዘርፉ ከአጠቃላይ የኢነርጂ አቅርቦት ውስጥ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሚጠቀም ሲሆን ይህም አብዛኛው የአገሪቱ የኢነርጂ አቅርቦት ምንጮች ላይ ያለው ጥገኝነት ለደን መራቆት፣ ለአፈር ልምላሜ መቀነስ፣ ለማገዶ እንጨት እጥረትና ዋጋ መናር የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ዘመናዊ የኢነርጂ ምንጮች ለአጠቃላይ የኢንርጂ አቅርቦት ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ ይሁን እንጂ አቅርቦታቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቅ ነው። የአገሪቱ የኢነርጂ ችግር የተወሳሰበ፣ በሌሎች ክፍለ-ኢኮኖሚዎች እንቅስቃሴና በኅብረተሰቡ አኗኗር ወሳኝ ተፅእኖ የሚያሳድርና አፋጣኝ እስትራክቸራል ለውጥ ካልታየበት እየተባባሰ ወደሚሄድ ቀውስ የሚያመራ እንደመሆኑ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ አግባብነት ያለው ፖሊሲ ያስፈልገዋል።

በ1992 ዓ.ም. የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካ አገሮችን በነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታን (በሚሊዮን ኪሎ ዋት/በሰዓት) በንጽጽር ማየት በኢነርጂው መስክ ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል። በኢትዮጵያ 22.2 ብቻ ሲሆን በኬንያ 129.5፣ በግብፅ 861.1 ማለትም የግብጽ ምርት የኢትዮጵያን 24 ጊዜ ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በመሬት አቀማመጧና ባላት የውሃ ሃብት ምክኒያት እጅግ በጣም በርካታ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችም

በቅርብ ጊዜ ተገንብተው አገልግሎት እንደሚሰጡ የሚጠበቅ ቢሆንም እነዚህ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች የሚሰጡት የኢነርጂ መጠን በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ሊገኝ ከሚችለው ኢነርጂ ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እስካሁን ድረስ በተደረጉ ግርድፍ ጥናቶች በተለያዩ ተፋሰሶች በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ የውሃ ኢነርጂ ማመንጨት እንደሚቻል ተጠቁሟል። የውሃ ሀብታችንን ተጠቅመን የኤሌክትሪክ ኃይል በብቃት ልናመነጭ ባለመቻላችን እየተጐዳን ነው። አማራጭ ኢነርጂ በማቅረብ የደኖቻችንን መጨፍጨፍ መግታት አልቻልንም።

የተለያዩ የኃይል ማመንጫ አማራጮች ቢኖሩም የኢትዮጵያ የቴክኒዎሎጂ አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ በውኃ ኃይል በሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኢነርጅ ላይ ተወስናለች። በዚህ የኃይል ምንጭም ቢሆን ከሌሎች አፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ እጅግ አነስተኛ ነው። በዓለም ባንክ መረጃ መሠረት ከሠሀራ በታች ያሉ ሀገሮች አማካይ የኤነርጅ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ወደ 454Kwh ብቻ ነው። ሲሆን (በዓለም ደረጃ ካለው አማካይ ፍጆታ ወደ 1/5ኛ የሚጠጋ) የኢትዮጵያ ግን 22Kwh ነው። ብቻ ነው። በቂና አስተማማኝ የኢነርጅ አቅርቦት ለኢንዱስትሪላይዜሽን አንዱ ቅድመ ሁኔታ ቢሆንም በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው። ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ መሆን የቻለው 5% ብቻ ነው። ሀገሪቱ ከ15-30 ሺ ህ ሜጋዋት የሚሆን ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጨት የሚችሉ ትላልቅ ወንዞች ቢኖሯትም ከዚህ አቅም ውስጥ መጠቀም የቻለችው ከ1% ያነሠ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው ችግር የአቅርቦቱ ማነስ ብቻ ሣይሆን አስተማማኝ አለመሆኑም ጭምር ነው። ባልተጠበቀ ሁኔታ የኤሌክትሪክ መቋረጥ ወይም ጉልበት መቀነስ ስለሚያጋጥም የምርትና አገልግሎት ስራዎች ይቋረጣሉ አንዳንዴ የአቅርቦቱን ችግር በመቀነስ የኤሌክትሪክ ስርጭት በራሽን መልክ የሚዳረስበት አሠራር ቢኖርም የራሱ ብዙ ጉድለቶች አሉበት። የኤሌክትሪክ መቋረጥ የግልና የመንግሥት አገልግሎት መስጫና ማምረቻ ተቋሞችን ገቢ ከመቀነስ አልፎ ለተጨማሪ ወጪ ያጋልጣቸዋል። በተለይ የራሣቸው ጀነሬተር የሌላቸው ኪሣራ ያጋጥማቸዋል። ሥራ ተሠራም አልተሠራም ለሠራተኞቻቸው ደሞዝና አበል ስለሚከፍሉና ሌሎችንም ተጨማሪ ወጪዎች ስለሚያወጡ የሚያጋጥማቸው ኪሣራ ከፍተኛ ነው። በተቋሞቹ ብቃትና ትርፋማነት ላይ ከሚፈጠረው ችግር ባሻገር አዳዲስ ኢንቨስትሜንት በተለይም የውጭ ኢንቨስትሜንት እንዳይስፋፋ እንቅፋት ይፈጥራል። ምክንያቱም መሠረታዊ የመሠረተ ልማት አገልግሎት በሌለበት ሀገር ውስጥ ሃብቱን፣





ዕውቀቱንና ጊዜውን ለማጥፋት የሚፈልግ የውጭ ባለሃብት ማግኘት ስለሚከብድ ነው።

- **የውኃ አቅርቦት**

በኢትዮጵያ የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ኋላቀርና ብቃት የጐደለው ነው። በመላ ሀገሪቱ የተዘረጋው የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ከ20% ብዙም አይበልጥም። ይህ መጠን ከውኃው አቅርቦት አስተማማኝነትና ዘላቂነት አኳያ ሲታይ ደግሞ ሽፋኑን ከዚህም ያነሠ እንደሚሆን የታወቀ ነው። በተደጋጋሚ ጊዜ የአገልግሎት መቋረጥና የአቅርቦት መጠን መቀነስ ይታያል። የንጽህና ደረጃው ዝቅተኛ መሆንም ሌላው ችግር ነው። ለምሣሌ በአዲስ አበባ ከተማ ካለው የውኃ አቅርቦት መጠን 1/3ኛው በውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ዝገትና መቀደድ የተነሣ የተበከለ ነው።

- **መገናኛ**

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝበት ዋነኛ መስክ ቢኖር የመረጃ ቴክኒዎሎጅ ነው። የኢንፎርሜሽን ቴክኒዎሎጅ ሲባል ኮምፒዩተርን፣ የኮምፒዩተር መረብን፣ ሬዲዮን፣ ቴሌቭዥንን ስልክን፣ ፋክስን፣ የኢሌክትሮኒክስ ኢሜይልን፣ ኢንተርኔትን፣ ቴሌ ኮንፈረንስን፣ ቪዲዮ ኮንፈረንስን፣ ወዘተ... ያጠቃልላል። የኮምፒዮተር አገልግሎት የሚታወቀው በጥቂት ዋና ዋና ከተሞችና በተመረጡ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ውስጥ ብቻ ነው። የኢንተርኔት ግንኙነት አገልግሎት በሚገባ ጥቅም ላይ የዋለ አይደለም። በሀገር ደረጃ የኢንተርኔት ግንኙነት አገልግሎት ዝቅተኛ ሲሆን እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ከእያንዳንዱ 10000 ሰው መካከል አንድ እንኳ አይደርሰውም።

- **የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) አንፃራዊ ሁኔታ**

በ1992 ዓ.ም. የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካ አገሮችን በየአንድ ሺ ህ ሰው የነበረውን ስልክ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርሻ በንጽጽር ማየት በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም በኩል ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል። ቴሌፎን መስመርን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ 3 ብቻ ሲሆን በኬንያ 9፣ በሱዳን 3፣ በግብፅ 9 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 18 ነው። ሞባይልን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያና ሱዳን ወደ ዜሮ የተጠጋ ሲሆን በኬንያ 1፣ በግብፅ እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 14 ነው። እንደዚሁም ቴሌቪዥንን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ 6 ብቻ ሲሆን

በኬንያ 22፣ ሱዳን 173፣ በግብፅ 183 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 59 ነው። ሬዲዮን በተመለከተ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ 196 ሲሆን በኬንያ **104**፣ ሱዳን 271፣ **በግብፅ 160** እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 214 ነው።

የኮምፒዩተርና ኢንተርኔት አገልግሎት ድርሻን በተመለከተም ኢትዮጵያ የምትገኝበት ደረጃ ዝቅተኛ ነው። ፐርሰናል ኮምፑዩተር (የአንድ ሚሊዮን ሰዎች ድርሻ)፤ በኢትዮጵያ 740 ብቻ ሲሆን በኬንያ 4240፣ በሱዳን 2940፣ በግብፅ 1200 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 8770 ነው። የኢንተርኔት አገልግሎት በተመለከተ ደግሞ (የአንድ ሚሊዮን ሰዎች ድርሻ)፣ በኢትዮጵያ 10 ብቻ ሲሆን በኬንያ 250፣ በግብፅ 550 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 2300 ነው።

## *2.14 የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር እጦት*

ኢትዮጵያ አሁን የምትገኝበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ በታወቁት ዓለም አቀፍ የልማትና የዕድገት መመዘኛዎች ሲታይ እጅግ አሣፋሪ ነው። ለምሣሌ ስለአፍሪካ መልካም አስተዳደር ሁኔታ ለመለካትና ለመገምገም በ1996 ዓ.ም. የአፍሪካ ኤኮኖሚ ኮሚሽን በ28 አፍሪካ አገሮች ላይ ባደረገው ጥናት በፖለቲካዊ ውክልና፣ ሙስናን በመቆጣጠር፣ በኢኮኖሚ አመራር፣ በሚዲያና በሲቪል ማህበረሠብ ድርጅቶች ነጻነት፣ በዴሞክራሲ ተቋሞች ምሥረታና ብቃት፣ በአፈጻጸም ውጤታማነት ወዘተ... ኢትዮጵያ የምትገኝበት ደረጃ ከመጨረሻዎቹ 2ኛና 3ኛ መሆኑን አረጋግጧል። ሀገሪቱ በዚህ በ21ኛ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ እንኳ ከጭቆና አገዛዝ ለመገላገል አልቻለችም። በሀገሪቱ የረጅም ዘመን የመንግሥት ታሪክ ውስጥ አንደኛው የጭቆና አገዛዝ በሌላኛው እየተተካ ከመኖሩ በስተቀር የዴሞክራሲ ሥርዓት አልተፈጠረም። ሕዝቡም ከድህነት ወደ ድህነት ከመሸጋገር የተለየ ዕድል አላገኘም። ለዕድገትና ለልማት የተመቸ የተፈጥሮ ፀጋ ቢኖርም ይኸንን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚረዳ መልካም አስተዳደር ባለመመስረቱ ኢትዮጵያ ሣታጣ ያጣች ለመሆን ተገዳለች።

ጥሩ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖር ብቻውን የረባ ውጤት ሊያስገኝ እንደማይችል ከኢትዮጵያ የተሻለ ምሳሌ የለም። ይኸ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሃብት የሌላቸው ነገር ግን ለእድገትና ለልማት መልካም ራዕይና ቁርጠኝነት ያለው መልካም አስተዳደር መፍጠር የቻሉ ሌሎች ሀገሮች ከኢትዮጵያ ኋላ እየተነሱ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየቀደሟት ሄደዋል። የኢትዮጵያን ችግር አስከፊ የሚያደርገው ከችግሯ መንጥቆ ሊያወጣ የሚችል የዴሞክራሲ





ሥርዓት ገና ያልፈጠረች መሆኗ ብቻ ሳይሆን አሁን በሀገሪቱ የነገሠው አገዛዝ ከበፊቶቹ ሁሉ የባሰ አፋኝና ከፋፋይ መሆኑ ነው።

የአሁኑን አገዛዝ ከበፊቶቹ የከፋ ያደረገው የመንግሥት ሥልጣን በጠመንጃ ኃይል መያዙ ብቻ አይደለም። ይህ ለአሁኑ አገዛዝ ብቻ የተለየ መገለጫ ባህርይ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በፊት የነበሩትም አገዛዞች የመጡበትና የሄዱበት መንገድ ነው። የኋላ ታሪኩ ከኮምኒዝም አመለካከት ጋር የተቆራኘ መሆኑ ብቻም አይደለም። በመላው አለም የኮሙኒዝምን ባንዲራ ሲያውለበልቡ የከረሙ በርካታ ቡድኖችና ተቋሞች ዛሬ አስላለፋቸውን ቀይረው ቆመዋል። የዚህ አገዛዝ ችግር ከዚህ ለየት ያለ ነው። አንደኛው የችግሩ ገጽታ ካለፈው አቋሙና ባህርይው ጨርሶ ለመላቀቅ በማያስችል የዞረ ድምር (hangover) የታሰረ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛውና ነገር ግን እጅግ አደገኛው ችግር ጫካ ውስጥ ተኮትኩቶ ባደገው አምባገነንነት ላይ መንግሥታዊ ሙሰኝነትን ሊደርብ መቻሉ ነው። የአሁኑ አገዛዝ የነፃ ገበያ ሥርዓት ደጋፊና አፍቃሪ ካፒታሊዝም ለመምሰል ቶሎ ብሎ ጭንብል ቢያጠልቅም ለዚህ ሥርዓት የሚገዛ ግልጽነትና የአሰራር ዲስፕሊን በተግባር ማሳየት አልቻለም።

በድርጅት ፕሮግራሞቹና በመንግሥት የፖሊሲ ሠነዶች ውስጥ ያሰፈራቸው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አቋሞቹ ለነፃ ገበያና ለካፒታሊዝም ሥርዓት ግንባታ ባዕድ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተፃራሪ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት መገመት የሚቻለው አገዛዙ ነፃ ገበያና የካፒታሊዝም ሥርዓት ተቀብያለሁ የሚለው ምርጫ በማጣት እንጂ ለሀገር እድገትና ልማት ይጠቅማል ከሚል እምነት አለመሆኑን ነው። በአሁኑ ጊዜ ነጻ ገበያንና ካፒታሊዝምን ከፊት ለፊት እየተጋፈጡ የመንግሥት ሥልጣን ይዞ መቆየት እንደማይቻል በመገመትና ከምዕራቡ ዓለም ብድርና እርዳታ ለመለመን ሳይወድ በግድ ያንጠለጠለው መፈክር እንጂ ለልማት የሚያዋጣ መንገድ ነው ከሚል እምነት ተነስቶ በቁርጠኝነት የያዘው አቋም አይደለም። በመሆኑም ካለፈው ኮሚኒስታዊ አመለካከት ጨርሶ የተቆራረጠና ለሌላ አዲስ ራዕይ በሙሉ ልብ የተሰለፈ መሆኑን በእርግጠኝነት ለመረዳት በሚያስቸግር ሁኔታ ራሱን ደብቆ የተቀመጠ አገዛዝ ነው። እንዲህ ዓይነት መንታ አቋም የያዘ አመራር የኢትዮጵያን ችግር ሊፈታ ቀርቶ ራሱንም ከችግር ማውጣቱ አጠራጣሪ ነው።

የአሁኑ አገዛዝ ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ መፈክሮችን ሲያነሳና ሲጥል ቢከርምም የሀገሪቱን ችግር ከማባባስ በስተቀር

ያስገኘው መሻሻል የለም። በተለያዩ ጊዚያት የመዋቅር ማሻሻያ፣ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም፣ የተሃድሶ እርምጃ፣ የድህነት ቅነሳ ወዘተ... የሚሉትን አጀንዳዎች ይዞ ላይ ታች ሲል የከረመውም በውጭ መንግሥታትና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ግፊት እንጂ ልማት ለማምጣት ካለው ፍላጎትና ዝግጁነት በመነሳት አልነበረም። እነዚህን አጀንዳዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሙሉ እምነት፣ አደረጃጀትና አሰራር በሌለበት ሁኔታ "ይህንን አድርግ" የሚል ውጫዊ ጫና በተፈጠረ ቁጥር የራሱ ያልሆነ አጀንዳ አንጠልጥሎ በመሮጥ የሚሻሻል መዋቅር፣ የሚታደስ አመራርና የሚቀነስ ድህነት ሊኖር አይችልም። የመዋቅር ማሻሻያም ይሁን የአመራር ተሃድሶ ወይንም የድህነት ቅነሳ እንዲኖር በቅድሚያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር በቦታው ላይ መገኘት አለባቸው። የአሁኑ አገዛዝ ደግሞ ከዴሞክራሲና ከመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መርሆዎች የተነጠለ አገዛዝ ነው። የዚህ አገዛዝ እውነተኛ መገለጫዎች በጠመንጃ ኃይል የተመሠረተ የፖለቲካ ሥልጣንና በዚህ ሕገወጥ ሥልጣን ላይ የተገነባ ተቋማዊ ሙስና ናቸው።

የክልሎችን ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን በሚጋፋ መንገድ የወጣው ጣልቃ የመግባት አዋጅና የዋስትና መብትን የሚከለክለው የፀረ-ሙስና አዋጅ፣ ሃሣብን የመግለጽና መረጃ የማግኘት ነጻነትን የሚገድበው አዋጅ፤ ወዘተ. የዜጎችን ሠርቶ የመኖር፣ ሃብት የማፍራት መብት የሚጻረሩና የአስፈጻሚውን አካል ሥልጣን ገደብ የለሽነት የሚያረጋግጡ ናቸው። ሕግ የማውጣት ሥልጣን አለው የሚባለለት ፓርላማ የሕዝቡን ልዩ ልዩ አመለካከቶች፣ ጥቅሞችና ፍላጎቶች የሚወክሉ የሕዝብ ተወካዮች ሣይሆኑ በአብዛኛው ለገዥው ፓርቲ ባላቸው ታማኝነት በድርጅታዊ ስራ የተመለመሉ ሰዎች የተሰባሰቡበት በመሆኑ ሥራ አስፈጻሚው የሚያቀርቡለትን አዋጅ ከማጽደቅ የዘለለ ሚና ሊጫወት አልቻለም። የሀገሪቱ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ሲደፈር፣ በሕዝብ ላይ የሠብዓዊ መብት ረገጣና ጭፍጨፋ ሲፈፀም እንኳ መጠየቅ አልቻለም። ፓርላማው ያፀደቀው ሕግ ተዛብቶ በነጋሪት ጋዜጣ ሲወጣ፣ ሥራ ላይ እንዳይውል ልዩ ልዩ መሠናክሎች ሲፈጠሩ ለምን ብሎ የመጠየቅ፣ ነጻና ዴሞክራዊ ተቋሚችን የመመስረት አቅም የሌለው ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሕዝቡ ልዩ ልዩ ጥቅሞቹንና መብቶቹን አቻችሎ ለመኖር የሚያግዘውን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በነጻነት እንዲመሠርት እስካሁን ዕድል አልተሠጠውም። አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት አንድ የፖለቲካ ቡድን እንደመሠለው አዘጋጅቶ በሕዝብ ላይ የጫነው እንጅ






ሕዝብ በነጻነት መክሮና ፈቅዶ ያዘጋጀው አይደለም። ሕገ መንግሥቱ ለይስሙላ በሠፈሩ የሠብዓዊ መብት አንቀጾች ከመሸፋፈኑ በስተቀር የገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ቅጅ ነው። በመሆኑም እስካሁን ድረስ በሕዝብ ፍላጐትና ነጻ ውሣኔ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ባለመኖሩ ሀገሪቱ በጠመንጃ ኃይል በሚተማመን አገዛዝ ስር እንደወደቀች ነው። አገዛዙ ሁሉን ነገር በጫካ ሕግ ለመምራት ስለወሠነ የሕዝቡን መብትና ጥቅም የሚያስከብር የሕግና የሞራል ሥርዓት አለ ለማለት አይቻልም።

## 2.14.1 ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም አለመኖር

የፍትህና የዳኝነት ተቋማት በጠመንጃ ኃይል ለተገነባ ሥልጣን መሣሪያ እንዲሆኑ ስለተፈለገ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መርህ ተዋቅረው እየሠሩ ነው። በዚህም የተነሣ ሕግና ፍትህ ተረግጠው በአገዛዝ ኃይልና ሥልጣን ተተክተዋል። የሕግ ሞያ፣ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው በወረንጦ እየተለቀሙ ተባረው በፍትህና ዳኝነት መዋቅሩ ውስጥ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ካድሬዎች ተሠግስገዋል። በዚህ መንገድ ነጻ ዳኝነትና የሕግ የበላይነት በመጥፋቱ ማንም ዜጋ መብቱ ሲደፈር አቤቱታ አቅርቦ ፍትህ የሚያገኝበት ዕድል ተዘግቷል። የፍትህና የዳኝነት መዋቅሩ ነጻ ሆኖ እንዳይንቀሣቀስ በመንግሥት አስፈጻሚው አካል ቀጥተኛ ተፅእኖ ስር ስለወደቀ የዜጎችን ነጻነት ማስከበር የሚያስችል ምንም ዓይነት ሕጋዊ መተማመኛ የለም። ዳኞች የሚመለመሉበት መስፈርት በሞያ ብቃት፣ በመልካም ሥነ ምግባርና በነፃ አመለካከት ሣይሆን በፖለቲካዊ ታማኝነት ነው። ለዚህ ሲባል ፖለቲካዊ ታማኝነት ያላቸው ዳኞች ከሲቪል ሠርቪስ የለብ ለብ ሥልጠና እየወሰዱ በፍትህ ተቋሙ ውስጥ ይመደባሉ። በአሁኑ ሕገ መንግሥት በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ግልጽ የሥልጣን ክፍፍል ባለመኖሩ ተጠሪነታቸው ለፓርላማ ነው የተባሉትን የመገናኛ ብዙሃን፣ የምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ አካላትና የመሣሰሉትን ተቋሞች ስልጣን ነጥቀው ሕግ አስፈፃሚው አካል በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደፈለጉ ይወስኑበታል። ሕግ አስፈጻሚው የሕግ አውጭውንና የፍትህ አካሉን ሥልጣን የሚሸረሽሩ አዋጆችን እያወጣ ራሱን ከሕግ በላይ አድርጐ ቁጭ ብሏል። ዜጐች የዋስትና መብት፣ ሃብትና ንብረታቸውን ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያለመነጠቅ፣ ሃሣባቸውን የመግለጽና መረጃ የማግኘት፣ ነጻ ማህበር የመመሥረት፣ ሠላማዊ ተቃውሞ የማድረግ መብት ወዘተ... በተግባር የላቸውም።

አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሕዝብ ፈቃድና ነጻ ውሣኔ

የተመሠረተ ባለመሆኑ የአሠራር ግልጽነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሚባሉት የመልካም አስተዳደር ዋነኛ ባህርያት ዋጋ የላቸውም። በማንኛውም የሕዝቡን ጥቅም በሚመለከት የፖሊሲ ቀረጻ ላይ ሕዝቡ አስተያየት የሚሠጥበት፣ ሃሣብ የሚያፈልቅበትና ንቁ ተሣትፎ የሚያደርግበት አሠራር የለም። የሕዝቡ መብት ገዥው ፓርቲ በራሱ መንገድ ፖለሲ አውጥቶና መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ከጨረሠ በኋላ ለይስሙላ በሚያዘጋጃቸው መድረኮች እየተገኘ ባለቀ ጉዳይ ላይ መነታረክ ብቻ ነው። ስለዚህ በሕዝብ ፍላጐትና ነጻ ውሣኔ ላይ የተመሠረተ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በሌለበት አገዛዝ ስር ዜጐች ለልማት የሚሠለፉበት ሁኔታ ቀርቶ በሕይወት ለመኖር እንኳ ምንም ዓይነት መተማመኛና ዋስትና የላቸውም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ዕውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ሃብታቸውን ለልማት እንዲያውሉ የሚደፋፈሩበት መንገድ የለም። በሕይወት ለመኖር እንኳ ነጻነት የሚሠጥ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ ዜጐች የልማት ተነሣሽነት ሊኖራቸው አይችልም። የሕግ የበላይነት በጠፋበትና የጠመንጃ ኃይል ራሱ ሕግ በሆነበት አገዛዝ ስር ሆኖ ልማት ማምጣት ይቅርና ስለልማት ማሰብም አይቻልም።

## 2.14.2 ተቋማዊ ሙስና

የአሁኑ አገዛዝ ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የተነጠለ መሆኑ የሚረጋገጥበት ሁኔታ በሀገሪቱ ውስጥ የነገሠው ሙስና ነው። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሙስና በድብቅ የሚካሄድና በግለሠቦች የሚፈፀም ተራ ሌብነት ተደርጐ የሚታይ ቀላል ነገር አይደለም። አሁን ያለው ሙስና የፖለቲካ ድጋፍ ያለውና በይፋ የሚካሄድ የተደራጀ ዘረፋ ነው። ሀገሪቱ ውስጥ የነገሠው የፖለቲካ ሥልጣን አወቃቀርና አሠራር ይኸንን በይፋ የሚያደፋፍር ነው። በመሣሪያ ኃይል የተገኘን የፖለቲካ ሥልጣን የበላይነት በኢኮኖሚ መስክ በሚገኝ የበላይነት መደገፍ ይገባል በሚል ፍልስፍና የተቃኘ ነው። በሁሉም ዘርፍ የገዥውን ፓርቲ ጥቅም በማስቀደም ሥልጣንን ጠብቆ ማቆየት ይገባል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

የአሁኑ አገዛዝ ሀገርን የማልማት ሃሣብ ያለው ሣይሆን ሕገወጥ ዘረፋ እያካሄደ በሀገርና በሕዝብ ኪሣራ ራሱን ለማልማት የቆመ ነው። ለዚህ ዓላማው መሣካት ሁሉም የልማት ኃይል በሚችለው መስክ ተሠማርቶ የሚሠራበት ዕድል እንዳይኖር የተለያዩ ወጥመዶችን በማዘጋጀትና በመጥለፍ ካለተቀናቃኝ ብቻውን መጋለብ ይፈልጋል። በልማት ተሣትፎ ማድረግ የሚፈልጉትን እንደጠላት የሚመለከታቸው፣ ጥገኛ የሚል ተቀጽላ ስም የሚያወጣላቸውና ሰበብ እየፈጠረ የሚጠልፋቸው በዚህ የተነሣ ነው።



የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ(ቅንጅት) አባል ድርጅቶች
መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድኅን፣ ኢዴሊ እና ቀስተ ደመና ናቸው።



በየትኛውም የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ካለጉቦ ጉዳይ ማስፈፀም የማይሞከር ብቻ ሣይሆን የሚጠየቀው የጉቦ መጠንም በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ ላይ መድረሱ ዝም ብሎ በድንገት የተፈጠረ ክስተት አይደለም። ይህ ሁኔታ የተከሠተው በሲቪል ሠርቪሱና በሌሎችም የመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ የተሠገሠገው የገዥው ፓርቲ ሠራዊት ይኸንን እንዲፈጽም የሚያበረታታ ድጋፍና ይሁንታ ስለሚያገኝ ነው። የዚህን አገዛዝ ፖለቲካዊ ልዕልና እስከተቀበለና በሥርዓቱ መሪዎች ግምገማ አደጋ ሊያመጣ ይችላል ተብሎ እስካልተጠረጠረ ድረስ በየትኛውም ሁኔታ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ የተመደበ የገዥው ፓርቲ አባል ጉቦ በላህ ተብሎ አይጠየቅም። እያንዳንዱ ባለሥልጣን ለሾመው ሌላ ባለሥልጣን ታማኝ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ በሕግ እጠየቃለሁ፣ በሕዝብ እወቀሣለሁ ብሎ የሚሠጋበት ሁኔታ የለም። በፖለቲካ አመራሩ ቁልፍ ሥልጣን ላይ የተቀመጡት ትላልቅ ሹሞች እስከወደዱት ድረስ ሕግ ጥሰሃል፣ የሠው መብት ደፍረሃል ተብሎ አይከሠስም። ግፋ ቢል ድርጅታዊ ስብሠባ በሚባለው ዝግ ችሎትና ግምገማ ሂሱን ተቀብሎ ተሃድሶ አድርጓል ይባልለታል። የወያኔ/ኢህአዴግ ባለሥልጣናትና አባላት ከደሞዛቸው ጋራ የማይመጣጠን የመኖሪያና የንግድ ቤት፣ ውድ መኪና፣ የቅንጦት ዕቃ፣ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆነዋል። ከ14 ዓመታት በፊት የእግራቸው መጫሚያና የረባ ልብስ ያልነበራቸው ሽምቅ ተዋጊዎች ከባዶ መሬት ተነስተው በሚሊዮን የሚገመት ንብረት ባለቤትና የናጠጡ ከበርቴዎች የሆኑበት ሙስና በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ነው።

ስለዚህ እየዘረፉ ግለሂስና ተሃድሶ በማድረግ ከተጠያቂነት ነጻ መሆን ስለሚቻል በየትኛውም የመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገኝ የገዥው ፓርቲ ባለሥልጣንና ተራ አባል ከተገልጋዩ ሕዝብ በሚቀበለው ጉቦ ብቻ አልጠግብ ብሎ የመንግሥትን ንብረትና ገንዘብ እየዘረፈ መክበሩን ተያይዞታል። የሀገር ሃብትና ንብረት መዝረፍ፣ ጉቦ መቀበልና የዜጐችን መብት መጣስ በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆን ኖሮ በአሁኑ አገዛዝ ውስጥ ከላይ እስከታች ከተሠማራው የፓርቲ አባል መካከል ነጻ የሚሆን ስለማይገኝ ከሣሽና ተከሣሽን መለየትም ባልተቻለ ነበር።

የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ተቋማዊ ሙስና ከሚገለጽባቸው መስኮች አንደኛው ፕራይቬታይዜሽን የሚባለው ፕሮግራም ነው። በመንግሥት ይዞታ ስር የነበሩትን የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር በአዋጅ ሥልጣን የተሠጠው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተቋቋመ ከተባለ በኋላ ከገዥው ፓርቲ



የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ(ቅንጅት) አባል ድርጅቶች
መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድኅን፣ ኢዴሊ እና ቀስተ ደመና ናቸው።

ጋር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ትስስር ያላቸው ሰዎች የተጠና የሥራ ክፍፍል አድርገው ከፊሉ የጨረታ ኮሚቴ አባል ከፊሉ ደግሞ ተጫራች እየሆኑ ንብረቱን ተከፋፈሉት፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወደ ግል ንብረትነት ተዛወሩ ከተባሉት የመንግሥት ንብረቶች ውስጥ ከጥቂቶቹ በስተቀር ሌሎቹ ለገዥው ፓርቲ አባላት፣ የትግል አጋሮችና ዘመድ አዝማዶች በአነስተኛ ዋጋ እንዲከፋፈሉ በመደረጋቸው በስጦታ እንደተሠጡ የሚቆጠሩ እንጅ እንደተሸጡ የሚታዩ አይደሉም፡፡

በዚህ አገዛዝ የተመሠረተውን ተቋማዊ ሙስና ለማየት የሚያስችለው ሌላ ነጥብ ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የራሱን የንግድ ኩባንያዎች የከፈተበት ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህን ኩባንያዎች በሚመለከት በቅድሚያ የሚነሣው ነጥብ የኩባንያዎቹ መነሻ ካፒታል የተገኘበት ምንጭ ነው፡፡ ለኩባንያዎቹ ማቋቋሚያ የሆነው ካፒታል በዋናነት የተገኘው አሁን የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው አገዛዝ አማጺ ቡድን በነበረበት ጊዜ ከመንግሥት፣ ከሕዝባዊ ማህበራት፣ ከአገልግሎትና አምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ ከከተማ የሕዝብ ሱቆች፣ ከግለሠቦች ወዘተ በኃይል እየነጠቀ ከወሠደው ገንዘብና ንብረት ነው፡፡ በትግራይ ሕዝብ ስም የተሠበሠቡ የውጭ ዕርዳታና የመንግሥት ሥልጣን ከያዘም በኋላ ከሕግ ውጪ ከመንግሥት ካዝና ወደ ገዥው ፓርቲ የዞረ ከደርግ መንግሥትና ከግለሠቦች የተወረሠ ገንዘብና ንብረትም የኩባንያዎቹ ንብረት ሆኗል፡፡ ገዥው ፓርቲ ከአባላትና ከደጋፊዎች ያገኘው ገንዘብና ንብረት ብቻ ከጦርነት ተርፎ ለንግድ ኩባንያዎቹ የሚበቃ እንዳልሆነ ስለሚታወቅ የኩባንያዎቹ የካፒታል ምንጭ በአብዛኛው በሕገወጥ ዘረፋና ቅሚያ የተሠበሠበ ገንዘብና ንብረት ነው፡፡ የዚህ ንብረትና ገንዘብ ሕጋዊ ባለቤቶች በፍርድ ቤት ክስ መስርተው ፍትህ የሚያገኙበት ሁኔታ በመጥፋቱ ገዥው ፓርቲ በግፍ የሠበሠበውን ሃብትና ንብረት የሥልጣኑ መደገፊያና የአገዛዙ ዕድሜ ማራዘሚያ ሆነው የሚያገለግሉ የንግድ ኩባንያዎችን መስርቶበታል፡፡

ከኩባንያዎቹ ካፒታል ምንጭ ሌላ የተቋቋሙበትና የሚሠሩበት አግባብም ሕገወጥ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ "እንደውሜንት" ናቸው በሚል ሽፋን የሚያነሣው መከራከሪያ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ፍትሃብሔር ሕግ አንቀጽ 483 እንደተደነገገው "ኢንደውሜንት" ማለት "ትርፍ ለማግኘት ሣይሆን ለሕዝብ ጥቅም በሚያስገኝ የተወሠነ ዓላማ ላይ የዋለ፣ የማይመለስ፣ ቀጣይ የሆነ አገልግሎት እንዲሠጥ የተመደበ ገንዘብና ንብረት ነው" በሚል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ እነዚህ ኩባንያዎች ግን ከፍተኛ ትርፍ በሚገኝባቸው የተመረጡ የሥራ መስኮች የተሠማሩና ለትርፍ





የሚሠሩ በመሆናቸው በሀገሪቱ ሕግ ስለኢንደውሜንት ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሕገ ወጥ ድርጊት እየፈፀሙ ነው፡፡ ኩባንያዎቹ ሼር ባለቤትነት ድርሻ ባላቸው የግል ተቋሞችና ባለሃብቶች ሽርክና የተመሠረቱ ናቸው እንዳይባል የሼር ባለድርሻ ሆነው የተመዘገቡት የፓርቲው ንግድ ተቋሞችና ከፍተኛ መሪ ካድሬዎች ራሣቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የፓርቲ መሪዎች ደግሞ ለ17 ዓመታት በሽምቅ ውጊያ ውስጥ የቆዩ እንደመሆናቸው ይኸንን ያህል ካፒታል ያላቸው ኩባንያዎችን በሽርክና ለመክፈት የሚያስችል አቅም አልነበራቸውም፡፡ የኩባንያዎቹ ባለድርሻ ሆነው የተመዘገቡት አብዛኛዎቹ ካድሬዎች በበርሃ ውጊያ የቆዩ እንጂ ለኩባንያ ማቋቋሚያ የሚሆን ካፒታል የሚያመነጭ ፋብሪካ አቋቁመው፣ እርሻ አልምተውና ንግድ አካሂደው ገንዘብና ሃብት ያከማቹ አልነበሩም፡፡ ከዚህ ሌላ ኩባንያዎቹ አትራፊ በሆነ የንግድ ስራ የተሠማሩ ቢሆንም የሀገሪቱን የንግድ ሕግ በተከተለ መንገድ የተቋቋሙና የሚሠሩ ካለመሆናቸውም በላይ ገቢያቸውና ወጪያቸው የሚመረመርበት ሁኔታ መኖሩ አይታወቅም፡፡

ገዥው ፓርቲ ኢንደውሜንት ናቸው፤ ለንግድ የተቋቋሙ የሼር ኩባንያዎች ናቸው ወዘተ... የሚል ስም መስጠት የፈለገበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ፓርቲዎች ለትርፍ የሚሰራ ኩባንያና የንግድ ድርጅት እንዳይከፍቱ በሕግ የተከለከሉ ስለሆኑ ለዚህ ማምለጫ ዘዴ የፈጠረ መስሎት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉም ሁኔታ መውጫ በሌለው ሕገወጥ መንገድ የተቋቋሙና የሚሰሩ በመሆናቸው በእስካሁኑ አደረጃጀትና አሰራር የሚቀጥሉበት እድል የተዘጋ ነው፡፡ ይኸንን በመገንዘብ ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገዥው ፓርቲ አንድ አዲስ ስልት መጀመሩ ግልፅ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይኸውም እነዚህ ኩባንያዎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለሃብቶች ጋር በጋራ የሚሰሩበትና በሰብ ኮንትራት መልክ ትስስር የሚፈጥሩበትን አካሄድ እየተከተለ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ትስስር ከተፈጠረና የባለቤትነት መብቱን ከሌሎች ጋር መጋራት ከተቻለ በእያንዳንዱ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ንብረትና ገንዘብ ላይ የተለየ ጥያቄ ለማንሳት የማያስችል ውስብስብ ሁኔታ ስለሚኖር ቀስ በቀስ ተቃውሞው እየተዳከመ ይጠፋል በሚል ሂሣብ የተሰላ ነው፡፡

ይኸኛውም ስልት ወንዝ የሚያሻገር አይደለም፡፡ እንዲያውም ከሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ጋር የሚመሰረቱ ሽርክናዎች የገዥውን ፓርቲ ኩባንያዎች ካፒታል በዓይነትና በመጠን እየለዩ ለማወቅ የሚያስችሉ ግልጽ መረጃዎችን ከእስከዛሬው በተሻለ ለማግኘት ስለሚረዱ ሕገወጥ በሆኑት የፓርቲ ኩባንያዎች ላይ የሚነሳውን ሕጋዊ ጥያቄና ተቃውሞ ለማጠናከር አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡

የገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ሕገወጥነት በካፒታል ምንጫቸውና በተቋቋሙበት ሁኔታ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን በአሰራራቸውም ላይ የሚንፀባረቅ ነው። ይኸውም በችርቻሮና ጅምላ፣ በአስመጭነትና በላኪነት፣ በሕንፃ፣ በመንገድና በግድብ፣ ኮንስትራክሽን፣ በኃይል ማመንጫ ግንባታና በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ በባንክና በኢንሹራንስ፣ በሕትመትና በማስታወቂያ፣ በሕዝብ ትራንስፖርትና በጭነት ማጓጓዣ፣ በገጠርና በከተማ አነስተኛ ብድር ተቋማት፣ በእርሻ ግብዓቶች ስርጭት፣ በትምህርትና በጤና አገልግሎት፣ በኪነጥበብና በመገናኛ ብዙሃን ወዘተ ያልገቡበት መስክ የለም። እነሱ በገቡበት መስክ ሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች እንዳይሳተፉ ከፍተኛ የፖሊሲና የቢሮክራሲ መሰናክሎች ይፈጠሩባቸዋል። ይኸንን ሁሉ ተፅእኖና መሰናክል አልፈው ወደመስኩ ለመግባት ከቻሉ ደግሞ ከፓርቲ ኩባንያዎች ጋር በነፃነት መወዳደር እንዳይችሉ ልዩ ልዩ እንቅፋቶች ሆን ተብለው ይደቀኑባቸዋል። አማልጋሜትድ ሊሚትድ ኢትዮጵያ የሚባለው የግል ኩባንያ የእርሻ ግብዓቶችን በማቅረብ የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ከሆኑት ከእነ አምባሰል ጋር እየተወዳደረ እንዳይሰራ በፌዴራልና በክልል የመንግሥት አካላት ተከታታይ የሆነ ከባድ ተፅእኖ ስለተደረገበት ከውድድሩ ለመውጣት የተገደደበትን ተጨባጭ ማስረጃ ማየት ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ገበሬው በጥራትና በዋጋ የተሻለውን ግብዓት መርጦ ለመግዛት እንዳይችል ተደርጓል።

የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆኑት ሱርና ላሊበላ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ሌሎች የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ሊያገኙት ያልቻሉትን የስራ እድል እንዲያገኙ የሚደረግላቸውን የተለየ እንክብካቤ በማስረጃነት ማየት ይቻላል። የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ትራንስ ኢትዮጵያ ሌሎች የግል ባለሃብቶችና የመንግሥት የጭነት ማጓጓዣ ተቋሞች እየተከለከሉ በውጭ ምንዛሬ የትራንስፖርት ክፍያ እያገኘ ከውጭ የሚገቡ እርዳታዎችንና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን እንዲያጓጉዝ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ጉና የንግድ ድርጅት ቡናን ወደ ውጭ በመላክ ከሌሎች የግል ባለሃብቶችና ከመንግሥት ቡና ላኪ ድርጅት የበለጠ ሚና እንዲጫወት የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል። የግል ባንኮች ተቀማጭ ካፒታላቸው እስከ 75% ካልደረሰ አንድም ይቀላቀላሉ አሊያም ይዘጋሉ የሚል ሕግ ቢኖርም ይኸንን ሕጋዊ ግዴታ ያልተወጣውና የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ወጋገን ባንክ ከሕግ ውጭ ስራውን እንዲሰራ የተደረገለትን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል። ለሌሎች የግል ባለሃብቶች በከባድ ውጣ ውረድና ከጠየቁት እጅግ ባነሰ መጠን የሚገኝ የመንግሥት ባንኮች ብድር የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆኑት ኤፈርት፣ ጉና፣ አምባሰልና ሌሎቹም በቀላሉ እንዲያገኙ







የሚደረግላቸውን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል። የግል ባለሃብቶች የብድር መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምላቸው የሚያቀርቡት ሕጋዊ ጥያቄ እየታጠፈ ንብረታቸው ሲወረስና በሀራጅ ሲሸጥ የፓርቲው ንግድ ኩባንያዎች ያልከፈሉት እዳ እንደተቆለለ ሌላ ተጨማሪ ብድር እንዲያገኙ የሚደረግላቸውን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል። የባንክ ብድር የሚያገኙበትና የሚመልሱበት ግልጽ አሠራር ካለመኖሩም ሌላ እስካሁን የወሠዱት ብድር ከንግድ ባንክ ወደልማት ባንክ ለምን እንደተሸጋገረ ግልጽ ባይሆንም የንግድ ባንክ በዓለም አቀፍ ኦዲተሮች ሲመረመር ስለፓርቲ ኩባንያዎች ብድር ምስጢር እንዳይወጣ ለመደበቅ ሣይሆን አይቀርም።

በተለያዩ ጨረታዎች አስቀድመው የጨረታ ምስጢርና የማሸነፊያ ምክር ስለሚያገኙ ከገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ጋር ተወዳድሮ ለማሸነፍ የተቻለበት እድል እጅግ የመነመነ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል። የመንግሥት ትምህርት መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅትና ሌሎች የግል ሕትመት ድርጅቶች የሚሳተፉበት እድል ተዘግቶ የሜጋ አሳታሚ ድርጅት የሚባለው የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የተማሪዎችንና የመምህራንን መፃህፍት በብቸኝነት እያተመ እንዲያሰራጭ ብቻ ሳይሆን ከውጭ የሚገቡ መፃህፍትንም በሞኖፖል እንዲያስገባና እንዲያሰራጭ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ በአስረጅነት ማንሳት ይቻላል። በኤፈርት ስር በእንግሊዝ የተቋቋመና ታወር ትሬዲንግ የሚባል የንግድ ድርጅት ለሜጋና ብርሃንና ሠላም ወረቀት እያቀረበ የሚነግድበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። የብሮድካስቲንግ አዋጅ በስራ ላይ እንዲውል ሳይደረግና የግል ባለሃብቶች በዚህ ዘርፍ እንዲሳተፉ የሚያስችል ፈቃድ መስጠት ከመጀመሩ በፊት የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነው ሬዲዮ ፋናና ድምፀ ወያኔ በሕገወጥ መንገድ የሬዲዮ ማሰራጫ አየር ሞገድ ያገኙበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። የድርጅት ልሣን የሆነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣና መጽሔት ማስታወቂያዎችን እያተመ ይነግዳል። የገዥው ፓርቲ ኩባንያ የሆነውና ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል የሚባለው የዜና አገልግሎት ተቋም የመንግሥት ዜና አገልግሎት ከሆነው ኢዜአ የበለጠ ዜና ከውስጥና ከውጭ እንዲሰበስብ፤ እንዲገዛና እንዲሸጥ የሚደረግለትን ልዩ ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ የፓርቲ ኩባንያዎች በሚያካሂዱት ስራ የሚጠቀሙበትን የመሬት፣ የቤትና ሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎት የሚያገኙት ከሌሎች ጋር ተወዳድረው እያሸነፉ ሣይሆን በመንግሥት ትዕዛዝ ነው። ከዚህም ሌላ ለሚገለገሉበት መሬትና ቤት ተገቢ ኪራይ የስራ ግብርና ታክስ ለመንግሥት የሚከፍሉ መሆናቸው በግልጽ አይታወቀም።

ከዚህ የባሰው ሙስና ለግብርና ግብዓት ከውጭ አበዳሪ ድርጅቶች

መንግሥት በሀገሪቱ ስም የሚያገኘውን ብድርና እርዳታ ለገዥው ፓርቲ ኩባንያዎች ንግድ ማካሄጃ እንዲሆን የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ይኸንን በሀገር ስም የተገኘ ብድር እነአምባሰል እየወሰዱና የግብርና ግብዓት ከውጭ ገዝተው ለገበሬው በውድ ዋጋ እየሸጡ ትርፉን ወደ ፓርቲው ካዝና ያስገባሉ፡፡ እዳውን ሀገሪቱ ትከፍላለች፡፡ ለገጠርና ለከተማ አነስተኛ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት እየተባለ በገዥው ፓርቲ የተከፈቱ ተቋሞች በብድርና በእርዳታ ከተገኘ ገንዘብ ወይም ለሌላ ዓላማ በመንግሥት ባንክ ከተቀመጠ ገንዘብና ከመንግሥት መደበኛ በጀት እያዞሩ በብድር መልክ ካከፋፈሉ በኋላ ትርፉን ወደ ገዥው ፓርቲ ካዝና ያስገባሉ፡፡ እዳውን ድሃው ሕዝብ ከጉሮሮው እየተነጠቀ ይከፍላል፡፡ ጉና ንግድ የሚባለው የገዥው ፓርቲ ኩባንያ ቡና ሸጦ ካገኘው የውጭ ምንዛሬ፣ ወይም ትራንስ ኢትዮጵያ እቃ በውጭ ምንዛሬ ክፍያ አጓጉዞ ካገኘው የውጭ ምንዛሬ ምን ያህሉን ለብሔራዊ ባንክ ምን ያህሉን ወደገዥው ፓርቲ ካዝና ገቢ እንደሚያደርግ በግልፅ አይታወቅም፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ሁሉም የሀገር ሃብትና ንብረት ለሁሉም ዜጎች መገልገያ ወደ ሆኑት የመንግሥት ካዝናዎችና ግምጃ ቤቶች ሳይሆን ወደገዥው ፓርቲ ቋት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

በዚህ መንገድ ተዘርዝረው የማያልቁ የሙስና ገጽታዎችን መጥቀስ ቢቻልም ዋናው ነገር በሀገሪቱ አሁን የተከሰተው ሙስና የገዥው ፓርቲ ሙሉ እውቅናና ድጋፍ የሚደረግለት ይፋ የሆነ ተቋማዊ ሙስና እንጂ በግለሰብ ደረጃ የሚካሄድና በድብቅ የሚፈፀም ተራ ሌብነት አለመሆኑ ነው፡፡ ይኸንን ሁሉ ግልፅ ዘረፋ ሲያካሂድ የሚጠየቅበት ወይንም የሚከሰስበት መንገድ ሁሉ የተዘጋና ራሱን ከሕግ በላይ አስቀምጦ በአፈናና በንጥቂያ የሚኖር ጠያቂ የሌለው አገዛዝ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሙስናን ይከላከላል በሚል የተቋቋመው የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ባለመሆኑ የአገዛዙን ተቀናቃኞች ለመጥለፍና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚያገለግል ሽፋን ከመሆን የዘለለ ፋይዳ አላስገኘም፡፡ ተቋሙ ነጻ ተቋም ቢሆን ኖሮ የሙስና መሠረት የሆነው የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝና ግንባር ቀደም ሙሰኛ የሆኑት የሥርዓቱ መሪዎች ሥልጣን ላይ የሚቆዩበት ሁኔታ አልነበረም፡፡

ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ተቋማዊ ሙስና በነገሠበት፣ ነፃ የገበያና የፍትህ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስለሀገር ልማት፣ ስለኢንቨስትሜንት መስፋፋትና ስለ ግል ባለሀብቶች ተሳትፎ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡ ይኸንን ተቋማዊ ሙስና ከመሠረቱ የሚያስወግድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሳይመሠረት ኢትዮጵያን ከድህነት ሰልፍ ማውጣትና የሕዝቡን







የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽል ልማት ማምጣት እጅግ አስቸጋሪና የማይቻልም ነው፡፡

## 2.14.3 የአሰራር ነፃነት የሌለው ሲቪል ሠርቪስ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሠርቪስ ገለልተኛነት ጠፍቶ ፖለቲካዊ ገጽታው እንዲጉላ ሆኖ ተደራጅቷል፡፡ ከገዥው ፓርቲ ጋር አንድ ወጥ የሆነ ሥራ የሚሠራ ፖለቲካዊ ተቋም እንዲሆን በመደረጉ የአንድ ፓርቲ ፖለቲካዊ አጀንዳ ማስፈጸሚያ እንጅ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም መሆኑ አብቅቷል፡፡ የአሁኑ የሲቪል ሠርቪስ ተቋም ነጻነትና ገለልተኛነት ብቻ ሣይሆን ግልጽነትና ተጠያቂነትም የለውም፡፡ የገዥው ፓርቲ አንድ ቅርንጫፍ እስኪመስል ድረስ በፖለቲካ ተፅእኖ ስር ወድቆ በሲቪስ መዋቅር መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ለማየት በማይቻልበት የተቆላለፈ መንገድ በመደራጀቱ የሚፈለገውን ቀልጣፋ አገልግሎት፣ የሥራ ጥራትና ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም፡፡

በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለው የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም የገዥውን ፓርቲ ፖለቲካዊ ቁጥጥር ይበልጥ ለማጥበቅ የታለመ መሆኑን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የማሻሻያ ፕሮግራሙ ሠራተኞች የተሣተፉበትና ብቃት ባላቸው ሞያተኞች የተዘጋጀ ሣይሆን የገዥው ፓርቲ መሪ ካድሬዎችና የኮር አባሎች ቢሮአቸውን እየዘጉ በተናጠል መክረውና ዘክረው ያረቀቁት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የተቀየሰውን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ የረጅም ጊዜ ተቋማዊ ልምድ፣ የሠለጠነ ሞያተኛና ሕጋዊ አቋም ያለውን መደበኛ የሲቪል ሠርቪስ መዋቅር በማዳከምና ሌላ የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት የሚባል ተደራቢ ተቋም በአዲስ መልክ በመክፈት የሠው ኃይል፣ ገንዘብና ጊዜ የሚያባክን አላስፈላጊ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ተመሣሣይ ስራ የሚያከናውኑ ሁለት ተቋሞች በሚኖሩበት ጊዜ የሥራ ሽሚያ፣ መደራረብና መዘበራረቅ ከመፍጠር በስተቀር ሌላ ውጤት ሊገኝ ባይችልም በእኛ ሀገር እየተፈፀመ ያለውም ይኸው ነው፡፡

የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያውን ተከትሎ ተደጋጋሚ የመዋቅርና የሰው ኃይል ብወዛ እየተካሄደ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ አንድ የታቀደ ስራ ዘላቂ ውጤት ማምጣት አለመምጣቱን ለመገምገም የሚያበቃ የመገምገሚያ ጊዜና መረጋጋት ከጠፋ ዓመታት እየተቆጠሩ ነው፡፡ አንደኛው ዓይነት የአደረጃጀት አማራጭ በሥራ ላይ ውሎ በሚገባ ሣይፈተሸ ሌላ ዓይነት አማራጭ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ የመጀሪያው ድክመትና ጥንካሬ

በዝርዝር ሣይጠና አዲሱ ይጀመራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሠራተኛው ተረጋግቶ ለመስራት አለመቻሉ ብቻ ሣይሆን ተቋማዊ ልምዶችና መረጃዎችም ደብዛቸው እየጠፋ ነው፡፡ ሀገሪቱ ተቋማዊ መረጃዎችን ለማሣደግ ያላት ዕድል እየተበላሸ ነው፡፡

በሲቪል ሠርቪሱ የሚካሄደው ትርምስ ገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ደጋፊዎቹን ለመጥቀምና ተቃዋሚዎቹን ለመጉዳት እንዲችል ከማድረግ በስተቀር ያስገኘው ትልቅ ፋይዳ የለም፡፡ በሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ሠበብ የመንግሥት ሠራተኞች ቅጥር፣ ዕድገት፣ የደሞዝ ጭማሪ፣ ዝውውር፣ የሥራ ላይ ሥልጠናና የመሣሠሉ ሥራዎች የሚመሩበት ሕጋዊ ሥርዓት በፖለቲካ ውሣኔ ተተክቷል፡፡ የመንግሥት ሠራተኞችን መብትና ጥቅማ ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚወሠኑበት ሕጋዊ አሠራር ቀርቶ ሁሉም ነገር በፖለቲካ ሹማማምንቶች መልካም ፈቃድ እየተከናወነ ነው፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የተደራጁ የገዥው ፓርቲ ሕዋሶች ሲቪል ሠርቪሱን እንዳሻቸው እያሽከረከሩት ነው፡፡ ለፓርቲ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ከችሎታቸው ጋር የማይመጣጠን የሥራ ምደባና የደሞዝ ደረጃ እየፈቀዱ አብዛኛው ሠራተኛ በመንግሥት ሕግና ሥርዓት ከደረሰበት የሥራ መደብና የደሞዝ እርከን ያወርዱታል፡፡ ካለበቂ ምክንያት የሚያንሣፍፉትና ከሥራ የሚያባርሩትም ብዙ ነው፡፡ ግልጽ የሆኑ የሥራ አፈጻጸም ውጤት መለኪያዎችን አስቀርተው ግምገማ የሚባል ድርጅታዊ አሠራር ተክተዋል፡፡ በዚህም የተነሣ በሲቪል ሠርቪሱ ውስጥ የሥራ ተነሣሽነት፣ ውጤታማነትና መረጋጋት ጠፍቶ በአንፃሩ ሙስናና ሥርዓተ አልበኝነት ነግሷል፡፡

ለካድሬዎች ውለታ መክፈያ አዳዲስ መስሪያ ቤቶችና መዋቅሮች ይከፈታሉ፡፡ ችሎታቸው የማይፈቅደው ሹመት ይሠጣቸውና ከስር አማካሪ ይመደብላቸዋል፡፡ አንዳንዴ በቂ ጥናት ሣይኖር መስሪያ ቤቶች ለሁለት ለሦስት ይከፈሉና አላስፈላጊ የሪሶርስ ብክነት ከደረሰ በኋላ እንደገና ይዋሃዳሉ፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ መስሪያ በቶች ሲለያዩና ሲገጣጠሙ የረባ ቁምነገር ሳይሠራ የሚቀርበት ሁኔታ አለ፡፡ በአጠቃላይ ሲቪል ሠርቪሱ ከትርምስ ነጻ ሆኖ ለመስራት የሚያስችለው መረጋጋት አጥቶ እየታመሠ ነው፡፡

ከሲቪል ሠርቪሱ በተለየ ሁኔታ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚተዳደረው ሠራተኛም መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር የሚችልበት አስተማማኝ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ የቀድሞውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ችግሮች ይፈታል ተብሎ የተዘጋጀውና የካቲት 18 ቀን 1996 በታተመው







ነጋሪት ጋዜጣ የወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 የሠራተኛውን መሠረታዊ ጥቅሞች በሚገባ የማያስጠብቅ በመሆኑ ከፍተኛ ተቃውሞ አስነስቷል፡፡ አዋጁ ሠራተኛው ሥራውን በፍላጐት ሲለቅ የአገልግሎት ካሣ የማግኘት መብቱን በሚገባ አያስከብርም፡፡ ከስራ ለመልቀቅ መፈለጉን የሚያስታውቅበት ጊዜ በቀድሞው አዋጅ ከነበረው እንዲረዝም ከመደረጉም ሌላ ይኸንን ካልፈፀመ ደሞዙን የሚቀጣበት ግዴታ ተደንግጓል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ቦርድና ፍ/ቤቶች ሠራተኞች በደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ረገድ የሚያቀርቡትን አቤቱታ የማስተናገድ ሥልጣን አልተሠጣቸውም፡፡ አላግባብ ከሥራው የተባረረ ሠራተኛ ወደ ስራው እንዲመለስ ሲወሠንለት የተቋረጠበትን ደሞዝ ሙሉ በሙሉ እንዲያገኝ አይፈቅድም፡፡ ማግኘት የሚችለው ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት ያለውን ብቻ ነው፡፡ እነዚህና የመሣሠሉት ጉድለቶች እንዲታረሙ አዋጁ ከመጽደቁ በፊት ሠራተኞች ቅሬታቸውንና ተቃውሟቸውን ቢያቀርቡም ተገቢ መልስ የሚሠማቸው ባለማግኘታቸው ሕጉ በዘፈቀደ ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

## 2.14.4 አስከፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣና የእርስ በርስ ግጭቶች

ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ለሠው ልጅ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መረጋገጥ እንደቆመ ለማስመሠል ሙከራ ቢያደርግም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ቢያሠፍርም ሊያከብራቸውና ሊመራባቸው አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ገዥው መንግሥት በሚፈፅመው ተግባር ሕገ-መንግሥት የጻፈና ስለዴሞክራሲም ሆነ ስለሰብዓዊ መብት የሚሠብክ ሁሉ ዴሞክራሲያዊ እንዳልሆነ ጥሩ ማረጋገጫ ሊሆን ችሏል፡፡

በዚህ መንግሥት የተፈፀሙት የሠብዓዊ መብት ረገጣዎች በዓይነታቸው፣ በባህርያቸውና በመጠናቸው እጅግ በርካታ እንደመሆናቸው ሁሉንም እዚህ ላይ መዘርዘር አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያግዙ ጥቂት እውነታዎችን ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የፈፀማቸውን የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ የሚከታተላቸውና የሚያውቃቸው ቢሆንም ሆን ብለው መረጃዎችን የሚመዘግቡና በይፋ የሚያወጡ የሠብዓዊ መብት ተንከባባቢ ተቋሞችና መንግሥታት በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጁ ሕዝብ እንዲያውቀው ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣ የተመዘገቡ ሀቀኛ መረጃዎችን መሠረት

በማድረግ ተደጋጋሚ ክስና ወቀሣ የሚቀርብበት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ጥፋቱን አምኖ የተቀበለበት፣ በደል ለደረሠባቸው ይቅርታ የጠየቀበት፣ በጥፋቱ የተሣተፉ ባለሥልጣኖቹን ለሕግ ያቀረበበትና ጉዳተኞች የተካሱበት ጊዜ የለም፡፡ በወተር፣ በአረካ፣ በበደኖ፣ በንፋስ መውጫና በዝዋይ እስር ቤቶች በአደባባይ ኢየሱስ፣ በሀረሪ ጃርሶ ወረዳ፣ ሠሜን ኦሞ በሚገኙ የማሊና አሪ ተናጋሪ ሕዝቦች፣ በአምቦ፣ በወላይታ ሶዶ ሕዝብ፣ በቴፒ አካባቢ ሕዝብ፣ በአዋሣ ሕዝብ፣ በድሬደዋ ሕዝብ፣ በአዲስ አበባ፣ በአለማያ፣ በባህር ዳር፣ በጅማ፣ በደቡብ፣ በመቀሌ ዩኒቨርስቲዎች ወዘተ የተካሄዱ ጭፍጨፋዎች በመንግሥት ታጣቂዎች የተፈፀሙ ናቸው፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅቶችና ምዕራባዊያን መንግሥታት በኢትዮጵያ ስለሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ይፋ ያደረጓቸው ማስረጃዎች እንዳሉ ሆነው በኢትዮጵያ ሠብዓዊ መብቶች ጉባዔ እስካሁን የቀረቡት ዘገባዎች ብቻ እንኳ እጅግ አስደንጋጭ ናቸው፡፡ ከ2 ሺህ ዜጐች በላይ በፖለቲካ ምክንያት ሕገወጥ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ከ2200 በላይ በጥይት ቆስለዋል፡፡ ከ1ሺህ በላይ ተይዘው ተሠውረዋል፡፡ ወደ 11 ሺህ ዜጐች ሕገወጥ እስራት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ከ15 ሺህ በላይ ዜጐች ካለአግባብ ከስራ ተባረዋል፡፡ ወደ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጐች አሠቃቂ የሆነ ድብደባና ግርፋት ተፈጽሞባቸው አካለ ጐደሎ ሆነዋል፡፡ 2084 ዜጐች የጡረታ መብታቸውን እንዳያገኙ ተከልክለዋል፡፡ 71333 ዜጐች በፖለቲካ ምክንያት ስደትና መፈናቀል ደርሶባቸዋል፡፡ በርካታ ዜጐች የመኖሪያና የንግድ ቤታቸውን ተነጥቀዋል፡፡ ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያለው ልዩ ልዩ ዓይነት ንብረት ተዘርፈዋል፡፡ 14264 ቤቶች በሕገ ወጥ መንግድ ተቃጥለዋል፡፡ ከእዚህ ውስጥ ቤተክርስቲያንና መስጊዶች ይገኙበታል፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች ቤታቸው ፈርሶባቸዋል፡፡ በ10ሺህ ኩንታል የሚቆጠር እህል ተዘርፈዋል፡፡ በሺህ ሄክታር የሚገመት የማሣ ላይ ሰበብ ተቃጥሎባቸዋል፡፡ ከ1ሺህ በላይ ዜጐች የሥራ ቦታቸውን እንዲዘጉ በማድረግ የመስራት መብታቸውን ተነጥቀዋል፡፡ በርካታ ዜጐች የሻዕቢያ፣ የሕወሀትና የኢሕአዴግ የጦር ምርከኛ ሆነው ከተያዙ በኋላ የደረሱበት አይታወቅም፡፡ ይህ ሁሉ ግፍ የተፈፀመው ዜጐች በነጻነት ለመደራጀት፣ ሃሣባቸውን ለመግለጽና ተቃውሟቸውን ለማሠማት ያላቸውን ዴሞራክሲያዊና ሰብዓዊ መብት በኃይል ለማፈን ነው፡፡

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በሀገሪቱ ውስጥ ለእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት መንስዔ የሆኑ ችግሮችን የሚያስወግድ መፍትሔ እንዳለው ደጋግሞ ቢገልጽም ሁኔታዎች እየተባባሱ እንጅ እየተሻሻሉ አልመጡም፡፡ ከሪሶርስ





ሺሚያና ከቆዩ ባህላዊ ችግሮች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ነባር ግጭቶች እንዳሉ ሆነው አሁንም በፖለቲካ ምክንያት የሚታዩ ፍጥጫዎችና ጦርነቶች የሕዝቡን ሠላም እያወኩና የሀገሪቱን ደህንነት እየተፈታተኑ ናቸው፡፡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር፣ የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣ የአርበኞች ግንባር የሚባሉት፣ በጋምቤላና በሌሎችም የሀገሪቱ ክልሎች የሚገኙ ድርጅቶች የትጥቅ ትግል ከማድረግ ሌላ የተሻለ አማራጭ አላገኘንም ብለው ተሠልፈዋል፡፡ በመንግሥት በኩል እነዚህ ወገኖች አሉን የሚሏቸውን ጥያቄዎችና ስጋቶች በአግባቡ ለመገንዘብና ተገቢ መፍትሔ ለመስጠት የሚደረግ ገንቢ ጥረት የለም፡፡ ተቃናቃኞችን በኃይል ለማጥፋት የማያባራ አሠሣና ዘመቻ ከማድረግ በስተቀር መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ ፖለቲካዊ መፍትሔ ሲፈለግ አይታይም፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ትግራይ ሆቴል፣ ብሉ ቶፕስ፣ ግዮን ሆቴል፣ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል፣ በድሬደዋ ራስ ሆቴልና መኮንን ቡና ቤት በተለያዩ የሀገሪቱ ማዕዘናት የደረሱ ፍንዳታዎች የሽብርተኛ ድርጊት ናቸው ቢባልም በአብዛኛው ፖለቲካዊ መንስዔ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ መንግሥት የሚከተለው የጐሣ ፖሊሲ በሀገሪቱ የእርስ በርስ ግጭቶች እንዲባባሱና አስከፊ መልክ እንዲይዙ እያደረገ ነው፡፡ በአርባ ጉጉ፣ በአርሲ ነገሌ፣ በመተከልና በቤንች ማጂ የተካሄዱ የጐሣ ግጭቶች በፖለቲካዊ ግፊት የተከሠቱ ነበሩ፡፡ በጉጂ ኦሮሞና በጌዲኦ ሕዝብ መካከል፣ በምሥራቅ ወለጋ ጊዳ ኪራሞና አቢደንገሮ ወረዳዎች በሠፈሩ ዜጐች ላይ የተከሠተው ችግር፣ በወላይታና ጋሞ ሕዝብ መካከል፣ በአሬሮ ወረዳ በጌሪና የቦረና ኦሮሞ መካከል፣ በአኙዋክና ኑዌር ሕዝብ መካከል፣ በአማራና በአፋር፣ በአፋርና ሶማሊያ፣ በአፋርና ኦሮሞ፣ በኦሮሞና በሶማሊ ወዘተ ሕዝብ መካከል፣ በተደጋጋሚ ጊዜያት የተከሠቱ ግጭቶች የጐሣ ፖለቲካው ውጤቶች ናቸው፡፡ በአርባ ጉጉ፣ በምዕራብ ሐረርጌ፣ በወለንጪቲና በአንዋር መስጊድ ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የተከሠቱ ግጭቶች ሣይቀሩ ዋነኛ መሠረታቸው መንግሥት የሚያራምደው የጐሣ ፖለቲካ ነው፡፡ እነዚህ ፖለቲካዊ ፍጥጫዎችና የእርስ በርስ ግጭቶች የተባባሱት ዴሞክራሲያዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ባለመኖሩና በሀገሪቱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውሉና ውጤትም ሲያስገኙ የነበሩት ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች ችላ በመባላቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ የአሁኑ አገዛዝ አስከፊ ለሆነ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ ለፖለቲካ ፍጥጫ፣ ለጐሣ ግጭትና ለእርስ በርስ ጦርነት መነሻ መሠረት ነው፡፡ እንደዚህ ላለው የመብት ረገጣ፣ ፍጥጫና ግጭት መነሻ የሆነ ፖሊሲ የሚያራምድ መንግሥት በሥልጣን ላይ እንዲቀጥል እንደገና ሌላ ዕድል ከተሰጠው ሕዝቡና ሀገሪቱ ከእስካሁኑ የባሠ ብጥብጥና እልቂት ለማስተናገድ

ይገደዳሉ፡፡

## 2.15 የሀገር ሉዓላዊነት መደፈር

የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ የመንግሥትን ሥልጣን በጠመንጃ ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቡን ብሔራዊ ጥቅሞች ለውጭ ኃይል አሣልፎ በመስጠት በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅና ወደር የማይገኝለት የክህደት ተግባር ፈጽሟል፡፡

የኤርትራን ግንጠላ የሚደግፍ ሕዝበ ውሣኔ እንዲደረግ የፈቀደው የኢትዮጵያን ጥቅም እንደሚጐዳ አስቀድሞ እያወቀና ሆን ብሎ ነው፡፡ የሀገሪቱን ጥቅሞች የሚከላከል፣ የሕዝቡን ሃሣብና ፍላጐት የሚወክል በሕዝብ የተመረጠ ሕጋዊና ቋሚ መንግሥት በሌለበት የሽግግር ወቅት የሻዕቢያን ሃሣብ ደግፎ ለኤርትራ ግንጠላ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲተባበሩ ማመልከቻ የጻፈውና ኢትዮጵያ ውስጥ ድምጽ ለሚሠጡ ኤርትራዊያን ዳስና ድንኳን ከማዘጋጀት ጀምሮ ጠቅላላውን ሂደት ስፖንሰር በማድረግ የግንጠላው ተዋናይ ሆኖ የከረመው ይኸንን እንዲፈጽም የሚያስችል ሕጋዊ ውክልና ሣይኖረው ነው፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚወክሉ ሃሣቦች በነጻነት እንዳይንሸራሸሩ መድረኩ ሁሉ በተዘጋበት ሁኔታ ከሻዕቢያ ጋር ተመሳጥሮ ከሕዝቡ ፈቃድና ዕውቀት ውጭ ሂደቱ የሀገሪቱን ጥቅም በሚጐዳ መንገድ እንዲከናወን አደረገ፡፡ ሕዝበ ውሣኔው ከመካሄዱ በፊት መፍትሔ ማግኘት የነበረባቸው የድንበር ጉዳይ፣ የባህር በር ባለቤትነት ጉዳይ፣ ኤርትራ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ኤርትራዊያን ጉዳይ ምንም ዓይነት ትኩረት አላገኙም ነበር፡፡ በጣም የሚገርመው የኤርትራ ወረራ ዋዜማ አካባቢ የድንበር ጉዳይ አጨቃጫቂ ሆኖ ሲወጣ ጉዳዩ የሀገር መሆኑ ቀርቶ ከሻዕቢያና ከሕውሃት አመራሮች የተወከሉ አባላት የሚገኙበት የድንበር ኮሚሽን አቋቁመው በምስጢር የሚደራደሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

የወደብ ጉዳይ በተለያየ ጊዜ ሲነሣ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ሲሰጡ የነበረው መልስ ኢትዮጵያ ወደብ ባይኖራትም የምታጣው ነገር የለም የሚል ነበር፡፡ የወደብ ጥያቄ ማንሣት የሉዓላዊነትና የብሔራዊ ጥቅም ጥያቄ ሣይሆን የነፍጠኛነት አስተሣሰብ ውጤት ነው ይባል ነበር፡፡ ሀቁ ግን ወደብ የሌላቸው ሀገሮች ከውጭ የሚያስገቡት ኢንቨስትሜንት ወደብ ካላቸው ጋር ሲነፃጸር 34% ብቻ በመሆኑ ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ ይህ አቋምና ተግባር ደግሞ የለየለት የሀገር ክህደት ነው፡፡ ሥልጣን ላይ ያለው







መንግሥት በያዘው የተሣሣተ አቋምና በወሰደው አደገኛ እርምጃ የሀገሪቱ ዜጎች መብትና ነጻነት ተረግጧል፡፡ መዘዙ የሻዕቢያን የዕብሪት ወረራ፣ ያልተፈለገ የሕይወት መስዋዕትነትና የንብረት ውድመትን አስከትሏል፡፡ የሀገሪቱ ሉዓላዊነት እንዲደፈርና ሕጋዊ የግዛት ክልሏን ያለ አግባብ እንድትነጠቅ አድርጓታል፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ያለውን ግዴለሽነት በሚገባ የሚያውቀው የሻዕቢያ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ የኮንትሮባንድ ንግድ ሲያጧጡፍ፣ የሀገሪቱን ሠሊጥ፣ ቡናና ቆዳ እየዘረፈ ወደ ውጭ በመሸጥ የማይገባውን ጥቅም ሲያገኝ ከርሟል፡፡ ኤርትራ የውጭ ብድር እንድታገኝ ዋስትና በመስጠትና በኋላም ዕዳው ከኢትዮጵያ ካዝና እየወጣ እንዲከፈል በማድረግ ከባድ ጥፋት ፈጽሟል፡፡ ለኤርትራ መንግሥት ማቋቋሚያ በባንኮች በኩል ከ1.2 ቢሊዮን ብር በላይ ከተሠጠ በኋላ ውኃ በልቶት ቀርቷል፡፡ ኤርትራዊያን በባንክ አስቀምጠውት የነበረው ነው በሚል 50 ሚሊዮን ብር ለሻዕቢያ መንግሥት እንዲሠጥና የባንክ ማቋቋሚያ እንዲሆን ሠጥቷል፡፡ ለኤርትራ ማቋቂሚያና መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል 18 ሚሊዮን 1 መቶ ሺህ ብር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ተበድሮ ለሻዕቢያ እንዲሠጥ በአዋጅ ቁጥር 51/1985 መሠረት ወስኖ ተግባራዊ አድርጐታል፡፡ ይህ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥትና በኤርትራ ጊዜያዊ መንግሥት መካከል የተፈረመ የመልሶ ማበደር ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ በአሠብ ነዳጅ ማጣሪያ የድፍድፍ ዘይት ለማጣራት፣ ለማጣሪያው ዕድሣትና ለወደብ ማስፋፊያ፣ ለፋብሪካ መለዋወጫ፣ ለኬሚካል፣ ለኢንሹራንስ ወዘተ… በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚሸፈነው በኢትዮጵያ ወጪ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ በውጭ ምንዛሬ ከውጭ ሀገር የምታስመጣውን ድፍድፍ ዘይት በአሠብ ማጣሪያ ካጣራች በኋላ፣ ለኤርትራ የተጣራ ዘይት የምትሸጠው በውጭ ምንዛሬ ሣይሆን በኢትዮጵያ ብር ነበር፡፡ አዲስ አበባ በሚገኘው የኤርትራ ኤምባሲ ቅንብር “ሬድ ሲ ትሬዲንግ” የሚባል ድርጅት ሲቋቋም፣ በኮንትሮባንድ፣ የገንዘብ ምንዛሬና በሐሠተኛ ብር ስርጭት ተሰማርቶ የኢትዮጵያን ነጋዴዎች ለኪሣራ ሲያጋልጥ የሚጠይቀው አልነበረም፡፡ በኢትዮጵያ የነበረው የሻዕቢያ አምባሳደር “ሆርን ኦፍ አፍሪካ” የሚባል ባንክ ሲያቋቁም በወያኔ/ኢሕአዴግ ሙሉ ትብብር የተፈፀመ ነበር፡፡ ይኸንን ሁሉ ሕገወጥ ድርጊት የሚቃወምና የኢትዮጵያን መጐዳት የሚመለከት ሃሣብ ሲነሣ በወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች በኩል ይሠጥ የነበረው መልስ የተጐዳችው ኢትዮጵያ ሳትሆን ኤርትራ ናት የሚል ነበር፡፡ በአጠቃላይ ሻዕቢያ ከኢትዮጵያ በሚዘርፈው ሃብት ራሱን የአካባቢው ልዕለ ኃያል አድርጐ ለመገንባትና በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ለማድረግ የሚያበቃውን ዝግጅት

እንዲያጠናቅቅ ዕድሉ የተሠጠው በወያኔ/ኢህአዴግ አማካይነት ነበር፡፡

አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከሻዕቢያ ጋር ያደርግ በነበረው ሕገወጥ ግንኙነት የሀገሪቷን ሃብት ከማዘረፍ አልፎ ሉዓላዊነቷንም አሣልፎ ሠጥቷል፡፡ ሻዕቢያ ኢትዮጵያ ውስጥ ሠፊ የስለላ መዋቅር ነበረው፡፡ በእርስ በርሱ ጦርነት ጊዜ ጉዳት አድርሰውብኛል የሚላቸውን ኢትዮጵያዊያንን በጠራራ ፀሐይ አፍኖ በመውሠድ የት እንዳደረሣቸው እስካሁን አይታወቅም፡፡ እነዚህን በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ተቃዋሚዎቹን ያፍንና ይገድል ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የሚደርሠው ከባድ ጉዳት የሚሠማቸው ወገኖች ቅሬታ ሲጠናከርና በሻዕቢያ ላይ ቁጥጥር እንዲደረግ የሚጠይቅ ግፊት ሲያይል ይባስ ብሎ ሻዕቢያ ፍላጐቱን በኃይል ለማስፈፀም የሚያስችል ዝግጅት ማድረጉን ተያያዘው፡፡ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት የሚያካትት ካርታ በሻዕቢያ ተዘጋጅቶ ይፋ ሆነ፡፡ ሻዕቢያ የራሱን የገንዘብ ኖት ለማሣተም ሲወስን ኢትዮጵያ የብር ኖት ለውጥ ማድረጓን አምርሮ ተቃወመ፡፡ በአስመራ፣ ምፅዋና አሠብ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እንደፈለጉ እንዳይንቀሣቀሱ ተከለከሉ፡፡ አደገኛ ቦዘኔ እየተባሉ ይታፈሱና እስር ቤት ይታጐሩ ነበር፡፡ በሻዕቢያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚሰራጨው ወሬ የኤርትራን ወታደርና ሲቪል ለጦርነት እንዲዘጋጅ የሚያሣስብ ነበር፡፡ በድንበር አካባቢ የሚያደርገው ትንኮሳና እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን ለመውረር እንደሚፈልግ የሚያመለክት ነበር፡፡ በድንበር አካባቢ የሚኖሩ የትግራይ ገበሬዎችና የአፋር አርብቶ አደሮች የሻዕብያን የወረራ ዝግጅት የሚመለከት ማሳሠቢያ ቢያቀርቡም የሚሠማቸው ጠፋ፡፡ የኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች ይኸንኑ ስጋት በመረጃ እያስደገፉ ለንባብ ቢያበቁም ጦርነት ናፋቂዎች እየተባሉ በመንግሥት ተወገዙ፡፡ ሻዕቢያ ባድመን ለመውረር በሚገሰግስበት ጊዜ በወቅቱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሚ/ር የነበሩት ሰው በፓርላማው ፊት ቀርበው የኢትዮጵያ ጦር ማንኛውንም የውጭ ጥቃት ለመመከት የሚያስችል ጠንካራ ቁመና እንዳለው ሪፖርት አደረጉ፡፡ በሠራዊቱ ዝግጁነት ምክንያት ኢትዮጵያን የሚደፍር ምድራዊ ኃይል የለም እያሉ ለፓርላማው ቢደሰኩሩም እውነቱ ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ ተከሰተ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከኤርትራ ወረራ ሊመጣ ይችላል በሚል ስትራቴጅያዊና ታክቲካዊ ዝግጅት በማድረግ ፋንታ የሻዕቢያን ወረራ የሚያደፋፍር እርምጃ ይወሠድ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት መካከል የአስመራ አየር ኃይል ደብረ ዘይት በሚገኘው የኢትዮጵያ አየር ኃይል እንዲሠለጥን የተደረገበት ሁኔታ አንደኛው ነው፡፡ ከሥልጠናው በተጨማሪ የአየር ኃይሉን የዳታ ቤዝ ጨምሮ የደህንነትና







ወታደራዊ ተቋሞችን የሚመለከት መረጃ ለሻዕቢያ ክፍት ሆኖ ተሠጠው፡፡ ደርግ ያቋቋማቸው የመከላከያ ኢንዱስትሪ ተቋሞች ስትራቴጅያዊ ጥቅም ሣይጠና እንዲፈራርሱ ተደረገ፡፡ ሀገሪቱ ከ50 ዓመታት በላይ የገነባቸው የመከላከያ ሠራዊት ሙሉ በሙሉ እንዲበተን ተወስኖ ለሽምቅ ውጊያ ሲያገለግል በነበረው የገበሬ ታጣቂ ተተካ፡፡ የሻዕቢያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ድንበር በሚጠጋበት ጊዜ እንቅስቃሴውን የሚገታ ኃይል የኢትዮጵያ መንግሥት በአካባቢው አላሠፈረም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሻዕቢያ ጦር የተፈጠረለትን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ኢትዮጵያን በቀላሉ ወረረ፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ደግሞ ከወረራው በኋላ ሀፍረታቸውን ሸጠው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የወረራ መርዶ ይዘው ቀረቡ፡፡ ሣናስበውና ሣንዘጋጅ ሻዕቢያ ከጀርባችን ወጋን እያሉ የአዞ እንባ ማንባት ጀመሩ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሻዕቢያን ወረራ መታገስ አልፈለገም፡፡ በከፍተኛ ቁጭትና እልህ ተነሣስቶ ወረራውን ለመቀልበስ ተንቀሣቀሰ፡፡ የሕዝቡ ቁጣና የአፀፋ መልስ ማንም ከጠበቀው በላይ ቢሆንም በኢትዮጵያ መንግሥት ግድየለሽነት የሻዕቢያ ጦር ቁልፍ የሆኑ ወታደራዊ ቦታዎችን አስቀድሞ በመቆጣጠሩና ጠንካራ የመከላከያ ምሽጐችን ለመገንባት በቂ ጊዜ አግኝቶ ስለነበር ኢትዮጵያ ውድ መስዋዕትነት ለመክፈል ተገደደች፡፡ ከሻዕቢያ ጋር በተደረገው የ30 ዓመታት ጦርነት ከደረሠው ኪሣራ የማያንስ መስዋዕትነት በ2 ዓመታቱ ጦርነት ከፈለች፡፡ ወደ 70ሺህ የሚጠጉ ዜጐች በጦርነቱ ሞቱ፡፡ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች ተፈናቀሉ፡፡ በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሃብትና ንብረት ጠፋ፡፡ ከዚህ ሁሉ መስዋዕትነት በኋላ ወረራው ተቀለበሠ፡፡ ኢትዮጵያ በጦርነት አሸንፋ ሉዓላዊነቷን አስመለሠች፡፡ ይሁን እንጂ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በሚገዛው ሀገርና ሕዝብ ላይ ሌላ ክህደት መፈፀሙን ቀጠለበት፡፡

በቅድሚያ የሻዕቢያን ወረራ ለመደምሰስ በተደረገው የአጭር ጊዜ ዝግጅት ኢትዮጵያ በቂ የሰው፣ የመሣሪያና የድርጅት አቅም መገንባት በመቻሏ የሻዕቢያን ጦር በማያዳግም ሁኔታ ለመምታት የሚያስችል ሠፊ እንቅስቃሴ እንደጀመረች ጠቅላይ ሚንስትሩ ጦርነቱ በ24 ሰዓታት እንዲቆም ያልታሠበ ትዕዛዝ ሠጡ፡፡ ባልተጠበቀ ሁኔታ ጦርነቱ በመቆሙ ኢትዮጵያ ከሻዕቢያ በኩል ሌላ ስጋት እንዳይፈጠርባት ዋስትና ሊሠጥ የሚችል ስትራቴጅያዊ ድል ሣትጨብጥ የተከፈለውን መስዋዕትነት ዋጋ የሚያሣጣ ጥቃት በራሷ መንግሥት ተፈፀመባት፡፡ የጦርነቱን መቆም ተከትሎ ከሻዕቢያ ጋር በአልጀርስ የተፈረመው ስምምነት ደግሞ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሣልፎ የሚሠጥ ሆነ፡፡

የአልጀርሱ ስምምነት የተመሠረተው ሞተው በተቀበሩ የቅኝ ግዛት

ውሎች ላይ መሆኑ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሣልፎ መስጠቱ ብቻ ሣይሆን ለወደፊት ሕልውናዋም አደጋ የሚጋብዝ ነው፡፡ የአልጀርሱ ስምምነት ምሰሶ ተደርገው የተወሠዱት እ.ኤ.አ በ1900፣ 1902 እና 1908 ኢጣሊያና ኢትዮጵያ የተፈራረሟቸው ውሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ውሎች ሁለቱ አገሮች በእቻነት የተፈራረሟቸው አልነበሩም፡፡ ኢጣሊያ በወቅቱ በኢትዮጵያ ላይ ተፅእኖ የማድረግ አቅም ነበራት፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ የኢጣሊያን ተፅእኖ ብቻ ሣይሆን ከሌሎች የውጭ ኃይሎች የሚቃጣባትን ጥቃት ሁሉ ለመመከት የተገደደችበት ወቅት ላይ ስለነበረች እነዚህ ውሎች ወዳ የፈረመቻቸው ውሎች ነበሩ የሚባሉ አይደሉም፡፡ እኩል የመደራደር አቅም ባልነበራቸው መንግሥታት መካከል በተፅእኖ የተደረጉ ስምምነቶች ደግሞ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ውድቅ ናቸው፡፡ ኢጣሊያ እ.ኤ.አ በ1935 በመላው ኢትዮጵያ የእብሪት ወረራ አድርጋ ኤርትራንና ኢትየጵያን አንድ ላይ በመጠቅለል በቁጥጥር ስር በማድረጓ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ጋር ያካሄደቻቸው ስምምነቶች ሙሉ ሙሉ ፈርሠዋል፡፡ ኢጣሊያ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ከተሸነፈች በኋላ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት ቀርቦ በፌደሬሽን እንዲዋሃዱ በሚወሠንበት ጊዜ የቀድሞዎቹ ስምምነቶች ውድቅ ሆነዋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጠው የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐት የሚያጣራ ኮሚሽን አቋቁሞና ኮሚሽኑም በኤርትራ ተገኝቶ የሕዝቡ ውሣኔ ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ መኖር እንደሆነ ካረጋገጠ በኋላ ያቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ ነው፡፡ የኢትዮጵያና ኤርትራ በፌደሬሽን እንዲተሣሠሩ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከመወሰኑ በፊት የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ተለይቶ የራሱን ነጻ መንግሥት ለመመስረት ከፈለገ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ሙሉ በሙሉ መከበር እንዳለበት በወቅቱ ኃያላን በሚባሉት የምዕራብ ሀገሮች (ኢጣሊያን ጨምሮ) መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡

ስለዚህ የአልጀርሱ ስምምነት ኢትዮጵያና ኢጣሊያ በ1900፣ በ1902ና በ1908 ባደረጉት ስምምነት ላይ ተመስርቶ መካሄዱ ሻዕቢያ ካደረገው ወረራ የበለጠ በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመ በደል ነው፡፡ በደሉን ከፍተኛ የሚያደርገው ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ማንም ሣያስገድደው ራሱ የፈፀመውና በጦርነት ለተሸነፈው ሻዕቢያ የተሠጠ ሽልማት መሆኑ ነው፡፡ ምንአልባት ከፌደረሽኑ መፍረስ በኋላ በተከሠቱት አዳዲስ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የተደረገ ነው እንዳይባል በአልጀርሱ ስምምነት ሠነድ ውስጥ ይኸንን በግልጽ የሚያሣይ ነገር የለም፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ.ኤ.አ በ1964 ያፀደቀው ሠነድ የስምምነቱ መነሻ ሆኖ ይጠቀስ ነበር፡፡ በ1964 የካይሮው ውሣኔ ላይ ቢመሠረት ደግሞ የመጨረሻው ቅኝ ገዥ





መንግሥት የደርግ መንግሥት ተደርጐ ስለሚወሠድና ኤርትራ ነጻ በወጣችበት ጊዜ የነበረው የአስተዳደር ወሠን መጠበቅ ስለሚገባው የአሠብ ራስ ገዝ ወደ ኤርትራ የሚጠቀለልበት ምክንያት አልነበረም፡፡ ከዚህም ውጪ ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸናፊ እንደመሆኗ ጥቅሞቿን ሙሉ በሙሉ ለማስከበር የሚያስችል የድርድር አቅም ስለነበራት ችግሩ የዘለቄታ መፍትሔ የሚያገኝበትን አማራጭ ለማቅረብ የተሻለ ዕድል ነበራት፡፡ የድንበሩ ጉዳይ በአዲስ መልክ ተጀምሮ ድርድር እንዲደረግበት ሃሣብ ማቅረብም ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ የታሪክ፣ የሕግና የዲፕሎማሲ አማራጮች እያሉ ለሉዓላዊነቷ የሚቆረቆር መንግሥት በማጣቷ ትልቅ ክህደት ተፈጽሞባታል፡፡

# 3. ቅንጅት ትኩረት የሚሰጥባቸው ጉዳዮች (አማራጭ መፍትሄዎች)

በሀገራችን ዲሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሠላምና ዘላቂ ልማት እንዲኖር ገዥው ፓርቲ የሚከተለውን የተሣሣተ አቅጣጫ ለመቀየር የሚያስችሉ የለውጥ እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ መውሰድ ቅንጅት ትኩረት የሚሠጠው ተግባር ነው፡፡ ለውጥ ከሚደረግባቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

## *3.1 ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ ማድረግ*

አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት የሕዝቡ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች የሚቻቻሉበት ማዕቀፍ ሆኖ ባለመዘጋጀቱ የሕገ መንግሥቱ ገዥ ሃሣብ የአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለማዊ እምነትና የፖለቲካ ፕሮግራም የሆነበት አደጋ ተከስቷል፡፡ በመሆኑም ሕገ-መንግሥቱን ከዚህ አደጋ በማውጣት ፓርቲዎች ወደ መንግሥት ሥልጣን በወጡና ከሥልጣን በወረዱ ቁጥር በማይቀያየርበትና በተነጻጻሪነት ረዘም ላለ ጊዜ በጥቅም ላይ በሚውልበት አኳኋን ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 9 ስለሕገ መንግሥቱ የበላይነት የተደነገገውን በመጣስ የወጡና ሥራ ላይ የዋሉ አዋጆች ይሠረዛሉ፡፡

በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት ክፍል አንድ ስር ከተዘረዘሩት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች መካከል ከአንቀጽ 18 እና 25 በስተቀር ሌሎቹ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ ሥልጣን በሚሠጠው አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) መሠረት ሊታገዱ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ሠብዓዊ መብቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚሠጡና የሚነፈጉ ባለመሆናቸው አንቀጽ 93 ማሻሻያ ይደረግበታል፡፡

በዚሁ ምዕራፍ ክፍል ሁለት ስር ከተዘረዘሩት ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከል ከአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በስተቀር ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች በአንቀጽ 93 ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በተደነገገ ሥልጣን እንደሚታገዱ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በአንቀጽ 29 የተደነገገው የአመለካከት እና ሃሣብን በነጻ የማራመድ፣ የመግለጽና የመሣሠሉት ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሠበብ የሚከለከሉበት ሥርዓት







ከባድ የመብት ጥሰት እንዲፈጠር በር የሚከፍት በመሆኑ አንቀጽ 93 ይሻሻላል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት በሚል የሠፈረው ድንጋጌ የሕዝብን መብት በተሟላ መንገድ እንዲያስከብር ሆኖ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ለመገንጠል የሚፈልጉትን መብት በማክበር አንድነትን ለሚፈልጉት ግን መብታቸውን የማያከብር ነው፡፡

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት መከበር አለበት የሚለው አመለካከት የአብዮታዊ ዴሞክራቶች እምነት እንጅ የሀገሪቱን ዜጐች ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች ለማቻቻል የሚጠቅም መርህ አይደለም፡፡ ስለሆነም ልዩነትን ለሚፈልጉት ብቻ ሣይሆን አንድነትን ለሚፈልጉትም መብታቸውን የሚያከብር ሠፊ ማዕቀፍ መኖር ስለሚገባው የዜጐች በግልም ሆነ በቡድን የራሣቸውን ዕድል በራሣቸው የመወሠን መብት እንዳላቸው በሚያረጋግጥ መንገድ ይሻሻላል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች የዜጐች የንብረት ባለቤትነት መብትን የሚቀናንሱና እርስ በርስ የሚቃረኑ በመሆናቸው ማሻሻያ ይደረግባቸዋል፡፡ በተለይም በንዑስ አንቀጽ 3 የሠፈረው ድንጋጌ የገጠር የእርሻ መሬትም ሆነ የከተማ መሬት በግል፣ በመንግሥትና በወል እንዲያዝ፣ የሚሸጥና የሚለወጥ እንዲሆን በሚያስችል መንገድ ይሻሻላል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ አራት አንቀጽ 46 የፌደራል ክልሎች የሚዋቀሩበት መስፈርት የሀገሪቱን ሕዝብ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች በሚያቻችሉ መስፈርቶች መሠረት ይስተካከላል፡፡ በዚህም መሠረት የፌደራሉ ክልሎች የሕዝብን ፈቃደኝነት፣ ታሪካዊና ባህላዊ ትስስርን፣ ቋንቋን፣ የሕዝብን አሠፋፈርና የመልክዓ ምድር አቀማመጥን፣ የልማት አመቺነትንና የአስተዳደር ቅልጥፍናን የመሣሠሉትን መመዘኛዎች ባገናዘበ መንገድ ይዋቀራሉ፡፡

በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነት የተደነገገው ሕግ አሻሚ ባልሆነ አገላለጽ ለፌደራሉ ምክር ቤት ይሆናል በሚል ይሻሻላል፡፡

በምዕራፍ አምስት የሥልጣን አወቃቀርና ክፍፍልን በሚመለከት በአንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 2 የፌደራሉ መንግሥትና የራስ በራስ አስተዳደር ክልሎች በሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና በዳኝነት ሥልጣን የተከፋፈለ ብቻ ሣይሆን የእርስ በርስ ቁጥጥርና ተመጣጣኝ የሥልጣን ሚዛን እንዲኖር በሚያስችል አግባብ ይሻሻላል፡፡

በምዕራፍ ስድስት አንቀጽ 53 የፌደራል መንግሥት ባለ ሁለት ምክር ቤቶች እንደሚሆን የሚገልፀው ድንጋጌ ሁለቱም ምክር ቤቶች ሕግ በማውጣት ረገድ እኩል ወይም ተመጣጣኝ ሥልጣን እንዲኖራቸው በሚያስችል መንገድ ይሻሻላል፡፡

የሕግ አውጪው ሥልጣን የሕዝቡን ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች በማቻቻል በሚያግዝ ደረጃ ትርጉም ያለውና የአስፈጻሚውንም ጣልቃ ገብነት ለመቆጣጠር የሚያስችል ብቃት እንዲኖረው፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ ክልልና የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተጠሪነት ለምክር ቤቱ እንዲሆን ተደርጐ ይሻሻላል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ክፍል አንድ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የመራጩን ሕዝብ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች የሚወክሉ እንደራሲዎች ወደ ፓርላማ እንዳይገቡ ስለሚያደርግ፣ የመራጩ ሕዝብ ድምጽ እኩል ዋጋ እንዲኖረው ስለማያስችልና ብዙ ድምፅ ዋጋ አልባ ስለሚያደርግ፣ ሠፊ ማህበራዊ መሠረትና ጠንካራ የሕዝብ ድጋፍ ያለው መንግሥት ለመመስረት ስለማያስችል እነዚህን ችግሮች ከመሠረቱ በሚያሰወገድ “የተመጣጣኝ ውክልና ምርጫ ሥርዓት” እንዲተካ ይደረጋል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 18 የሠፈረው ድንጋጌ ግልጽነት ስለሚጐድለው የሕግ አስፈጻሚው በሕግ የተሠጠውን ሥልጣን ያለ አግባቡ ተጠቅሞ ሲገኝ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲበተንና በአዲስ መልክ እንዲዋቀር ማድረግ፣ ጥፋቱ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሌላ ካቢኔ አባል ከሆነ ከሥልጣን ወርደው በሕግ እንዲከሠሱ መወሠን፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤትና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የትምምን ድምፅ (Vote Of Confidence) መስጠት የሚያስችለው ሥልጣን እንዲኖረው ሆኖ ይሻሻላል፡፡

በዚሁ ምዕራፍ ክፍል ሁለት በአንቀጽ 61 ስለፌደሬሽን ምክር ቤት አባላትና በአንቀጽ 62 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 9 ስለፌደሬሽን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ይህ ምክር ቤት





ከሕዝብ ተወካዮች ጋር ተመጣጣኝ ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዲኖረው በሚያስችል መንገድ ይሻሻላል፡፡ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያለው ምክር ቤት ከሆነ ደግሞ ሕገ መንግሥት የመተርጐም ሥልጣን የዚህ ምክር ቤት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሌላ መቆጣጠሪያና መከላከያ ሥርዓት ከሌለ ራሱ ሕገ መንግሥቱን የሚጻረር ሕግ የሚያወጣበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ ሕገ መንግሥት የመተርጐም ሥልጣን ራሱን ችሎ በሚቋቋም የሕገ መንግሥት ጉባዔ እንዲሆን በሚያስችል መንገድ ይሻሻላል፡፡ የሕገ መንግሥት ጉባዔ አመሠራረት የሕዝብን ውክልና፣ የሙያ ብቃትንና ገለልተኛነትን መሠረት ባደረገ መንገድ እንዲፈፀም የሚያስችል ድንጋጌ ይኖራል፡፡

የፌደራሉና የራስ በራስ አስተዳደር ክልሎች መንግሥት ምክር ቤቶች የሚመርጧቸው አፈጉባዔዎችና ምክትል አፈጉባዔዎች ኃላፊነታቸውን በገለልተኝነት እንዲፈጽሙ የሚያስችል ሕጋዊ ግዴታ ይደነገጋል፡፡

በምዕራፍ ሠባት አንቀጽ 71 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 ስለፕሬዝዳንቱ የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት በአንቀጽ 69 ከተደነገገው የርዕሰ ብሔርነት ሥልጣን ጋር የሚመጣጠኑ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ፕሬዝዳንቱ የሀገሪቱ ሕዝብ አንድነት ተምሳሌት ሆኖ በገለልተኝነት እንዲሠራ፣ ግጭቶችን በማስወገድና ሰብዓዊ ተግባሮችን በማስተባበር ተገቢ ሥልጣን እንዲኖረው በሚያስችል ድንጋጌ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡

በምዕራፍ ስምንት አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ዘመን ከተደነገገው በተጨማሪ ስለፕሬዝዳንቱ ሥልጣን እንደተደነገገው ሁሉ አንድ ሠው በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ሊመረጥ እንደማይችል በሚደነግግ የሕግ ሥርዓት ይሻሻላል፡፡

በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 74 ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በአንቀጽ 77 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር የሕግ አውጪውንና የሕግ ተርጓሚውን ሥልጣን በማይሻማ መንገድ እንደገና ይሻሻላል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የትምምን ድምጽ የመስጠት ሥልጣን እንዲኖረው ሆኖ ይሻሻላል፡፡

በምዕራፍ ዘጠኝ አንቀጽ 81 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 6 ድረስ ስለፌደራሉና የራስ አስተዳደር ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ክልል ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶችና ዳኞች አሿሿም የሠፈሩት ድንጋጌዎች የሕግ አውጪ አካላትን ሥልጣን በሚያረጋግጡና የሕግ

አስፈጻሚ አካላትን ጣልቃ ገብነት በሚያስቀር የሕግ አግባብ ይሻሻላሉ።

በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 82 ስለ ሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ አወቃቀር የተገለፀው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በሕገ መንግሥት ጉባዔ ማቋቋሚያ የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲጠቃለል ሆኖ ይሻሻላል። በአንቀጽ 83 እና አንቀጽ 84 ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጐም የፌደሬሽን ምክር ቤትና የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ በሕገ መንግሥት ጉዳይ ላይ ስለሚወስኑበትና ስለ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር የሠፈረው ድንጋጌ በተመሣሣይ መንገድ በሕገ መንግሥት ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ እንዲካተት ሆኖ ይሻሻላል።

በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ አስር አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለመከላከያ ሠራዊት ተግባር የተገለፀው ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የዜጐች ሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዳይጣስ የሚከላከል ሕጋዊ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ ይሻሻላል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለፀው ድንጋጌ የመከላከያ ሠራዊቱን፣ ፖሊስና ደህንነትን ገለልተኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የሕግ ግዴታ እንዲኖር ሆኖ ይሻሻላል። በምዕራፍ አስራ አንድ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 4 በፊደል የተገለፀው ድንጋጌ ገደብ እንደማይጣልባቸው ከጠቀሳቸው አንቀጾች የበለጠ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለአደጋ በመጋለጣቸው ለእነዚህ ጥበቃ ማድረግ በሚያስችል ሕጋዊ ድንጋጌ ይሻሻላል።

በተጠቀሠው ምዕራፍ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥራውን በገለልተኛነት የሚያካሂድ ከማንኛውም ተፅእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስለማቋቋምና ስለቦርዱ አባላት አሿሿም የተገለፁት ድንጋጌዎች የቦርዱን ገለልተኛነትና ነጻነት በሚያረጋግጥ የሕግ አግባብ ይሻሻላሉ።

የምርጫ ክልል አከላለል ከሕዝብ ቆጠራ ውጤት፣ ከመራጩ ሕዝብና ከተወዳዳሪ ፓርቲዎች መብት ጋር የተሣሠረ፣ ሠፊ ጥናትና ገለልተኛ አሠራር የሚጠይቅ ከፍተኛ ተግባር በመሆኑ ተጠሪነቱ ለሕግ አውጭው አካል የሆነ፣ ራሱን ችሎ የሚደራጅና ከማንኛውም ተፅእኖ ነጻ በሆነ የሕግ አግባብ የሚሠራ አካል እንዲሆን ይደረጋል።

ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል በአንቀጽ 104 እና 105 የሠፈሩት ድንጋጌዎች ፍጹም አሣሪ፣ አሻሚና ግልጽነት የጐደላቸው በመሆናቸው ይኸንን ችግር በሚያቃልል የሕግ ድንጋጌ ይሻሻላሉ።





## *3.2 የኢኮኖሚ ተሃድሶ ማድረግ*

በኢሕአዴግ የሥልጣን ዘመን ሥራ ላይ የዋለው "ገጠርን ማዕከል ያደረገ ግብርና መር ኢንዱስትሪ (ADLI)" የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጅ በተግባር ተፈትሾ ያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ለውጥና የኑሮ መሻሻል ባለመኖሩ አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጅ መከተል የግድ ነው። በመሆኑም ቅንጅት የሚያምንበት የልማት ፖሊሲ የእስካሁኑን ድክመት የማይደግምና ለሀገራችን መሠረታዊ የልማት ችግሮች ተገቢ መፍትሔ የሚሆን፣ ለሁሉም ክፍለ ኤኮኖሚዎች የተቀናጀ ዕድገት ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሠጥና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ ዋልታና ማገር ሆኖ መቆም ከሚገባው ሕዝብ የሚገኘውን ልዩ ልዩ ዓይነት ግብዓት በሠፊው የሚጠቀም ፖሊሲ ነው። ከዚህ መሠረተ ሃሣብ በመነሣት በሚከተሉት የኤኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች ተጨባጭ ለውጥና ተሃድሶ ለማድረግ ቅንጅት በርትቶ ይሠራል።

### 3.2.1 የገጠር ልማት

በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል የኢኮኖሚ ለውጥና ተሃድሶ እንዲኖር በቅድሚያ የገበሬው የመሬት ሕጋዊ ባለቤትነት መረጋገጥ አለበት። ገዥው ፓርቲ መሬትን በመንግሥት ባለቤትነት ስር እንዲቆይ በሚያደርግ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ በማሠር የገበሬውን መብት የገደበበትና የመሬትን ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ዋጋ ቢስ ያደረገበት ሥርዓት እንዲለወጥ ማድረግ የቅንጅት ቀዳሚ ተግባር ነው። በዚህ ምትክ መሬት በግል፣ በወልና በመንግሥት ይዞታ ሥር እንዲሆንና የይዞታ አወሣሠኑም በመሬት አጠቃቀም ረገድ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች ያሉትን ታሪካዊ፣ ባህላዊና መዋቅራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ ይደረጋል። በግለሰብ ይዞታ ስር የሚሆነውን መሬት ባለቤት የሆነው ገበሬ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣ ለማውረስና እንደሚፈልገው አድርጐ ለመጠቀም ያልተገደበ መብት እንዲኖረው የሚፈቅድ ሕጋዊ ዋስትና ይሠጠዋል።

የግብርናው ዘርፍ ብቻውን ለማደግና ለሌሎች የኤኮኖሚ ዘርፎች ጋር ቅንጅት መፍጠር እንዲችል ይደረጋል። በገጠር የእደ ጥበብ ሥራዎችንና አግሮ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት፣ በገጠሩ ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች የኢንዱስትሪ ማዕከላት በማድረግ በእርሻ ሥራ የተሠማራው ሕዝብ ቁጥር እንዲቀንስ ይደረጋል። ይህ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የግብርና ምርት ተፈላጊነት ስለሚጨምር የዋጋ መሻሻልና የገቢ ማደግ ይፈጠራል። በገጠር የዕደ ጥበብና የኢንዱስትሪ መስፋፋት የተለያየ የግብርና ምርት ፍላጐት

እንዲኖር ስለሚያግዝ ገበሬው የእህል ምርት በማምረት ብቻ ሣይወሠን የተሻለ ዋጋ የሚያወጡ ልዩ ልዩ ዓይነት ምርቶችን (production Diversfication) ለማምረት ይደፋፈራል፡፡ በዚህ መንገድ የሀገሪቱ ግብርና መዋቅራዊ ሽግግር ይፋጠናል፡፡ በዚህም የገጠሩ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል፣ የጠቅላላው ኢኮኖሚ ዕድገት ዘላቂነትና አስተማማኝነት ይረጋገጣል፡፡

የግብርናውን ምርታማነት በዘላቂነት ለማሣደግ የመሬትንና የጉልበትን ምርታማነት በማያቋርጥ ሁኔታ ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ቅንጅት ያምናል፡፡ በመሆኑም በግብርና መስክ የተሠማራውን ሕዝብ ጤንነትና እውቀት የሚያሻሻሉ ሁለገብ ጥረቶች በሠፊው ይደረጋሉ፡፡ በዚህም መሠረት ቅንጅት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል የጤና ሽፋን 80% እንዲሆን፣ የንፁህ መጠጥ ውኃ ሽፋን 50% እንዲደርስ፣ የመፀዳጃ አገልግሎትም ወደ 20% እንዲያድግ ጥረት ያደርጋል፡፡

በገጠር የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን 85% እንዲደርስ፣ ማንበብና ማጻፍ የማይችሉ ዜጎች ቁጥር ከ20% በታች እንዲወርድና ከልዩ ልዩ የግብርና ቴክኒዎሎጂዎችና ግብዓቶች አጠቃቀም ጋር የተያየዙ ሥልጠናዎች በሠፊው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

የሀገራችን ግብርና ከዝናብ ጥገኝነት እንዲላቀቅና ዘላቂ የመሬት ምርታማነት እንዲረጋገጥ የሚያስችል፡፡ የውኃ ማጠራቀሚያ ግንባታና የመስኖ መሠረተ ልማት ሥራ በሠፊው ይካሄዳል፡፡ በተለይም ባለፈው መንግሥት ተጀምረው ከፍተኛ የሀገር ሃብት፣ ዕውቀትና ጉልበት ከፈሠሰባቸው በኂላ በኢህአዴግ አገዛዝ የተቋረጡት የአልዌሮ፣ ጣና በለስና ዋቢ ሸበሌ መስኖ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሠጡ ጥረት ይደረጋል፡፡ ከመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ ጐን ለጐን ተጨማሪ መሬት እንዲለማ በማድረግ አሁን ጥቅም ላይ ከዋለው መሬት ላይ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ወይም የአሁኑን የእርሻ መሬት 25% የሚያክል መጠን እንዲታረስ ጥረት ይደረጋል፡፡ በእነዚህና በመሣሠሉት ፕሮግራሞች በመታገዝ አብዛኛው ገበሬ አሁን ባለው ከግማሽ ሄክታር ያነሰ ይዞታ ላይ ቢያንሰ በዓመት 3 ጊዜ ቢያመርት የይዞታ መጠኑ ወደ 1 ተኩል ሄክታር ከፍ ይላል፡፡ በዚያው መጠን የመሬት ምርታማነት ለመጨመር ትኩረት የሚሠጠው ሌላ ጉዳይ የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የፀረ ተባይ መድኃኒት፣ የተሻሻለ የእርሻ መሣሪያ ቴክኒዎሎጂና የመሣሰሉት ግብዓቶች አቅርቦትና የግብርና ምርምር ተግባር ነው፡፡







በመሆኑም በማዳበሪያ አቅርቦት ያለውን ችግር ለማስወገድ የገዥው ፓርቲ ንግድ ድርጅቶች በብቸኝነት የያዙትን የሞኖፖል አሠራር በሕግ በማስቀረት የግል ባለሀብቶች በዘርፊ የሚያስችል የገበያ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እስከተወሠን ጊዜ ድረስ ሥርዓት ተግባራዊ ዋጋ ድጐማ አሠራር ተግባር ላይ ይውላል፡፡

የዘመናዊ እርሻ ግብዓቶች አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሻሻል በግብርና ምርምር፣ በገጠር ልማት ሠራተኞች፣ በግብዓት አቅራቢዎችና በገበሬዎች መካከል የተቀናጀ አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የግብዓት አቅርቦቱ ችግሮች ከማስወገድ ጐን ለጐን የገበሬው ምርት ጥሩ ዋጋ የሚያወጣበትን መንገድ መፍጠር ስለሚገባ በወቅታዊ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ የግብይት ሥርዓት፣ የምርት ብክነትን የሚቀንስ የምርት ማከማቻ፣ ጥራት ማሻሻያ ዘዴና ቀልጣፋ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ጥረት ይደረጋል፡፡ የሀገሪቱን 40% የቆዳ የአፈር ጥበቃ ሥራ በመስራት የመሬትን ለምነት የሚጨምር ጥረት ይደረጋል፡፡

በገጠር የተንሠራፋውን ድህነት በመቀነስ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዚህ ረገድ ትኩረት ከሚሠጣቸው ተግባሮች መካከል ፈጣን የሕዝብ ብዛት መጨመር በገጠር ያስከተለውን ጫና መቀነስ አንደኛው ነው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የተቀናጀ የሥነ ሕዝብና የሥነ ተዋልዶ ፕሮግራም ሥራ ላይ በማዋል አሁን ያለውን አማካይ የወሊድ ምጣኔ ከ6 ወደ 4 እንዲወርድና የሕዝብ ብዛት ዕድገት ከ2% እንዲያንስ ጥረት ይደረጋል፡፡

የገጠሩን ሕዝብ አሠፋፈርና ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ስርጭት ጋር የተጣጣመ ለማድረግ በበቂ ጥናት፣ ቅድመ ዝግጅትና በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሠፈራ ፕሮግራም ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የሠፈራው ፕሮግራም በዘመቻ ሣይሆን በእርጋታና አቅምን ባገናዘበ ሂደት፣ ከፖለቲካ ቅኝት ነጻ በሆነና በአስተዳደር ክልል በማይገደብበት ሁኔታ ይካሄዳል፡፡

የገጠሩን ልማት ለማፋጠን የሚረዳ የኢንቨስትሜንት ማደፋፈሪያና ተስማሚ የግብርና ብድር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትሜንት የሚያደፋፍር የብድር ፖሊሲ በማውጣት ከጠቅላላው የብድር ገንዘብና የኢንቨስትሜንት ፍሰት መካከል የግብርናው ድርሻ በዘላቂነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የገጠር ፋይናንስ ገበያ እንዲያድግ የመንግሥትና የግል ባንኮች የግብርናን ምርታማነትና ትርፋማነት ታሣቢ ባደረገ የገበያ አሠራር ከገበሬው ጋር ቀጥተኛ በሆነ የድርድር ግንኙነትና የሕግ ስምምነት እያደረጉ መስራት የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ገዥው ፓርቲ ባቋቋማቸው የአነስተኛ ቁጠባና ብድር ተቋማት ምትክ በገበያ ሥርዓት የሚገዙና በሕብረት ሥራ ማህበራት ወይም በግል ባለሃብቶች የሚንቀሣቀሱ የገጠር ቁጠባና ብድር አገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

ለገጠር ልማት መፋጠን የሚያግዙ የኤሌክትሪፊኬሽን፣ የመረጃና የመገናኛ መሠረተ ልማት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ በተለይም በገጠር ያለው የመንገድ ትስስር መረብ ለልማት በሚያመች መንገድ እንዲስፋፋ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል፡፡

ሀገሪቱ ያላትን የእንስሳት ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም የዘርፉን ምርታማነትና ተፈላጊነት የሚጨምሩ ስልቶች ተቀይሠው ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ በመሆኑም የተሻሻሉ ዝርያዎችን ማብዛት፣ የጤና አገልግሎቱን በመጠንም ሆነ በጥራት ማሣደግ፣ ለመኖ ልማት ትኩረት መስጠት፣ የእንስሳት ሃብት አያያዝ ዘዴን ማሻሻል፣ አመቺ የገበያ ሁኔታ መፍጠርና በዚህ መስክ ለሚሠማሩ ባለሃብቶች የማበረታቻ ድጋፎችን ማድረግ ቅድሚያ የሚሠጣቸው ስራዎች ይሆናሉ፡፡

ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ 12% እና ከጠቅላላው የእንስሳት ሃብታችን ውስጥ 26% ድርሻ ያለው አርብቶ አደሩ ሕብረተሠብ ሕይወት እንዲለወጥ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ የዚህ አካባቢ ዋነኛ ችግሮች ተደጋጋሚ ድርቅ፣ በውኃና ግጦሽ ችግር የሚመጣ የደህንነት ስጋትና ከዚሁ ሪሶርስ ሽሚያ ጋር በተያያዘ የሚከሠት ግጭት፣ የእንስሳት መኖና ጤንነት ችግር፣ የእንስሳት ገበያ ፍላጐት ማነስና የዋጋ ዝቅተኛነት ሲሆኑ እነዚህን ማስወገድ የሚያስችልና የተቀናጀ ጥረት ይደረጋል፡፡ የአርብቶ አደሩ አካባቢ ልማት በግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲያችን ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተት ሆኖ በመጠጥ ውኃ፣ የእንስሳትን ምርታማነትና ተፈላጊነት ለማሣደግ እንዲቻል በደንና በመስኖ ልማት ላይ የተመሠረተ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን፡፡ የአርብቶ አደሩን ሕዝብ የመንቀሣቀስ ነጻነትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት በሚያረጋግጥ መንገድ የሕዝቡን የግጭት አፈታት ዘዴ ለማሣደግና ወደ ተረጋጋ ሕይወት ለማሸጋገር







የሚያስችሉ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ የግል ባለሃብቶች በአርብቶ አደሩ አካባቢ ገብቶ በዘመናዊ እርባታ፣ በወተት፣ በሥጋና በቆዳ ምርትና ግብይት ሥራ እንዲሣተፉ በመደገፍ፣ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ለመዘርጋትና በአርብቶ አደሩ ሕዝብ ውስጥ ተጨባጭ የኑሮ ለውጥ ለመፍጠር ብርቱ ጥረት ይደረጋል፡፡

የገጠር ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ ተቋሞች በጥናት እንዲደራጁ በሠው ኃይልና በቴክኒክ አቅማቸው እንዲጐለብቱ፣ አደረጃጀታቸውና አሠራራቸው ልምድ ለማዳበር በሚያስችል ዘላቂነትና ተከታታይነት ላይ እንዲመሠረት፣ የገጠር ልማት ሠራተኞችን ሥልጠና፣ ዕድገትና ዝውውር ግልፅነትን በተከተለ የሕግ አግባብ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጅያችንን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገው የፋይናንስ ድጋፍ የሚመነጨው ከመንግሥት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋሞች፣ ከሕዝብና ከዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ እንደመሆኑ መጠኑና አይነቱ ከልማት ፍላጐታችን ጋር መጣጣሙና ዘላቂነቱም አስተማማኝ መሆኑን የሚያረጋግጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይቀየሣሉ፡፡

የገጠር ልማት ፖሊሲያችን ውጤታማ የሚሆነው ለዘርፉ በሚሠጠው የተናጠል ትኩረት ብቻ ሣይሆን ከሌሎች ክፍለ ኤኮኖሚዎች ጋር እንዲተሣሠርና እንዲደጋገፍ በሚደረገው የተቀናጀ ጥረት ነው፡፡ በመሆኑም የልማት ስትራቴጅያችን ለኢንዱስትሪና ለአገልግሎት ዘርፉም ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሠጥና አንዱ ለሌላው የጥሬ ዕቃ ምንጭ ብቻ ሣይሆን አስተማማኝ የገበያ ስፍራም እንዲሆን በማድረግ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የኤኮኖሚ ዘርፎች እንዲህ ዓይነት ትስስር በመፍጠር ጠቅላላ የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ዕድገት ፍጥነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፡፡

እነዚህን ሁሉ ተደጋጋፊ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎች በማድረግ በግብርናው ዘርፍ በየዓመቱ 7% ዕድገት ማስመዝገብ፣ የገበሬዎችን የሠብል ምርት መጠን በዓመት ከ240 ኪ.ግ. በላይ ማሣደግ፣ የነፍስ ወከፍ የካሎሪ መጠን በቀን 2200 እንዲሆን ማስቻልና በአጠቃላይ የገበሬውን የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ አሁን ከሚገኝበት በእጥፍ በማሣደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፡፡ ተጨባጭ የኑሮ መሻሻል እንዲፈጠር ጥረት ይደረጋል፡፡ የገጠር ልማት ፖሊሲያችንና ስትራቴጂያችን ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በተለያየ ደረጃ በጥልቀት እንዲወያይበትና እንዲመክርበት ይደረጋል፡፡

## 3.2.2 የከተማ ልማት

የሀገራችን ከተሞች እስከፊ ለሆነ ድህነት የተጋለጡ በመሆናቸው የከተማ ልማት ፖሊሲያችን ቅድሚያ ትኩረት ድህነትን መቀነስ ነው። በከተማ ውስጥ የተንሠራፋውን ድህነት ለመቀነስ የሚቻለው ለከተማው ነዋሪ ሕልውና ወሣኝ ድርሻ ያላቸውን የአነስተኛ ዕደጥበባት አደረጃጀት፣ አሠራርና ግብይት ችግሮች በመፍታት ነው።

የአነስተኛ ዕደ ጥበባት ዋነኛ ችግሮች የማምረቻ ቦታ፣ የብድርና የመሣሪያ አቅርቦት፣ የምርት መሸጫ፣ ምርታማነታቸውንና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሣደግ የሚያስችል ሥልጠና ዕጥረት ናቸው። በመሆኑም በመላ የሀገሪቱ ከተሞች ለዕደጥበባት ዕድገት አስፈላጊ የሆኑት እርምጃዎች ሁሉ ይወሰዳሉ።

በብረታ ብረት፣ በእንጨት ሥራ፣ በስፌት፣ በጌጣጌጥ፣ በሽመና፣ በአልባሣት ሥራና በመሣሠሉት የእደ ጥበብ መስክ ለሚሰማሩ ዜጐች በቂና ተስማሚ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ በቅድሚያ የሚዘጋጅበትና ጥያቄው በሚቀርብበት ጊዜ ካለውጣ ውረድ የሚያገኙበት ሥርዓት ይዘረጋል። የአነስተኛ ኢንዱስትሪ መንደሮችና ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት በቅድሚያ ተገንብተው በተመጣጣኝ ኪራይ አገልግሎት እንዲሠጡ ይደረጋል።

የአነስተኛና ዕደጥበብ ሥራዎች እንዲስፋፉ የሚያግዝ የብድርና የመሣሪያ አቅርቦት ሥርዓት ይመቻቻል። የብድር ሥርዓቱ በፕሮጀክት አዋጭነት ምዘና ላይ የተመሠረተና ግልጽነትን የተከተለ ሆኖ በግልና በመንግሥት የፋይናንስ ተቋሞች አማካይነት ይቀርባል።

በአነስተኛ ዕደጥበብ ኢንዱስትሪ ብድር በማቅረብ የፋይናንስ ድጋፍ የሚሠጡ የገንዘብ ተቋሞች ጠንካራ አደረጃጀትና ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖራቸው የሚያስችል የሕግ ሥርዓት ይመቻቻል። የመሣሪያ ኪራይ አገልግሎት በመስጠት ዕደጥበባት የሚያገጥማቸውን የማምረቻ መሣሪያ ዕጥረት የሚያቃልሉ ተቋሞች እንዲደራጁ ይደረጋል።

በአነስተኛ ዕደጥበብ ሥራ የተሠማሩ ዜጐች የሥልጠና ድጋፍ የሚያገኙበት ተቋማዊ አሠራር ይደራጃል። የሚያመርቱት ምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲኖረው የሚያግዝ መለያ የሚወጣበትና የጥራት ማረጋገጫ የሚሠጥበት ሥርዓት ይፈጠራል።





በከተሞች የሰፈነውን ድህነት ማስወገድ የሚቻለው የሥራ ዕድል የሚያስገኝ ተከታታይ የልማት ተግባር በማከናወን ነው። በከተሞች ውስጥ የሚሠሩ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ሥራ ያጡትን ዜጐች ጉልበት በሚገባ መጠቀም በሚችሉበት አግባብ ተግባራዊ ይሆናሉ። የትምህርት፣ የጤና፣ የመንገድና መገናኛ፣ የመብራት፣ የውኃ፣ የስፖርት ማዘውተሪያና መዝናኛ ማዕከላት፣ የጽዳትና የፍሣሽ ማስወገጃ ግንባታዎች ለዜጐች የሥራ ዕድል በሚያስገኙበት አቅጣጫ ይቃኛሉ። እነዚህንና የመሣሠሉትን ሁለገብ ጥረቶች በማቀናጀት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በከተሞቻችን አሁን ያለውን ከ40% የበለጠ የሥራ አጥ ቁጥር ከ20% በታች እንዲወርድ ይደረጋል። በሀገሪቱ ከተሞች ከሚኖረው ሕዝብ መካከል 40% አካባቢ ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ሲሆን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ይኸ ቁጥር በግማሽ እንዲቀንስ ይደረጋል።

በከተሞች ውስጥ አነስተኛ ዕደጥበባትና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በማስፋፋት ለዜጐች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ትምህርታቸውን ጨርሠው ወይንም በተለያየ ምክንያት አቋርጠው የቤተሠብ ጥገኛ ለሆኑ ወጣቶች፣ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለጐዳና ተዳዳሪዎች፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ ረዳቶቻቸውን ላጡና በሴተኛ አዳሪነት ለተሠማሩ ዜጐች ልዩ ትኩረት ይሠጣል።

በከተሞቻችን የሚታዩት የጽዳትና የአካባቢ ብክለት ችግሮች እንዲወገዱ የሚያስችል ዘላቂ መፍትሄ ይፈለጋል። የአካባቢ ብክለትን በመከላከልና ጽዳትን በመጠበቅ ረገድ ሕዝቡ ግንባር ቀደም ሆኖ እንዲንቀሣቀስ በሚያስችለው አግባብ የማደራጀትና የማስተማር ሥራ ይከናወናል። የከተማ አካባቢ ብክለትን በመከላከል ጽዱና ለጤናማ አኗኗር የተመቹ እንዲሆኑ የሚያግዝ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ይውላል።

የደረቅና ፈሣሽ ቆሻሻን የማስወገድ ሥራ የሕዝብና የመንግሥትን የተቀናጀ ጥረት መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መስክ የግል ባለሃብቶች ተሣትፎ መኖር ትልቅ ጥቅም ስላለው ይኸንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጋዊና ተቋማዊ እርምጃዎች ይወሠዳሉ።

የከተሞች ፍሣሽ ማስወገጃ ሥርዓት ብክለትን በሚከላከልና የአካባቢ ንጽህናን በሚጠብቅ አግባብ እንዲከናወን በዲዛይን፣ በግንባታና በጥገና ሥራ ያሉትን ችግሮች የሚያስወግዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ይወሠዳሉ። (ለምሣሌ ለሕዝብ ከሚቀርበው የመጠጥ ውኃ 1/3ኛው የተበከለ ነው)። ለዚህ ጥረት

ውጤታማነት በቂ የሠለጠነ የሠው ኃይል፣ ጠንካራ የቴክኒክና የቴክነዎሎጂ አቅም መፍጠር ቅድሚያ የሚሠጠው ሥራ ይሆናል፡፡

በከተሞች ውስጥ ያለው ትልቅ ችግር የመሠረተ ልማት ዕጥረት እንደመሆኑ ከከተሞች ማስተር ፕላን ጋር በሚጣጣም፣ የሕዝቡን ፍላጐት በሚያገናዝብና የሚመለከታቸውን ወገኖች ተሣትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ የመፍትሔ እርምጃዎች ይወሠዳሉ፡፡ በዚህም መሠረት በከተሞች የግልና የጋራ መጠቀሚያ የውኃ መስመር በአዲስ አበባ አሁን ካለበት 55.7% ወደ 85% እንዲያድግ፣ በሌሎች ትላልቅ የሀገሪቱ ከተሞች አሁን ከሚገኝበት 50% ወደ 80% ከፍ እንዲልና ከ15% በታች በሆነባቸው ሌሎች ከተሞች ወደ 45% እንዲደርስና የቧንቧ መስመር ጨርሶ በሌለባቸው ከተሞች ደግሞ 30% ለሚሆነው ሕዝብ የውኃ መስመር ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፡፡

የከተሞችን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ በማስፋፋት በአዲስ አበባ በአሁኑ ጊዜ ከመኪና መንገድ ጋር የተገናኙት ቤቶች 65% ብቻ የሆኑበትን ሁኔታ በማሻሻል በሚቀጥሉት 5 ዓመታት 90% የሚሆኑትን ቤቶች ከመኪና መንገድ ጋር ለማገናኘት፣ በሌሎቹ ከተሞች አሁን ያለውን በአማካይ ከ40-50% የቤቶችና የመንገድ ትስስር ወደ 80% ለማሣደግ፣ ከ10% በታች የቤቶችና የመኪና መንገድ ትስስር ባለባቸው የሀገሪቱ ከተሞች ደግሞ ወደ 40% ለማሣደግና ምንም ዓይነት ግንኙነት ባልተፈጠረባቸው ከተሞች 30% የቤቶችና የመኪና መንገድ ትስስር እንዲኖር ጥረት ይደረጋል፡፡ በከተሞች ውስጥ ያሉትን የመኪና መንገዶች አስፓልት ለማድረግ ተገቢው ጥረት ይደረጋል፡፡

የውኃ መተላለፊያ መስመር አገልግሎት በአዲስ አበባ 33% ሲሆን በሌሎቹ የሀገሪቱ ከተሞች ደግሞ ከ30% በታች በመሆኑ ችግሩ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ አገልግሎት መጠናከር ትኩረት ማግኘት ያለበት በመሆኑ በሁሉም የሀገሪቱ ከተሞች ያለውን የውኃ መተላለፊያ መስመር ግንባታ ወደ 60% ለማሣደግ ጥረት ይደረጋል፡፡

የፈሣሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት አለመጠናከሩ የከተሞች ትልቅ ችግር ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ከደረቅ ቆሻሻ ብቻ ተሰብስቦ የሚወገደው 65% የሚሆነው ብቻ ሲሆን በሌሎቹ ትላልቅ የሀገሪቱ ከተሞች ከ3% በታች የሚሆነው ብቻ ነው ተሠብስቦ የሚወገደው፡፡ በዚህ ዘርፍ የነዋሪውን፣ የግል ባለሃብቱንና የመንግሥትን አቅም አቀናጅቶ በማንቀሣቀስ





የደረቅ ቆሻሻን የማስወገድ አቅም ወደ 90% እንዲያድግ፣ የፍሣሽ ቆሻሻን የማስወገድ አቅም ደግሞ ወደ 50% ከፍ እንዲል ጥረት ይደረጋል፡፡

ከ1986 የሕዝብ ቆጠራ መረጃ መሠረት በሀገሪቱ ከተሞች ካሉት ቤቶች ውስጥ የመጸዳጃ አገልግሎት ያላቸው 28% ብቻ ናቸው፡፡ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት 60% የሚሆኑት የከተማ ቤቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የመጸዳጃ ቤቶችን ቆሻሻ የማስወገድ አገልግሎት በግል ባለሃብቶች ተሣትፎ እንዲታገዝ በማድረግ አብዛኞቹ የከተማ ነዋሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት በሚሠጥባቸው የሀገሪቱ ከተሞች ውስጥ የግልና የጋራ ቆጣሪ የሌላቸው ቤት ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ ጨርሶ የመብራት አልግሎት የማያገኙ ከተሞችም አሉ፡፡ ለከተሞች ሁለንተናዊ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ የሆነው የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲስፋፋ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ሲሆን ጨርሶ አገልግሎቱን ያላገኙ ከተሞች ትኩረት ይሠጣቸዋል፡፡

የከተሞችን የመገናኛና ትራንስፖርት አልግሎት ደረጃ በማሣደግ የከተሞች አገልግሎት እንዲቀላጠፍና ሁለገብ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ትኩረት ይሠጣል፡፡

በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ የከተማ ቤቶች ግንባታና አስተዳደር ፖሊሲ ባለመኖሩ በከተሞች ውስጥ የተፈጠረው የቤት ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሣሠበ ነው፡፡ በዚህ ላይ ፈጣን የሕዝብ ዕድገትና ወደከተማ የሚደረግ መጠነ ሠፊ የሕዝብ ፍልሠት ተጨምሮ ችግሩን አስከፊ አድርጎታል፡፡ ይኸንን ችግር ከመሠረቱ ለማስወገድ የሚያስችሉና እርስ በርስ የሚደጋገፉ እርምጃዎች ይወሠዳሉ፡፡ በዚህ ረገድ ቅድሚያ ከሚሠጣቸው ጉዳዮች መካከል፡-

- የግል ባለቤትነትን የሚፈቅድ የከተማ መሬት ፖሊሲ ላይ በመመስረት የከተሞች መሬት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና አከታተም ሥርዓት ይዘጋጃል፡፡
- በከተሞች ውስጥ የሚካሄዱ ግንባታዎችና የልማት ሥራዎች በጥናትና በሥርዓት እንዲከናወኑ ለማድረግ የመኖሪያ፣ የኢንዱስትሪ፣ የመዝናኛና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጫ አካባቢዎችን ለይተው የሚያሣዩ

የማስተር ፕላን፣ የዕድገት ፕላንና የተግባር ፕላን ሥራዎች ይከናወናሉ። የከተሞችን ፕላን በሀገር ደረጃ የሚያጠና፣ የሚያዘጋጅና ለተግባራዊነታቸው ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሠጥ ተቋም በሕግ ይደራጃል።

- የከተሞች ፕላን በሚፈቅደው መሠረት የግል መኖሪያ ቤት መገንባት ለሚፈልጉ ዜጎች ተመጣጣኝ የሆነ ግብር የመክፈል ግዴታቸውን እየተወጡ ቤት እንዲገነቡና መሬቱንም በግል ባለቤትነት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል።

- በሀገሪቱ ከተሞች ውስጥ የሚታየውን አስከፊ የመኖሪያ ቤት ችግር መፍታት የሚቻለው በመንግሥት ብቻ ሣይሆን የግለሰቦችን ጥረት በመደገፍ መሆኑን በማመን በራሣቸው አቅም ቤት የሚገነቡ ዜጎችን የሚያደፋፍር አሰራር ተግባራዊ ይሆናል።

- የመኖሪያ ቤቶችን ችግር በማባባስ ረገድ አሁን በሥራ ላይ ያለው የሽያጭ ታክስ፣ የቤትና የቦታ ግብር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው መጠኑ እንዲቀንስ ይደረጋል።

- የመኖሪያ ቤቶችን በብዛት ገንብተው ለመሸጥና ለማከራየት ለሚፈልጉ የግል ባለሃብቶች ከመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ተቋሞች ጋር ሕጋዊ ውለታ እየፈፀሙ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል። በሊዝ መሬት ላይ የተሠራን ቤትና ሌላም ግብዓት ከሊዝ መብቱ ጋር ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ የማስተላለፍ መብት እንዲኖራቸው ይደረጋል።

- በቤቶች ግንባታና አስተዳደር ለግለሠቦች ከተሠጠው መብት በተጨማሪ የቤቶች ሥራ ማህበራትና የከተማ አስተዳደሮች ሕጋዊ መብት እንዲኖራቸው ይደረጋል። በማህበር ተደራጅተው ቤት ለሚገነቡ ዜጎች የመሠረተ ልማት በመገንባት፣ የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠትና በአነስተኛ ወለድ ብድር እንዲያገኙ በማድረግ የከተማ አስተዳደሮች ድጋፍ የሚሠጡበት ሥርዓት ይደራጃል። የከተማ አስተዳደሮች በራሣቸው አቅም ቤቶችን እየገነቡ ለማከራየትና ለመሸጥ የሚችሉበት አሠራር ተግባራዊ ይሆናል።

- ለኢንዱስትሪና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚካሄዱ ግንባታዎች ለከተማው ሕዝብ እንደሚሠጡት ጠቀሜታ ግልጽ በሆነ መስፈርት እየተመዘኑ መሬት በነጻ ወይም አነስተኛ በሆነ የሊዝ ዋጋ የሚያገኙበት







ሥርዓት ይመቻቻል።

- በሊዝ ዋጋ መሬት ገዝተው ግንባታ ለማካሄድ አቅሙና ፍላጐቱ ላላቸው ግለሠቦችና ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ መሬት እንዲያገኙ ይደረጋል።

- ለከተማው ነዋሪ ልማት፣ ጤንነትና ኑሮ አመቺ ያልሆኑ አካባቢዎችን በተጠና ፕላን ለማደስና ለመቀየር ጥረት የሚደረግ ሲሆን ይህ ተግባር ነዋሪዎቹን በማሣመን፣ ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል፣ አማራጭ የመኖሪያ ሁኔታ በማመቻቸትና ድንገተኛ የሆነ መፈናቀልን በሚቀንስ አግባብ ይፈፀማል።

- በደርግና በወያኔ/ኢሕአዴግ ያለአግባብ የተወሠዱ ቤቶችን ለሕጋዊ ባለቤቶቹ ለማስመለስ ከሚቀርቡ ልዩ ልዩ አማራጮች መካከል ለአሁኖቹ ባለ ይዞታዎች በረጅም ጊዜ ክፍያ ተሸጠው ሕጋዊ ባለቤቶቹ ገንዘባቸውን ወይንም ሕጋዊ ካሣቸውን እንዲያገኙ ማድረግ አንደኛው ነው። በከተሞችና በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ተገንብተው የተከራዩትን ቤቶች ደግሞ ግልጽ በሆነ የሽያጭ ሥርዓት ቀስ በቀስ ለነዋሪዎች የማስተላለፍ እርምጃ ይወሠዳል።

- ለከተማ ቤቶች ግንባታ እንቅፋት የሆኑትን የግንባታ ዕቃዎች ዕጥረት ለማስወገድ በሲሚንቶ፣ በድንጋይ፣ በአብነ በረድ፣ በብረታ ብረትና በቆርቆሮ ምርት መንግሥትና የግል ባለሃብቶች ተደጋግፈው የሚሠሩበት ሁኔታ ይመቻቻል።

- እነዚህንና የመሣሠሉትን ተደጋጋፊ ጥረቶች በማድረግ ከ1997-2008 ዓ.ም. ድረስ በሀገሪቱ ከተሞች እንዲገነቡ ከሚያስፈልጉት 4 ሚሊዮን ተጨማሪ የመኖሪያ ቤቶች መካከል ግማሽ ያህሉን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ ዜጐች በግልና በማህበር እንዲሠሩ የሚያስፈልገው ድጋፍ ሁሉ ይደረጋል። ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሚያስፈልገው ወጪ ከግለሠቦች፣ ከቤቶች ግንባታ ማህበራት፣ ከመንግሥት፣ ከውጭ የልማት እርዳታና ብድር በሚገኝ ገንዘብ የሚሸፈን ይሆናል።

- በከተሞች ያሉትን የድህነትና የልማት ችግሮች በማስወገድ ፈጣን ዕድገት እንዲያስመዘግቡና ለኑሮ የሚመቹ እንዲሆኑ ማድረግ የሚቻለው ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተደራጀና የከተማ አገልግሎትን በተቀላጠፈ

መንገድ መምራት የሚችል አስተዳደር ሲኖር ነው። እንዲህ ዓይነት አስተዳደር ሲኖር ለከተሞች ልማት እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የሕዝብ፣ የተደራጁ የሲቪል ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ባለሃብቶች ተሣትፎ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል። ስለሆነም የሀገራችን ከተሞች አስተዳደር በሕዝብ ቀጥተኛ ተሣትፎ እንዲመሠረት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው የአሠራር ነጻነት፣ የአመራርና የሞያ ብቃት እንዲላበስ የሚያደርጉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

- የሀገሪቱ ከተሞች ቴክኒካዊ ሥራዎችና አገልግሎቶች በሙያተኞች ፣ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ደግሞ በሕዝብ ተወካዮች የሚመሩበት አደረጃጀት የሚፈጠር ሲሆን ቻርተርድ የሚሆኑ ከተሞች ተጠሪነት ለሕግ አውጭው አካል ይሆናል።

## 3.2.3 የኢንዱስትሪ ልማት

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ልማት ዓላማችን በሁሉም የኤኮኖሚ ክፍሎች መካከል ትስስር መፍጠር፣ መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣትና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ነው። የሀገራችንን ኢኮኖሚ አወቃቀርና አሠራር ችግሮች ከመሠረቱ በማስወገድ በጠንካራ ትስስርና ሚዛናዊ በሆነ ቅንጅት ላይ የተመሠረተ ፈጣን ዕድገት ለማምጣት ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የበለጠ ኃላፊነት የሚሸከም ክፍለ ኤኮኖሚ ሊኖር አይችልም። ለኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት መስጠት ያለብን ከፍተኛ ቴክኒዎሎጂ የሚጠቀም ፋብሪካ ለመገንባት ብቻ ሣይሆን ባህላዊና ኋላቀር የሆነው ግብርናችን፣ የማዕድን፣ የኮንስትራክሽን፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ኤኮኖሚያችን ወደ ዘመናዊ አደረጃጀትና አሠራር መሸጋገር እንዲችሉ ነው።

ለኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት የምንሠጠው ጠቅላላ ኤኮኖሚውን የማንቀሣቀስ ኃላፊነት የመሸከምና የተሣሰረ ዘላቂ ሽግግር የማምጣት ሚና ስላለው ነው። በመሆኑም ይኸንን ዘርፍ ማልማትና የኤኮኖሚው አንቀሣቃሽ ሞተር የማድረግ ተግባር እንደ አማራጭ ብቻ ሣይሆን እንደግዴታ የሚታይ ነው።

በኢንዱስትሪ ልማት የሚተኮርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፡-

- አሁን ያሉትን ኢንዱስትሪዎች የቴክኒዎሎጂ ይዞታና ምርታማነት በማሻሻል በሙሉ አቅማቸው መስራት ወደሚችሉበት ደረጃ ማሸጋገር፣







- የግብርናንና የገበሬውን ምርታማነት በማሣደግ፣ በገጠርና በከተማ ውስጥ ያለውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቀነስና የዜጎችን ገቢና የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት ማካሄድ፣

- ግብርናን ጨምሮ ሁሉንም የኢኮኖሚ መስኮች ለማዘመን፣ እርስ በርስ ለማስተሣሠርና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚችሉ የብረታ ብረት፣ እንጅነሪንግ፣ ኬሚካል፣ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ የመሣሠሉ ስትራቴጅያዊ ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት የሚያስችል ፖሊሲ መከተል፣

- ሀገራችን በውድ ዋጋ ከውጭ የምታስገባቸውን የካፒታልና የፍጆታ ዕቃዎች በመተካት የውጭ ምንዛሬ ለመቆጠብና ከዓለም አቀፍ ቀጥተኛ ተፅእኖ ደረጃ በደረጃ ለመላቀቅ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት እንዲፈጠር ትኩረት መስጠት፣

- በተፈጥሮ ሃብት ላይ የተመሠረቱ አግሮ ኢንዱስትሪዎችን የቴክኒዎሎጂ ደረጃ በማሻሻል የውጭ ምንዛሬ ግኝታችንን የማሣደግ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በፋብሪካ የተመረተ ኤክስፖርት በአይነት፣ በጥራትና በመጠን እንዲስፋፋ ማድረግ፣

- የፋብሪካውን ኤክስፖርት አይነት በማብዛትና ጥራቱን በማሣደግ ወደ ሀገር ውስጥ ለምናስገባው ዕቃና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን አቅሙ እንዲጠናከርና በኤክስፖርትና በኢምፖርት መካከል ያለውን ሠፊ ክፍተት መቀነስ፣

- የውጭ ምንዛሬ ግኝታችንን የሚያሣድጉና የውጭ ምንዛሬ ወጪያችንን የሚቆጥቡ፣ የኤክስፖርትና የካፒታል ምርት የሚያመርቱ የፋብሪከ ኢንዱስትሪዎች ከማልማት ጐን ለጐን ከግብርናው የሚገኘውን ጥሬ እቃም ሆነ ሠፊ ጉልበት በመጠቀም የተሻለ ጥራትና ተወዳዳሪነት ያለው የኤክስፖርት ምርት እንዲጠናከር ማድረግ፣

- የኢንዱስትሪ ልማታችን በጠቅላላው ኤኮኖሚ ውስጥ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ ብቻ የተወሠነ ሣይሆን በራሱ በኢንዱስትሪው ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል ተገቢው ቅንጅትና ሚዛናዊ እድገት እንዲኖር የሚያስችለው የፋብሪካ ዘርፍ ፈጣን እድገት እንዲያሣይ ትኩረት ይሠጥበታል።

በአጠቃላይ በሀገራችን ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ በአስተማማኝ

ሁኔታ ከድህነት ለመውጣት የኤኮኖሚው ዋነኛ አንቀሣቃሽ ሞተር፣ መሪ የመሆን ተልእኮና ኃላፊነት መሸከም የሚገባው የኢንዱስትሪው ዘርፍ ነው። ይኸንን መርህ መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሥራ ላይ የሚውል ሲሆን ስትራቴጂው ታሣቢ የሚያደርጋቸው አበይት ቁምነገሮች አሉ። እነዚህም፡-

- ስትራቴጂያችን በሁሉም ክፍለ ኤኮኖሚዎች መካከል ትስስር ከመፍጠር አልፎ ቴክኒዎሎጅያዊ ብቃትን፣ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን እንዲያረጋግጥ ይደረጋል።

- በከፍተኛ ደረጃ ዳይናሚክ በሆነ ተነጻጻሪ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ኢንዱስትሪ ለመፍጠር የቴክኒዎሎጂ አቅም ብቻ ሣይሆን ቴክኒካዊ እውቀት ያለው የሠለጠነ የሠው ኃይል ስለሚያስፈልግ ለዚህም ትኩረት ይሠጣል።

ውጤታማ ኢንዱስትሪያዊ ልማት የሚገኘው ተነጻጻሪ ጥቅምን፣ የፋይናንስና የሠው ኃይል አቅምን ባገናዘበ መንገድ በተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ላይ ተመስርቶ ሥርዓት ባለው ቅደም ተከተል መስራት ሲቻል በመሆኑ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፡-

ሀ. ለእርሻ ዘመናዊ የቴክኒክ ግብዓቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፣

ለ. ለጠቅላላው ኤኮኖሚ ወሣኝና አስፈላጊ የሆኑትን አላቂና የካፒታል እቃ ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች፣

ሐ. የኢምፖርት ዋጋን ለሚቀንሱና የኤክስፖርት ገቢን ለሚያሣድጉ ኢንዱስትሪዎች፣

መ. የተሻለ ብቃትና የፈጠራ ችሎታ ለሚያሣዩ ኢንዱስትሪዎች

ሠ. ለሌሎቹ ኢንዱስትሪዎች የቴክኖዎሎጂ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ሚና ለሚጫወቱ ስትራቴጂካዊ (የኬሚካል፣ የኢንጅነሪንግ፣ የብረታ ብረት፣ የጥራት መቆጣጠሪያ መሣሪያ የሚያመርቱና የመሣሠሉት) ኢንዱስትሪዎች ተገቢው ትኩረት ይሠጣቸዋል።

የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂያችን ተግባራዊ እንዲሆን በመንግሥት በኩል ከሚወሠዱ እርምጃዎች መካከል በኢንዱስትሪ ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት፣ ሞያና ልምድ ያላቸው ሰዎች የሚገኙበት የኤክስፐርቶች ቡድን አቋቁሞ የኢንዱስትሪው ዘርፍ መሠረታዊ ችግሮች መለየት አንደኛው





ነው።

ኢንቬስትሜንትና ምርት ጐን ለጐን ተሣስረው እንዲንቀሣቀሱ በማድረግ በአንድ በኩል የውጭ ምርት በሚተካ ዘርፍ ውስጥ ከተሠማሩት ኢንዱስትሪዎች መካከል የተወሠኑትን መርጦ በታወቀ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚያስፈልገውን የድጐማ መጠንና የከለላ ድጋፍ ማቅረብ፤ በሌላ በኩል አዲስና ታዳጊ ለሆኑ የኤክስፖርት ኢንዱስትሪዎች የዓለምን የገበያ ውጣ ውረድ መቋቋም የሚያስችል የተወዳዳሪነት ብቃት እስኪያሟሉ ድረስ የመረጃ፣ የፋይናንስ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ከውጭ ፉክክር ለመከላከል የሚያስችል የጥበቃ እርምጃ መውሠድና ምርታቸውን ለማስተዋወቅ የሚያግዝ ሥርዓት መዘርጋት ሌላው አስፈላጊ እርምጃ ነው።

- ከውጭ የሚገቡትን በመተካትም ሆነ ወደ ውጭ ኤክስፖርት በማድረግ ለተሠማሩት የሚሰጠው ጥበቃና ልዩ ልዩ ድጋፍ የሚጠይቀው የወጪ መጠንና የጊዜ ገደብ ለሁሉም በእኩል ደረጃ የሚመደብ ስለማይሆን በግልፅ መስፈርት ምርጫ ይደረጋል። የተሻለው አማራጭ የተወሠኑ ዘርፎችን በጊዜያዊነት ከውጭ ፉክክር የመጠበቁን ሥራ በውጭና በሀገር ውስጥ ውድድር ለተሠማሩት ኢንዱስትሪዎች ከሚሠጡት የማበረታቻ ድጐማዎች ጋር ማቆራኘት ነው።

- በኢንዱስትሪዎች መካከል መዋቅራዊ ትስስር ብቻ ሣይሆን ስፔሻላይዜሽንን የሚያበረታታ የሠብ ኮንትራት አሠራር እንዲጠናከር ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጠው ነው።
- የኢንዱስትሪ ልማት የሚጠይቀውን ከፍተኛ የካፒታል አቅም ለመፍጠር ጠንካራ የፋይናንስ ሪሶርስ መኖር የግድ ነው። በሀገራችን ሁኔታ መሠረተ ሠፊ የፋይናንስ ሪሶርስ እንዲኖር፣ የግል ባንኮች ተሣትፎ እንዲያድግና የብሔራዊ ባንክ አደረጃጀትና አሠራር የኢንዱስትሪ ልማትን በሚያግዝ ሁኔታ እንዲስተካከል ይደረጋል። በባንኩ ላይ የሚደረገው ማስተካከያ የኢንዱስትሪ እውቀት እያላቸው የገንዘብ ችግር ያለባቸውን ወደልማት እንዲገቡ የማደፋፈር፣ ተነጻጻሪ ጥቅም አላቸው ተብለው የሚታመንባቸውን ኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ ችግር የማቃለል፣ የፋይናንስ ፍሰቱ ብዙም ጥቅም በሌላቸው መስኮች ላይ እየዋለ አላስፈላጊ ብክነት እንዳይፈጠር የመከላከል አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

- አሁን በሥራ ላይ ካለው የኢትዮጵያ ልማት ፈንድ በተጨማሪ የቴክኒክ እርዳታ ፈንድ፣ የሣይንስና ቴክኒዎሎጂ ማስፋፊያ ፈንድና የመሣሠሉ

ልዩ ልዩ ፈንዶች ይቋቋማሉ። ከእነዚህ ፈንዶች ሌላ የብድር ዋስትና ኩባንያዎችም ይፈጠራሉ። የረጅም ጊዜ ልዩ ብድርና የብድር ድጐማ፣ ረዘም ያለ የችሮታ ጊዜ ሥርዓት ይፈጠራል። እነዚህንና የመሣሠሉትን የፋይናንስ ማመንጫ ዘዴዎች ስራ ላይ ከማዋል ጐን ለጐን አቅርቦቱ ከኤክስፖርት መስፋፋት፣ ከምርታማነት መሻሻል፣ አዲስ ቴክኒዎሎጂ ከመላመድና ከመሣሠሉት የአፈጻጸም መመዘኛዎች ጋር እንዲተሣሠር ይደረጋል።

- ሁሉንም ዓይነት የውጭ ቴክኒዎሎጅ ሽግግር ለመደገፍ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ቴክኒዎሎጂው የሚገኝበት፣ የሚመረጥበት፣ የሚገዛበትና ልምምድ የሚደረግበት ሁኔታ ይመቻቻል።

- በቴክኒዎሎጂ መረጣ ወቅት በጉልበት ላይ የተመሠረተ ቴክኒዎሎጂ ሲመረጥ በካፒታል ከተመሠረተ ቴክኒዎሎጅ ሊገኝ የሚችለውን ብቃትና ተወዳዳሪነት በተወሠነ ደረጃ ማካካሱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል።

- የኢንዱስትሪ ልማታችን የአካባቢ ጉዳት የማያስከትልና ወጪን የሚቆጥብ መሆኑን ለማረጋገጥ በጉልበት ላይ የተመሠረቱትን ራቅ ወዳሉት አካባቢዎች በካፒታል ላይ የተመሠረቱትን ደግሞ ቀረብ ባሉት ማዕከላት የሚለሙበት አሠራር ይፈጠራል።

- የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የቴክኒዎሎጂ ግዥ ዋጋው እንዲቀንስ በማድረግ፣ ወደ ዘርፉ የሚገቡትን ለማጠናከር መንግሥት ራሱ መሣሪያዎችን በመግዛት ወይም የአጠቃቀም ሥልጠና ወጪን በመሸፈን፣ የቴክኒክ አማካሪዎችን ቀጥሮ በማሠማራትና ማበረታቻ በመስጠት፣ የቴክኒዎሎጅ ምንጭና ዋጋን የሚመለከቱ መረጃዎችን አፈላልጐ በማቅረብ፣ የቴክኒዎሎጂ ክህሎት ያላቸውን ከውጭ ተመላሽ ዜጐች በመቅጠርና በማበረታታት ድጋፍ የሚደረግበት ሁኔታ ይመቻቻል።

- በመንግሥት በኩል የሚደረገው ድጋፍ በዚህ ብቻ የተወሠነ ሣይሆን በኢንዱስትሪ ደረጃ የሚደረግን ምርምር መርዳት፣ የአዋጭነት ጥናትና ምክር መስጠት፣ ከባድና የተወሣሠቡ ቴክኒዎሎጅዎችን ለማጥናት ከውጭ ተቋሞች ጋር ጆይንት ቬንቸር መመስረት፣ ከኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ መሠረታዊ የምርምር፣ የሥርፀትና የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣ ያሉትን ቴክኒዎሎጂዎች ለማዘመን፣ ለማደስ፣ አውቶማቲክ ለማድረግና ለማሻሻል የሚያስችል ድጋፍ ማድረግን ይጨምራል።







- የተጠቀሱትን ድጋፎች ለመስጠት አሁን በሥራ ላይ ያሉት የሣይንስና ቴክኒዎሎጂ ኮሚሽን፣ የጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ልማት ድርጅትና የመሣሠሉት በቂ አይደሉም። እነዚህን እንደገና ከማደራጀት በተጨማሪ ከግሉ ዘርፍና ከውጭ የቴክኒክ ድጋፍ ሠጪዎች ጋር በመተጋገዝ ሌሎች አዳዲስ ተቋሞችና ማእከላት እንዲደራጁ ይደረጋል። ስትራቴጅውን ተፈጻሚ ለማድረግ አጠቃላይ ስራውን የሚያስተባብር ማዕከላዊ አካል፤ የመንግሥትን፣ የግል ባለሀብቱን፣ የሲቪል ማህበረሠቡና የሞያ ማህበራትን ተሣትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ ይቋቋማል።

- የኢንዱስትሪ ቴክኒዎሎጂያዊ አቅም የሚገነባው የተራቀቀ የቴክኒዎሎጅ መሣሪያ በመዋስ ብቻ ሣይሆን ከፍተኛ ክህሎት ያለው የሠው ኃይል በማፍራት ጭምር ነው። በመሆኑም በመደበኛ ትምህርት ቤት ከሚሠጠው የሞያ ትምህርት ባላነሰ ሁኔታ ልዩ የቴክኒክ ሥልጠና እንዲስፋፋ ይደረጋል። ለዚህም ተግባራዊነት የግሉን ክፍለ ኤኮኖሚና የመንግሥትን አቅም በማቀናጀት በተለያዩ መስኮች ሥልጠና የሚሠጡ ተቋሞችና ማዕከላት እንዲከፈቱ ይደረጋል።

- በኢንዱስትሪ ልማት ዋነኛው ትኩረት በቅድሚያ የሀገር ውስጥ ባለሃብትን አቅም በሚገባ መጠቀም ቢሆንም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትሜንትን መሣብም ጥቅም አለው። በዚህ ዘርፍ ውጤት ለማምጣት እንደቅድመ ሁኔታ የሚታዩት የፖለቲካ መረጋጋት፣ ብቁ የኤኮኖሚ አስተዳደር፣ ማራኪ ማበረታቻ፣ ነጻ የፍትህ ሥርዓት፣ የመሠረተ ልማት አገልግሎትና ምቹ የኤኮኖሚ አካባቢ መኖር በመሆናቸው እነዚህን ለማሟላት ብርቱ ጥረት ይደረጋል።

- የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅያችንን ውጤታማ የሚያደርግ ፈርጀ ብዙ ድጋፍ በመንግሥት በኩል በሚቀርብበት ጊዜ ብቃት ለጐደላቸውና ከመውደቅ ለማይድኑት ሣይሆን በተግባራቸው ውጤት ማሣየት ለቻሉት ዘርፎች እንዲሆን፤ የድጋፍ አሠጣጡም በመጠን፣ በአይነትና በጊዜ ተወስኖ እንዲሠጥ ጥረት ይደረጋል። የኢንዱስትሪው ባህርይ፣ ስትራቴጅያዊ ጥቅሙና ዘላቂነቱ እየታየ ከቀረጥ ነጻ ወይም ቅነሣ ማድረግ፣ የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ እንዲያገኝ፣ የድጐማ ድጋፍ፣ በነጻ ወይም በአነስተኛ ሊዝ የመሬት አቅርቦት፣ የመብራት ዋጋ ቅናሽ፣ የታክስ ሆሊደይና የመሣሠሉት ማበረታቻዎች ይሠጣሉ።

- የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው እምብርት የፋብሪካው ዘርፍ ቢሆንም ከሁሉም የኤኮኖሚ ዘርፎች ጋር ባለው ትስስር ምክንያት ብቻውን ተለይቶ መቆም ስለማይችል የተመቻቸ ጠቅላላ የማክሮ ኤኮኖሚ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የመሬት ፖሊሲው መጠነ ሠፊ የግብርና ግብዓት መጠቀምን እንዲፈቅድና በዘርፉ የሚሠማሩ ባለሃብቶች ሙሉ እምነት እንዲኖራቸው የግል ባለቤትነትን በሚያረጋግጥ አግባብ ይስተካከላል፡፡

- የፋይናንስ ፖሊሲያችን ለኢንዱስትሪ ልማት ፈጣንና ተመጣጣኝ ድጋፍ እንዲሠጥ፣ የኢነርጅ ፖሊሲያችን ይኸንኑ ልማት በሚገባ እንዲደግፍ ሆነው ይቀየሣሉ፡፡

- በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ፖሊሲያችን ግብ ለዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ትርጉም ያለው የኑሮ መሻሻልና ዘላቂ የኤኮኖሚ ዕድገት ማስገኘት መሆኑን ታሣቢ ባደረገ መንገድ ይቀረጻል፡፡

## *3.3 ልማትን የሚያፋጥን አገልግሎት ማስፋፋት*

በአሁኑ ጊዜ የአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው በመላው ዓለም ዋነኛው የልማት አቅም እየሆነ ነው፡፡ በሀገራችንም ጠንካራ የልማት መሠረት እንዲሆን ትኩረት ሊሠጠው ይገባል፡፡

3.3.1 በአገልግሎቱ ዘርፍ መሠረታዊ ለውጥ ከሚያስፈልጋቸው መስኮች መካከል የንግድ እንቅስቃሴ አንደኛው ነው፡፡ የንግድ መርሆዎቻችን ዋነኛ ይዘት በአንድ በኩል በአምራቹና በሸማቹ፣ በአገልግሎት ሰጪውና በተጠቃሚው መካከል ያለውን ግንኙነት ምቹና ቀልጣፋ ማድረግ፤ በሌላ በኩል በገቢና ወጪ ንግዳችን መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛኑ የተጠበቀና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የንግዱ መስክ ውጤታማ መሆን እንዲችል፡-

- ከፈቃድና ከአገልግሎት አሠጣጥ ቁጥጥር ጋር የተያያዙ የሕግ ሥርዓቶች በንግዱ ዘርፍ የተሠማሩትን ወገኖች የሥራ ፍላጐትና ተነሣሽነት የሚያጠናክሩ ሆነው ይሻሻላሉ፡፡

- በንግዱ ዘርፍ የተሠማሩ ወገኖች የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት የሚያግዝ፣ አማራጮችን የሚያሠፋ፣ ግልጽና ቀልጣፋ የሆነ የብድር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡







- በንግዱ መስክ የሚታየውን የገበያ መረጃ ጉድለት ለማስወገድ በመንግሥትና በንግድ ምክር ቤቶች ቅንጅት በዋና ዋና የንግድ አካባቢዎች ዘመናዊ አደረጃጀትና አሠራር ያላቸው የመረጃ ማዕከላት ይከፈታሉ፡፡

- በንግዱ ዘርፍ ሀገሪቱ ያላትን እምቅ አቅም ለማስተዋወቅና ከሌሎች አገሮች ጋር የንግድ ሽርክና ለመመስረት እገዛ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ የልምድ መለዋወጫና መተዋወቂያ ጉብኝቶች፣ የንግድ ትርኢቶችና የመረጃ ልውውጥ ሥራዎች በሠፊው ይካሄዳሉ፡፡ ለዚህም የሚያግዙ የኤግዚቢሽን ማዕከላት በዋና ዋና የንግድ አካባቢዎች ይቋቋማሉ፡፡

- በሀገሪቱ ከተሞች የሚቀየሱ የከተማ ልማት እቅዶች የንግድ ማዕከላትን ለማቋቋም የሚያስችል ራሱን የቻለ ክልል የያዙ ሆነው እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

- ከንግድ አገልግሎት የሚሠበሠበው ግብርና ታክስ አወሳሰን የሀገሪቱን የልማት ፍላጐት ብቻ ሣይሆን በነጋዴዎች የንግድ ሥራ መዝገብ የሚመዘገቡ መረጃዎችን በማገናዘብና በዘርፉ የተሠማሩትን ወገኖች የመክፈል አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የግብርና ታክስ ውሣኔ በተሟላ ጥናት ላይ እንዲመሠረት፣ ከአድሎ የፀዳና ሚዛናዊ እንዲሆን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው ትኩረት ይሠጠዋል፡፡ የታክስና ቀረጥ ሕጉ ግዴታቸውን የሚያሟሉትን የሚሸልም እንጅ የሚቀጣ መሆን ስለሌለበት ከእንዲህ ዓይነቱ ችግር ለመውጣት መሠረቱን በሚያሠፋ አሠራር ይሻሻላል፡፡ ከታክስና ግብር የሚሠበሠበው ገንዘብ አብዛኛው ለልማት ወጪ የሚውልበትና በቁጠባ መጠቀም የሚቻልበት አሠራር ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- የውጭ ንግድ ጉድለታችንን ለማሻሻል የኤክስፖርት ንግዳችን በጥቂት የግብርና ምርቶች ላይ ብቻ የተንጠለጠለበት ሁኔታ እንዲቀርና በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ዕድገት እንዲያሣይ የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሠዳሉ፡፡ የውጭ ንግዳችን ሌላው ድክመት ከተወሠኑ ሀገሮች ጋር ብቻ መተሣሠሩ እንደመሆኑ የንግድ አጋሮቻችንን በማብዛት የንግድ አማራጮቻችንን ማስፋት፣ ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጠው ይሆናል፡፡ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የውጭ ንግዳችንን

አቅም በማሣደግ የገቢ ንግዳችንን ወጪ በመሸፈን አሁን ከሚሠጠው የ20-30% ድርሻ ወደ 50% ለማድረስ ጥረት ይደረጋል፡፡

- በንግድ መስክ የተሠማሩትን ወገኖች ተወዳዳሪነት ለማሣደግና የተገልጋዩን ጥቅም ለመጠበቅ የሚያስችል የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

- ሕጋዊ በሆነ የንግድ ተግባር የተሠማሩትን ባለሃብቶች ለማበረታታት የሚያግዙ የመረጃ፣ የሥልጠና፣ የብድር፣ የቀረጥ ቅነሣ፣ የታክስ እፎይታ፣ የግብር ምህረት፣ የግንባታ መሬትና ሌሎች ድጋፎች የሚደረጉ ሲሆን ሕገወጥ በሆነ ንግድ የተሠማሩትን የሚያስተምር፣ የሚቆጣጠርና የሚቀጣ ስትራቴጅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

3.3.2 የባንኮችን አደረጃጀትና አሠራር በመለወጥ የቁጠባና የብድር አገልግሎትን የሚያሻሻል እርምጃ መውሠድ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም፡-

- ከመንግሥት አስፈጻሚው አካል ቀጥተኛ ተፅእኖ ነጻ ሆኖ ለመስራት የሚያስችል ሥልጣን (ኦቶኖሚ) ያለው የፌደራል ባንክ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

- የአሠራር ነጻነት ያለው የፌደራል ባንክ ከመመስረት በተጨማሪ በፋይናንስ አገልግሎት የግል ባንኮች ተሣትፎና የገበያ ኃይሎች ሚና እየጨመረ እንዲሄድ የሚያስችል የፋይናንስ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- አሁን ያለው የፋይናንስና የብድር ፖሊሲ ለተበዳሪው ቢዝነስ ወይም ፕሮጀክት አዋጭነትና በአበዳሪውም ሆነ በተበዳሪው መካከል መኖር ለሚገባው አጋርነት ትኩረት የሚሠጥ ሣይሆን 30% የማስያዣ ገንዘብ ባንክ እንዲያስገቡ ማስገደድን መተማመኛ ያደረገ በመሆኑ በተሻለ ፖሊሲ ይቀየራል፡፡ በዚህም መሠረት የፕሮጀክቶችንና ቢዝነሶችን አትራፊ መሆን አለመሆን በማጥናትና የብድር ማስያዣ እንዲሆኑ በማድረግ የባለሃብቶችን የመበደር ፍላጐት ለማደፋፈር፣ በባንኮች ውስጥ ተበዳሪ አጥቶ ያለአገልግሎት የሚቀመጥ ትርፍ ገንዘብ እንዳይኖርና አስቀማጮችንም የሚያበረታታ ወለድ መክፈል እንዲቻል የሚያደርግ ስትራቴጅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡






- የትሬዠሪ ቢል፣ የቢድ ቦንድ በተለይም የውጭ ምንዛሬ የሚወሠነው ሙሉ በሙሉ በገበያ ኃይሎች ሣይሆን በብሔራዊ ባንክ አማካይነት እየተመጠነ በራሽን መልክ የሚታደል በመሆኑ አስመጪዎች ለመግዛት የሚፈልጉትን ምርትና አገልግሎት መግዛት እንዳይችሉ ያሣደረውን ጫና የሚያስወግድ እርምጃ ይወሠዳል፡፡

- ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በባንክ ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጠው በሀገሪቱ ከፍተኛ የመቆጠብ ባህልና አቅም ስለተገነባ ሣይሆን ከቁጠባ፣ ከወለድና ከብድር ፖሊሲ ችግር ጋር በተያያዘ የሀገር ውስጥ ብድር እየቀነሰ በመምጣቱ ምክንያት እንደመሆኑ አስቀማጮችንና ተበዳሪዎችን የሚያደፋፍር አዲስ የወለድና የብድር ስትራቴጅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

3.3.3 የወለድና የብድር ፖሊሲውን ከማሻሻል ጐን ለጐን ወደ ኢንቨስትሜንት መግባት የሚፈልጉትን የልማት ኃይሎች የገንዘብ እጥረት ለማስወገድና በተለይም የረጅም ጊዜ ብድር እንዲጠናከር ለመደገፍ የብድር ማግኛ አማራጮችን የሚያሠፉ፣ አሠራሩን ቀላልና ግልጽ የሚያደርግ እርምጃ ይወሠዳል፡፡ የገንዘብ ተቋሞች የአጭርና የረጅም ጊዜ ብድር የማቅረብ አቅማቸው እንዲጐለብት፣ ብድር የመሠብሠብ አሠራር ዘመናዊ እንዲሆን፣ ተበዳሪውም ብድርን በወቅቱ የመመለስ ባህልንና ታማኝነትን እንዲያዳብር የሚያግዙ የሕግ ሥርዓቶች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

- በአበዳሪ ተቋሞችና በተበዳሪዎች መካከል የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች ለመፍታት ከአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ውሣኔዎች ይልቅ ሁሉንም ወገኖች በእኩልነት በሚያስተናግድ ሕጋዊና ፍትሃዊ የፍርድ ሥርዓት መጨረስ የሚቻልበት አሠራር ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- የኢንቨስትሜንት ሕጉ በተደጋጋሚ ጊዜ የተሻሻለ ቢሆንም የሚፈለገውን ያህል የኢንቨስትሜንት ተሣትፎ ባለመፍጠሩ በተለይም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትሜንትን በሚገባ ሊስብ ባለመቻሉ ተጨማሪ የማበረታቻ ሥርዓቶች እንዲኖሩ፣ አስተማማኝ የውስጥ ሠላምና መረጋጋት እንዲሠፍን፣ ነጻ የፍትህ ሥርዓትና እምነት የሚጣልበት የፋይናንስ አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

3.3.4 በዘመናችን ለማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ልማት እጅግ ቁልፍ መሣሪያ የመረጃ መረብና ፍሰት ነው፡፡ የዓለም ሕዝብ እየተቀራረበ፣ ገበያዎች

እየተዋሃዱ፣ የውድድር አድማስ እየሠፋና የፖለቲካ አጥር እየተሠበረ በሚገኝበት በዚህ ዘመን አስተማማኝ የመረጃ መረብ መዘርጋት ያልቻለ ወገን በሁሉም ነገር የመበለጥ እድል ያጋጥመዋል፡፡ ስለዚህ የሀገራችንን ንግድና ኢንቨስትሜንት በአጠቃላይ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የኮምፒዮተርና የኢንተርኔት መረብ፣ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የስልክ፣ የፋክስ፣ የኤሜይል፣ የቴሌ ኮንፈረንስ፣ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ወዘተ አገልግሎት በሠፊው የሚዘረጋበት ተጨባጭ እርምጃ ይወሠዳል፡፡ በዋና ዋና ከተሞችና የንግድ አካባቢዎች ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ የመረጃ ማዕከላት በግሉ ባለሃብትና በመንግሥት እዲከፈቱ ይደረጋል፡፡

3.3.5 ለኢኮኖሚ ልማት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚኖራቸው ምንጮች መካከል የቱሪዝም ኢንዱስትሪ አንደኛው ነው፡፡ ሀገራችን በዚህ ሃብት ለመጠቀም የሚያስችል እምቅ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መስህብ ስላላት ከዚህ ዘርፍ የሚገኘው ገቢ የውጭ ምንዛሬ አቅማችንን እንዲያጠናክር፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድል እንዲፈጥር የሀገሪቱን መልካም ገጽታ እንዲያጐለብት ለጠቅላላው ብሔራዊ ገቢ ያለው ድርሻ ከፍ እንዲል በሚያስችለው መንገድ ተደራጅቶ እንዲንቀሣቀስ ትኩረት ይሠጠዋል፡፡

3.3.6 በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በባንክና በተለያዩ መንገዶች ወደ ሀገር ቤት የሚላክ በየዓመቱ ወደ 2 ቢሊዮን ዶላር ገደማ እንዳለ ቢገመትም ይኸንን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሠራር ስልት ባለመዘጋጀቱ ልማታችንን በሚገባ እየደገፈ አይደለም፡፡ ስለዚህ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዜጐች ወደ ሀገር የሚገባው ገንዘብ (Remitance) ልማታችንን እንዲደግፍ የሚያደርግ ተስማሚ ዘዴ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## *3.4 ማህበራዊ ፍትህን የሚያረጋግጥ ልማት*

### 3.4.1 ትምህርት

ቅንጅት በትምህርቱ ዘርፍ ያሉትን ችግሮች የሚፈታ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት መዘጋጀት አለበት ብሎ ያምናል፡፡ በቅንጅቱ እምነት ለሀገሪቱ የሚያስፈልጋት ሥርዓተ ትምህርት ዓለማዊ ሁኔታዎችን ከአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለማዊ እምነት ባሻገር መረዳት የሚችል ዜጋ መፍጠር ነው፡፡





ስለሆነም ፖሊሲውን በመቅረፅና ይዘቱን በመወሰን ረገድ ኃላፊነት ያለባቸው መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆችና መላ ዜጎች ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ እንደገና መቀረጽ ያስፈልጋል፡፡ ፖሊሲውን ተግባራዊ የሚያደርገው የትምህርት አመራርና አስተዳደሩም ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በሕዝብና በባለሞያዎች፣ በመምህራንና በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ መመስረት ይኖርበታል፡፡

ሥርዓተ ትምህርቱ ከአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለማዊ እምነት የተለየ እንዲሆን በማድረግ ዜጐች በነጻነት እንዲያስቡ፣ እንዲሠሩና እንዲኖሩ የሚያስችል ሕዝባዊ ፖሊሲ ሆኖ ይሻሻላል፡፡ የማሻሻያው ዓላማ ሥርዓተ ትምህርቱ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ ሥልጣን በወጡና ከሥልጣን በወረዱ ቁጥር ሁልጊዜ እየተቀየረ ከዜሮ የሚጀመርበትን አባካኝ አሠራር እንዲያስወግድ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡

የትምህርቱ መዋቅር በ6+2+4 እንዲቀየርና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ከ7-12ኛ ክፍል ያለው ሆኖ የመለስተኛ፣ የመካከለኛና የማዘጋጃ ሁለተኛ ደረጃ በሚሉ ሦስት ደረጃዎች ይከፈላል፡፡ 10ኛ ክፍል ላይ የሚሠጠው ፈተና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ መሆኑ ቀርቶ ወደ ቴክኒክ ሞያ ማዘጋጃና ወደ ቀለም ትምህርት ማዘጋጃ 2ኛ ደረጃ የሚገቡ ተማሪዎች የሚለዩበት እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ወደ ሁለቱም ማዘጋጃዎች የሚገቡ ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል ፈተና የማለፊያ ውጤት ያላቸው እንዲሆኑ፣ ወደ ቀለምና ወደ ቴክኒክ ሞያ ማዘጋጃ የሚገቡትን ለመለየት የተማሪዎቹ ምርጫ፣ ከ9-10ኛ ክፍል በነበራቸው የትምህርት ቆይታ ጊዜ ያስመዘገቡት ውጤትና የትምህርት ተቋሞቹ የመቀበል አቅም ተጨማሪ መመዘኛ ሆነው የሚያገለግሉበትን አሠራር ታሣቢ ያደረገ ነው፡፡

ከቅንጅቱ የቀረበው አማራጭ ሁሉም የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ፈተናውን እስካለፉ ድረስ እንዲገቡና ሁለቱም የማዘጋጃ መስኮች ራሣቸውን የቻሉ እንዲሆኑ በማድረግ ሣይወሠን በሁሉም አቅጣጫ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ያለውን ዕድል ክፍት የሚያደርግ ነው፡፡ የቴክኒክ፣ ሞያና የቀለም ማዘጋጃ ትምህርት ለ2 ዓመታት የሚሠጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሆኖ በዚህ ወቅት የሚሠጠው ትምህርት ለሥራ ብቁ የሚያደርግና ለከፍተኛ ትምህርትም በሚገባ የሚያዘጋጅ እንዲሆን ማድረግ ይገባል ብሎ ቅንጅቱ ያምናል፡፡

የቅንጅቱ አማራጭ ሃሣብ ትምህርት መማር የእያንዳንዱ ሰው

ሰብዓዊ መብት በመሆኑ አቅሙ እስከፈቀደና መማር እስከፈለገ ድረስ የመማር መብቱ ምንጊዜም ሊከበርለት ይገባል የሚል ነው።

በሞያና በቀለም ማዘጋጃ /በ11ኛ 12ኛ ክፍል/ የሚሰጠውን ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ወስደው ባመጡት ውጤት መሠረት በተለያየ የሞያ መስክ ለዩንቨርስቲ ዲፕሎማና ዲግሪ ትምህርት በመንግሥትና በግል ተቋሞች ዘርፍ ይደለደላሉ። የሚከታተሉት ትምህርት እንደትምህርቱ ዓይነትና ባህርይ ለዲፕሎማ ከ2-3 ዓመታት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ4-5 ዓመታት የሚወስድ ሆኖ ብቁ ሞያተኞችን በሚያፈራ መንገድ ይሠጣል። ወደ ሙያ ማሠልጠኛ ተቋም ገብተው ሥልጠና የወሠዱ ተማሪዎችም የሚመደበውን የሁለት ዓመት የሥልጠና ጊዜ ሲያጠናቅቁ በተመሣሣይ ሁኔታ የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወስደው ባመጡት ውጤት መሠረት በመንግሥትና በግል የከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋሞች ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ይደረጋል። በሞያ ማሠልጠኛ የሚሠጠውን ትምህርት ተከታትለው ላጠናቀቁ ተማሪዎች የሥራ ማዘጋጃ ትምህርት ያጠናቀቁ መሆናቸውን የሚገልፅ ሠርተፊኬት ይሠጣቸዋል። በተለያየ ምክንያት የከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ካልቻሉና ወደ ሥራ ዓለም ለመሰማራት ከፈለጉ ያገኙት ሠርተፊኬት በሚመጥነው የሥራ ደረጃ የግላቸውን ሥራ ለማካሄድና በሌላም ተቋም ተቀጥረው ለመሥራት ይችላሉ። በቀለም ትምህርት ማዘጋጃ 12ኛ ክፍል ላጠናቀቁ ተማሪዎችም በተመሣሣይ ሁኔታ የማጠናቀቂያ ሠርትፍኬት ይሠጣቸዋል።

መምህራን በቂ የሞያ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከወቅቱ የኑሮ ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ወርሃዊ ደመወዝና ልዩ ልዩ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሞያ ሥነ-ምግባራቸውን ለማዳበርና መብታቸውን ለማስከበር የሚያስችል ነፃ ማህበር እንዲኖራቸው ይደረጋል። በሁሉም እርከኖች ከፍተኛ ውጤት ለሚያገኙ ተማሪዎች ማበረታቻ ሽልማት የሚሠጥበትን ቋሚ አሠራር መከተል፣ የተለየ ተሠጥኦና ከፍተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ችሎታቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉና ለሌሎችም አርዓያ እንዲሆኑ ትምህርታቸውን የሚከታተሉበት የተለየ ክፍል ማዘጋጀት፣ በመማር ማስተማሩ ስራ የተለየ ፈጠራና ውጤት ያስመዘገቡ መምህራንና ወላጆች የማበረታቻ ሽልማት የሚያገኙበት ቋሚ አሠራር እንዲኖር ማድረግ ቅንጅቱ ትኩረት የሚሠጥበት ይሆናል።



የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የምርጫ ማኒፌስቶ 1997 ዓ. ም.

አሁን ያለውን አመቺ ያልሆነ የስራ ሁኔታና የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት ማስቀረት በትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደር ረገድ መወሰድ ከሚገባቸው እርምጃዎች መካከል የመጀመሪያው ይሆናል። በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሚመሩባቸውን አጠቃላይ መርሆዎችና ሕጋዊ ሥርዓቶች ተፈፃሚነት ከመከታተል በስተቀር በእለት ከዕለት አስተዳደራዊና የመማር ማስተማር ጉዳያቸው ውስጥ መንግሥት ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ እንዲቀር ይደረጋል። መንግሥት ለምርምር፣ ለግንባታና ማስፋፊያ ስራ የሚውል ፋይናንስ በመመደብ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚገባው ቢሆንም ይኸንን ሽፋን በማድረግ የአሠራር ነፃነታቸውን ጨርሶ እስከመቀማት የሚደርስ ተፅእኖ የሚያደርግበት ሁኔታም ይወገዳል።

የትኛውም የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ እንደሚገኙ ነፃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሀገራችን ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የራሳቸውን ቻርተር በራሳቸው ውሳኔ አዘጋጅተው መመራት አለባቸው። የራሳቸውን መሪዎች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድና የብቃት መመዘኛዎችን መሠረት ባደረገ ሁኔታ የመምረጥ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። ተማሪዎችም የመደራጀት፣ ሃሣባቸውን የመግለጽ፣ የአካዳሚክና የመብት ጥያቄዎችን የማቅረብ ነፃነታቸውን በሚያረጋግጥ መንገድ የራሳቸውን ደንብ ማውጣትና መሪዎቻቸውን በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመምረጥ ሙሉ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። የአካዳሚክ ስታፍ አባላት ብቻ ሳይሆኑ በተቋሞቹ ውስጥ የተመደቡ ሌሎች ሠራተኞችም መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና በአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ የሚጠበቅበትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማሕበረሰቦች ተገቢው አስተዳደራዊና አካዳሚያዊ ነፃነት እንዲኖራቸው ይደረጋል።

በመርህ ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ወጪን ተማሪዎች እንዲጋሩ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታና የዜጎች ድህነት እጅግ አሳዛኝ በሆነ ደረጃ በሚገኝበት በአሁኑ ጊዜ ይኸንን ተግባራዊ ማድረግ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም። ወጪን የመጋራቱ አሠራር ተፈፃሚ መሆን የሚገባው በቅድሚያ ድህነትን በመቀነሱ ትግል አንድ ዓይነት ተስፋ የሚጣልበት ውጤት ሲመዘገብ፣ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የማያቋርጥና አስተማማኝ የዕድገት መስመር መያዙ ሲረጋገጥ፣ የሕዝቡም ድህነት ሲሻሻልና አስተማማኝ የኑሮ ዋስትና መፈጠር ሲጀምር ብቻ ነው። ይህ እስከሚሆን ድረስ መንግሥት የትምህርት ወጪን ለመሸፈን መውሰድ ያለበት እርምጃ የታክስ መሠረቱን ማስፋት፣ ከድሃው ሕብረተሰብ የሚሰበሰበውን ቀረጥና


የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ(ቅንጅት) አባል ድርጅቶች
መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድኅን፣ ኢዴሊ እና ቀስተ ደመና ናቸው።

ግብር ከሙስናና ከብክነት መጠበቅ፣ የትምህርት ተቋሞች ወጪያቸውን ለመደገፍ የሚያስችል የምርትና የምርምር ተግባር እያካሄዱ ገቢ የሚያገኙበትን መንገድ መፍጠር፣ ከፍለው መማር ለሚችሉት ዜጐች የግል ትምህርት ተቋሞች ሠፊ አገልግሎት እየሰጡ በመንግሥት ትምህርት ተቋሞች ያለውን መጨናነቅ እንዲያቃልሉ መደገፍና ከውጭ ከሚገኘው የልማት ዕርዳታና ብድር ውስጥ የትምህርትን ድርሻ ማሣደግ ነው፡፡

መንግሥት ለትምህርት የሚያወጣውን ወጪ ለመቀነስና የዜጐችን የመማር ዕድል ለማስፋት ጠቃሚ አስተዋፅዖ የሚኖረው አንዱ መንገድ የግል ባለሀብቱና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሣትፎ እንዲያድግ በልዩ ልዩ መልክ መደገፍና ማበረታታት ነው፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ባለሃብቶች በትምህርቱ ዘርፍ አሁን ያላቸው ተሣትፎ ሲታይ ዝቅተኛ በመሆኑ ይህ ሁኔታ እንዲለወጥ የብድር፣ የመሬት፣ የታክስ ቅነሣና የመሣሠሉትን ድጋፍና ማበረታቻዎች ስራ ላይ በማዋል ሚናቸውን ማሣደግ ያስፈልጋል፡፡

ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ቁጥራቸው እንዲጨምር፣ ሥርጭታቸው ፍትሃዊ እንዲሆን፣ የመቀበል አቅማቸው እያደገ እንዲሄድ፣ ሀገሪቱ በምትፈልገው መስክና የጥራት ደረጃ ሞያተኞችን እንዲያፈሩ፣ የሚያደርጉት ምርምርም በሀገሪቱ መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ በሚያስችል አቅጣጫ መቃኘት አለባቸው፡፡

የስኮላርሽፕና የተልዕኮ ትምህርት ዕድሎች ለሁሉም ዜጎች በእኩል ደረጃ መሰጠት ይገባቸዋል፡፡ መመዘኛውም አካዳሚያዊ ብቃትና የሀገሪቱ የሞያተኛ ፍላጎት ሆኖ አሠራሩ ደግሞ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ይኽንን ተግባር በኃላፊነት የሚመራ፣ ነፃ አደረጃጀትና አሰራር ያለው አንድ የውጭ ሀገር ስኮላርሽፕና የተልዕኮ ትምህርት ኤጀንሲ መቋቋም ይኖርበታል፡፡

የትምህርቱን ዘርፍ የበጀት ድርሻ ማሳደግ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለትምህርት ከሚመደበው ወጪ ውስጥ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ድርሻ 67%፣ የ2ኛ ደረጃ 20%፣ የከፍተኛ ትምህርት ድርሻ 13% ገደማ ነው፡፡ በሁሉም ደረጃዎች የሚመደበው ወጪ እኩል ማደግ አለበት ባይባልም ሚዛኑን የጠበቀና ተከታታይ የሆነ ዕድገት እንዲኖር ማድረግ የግድ ነው፡፡ ስለዚህ ለትምህርት የሚመደበው በጀት በየጊዜው እንዲጨምርና በተለይም ለ2ኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት የሚመደበው ድርሻ ከአሁኑ የተሻለ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል ብለን እናምናለን፡፡





## 3.4.2 በመከላከል ላይ የተመሠረተ የጤና ልማት

- ብዙዎቹ የሀገራችን የጤና ችግሮች ለመከላከል የሚቻሉ ተላላፊ በሽታዎችና ከአመጋገብ ጉድለት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም የጤና ፖሊሲያችን በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ ሆኖ የሕዝብ ብዛት ቁጥርን፣ ተስማሚ የኑሮ ሁኔታዎችን፣ የምግብና ንፁህ ውኃ አቅርቦትን፣ የትምህርት አገልግሎትን፣ የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅን፣ የመንገድና ትራንስፖርት መስፋፋትንና የመሣሠሉትን መሠረታዊ አገልግሎቶች ታሣቢ አድርጐና በእነዚህ መስኮች ከሚደረጉ ማሻሻያዎች ጋር በተሣሠረ መንገድ ተቀርጾ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

- ወባና ሣንባ ነቀርሣን ጨምሮ ከጥንቃቄ፣ ከንጽህናና ከአመጋገብ ጉድለት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ሠፊ የሕዝብ ተሣትፎ ለመፍጠር መንግሥትን፣ ሕብረተሠቡንና ሌሎችን አጋሮች ሁሉ የሚያካትት አደረጃጀትና አሠራር ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- የእናቶችንና ሕጻናትን ጤንነት የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን ሥራ ላይ በማዋል በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ከወሊድ ጋር በተያያዘ የጤና ችግር የሚሞቱትን እናቶች ቁጥር በግማሽ ለመቀነስ፣ በአሁኑ ጊዜ ከአንድ ሺህ ህፃናት መካከል አንድ ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱትን ሕፃናት ቁጥር ወደ 50 ለማውረድ፣ አምስት ዓመት ሣይሞላቸው የሚሞቱትን 187 ሕጻናት ቁጥር ወደ 60 ለማውረድ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

- የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት በከተማና በገጠር እንዲሻሻል፣ የመፀዳጃ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ፣ የሕክምና ተቋሞች ሥርጭትና የሕክምና ባለሞያዎች ምደባ አብዛኛውን የገጠር አካባቢ እንዲሸፍኑ ለማድረግ ትኩረት ይሠጣል፡፡

- በጤና አገልግሎት አሠጣጥ የመድኃኒት ጥራት ቁጥጥር ትኩረት የሚደረግበት ሲሆን የባህላዊ መድኃኒቶችን አጠቃቀም ችግሮች ለመቀነስና ከዘመናዊ ሕክምና ጋር ለማቀናጀት የሚያግዙ ስልቶች ይቀየሣሉ፡፡

- የሕክምና አገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓቱ በማምረት ተግባር ለሚሣተፉ፣ እስካሁን በአገልግሎት አሠጣጡ ተረስተው ለቆዩት አካባቢዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ በሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አደጋዎች ለተጠቁ ወገኖች፣ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ትኩረት እንዲሠጥ ሆኖ ይቃኛል፡፡

- በጤናው ዘርፍ በዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ የሠለጠነ በቂ የሠው ኃይል ለማፍራት በሕብረተሠቡ ፍላጐት ላይ የተመሠረቱ ሥልጠናዎችና የአቅም ግንባታ ተግባሮች ይከናወናሉ፡፡

- በአሁኑ የሀገራችን ሁኔታ ዋነኛው የጤና አገልግሎት ሠጪ አካል መንግሥት ቢሆንም ለዘርፉ የሚመደበው በጀት እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ትርጉም ያለው ዕድገት እንዲያሳይ ከመንግሥት፣ ከውጭ አበዳሪዎችና እርዳታ ሠጪዎች፣ ከሕዝቡና ከግል ባለሃብቱ ከሚገኘው ሪሶርስ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት ለጤና አገልግሎት እንዲመደብ ይደረጋል፡፡
- የግል ባለሃብቶች በጤና ዘርፍ ያላቸው ተሣትፎ እንዲጨምር በፈቃድ አሠጣጥ፣ በሰው ኃይል ሥልጠና፣ በብድርና በመሬት አቅርቦት ረገድ አመቺ የሕግ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የታክስ ቅነሣና ሌሎች ማበረታቻ መንገዶችም ይቀየሣሉ፡፡

- የኤች አይቪ ኤድስ ስርጭት በሀገር እና በሕዝብ ላይ እያስከተለ ያለውን ከፍተኛ ቀውስ ለመለወጥ ተገቢውን የገንዘብና የሰው ኃይል አቅርቦት በመመደብ መንግሥት ጉልህና ምሳሌነት ያለው ሚና ይጫወታል፡፡

- የተቋማት ዝግጅትና አደረጃጀት የኤች አይ ቪ ኤድስን ችግር በተቻለ ፍጥነት ለመቋቋም ስለሚረዳ ከሀገር አቀፍ እስከ ቀበሌ ደረጃ ሕዝቡን ያሳተፈ መዋቅር መዘርጋትና ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም መንግሥት ግልፅ የሆነ ብሔራዊ ዓላማ እና ስትራቴጂ በመንደፍ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ጠንካራ ትብብር የሚፈጥር እርምጃ ይወስዳል፡፡

- በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ ዜጐች ከእስካሁኑ በላቀ ሁኔታ የአድቮኬሲ ስራ እንዲሠሩና ኤች አይቪ ኤድስን በሚመለከት ያለው ሪሶርስ በተቀናጀ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በአገር አቀፉ የኤች አይቪ ኤድስ ሴክሬታሪያት መካከል ያለውን ውዝግብ ከመፍታት በተጨማሪ ራሱን በቅጡ መምራት ለተሳነው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ይህን መሠል አጣዳፊና አንገብጋቢ አገራዊ ችግር ከማሸከም ይልቅ ሴክሪታራያቱ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት ተጠናክሮ የሀገሪቱን ሕዝብ ከኤች አይቪ ኤድስ ወረርሽኝና እልቂት







መታደግ በሚችልበት መልኩ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

- የመገናኛ ብዙሓን ሕዝቡን እንዲያስተምሩ ማመቻቸትና በተለይ ደግሞ እንደሌላው ዓለም ሁሉ የግል ሬዲዮና ቴሌቪዥንም ተቋቁመው በበሽታው ላይ የሚታወጀውን ጦርነት በማገዝ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

- ፖሊሲው ሕዝብንና የሚመለከታቸውን ወገኖች ባላሳተፈ ሁኔታ ከተረቀቀ በኂላ ለሰባት አመት ያለአንዳች እርምት በመቀመጡ ጊዜ ያለፈበት ስለሆነና ኤች አይ ቪ ኤድስ በየጊዜው ተቀያያሪ ባህሪ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ እየተስፋፋ የሚሄድ በሽታ በመሆኑ ሕዝብንና የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ በማሳተፍ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

- ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመዋጋት እንቅፋት የሆኑ የሕግ ክፍተቶችን ለመሙላትና ተጨማሪ የሕግ አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በሀገሪቱ ወንጀለኛ መቅጫና ፍትሃብሔር ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

- በበሽታው የተጠቁ ወገኖቻችን በአስፈሪ ፍጥነት እና መጠን እየረገፉ በመሆናቸው ለእነዚህ ወገኖች የመድሃኒት አቅርቦት በተቻለ ፍጥነት የሚዳረስበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ጐን በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STDS) ለመከላከል ከፍተኛ ትኩረት ይሠጣል፡፡

- በፈቃደኝነት ምክርና ምርመራ (V.C.T) አገልግሎት አሁን ያሉበት ችግሮች ተፈተው በሰው ኃይል የሚጠናከርበትና በስፋትና በነፃ የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

- በየዓመቱ የሕዝብ፣ የመንግሥት እና የተለያዩ ተቋማት እንቅስቃሴ በኤች አይቪ ኤድስ ዙሪያ ምን ውጤት እንዳመጣ ለማወቅ ከሕዝቡና ከሚመለከታቸው አካላት አስተያየት በመሰብሰብ እርምቶችን መውሠድና ከዚህም በመነሳት የተሻሉ መፍትሄዎችን መፈለግ ቅንጅት ትኩረት የሚሠጣቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡

## 3.4.3 ለወጣቱ ችግሮች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት

የወጣቶችን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ዋነኛ ግቡ ብሩህ ራዕይና ጠንካራ ተስፋ ያላቸው፣ ለወገኖቻቸውና ለሀገራቸው

የሚቆረቆሩ፣ ስለራሣቸውና ስለሀገራቸው የወደፊት እድል ማማር በሁሉም መስክ በጐ አስተዋፅኦ ለማድረግ የወሠኑ ዜጐችን ማፍራት ነው።

ይኸንን ግብ ለማሣካት የሚረዳ በወጣቶች ተሣትፎና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ግልጽ ብሔራዊ ፖሊሲ ማውጣትና ተስማሚ የአፈጻጸም መመሪያዎች ማውጣት የመጀመሪያው የመፍትሔ እርምጃ ነው።

የሀገሪቱ የወደፊት እድል የሚወሰነው በወጣቶቻችን ነው። ለኢትዮጵያ ወጣቶች አሁን የሚደረገው ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር በመጪው ጊዜ የሀገራችን መዳረሻ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያሣይ ነው። ስለሆነም ቅንጅት ለሥልጣን ቢበቃ ወጣቶችን በሚመለከት የሚያወጣው ፖሊሲ ለሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ትኩረት ይሠጣል።

1. የሀገራችን ሥርዓተ ትምህርት የወጣቶችን የመስራት ፍላጐት የማይገድብ፣ ለሥራ የሚያበቃ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጥ ሆኖ ይዘጋጃል።

2. መንግሥት፣ የግል ባለሃብቶች፣ ራሣቸው ወጣቶችና መላው ሕብረተሠብ ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ ይመቻቻል።

በገጠር ለሚገኙት ወጣቶች ከእርሻ ስራ ውጭ የሚሠማሩበት የሥራ ዕድል ይፈጠራል። ለዚህ ዓላማ የሚያገለግሉ የእደ ጥበብ፣ የመሠረተ ልማት ግንባታና የአግሮ ኢንዱስትሪ ፕሮግራሞች ተቀይሠው ሥራ ላይ ይውላሉ።

በከተማ ውስጥ ለሚገኙትና ከገጠር ወደ ከተማ ለሚፈልሱት ወጣቶች የሥራ አማራጮችና ዕድሎችን የሚያሠፋ ሠፊ የኢንቨስትሜንት እንቅስቃሴና የኢንዱስትሪ ልማት ይካሄዳል።

በመንግሥት የሚነደፉ የልማት ፖሊሲዎች፣ የትምህርት የጤናና የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂዎች የወጣቱን የሥራ ማጣት ችግር የመፍታት ተልዕኮ እንዲያሟሉ ሆነው ይዘጋጃሉ።

ወጣቶች ሥራ እንዲፈጥሩ የሥልጠና፣ የምክር፣ የብድር፣ የመሬት፣ የፈቃድና የመሣሰሉት ድጋፎች የሚቀርቡ ሲሆን እነዚህን ድጋፎች ከምርጫ ዘመቻና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ጋር የማያያዝ ግድፈት እንዳይኖር የሚያስችል ሥልት ይቀየሣል።





3. የሀገራችን ከተሞች የሚነድፏቸው መሪ ፕላኖች፣ የዕድገትና የተግባር ዕቅዶች ከሕብረተሠቡ ቁጥር አብዛኛውን ድርሻ ለሚሸፍነው ወጣት የሕብረተሠብ ክፍል የስፖርት ማዘውተሪያ፣ መዝናኛና የዕረፍት ጊዜ ማሣለፊያ ማዕከላትን ለማስፋፋት በሚያስችል መንገድ ይዘጋጃሉ።

4. የሀገሪቱ የፖለቲካ ኃይል በአብዛኛው የሚመነጨው ከወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል እንደመሆኑ ወጣቱን እንደ ስጋት ሣይሆን እንደለውጥ አንቀሣቃሽ ሞተር በመቁጠር በፖለቲካ ውሣኔ አሠጣጥ ሠፊ ተሣትፎ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት በፓርላማ ውስጥ የወጣቶች ውክልና እንዲጨምርና የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እንዲኖር ከማድረግ ባሻገር ወጣቶች የራሣቸውን ጉዳይ እየመከሩ በፖሊሲ አውጭዎች ላይ ተፅእኖ ለማሣረፍ የሚረዳቸው የወጣቶች ፖርላማ ይመሠረታል። ሥልጣን ላይ ለወጣ ፓርቲ ተላላኪ እንዲሆኑ ሣይሆን ለወጣቶች መብትና ጥቅም የሚሠራ፣ የወጣቱን ፖለቲካዊ ተሣትፎና የልማት ጥረት የሚያቀናጅ ነጻ የወጣቶች ማህበር በሀገር ደረጃ ይቋቋማል።

የወጣቶች ጉዳይ የአንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ኃላፊነት ብቻ ተደርጐ የሚታይ ሣይሆን የሀገርና የሕዝብ ጉዳይ እንደመሆኑ በአብዛኛዎቹ የመንግሥት ተቋሞች፣ በሲቪክ ማህበራት፣ በሕብረተሰቡ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች ውሰጥ የወጣቶችን ሁለገብ ተግባር የሚደግፉ መዋቅሮች እንዲፈጠሩ ይደረጋል።

## 3.4.4 ተጨባጭ ጥረት ለሴቶች እኩልነት

- የሀገራችን ሕዝብ ብዛት በጾታ ከፍፍል ሲታይ የሴቶችና የወንዶች ድርሻ 50 በ50 ነው። ይሁን እንጂ ለሴቶች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ በሁሉም መስክ ያላቸው ተሣትፎ ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ወደኋላ የቀረ ነው።

- በኢትዮጵያ ሁኔታ በቤት አያያዝና በሕጻናት አስተዳደግ የሴቶች ኃላፊነት ከፍተኛ እንደመሆኑ እነርሱን ማስተማር ማለት ሕብረተሠቡን ማስተማር ማለት ነው። ነገር ግን በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሴቶች ተሣትፎ ከወንዶች ያነሠ ነው። ስለዚህ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በየትኛውም ደረጃ የሴቶች የትምህርት ተሣትፎ ከወንዶች ጋር እኩል እንዲሆን ይደረጋል።

- ይህ ዓላማ ተጨባጭ እንዲሆን በተለይም የገጠር ሴቶች ያሉባቸውን ጫናዎች የሚያቃልሉ እርምጃዎች ይወሠዳሉ። በመሆኑም ንፁህ የመጠጥ ውኃ አገልግሎት ባልተዳረሰባቸው የገጠር አካባቢዎች አገልግሎቱን ለማዳረስ ቅድሚያ ትኩረት ይሠጣል። ለዋና ዋና መንገዶች ቅርበት ያላቸው የገጠር መንደሮች የኤሌክትሪክ ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ የገጠር ኢነርጅ እንዲስፋፋና ከዋና መንገድ የራቁት ደግሞ በውኃና በናፍታ የሚሠሩ የእህል ወፍጮዎች እንዲቋቋሙ፣ በዚህ ሥራ የግል ባለሃብቶች በሠፊው እንዲሣተፉ ይደረጋል።

- በጤና አገልግሎት አሠጣጥ የሴቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ጥረቶች ይደረጋሉ። በተለይም ለእናቶች ወሊድ አገልግሎት፣ ንጽህናና ጤና አጠባበቅ የሚረዱ የጤና ፓኬጆች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይሆናሉ። በአሁኑ ጊዜ 95% የሚሆኑት እናቶች ልጆቻቸውን የሚወልዱት የሃኪም እርዳታ በሌለበት ሁኔታ በቤታቸው ውስጥ ሲሆን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሕክምና ባለሞያና ሥልጠና በተሠጣቸው የአካባቢ አዋላጆች በማከናወን ይሽንን ቁጥር ወደ 50% ዝቅ እንዲል ይደረጋል። ከወሊድ ጋር በተያያዘ ከእያንዳንዱ 100 ሺህ እናቶች መካከል የሚሞቱትን 871 እናቶች ቁጥር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በግማሽ እንዲቀንስ ይደረጋል። የአሁኑ የሀገራችን የወሊድ ምጣኔ በአማካይ 6 ሲሆን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ወደ 4 ዝቅ እንዲል የሚያስችል የቤተሠብ ምጣኔና የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ፕሮግራም ሥራ ላይ ይውላል።

- በከተማ ውስጥ ከሚገኙት ሥራ አጥ ዜጐች የሴቶች ቁጥር ከወንዶቹ ጋር ሲነጻጸር ከእጥፍ በላይ ሲሆን በገጠር ደግሞ ከ4 እጥፍ በላይ በመሆኑ የሥራ ማጣትን ችግር ለማቃለል በሚዘረጉ ፕሮግራሞች ሁሉ የሴቶችን ተሣትፎ የሚያረጋግጡ እርምጃዎች ይወሠዳሉ። በሥራ ፈጠራ፣ በኢንቨስትሜንትና በልማት ተግባሮች የሴቶች ተሣትፎ እንዲጠናከር የሚያስችሉ የቴክኒክ፣ የሞያ ሥልጠና፣ የምክርና የብድር ድጋፎች በስፋት ይቀርባሉ።

- አማራጭ በማጣት ለጤንነት አደገኛ በሆነ የሥራ መስክ የተሠማሩትንና ወደ ውጭ ሀገር የማሠደዱትን ሴቶች ችግር የሚያቃልል ጥረት ይደረጋል።

- ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሣትፎ መጠናከር የኢንፎርሜሽንና መረጃ






ቴክኒዎሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ ወሣኝ ነው። በመሆኑም ሴቶች የስልክ፣ የኢንተርኔት፣ የኮምፒዩተር፣ የቴሌቪዥንና የሬዴዮ አክሰስ እንዲኖራቸው ልዩ ልዩ ጥረት ይደረጋል።

- በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሚካሄድ ጥረት ከ10 ዓመታት ባለበለጠ ጊዜ አሁን በፌደራል ፓርላማ ያላቸው 7.7% ድርሻ ወደ 50%፣ በክልል ምክር ቤት አሁን ያላቸው 11.4% ድርሻ ወደ 50%፣ በወረዳ ምክር ቤት ያላቸው 7% ወደ 50% እንዲሁም በቀበሌ ምክር ቤት አሁን ያላቸው 14% ድርሻ ወደ 50% እንዲደርስ የሚያስችሉ ሁለገብ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ። ለዚህ ተግባራዊነት የሚረዳ የምርጫ ሥርዓትና የሕግ መሠረት እንዲኖርም ቅንጅቱ ልዩ ትኩረት ያደርጋል።

- በመንግሥት ሥራ ውስጥ በውሣኔ ሠጪነት የኃላፊነት ቦታ ላይ አሁን ያላቸው 2% ተሣትፎ ወደ 20% እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ይካሄዳል። በአጠቃላይ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ የሴቶችን ድህነትና ኋላቀርነት የሚያስወግዱ በአንጻሩ ተጠቃሚነታቸውንና ሕይወታቸውን የሚያሻሽሉ ጥረቶች ይካሄዳሉ።

- ሴቶች የንብረት ባለቤትነት መብት እንዲኖራቸው፣ ከሚደርስባቸው የባህል ተፅእኖና ሕገወጥ ጥቃቶች እንዲጠበቁ፣ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ እንዲያገኙ፣ በጾታቸው ምክንያት አድሎ እንዳይደርስባቸውና ሕጋዊ መብቶቻቸው እንዲጠበቁ የሚያስችሉ ሥርዓቶች በሀገሪቱ የሕግ ማእቀፍ ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

- በፖሊሲ አውጭዎች ላይ ተፅእኖ ማሣደር የሚችል አቅም እንዲኖራቸው፣ የጋራ ፍላጐቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሚያግዝ መድረክ እንዲያገኙና ጥረታቸውን በተቀናጀ መንገድ ለማስተባበር እንዲችሉ በራሣቸው ፈቃድ ላይ የተመሠረተና ከገዥው ፓርቲ ፖለቲካዊ ተፅእኖ ነጻ የሆነ ማህበር እንዲያቋቁሙ ይደረጋል።

## 3.4.5 የሠራተኞችን የሥራ ሞራል የሚያነሣሣ ጥረት ማድረግ

- የሀገሪቱን ሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት የሚያሣድግና ፈጣን ለሆነ ልማት የሚመች የኢንዱስትሪ ሠላም ለመፍጠር የሚያስችሉ የሕግና የአደረጃጀት ሥርዓቶች ተግባራዊ ይሆናሉ።

- የኢንዱስትሪ ሠላምና የሥራ ተነሣሽነት የሚኖረው በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በሕግ አግባብ ለመምራትና ለመወሠን የሚያስችል የሠራተኛና አሠሪ አዋጅ ሲኖር እንደመሆኑ ይኸው አዋጅ የሁሉንም ወገኖች ንቁ ተሣትፎና መብት በሚያረጋግጥ መንገድ ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- የሠራተኞችን የመደራደር አቅም የሚያጠናክር ድርጅታዊ አቅምና የሕግ ድጋፍ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ለሠራተኞች ጥቅምና ፍላጐት መከበር ተግቶ የሚሠራ ነጻ ማህበር እንዲመሠረትና ገደብ የሌለው የአሠሪዎችና የመንግሥት ተፅእኖ እንዳይኖር የሚከላከል የሕግ ሥርዓት ይቋቋማል፡፡

- የሠራተኞችን ማህበራዊ ደህንነት ለማረጋገጥ በሥራ ዋስትና፣ በደሞዝ፣ በሥልጠና፣ በካሣ ክፍያ፣ በሥራ ፈቃድ፣ በሕክምናና በመሣሠሉት መሠረታዊ ጥቅሞቻቸው ላይ የሚያደርጉት ድርድርና የሚፈርሙት የሕብረት ስምምነት በሚጣስበት ጊዜ አቤቱታ የሚያቀርቡበት የግልግል ሥርዓትና የአሠሪና ሠራተኛን ክርክር የሚመለከት ፍርድ ቤት ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ይቋቋማል፡፡

- አሁን በሥራ ላይ ያለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሠራተኞችን መብት ለማስከበር የማያስችሉ ችግሮች ስላሉበት እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

## 3.5 ለተረሱት ወገኖችና አካባቢዎች ትኩረት የሚሠጥ መሠረተ ልማት

- በሀገሪቱ የሚካሄዱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በሁሉም መስክ ፈጣንና ዘላቂ ዕድገት ለማምጣት የሚቀየሱ ስትራቴጅዎችን ለመደገፍ በሚችሉበት ሥርዓት እየታቀዱ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋሉ፡፡

- የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከሕዝቡ በሚሠበሠብ ግብር፣ በሕዝብ ስም በሚገኝ ብድርና እርዳታ የሚካሄዱ እንደመሆናቸው ስራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ሁሉንም ዜጐችና አካባቢዎች ተጠቃሚ ማድረጋቸው እንዲረጋገጥ አስፈላጊው የጥንቃቄ እርምጃ ይወሠዳል፡፡

- የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከዚህ በፊት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ላልሆኑ፣ ትኩረት ተነፍጓቸው ለቆዩትና ከፍተኛ እጥረት ላለባቸው ዜጐችና አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት፣ መላው ዜጐችና ልዩ ልዩ





አካባቢዎች የሀገሪቱን ሃብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም መብታቸውን በማረጋገጥ ማህበራዊ ፍትህን የሚያሰፍን ጥረት ይደረጋል፡፡

- የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች፤ በወንዶችና በሴቶች፣ በሃብታምና በድኃ፣ በከተማና በገጠር፣ በመሃልና በጠረፍ ወዘተ መካከል በተለያዩ ሁኔታዎች ያሉትን ልዩነቶች የማጥበብ ዓላማ እንዲያሣኩ ትኩረት ይሠጣል፡፡

## 3.6 የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓትን ማሻሻል

- በመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ በሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶችና በግል ባለሃብቶች ስር የሚተዳደሩ ሠራተኞች ልዩ ልዩ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን የሚያገኙበት ሕግና ሥርዓት ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ይውላል፡፡

- በሕመም፣ በአደጋ፣ በእድሜና በመሣሠሉት ምክንያቶች የራሣቸውን ሕይወት መምራት ላልቻሉ ዜጐች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ወላጅና አሣዳጊ አልባ ለሆኑ ሕጻናት፣ ለጦር ጉዳተኞችና ብሔራዊ ግዴታዎችን ለተወጡ ዜጐች ማቋቋሚያ ድጋፍ የሚሆን የማህበራዊ ዋስትና ፈንድ ይመሠረታል፡፡

- የማህበራዊ ዋስትናን ሽፋንና መጠን ለማሣደግ የሚያስችል ሠፊ የፋይናንስ መሠረት እንዲኖር ዜጐች ከሚያገኙት ገቢና ከተለያዩ የማህበራዊ ዋስትና የፋይናንስ ምንጮች የሚሠበሠበው ገንዘብ በየጊዜው የሚጨምርበትና ዘላቂነቱ የሚረጋገጥበት ሕጋዊ አደረጃጃትና አሠራር ይፈጠራል፡፡

- የጡረተኞች አበል በየጊዜው ከሚፈጠረው የኑሮ ውድነት ጋር በሚጣጣም መንገድ ማሻሻያ ይደረግበታል፡፡

- አሁን በሥራ ላይ ያለው የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ፣ የፖሊሲው ማስፈጸሚያ ሕጐችና መዋቅሮች እንዲሻሻሉና በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመ የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ፣ አደረጃጀትና አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 3.7 ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ትኩረት የሚሠጥ የውጭ

## ፖሊሲ

- የውጭ ግንኙነት መርሃችን በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሠላምና ዘላቂ ልማት እንዲኖር ባለን አቋም ላይ የሚመሠረት ነው፡፡ በመሆኑም በሁሉም ዘርፍ የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የሕዝብን ብሔራዊ ጥቅሞች ማስጠበቅ የውጭ ግንኙነታችንን የሚገዛ ዋነኛ መርህ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ገዥው ፓርቲ በሀገሪቱ ሉዓላዊነትና በሕዝቡ ጥቅሞች ላይ የፈፀማቸውን የክህደት ተግባሮች ለማስተካከል የሚያስችሉና የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅሞች በሚገባ የሚያስከብሩ በታሪክ፣ በሕግና በዴፕሎማሲ ላይ የተመሠረቱ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡

- የኤርትራ መገንጠል በተፈፀመበት ጊዜ የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚጐዱ፣ የሁለቱን ሕዝቦች ዝምድናና ግንኙነት የሚያበላሹ፣ ለማያባራ ግጭት መንስኤ የሚሆኑና ለአካባቢው ሠላም ጠንቅ የሚፈጥሩ ጉልህ ስህተቶች በመሠራታቸው እነዚህን ለማረም የሚያስችሉ ሠላማዊና ሕጋዊ እርምጃዎች ይወሠዳሉ፡፡

- የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ሕጋዊና የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብም በሚገባ የሚገነዘበው ቢሆንም የገዥው ፓርቲ በያዘው የተሣሣተ አቋም ለውይይት እንኳ የሚቀርብበት ዕድል ተዘግቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥያቄ ከሉዓላዊነትና ከብሔራዊ ሕልውና ጋር የተያያዘ ሕጋዊ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩ በሠላማዊ መንገድና በሁለቱ ሕዝቦች ስምምነት መፍትሔ እንዲያገኝ ዓለም አቀፉ ሕብተረሰብም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ድጋፍ እንዲሠጥ ጥረት ይደረጋል፡፡

- ወሠን ተሻጋሪ ወንዞቻችንን በሚመለከት ከዚህ በፊት በአንዳንድ የአካባቢ መንግሥታት የተደረሱ የተናጠል ስምምነቶች ተሠርዘው ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም እንዲኖር በሚያስችሉ ስምምነቶች እንዲተኩ ትግል ይደረጋል፡፡

- ኢትዮጵያ ከጐረቤቶቿ ጋር ያላት ግንኙነት በእኩልነት፣ በጋራ ጥቅም፣ በመተማመን፣ በመልካም ጉርብትና መርህ ላይ የተመሠረተና ሠላማዊ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፡፡

- ከሽብር፣ ከብጥብጥና ከጦርነት የፀዳ ዓለም እንዲኖር በሚደረገው ዓለም አቀፍ ጥረት ውስጥ ኢትዮጵያ ተገቢ ድርሻዋን እንድትወጣ ይደረጋል፡፡





- በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ የሚታዩት ኢ-ፍትሃዊነት ችግሮች እንዲወገዱ በተለይም በታዳጊ አገሮች ላይ የሚጫኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ገደቦች እንዲቀሩና የጋራ ጥቅምን ታሣቢ በማድረግ በአጋርነት መንፈስ የተቃኙ አዲስ ዓይነት ግንኙነቶች እንዲመሠረቱ ኢትዮጵያ ብርቱ ትግል ታደርጋለች፡፡

- አለመግባባቶች እና ግጭቶች እንዳይፈጠሩ መከላከልና ከተፈጠሩ ደግሞ በሠላማዊ መንገድ መፍታት የውጭ ግንኙነታችን ዋነኛ መርህ ነው፡፡

## 3.8 የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተቋሞችን መመሥረት

በፌደራልና በክልል ደረጃ በሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ሕግ ተርጓሚው መካከል ግልጽ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል መኖሩን የሚያረጋግጥ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ይፈጠራል፡፡

የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጋዊ ተቋሞች ይደራጃሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ሀ. ዜጎች ሃሣባቸውን የመግለጽና መረጃ የማግኘት ነጻነታቸው በማንኛውም ሁኔታ እንዳይደፈር የሕግ ጥበቃ ይደረጋል፡፡ የመረጃ ምንጭና የሃሣብ መግለጫ የሆኑት የመገናኛ ብዙሃን ሥልጣን ከያዘ ፓርቲ ተፅእኖ መላቀቅ በሚያስችላቸው መንገድ ይደራጃሉ፡፡ በተለይም በመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የተሠማሩትን ክፍሎችና የተቋሞቹን አሠራር ነፃነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ አመራራቸው ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ከሲቪክ ማህበራት የተውጣጡ ሰዎች በሚገኙበት ቦርድ እንዲያዝና ተጠሪነታቸውም ለሕግ አውጭው እንዲሆን ይደረጋል፡፡

- የመንግሥት አስፈጻሚው አካል ተቋሞቹን በሥልጠናና በተለያዩ መስኮች እንዲደግፍ በሕግ ከተሠጠው ኃላፊነት ውጭ በአሠራር ነፃነታቸው ላይ ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክል የሕግ ሥርዓት ይወጣል፡፡
- በመገናኛ ብዙሃን ሥራ የተሠማሩ የግል ባለሃብቶችና ሞያተኞች በነጻነት እንዲሠሩ የሚያስችል የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡

- የዜጎችን ሃሣብን የመግለጽና መረጃ የማግኘት ነጻነት የሚገድቡ አዋጆችና መመሪያዎች ይሠረዛሉ፡፡

ለ. ነፃ የፍትህ ሥርዓት መኖሩን ለማረጋገጥ የፍትህ ተቋሙ አደረጃጀት፣ አሠራርና ተጠሪነት ከአስፈጻሚው አካል ጣልቃ ገብነት የሚጠበቅበት ሕጋዊ ድንጋጌ ይወጣል።

- በፍትህ ሥራ የሚሠማሩ ሰዎች መመዘኛ የሞያ ብቃትና መልካም ሥነ ምግባር ሆኖ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ተፅእኖ መላቀቃቸውን የሚያረጋግጥ፣ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር ጥፋት ቢሠሩ የሚቀጡበት የሕግ አግባብ ግልፅ ሆኖ ይወጣል።

- በፍትህ ተግባር ድርሻ ያላቸው የፖሊስ ተቋሞች ከአስፈጻሚው አካልና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻ ሆነው እንዲደራጁና እንዲሠሩ ይደረጋል።

- የፖሊስ ተቋሞችና አባላት የሕዝቡን መብት በሚጥስ ፣ በሕግ ሥርዓት የተቋቋሙ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በሚጐዳ፣ ለገዥው ፓርቲ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ተግባር ተሠማርተው ከተገኙ የሚቀጡበት ግልፅ የሆነ የህግ ሥርዓት ይወጣል።

- በመብት ረገጣና በሥልጣን ብልግና የተሠማሩ የገዥው ፓርቲ አባላትና የመንግሥት ሹማምንቶችን ለመመርመርና ወደ ሕግ ለማቅረብ የሚያስችል የሕግ ሥልጣን ይሠጣቸዋል።

- የፖሊስ ተቋሞች ተጠሪነት ለሕግ አውጭውና ለሕዝቡ እንዲሆን ይደረጋል።

ሐ. የመከላከያ ኃይልና የደህንነት ተቋሞች በመብት ረገጣ እንዳይሣተፉ፣ በማንኛውም የሲቪል ተቃውሞ ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ፣ ሥልጣን ላይ የወጣ ፓርቲ ተቀጥላ ከመሆን አደጋ እንዲጠበቁ፣ የሀገርንና የሕዝብን ሉዓላዊነትና ደህንነት ከማስከበር ውጭ ባልታጠቁ ሲቪሎችና ለፖለቲካ ሥልጣን በሚታገሉ ሠላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ በደል እንዳይፈጽሙ የሚከለክል ሕግ ይወጣል።

- የእነዚህ ተቋሞች ተግባር ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ለማረጋገጥ ለሕግ አውጭው አካል ሪፖርት የሚያደርጉበት አሠራር ይፈጠራል።







- በሕግ ሥርዓት የተቋቋሙ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደ ብሔራዊ ስጋትና የደህንነት አደጋ አድርገው እንዳያዩ የሚከለክል ሕግ ይወጣል።

መ. የሀገሪቱ ሲቪል ሠርቪስ ፓርቲዎች ወደ ፖለቲካ ሥልጣን በወጡና ከሥልጣን በወረዱ ቁጥር እየፈረሠ እንደገና የሚቋቋምበት አሠራር ተወግዶ የአደረጃጀትና አሠራር ነጻነት እንዲኖርና የሥራ ልምድና የተቋሞች መረጃ ተከታታይነት እንዲረጋገጥ በሚያስችል መንገድ ይዋቀራል።

- አሁን የተቋቋመው ሲቪል ሠርቪስ የሕግ ሥርዓትን ባልተከተለ አሠራር የገዥው ፓርቲ አምሣል እንዲሆን በመደረጉ ማስተካከያ ይደረግበታል። በፖለቲካ ሹመት ከሚያዙ የአመራር ቦታዎች በስተቀር በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የሲቪል ሠርቪስ የሥራ መደቦች በሞያ ብቃት መመዘኛና ግልጽ በሆነ የሠራተኛ አቀጣጠር የሚያዙበት መንገድ ይፈጠራል።

- በፖለቲካ ታማኝነት፣ በተለያዩ የትስስር ምክንያቶችና ግልጽ በሆነ አድሎ የማይገባቸውን ጥቅም ያገኙና በአንጻሩ በግፍ አሠራር የሚገባቸውን ጥቅም ያጡ የሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞችን ጉዳይ የሚያጣራ ኮሚሽን ተቋቁሞ ለሕግ አውጭው አካል ሪፖርት ከቀረበ በኋላ ሕጋዊ የማስተካከያ እርምጃ ይወሠዳል።

- የሲቪል ሠርቪሱ አደረጃጀትና አሠራር ከአስፈጻሚው አካል ቀጥተኛ ተፅእኖ ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥ ተጠሪነቱ ለሕግ አውጭው አካል እንዲሆን ይደርጋል።

ሠ. በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው የሥልጣን ክፍፍልና ግንኙነት ሚዛናዊና ግልጽ በሆነ የሕግ ሥርዓት እንዲመራና በሀገራችን የሚቋቋመው የፌደራል ሥርዓት ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጋዊ እርምጃዎች ይወሠዳሉ።

ረ. በሀገራችን ውሰጥ የመደራጀት ነፃነትን የሚገድቡ እንቅፋቶችን ሁሉ በማስወገድ በነጻነት ተደራጅተው የሚንቀሣቀሱ የሲቪክ ማህበራት እንዲስፋፉ ይደረጋሉ።

# 4. ማጠቃለያ

## *4.1 የማኒፌስቶው አፈፃፀም*

ቅንጅት የመራጩን ውክልና ባገኘ በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ በማኒፌስቶው የተዘረዘሩትን የትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት ያደረገ ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር ተሠርቶ ለሕዝቡ ይፋ ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ ዓመት ሚያዝያ 30 በማኒፌስቶው አፈጻጸም ላይ የተዘጋጀ የግምገማ ሪፖርት ለሕዝብ ይቀርባል፡፡

ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ አስከፊና አዋራጅ ከሆነ ድህነት ውስጥ መግባቱንና ማኒፌስቶውን ለማስፈፀም የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ይገነዘባል፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ጥንካሬና ከድህነት ለመውጣት ባለው ጥልቅ ፍላጐት ይተማመናል፡፡ ስለዚህ ቅንጅትን መምረጥ ከድህነት ለመውጣት የሚደረግ ቁርጠኛ ውሣኔ ነው፡፡

ቅንጅትን መምረጥ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለመፍጠር፣ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የኤኮኖሚ ፖሊሲን ለመደገፍ፣ ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጥ ማህበራዊ ፖሊሲን ሥራ ላይ ለማዋል፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ የሚደረግ ውሣኔ ነው፡፡

ቅንጅትን መምረጥ ሁሉም ዜጐቿ ፍላጐታቸውን ለማሣካት እኩል እድል እንዲያገኙና በጋራ ሀገራቸው እኩልና የተከበረ ቦታ እንዲኖራቸው የማድረግ ራዕይ ላለው ሕዝባዊ የፖለቲካ ድርጅት የሚሠጥ የፖለቲካ ሥልጣን ውክልና ነው፡፡

ቅንጅት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ፣ አስተማማኝ ሠላምና ዘላቂ ሠላም እንዲረጋገጥ ያለውን ግልጽ ራዕይ፣ ፍላጐትና ዝግጁነት በመገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲመርጠውና የሥልጣን ውክልና እንዲሠጠው በአክብሮት ይጠይቃል፡፡






## *4.2 ሀገራዊ ጥሪ*

1. በሕዝብ ፈቃድ ወደ ተመሠረተ የዴሞክራሲ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ለመሸጋገር ቅንጅትን ምረጡ፤
2. በሀገራችን የፖለቲካ ፍጥጫ፣ የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሠስ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቆም የሚያደርግ ብሔራዊ እርቅ እንዲኖር ቅንጅትን ምረጡ፤
3. በመንግሥት አስተዳደርና አመራር ግልጽነት፣ ታማኝነት፣ ሀቀኝነትና ዘላቂነት (consistency) እንዲኖር ቅንጅትን ምረጡ፤
4. በሕዝቡ መካከል በውይይት፣ በመደማመጥና በመቻቻል ላይ የተመሠረተ እኩልነትና ዘላቂ አንድነት እንዲኖር ቅንጅትን ምረጡ፤
5. የሕግ የበላይነት፣ የግለሰብ ነጻነት፣ የግል ሃብት ባለቤትነትና የሕዝብ ማህበራዊ ደህንነት እንዲከበር ቅንጅትን ምረጡ፤
6. የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም እንዲከበር ቅንጅትን ምረጡ፤
7. ማህበራዊ ፍትህ ለሚያረጋግጥ የኤኮኖሚ ዕድገት ቅንጅትን ምረጡ፤
8. የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ተስፋ እውን የሚያደርግና ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚጠቅም የኤኮኖሚ ዕድገት እንዲመጣ ቅንጅትን ምረጡ፤
9. ከሁሉም በፊት በገጠርና በከተማ ውስጥ የተንሠራፋው ድህነት እንዲወገድና ወደ ብልፅግና ጉዳና ለማምራት የሚያስችል የኤኮኖሚ እድገት በሀገራችን ለመፍጠር ቅንጅትን ምረጡ፡፡

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለኢትዮጵያ!

1997 ዓ.ም.
**አዲስ አበባ**